# አሸናፊው
# የክርስቲያን
# ኑሮ ።

## የመጽሐፈ ኢያሱ ጥናት ።

ከዶክተር አላን ሬድፓዝ ።
በዋቅጅራ ጉባ
ወደ አማርኛ ተተረጐመ ።

# ከተርጓሚው ።

በ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. በአዲስ አበባ ወኅኒ ታስሬ ሳለሁ ሚስተር አላን ሬድፓዝ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የደረሰውን «አሸናፊው የክርስቲያን ኑሮ» የሚባለውን መጽሐፍ ሳነብ ሳለሁ አሸናፊው የክርስቲያን ኑሮ ምን እንደሆነ፣ እንዴትስ እንደሚገኝ ለማወቅ ቻልሁ ። እስከ ዛሬ ድረስ ሚስተር አላን ሬድፓዝን ያላየሁትና የማላውቀውም ሰው ቢሆንም፣ አብሮኝ ብዙ ዘመን በመኖር የልቤን ምሥጢርና ችግር እንደሚያውቅ ሰው ስለሚጽፍ፣ መጽሐፉ ወደ አሸናፊው የክርስቲያንነት ኑሮ የምገባበትን በር ከፈተልኝ ።

አብረውኝ በወኅኒ ቤቱ ለነበሩ አንዳንድ ጓደኞቼ ወደ አማርኛ እየተረጎምኩ ከመጽሐፉ አንዳንዱን ክፍል ስነግራቸው፣ ሕሊናቸውን እንደነካ ስለነገሩኝ «ለካስ በሰው ሁሉ ልብ ያለው መንፈሳዊ ችግር አንድ ነው» በማለት፣ መጽሐፉን በሞላ ወደ አማርኛ ለመተርጎም ቁርጥ ሐሳብ አደረግሁ ።

የመጽሐፉን ትርጉም ከፍጻሜ እንዳደርስ በምፈልገው ሁሉ ለረዱኝና ላደፋፈሩኝ ለወኅኒ ቤቱ አስተዳዳሪ ለሌተና ኰሎኔል ብርሃኔ ወልደየስና ለሌሎች መኰንኖች ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። በሐሳብና በጸሎታቸውም በብርቱ ለደገፉኝ ለባለቤቴ ለወይዘሮ ጌጤ አመንሲሳ፣ ለአቶ ሙሉጌታ ወልደሚካኤል ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ።

የመጽሐፉም ትርጉም በአዲስ አበባ ወኅኒ ቤት ኅዳር ፳ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. አለቀ ።

ይህ መጽሐፍ በወኅኒ ቤቱ ለሚገኙ እስረኞችና ሠራተኞች ለቀሩትም ሁሉ እውነተኛውን የክርስቲያንነት ኑሮ እንዲያስገኝ ምኞቴ ነው ።

ቀቅጅራ ጎባ ።

# መግቢያ ።

አላን ሬድፓዝ ሲሰብክ ላልሰሙ ሰዎች የምነግራቸው ሚስተር ሬድፓዝ «በዓ ውሎ ነፋስ የሚነቃነቅ ወርከ» እንጂ «ተራ ነፋስ የሚወዘውዘው ሸምበቆ» እንዳልነበረ ነው ። ጥሩውና እውነተኛው የወንጌል ትልቅነት በንጽሕናና በኃይል በሕይወቱ ይነፍሳል ።

እንደ ብዙዎቹ ሰባኪዎች ፣ በእውነቱም በጣም ጥሩ እንደሚሰብኩት ሳይሆን ፣ የአዲስ ኪዳንን መልእክት አንድ መሆን ያረጋገጠና የዚህንም መልእክት በብሉይ ኪዳን አስቀድሞ መገለጽ በደንብ የሚያውቅ ሰው ነው ። እኛ ንስሐ ያልገቡትንና ያላመኑትን «በክርስቶስ እመን !» ብዙ ጊዜ ለሚታገልና ለተደናገረ ክርስቲያን «በርታ ፣ በብዙው ጸልይ ፣ ወደ ፊትም ግፋበት ፣ ጊዜ ውሰድ» እንላለን ። ነገር ግን የተሻሻለ ውጤት አናገኝበትም ።

ምን ጎደለ ? የጎደለው ኃይልን የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ባለጠግነት ሁሉ ነው ። ይህ ሥርዓትን ከከንቱ ድካምና መሸነፍ ያድነዋል እንጂ አያስቀረውም ።

የልብ ቀስቃሽ በሆነው በዚህ መጽሐፍ ገጾች ውስጥ የኃያል ፣ የጤናማና የተ ብራራ ሕይወት አኗኗር ምሥጢር ተገልጾአል ። ይኸውም አስገራሚ በሆነው ቅዱስ ጽሑፍ በመጽሐፈ ኢያሱ ይገኛል ።

አንባቢያን ስለ ትምህርቱ አገላለጽና ስለ ዓረፍተ ነገሮቹ አቀማመጥ ትችት መስጠት አይገባቸውም ። የደራሲውንም ዋና ዓላማና የሐሳብ መሠረት ሁሉም ሳይ ረዱ አያልፉም ። ለአንባቢያን በትህትና የማሳስበው ይህ ነው ። የቃላትና የአነጋገር ቆርጣሚ ከመሆን የእውነት ቀማሽ መሆን ይሻላል ።

በአላን ሬድፓዝ አገልግሎት እንደ እሳት ወላፈን ሲንበገበግ ያየሁት ለክርስቶሳዊ ሕይወት ያለ ምኞት ነው ። ያ ነበልባል ተቀጣጥሎብኛል ፤ ባንተም ሊያደርግ ይችላል ።

እነዚህ ገጾች «የሃይማኖት ትምህርትን ለመግለጽ» የታቀዱ አይደሉም ፤ ነገር ግን «መንፈሳዊ ነበልባል ወርዋሪዎች» ናቸው ።

ጳውሎስ ኤስ ሪስ ።

# መቅድም ።

የእግዚአብሔር ቃል የሚገለጽበትና ለእርሱም የምንከላከልበት ዓይነተኛ መንገድ ቃሉን በግልጽ ማስተማር ነው። ከኦሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያ ቁጥር እስከ ራእይ ዮሐንስ የመጨረሻው ቁጥር እያንዳንዱ ገጽ የእግዚአብሔርን እውነተኛነትና ትክክለኛነት ያሳያል ። በታሪክም ሆነ በሳይንስ ረገድ እያንዳንዱ ገጽ ትክክለኛ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሁሉ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በመሠረቱ የታሪክ ወይም የሳይንስ መዝገብ አይደለም ። ዋናውን የመጀመሪያ ዓላማው የእግዚአብሔር መግለጫ መሆኑ ነው ። ለእግዚአብሔር ፍቅር፣ ለኃጢአታችን፣ ለፍርዱ፣ ለጽድቁ፣ ለምሕረቱና ለደኅንነት ላዘጋጀው እቅድ ምሥጢር መክፈቻ ቁልፍ አድርጎ ሰጥቶናል ።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ መሆኑን ከተገነዘብን አዲስ ትርጉም እናገኝበታለን። የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በማይተዋወቁ ሰዎች፣ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች፣ በተራራቁ አገሮችና አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በሚሆኑ ጊዜያት ውስጥ ተጽፈው የተጠራቀሙ ናቸው። ሆኖም በመጽሐፉ የሚገኘው ዓላማ አንድ ስለሆነ ሐሳቡን ያመነጨና በሥራ ላይ ያዋለ የመጨረሻውን ከመጀመሪያ ጀምሮ የሚያውቅ አምላክ መሆኑን እንረዳለን ። መጽሐፍ ቅዱስ የዓለምን ታሪክ ወይም ሳይንስ ለማስተማር ሳይሆን ለአንድ ዓላማ የተጻፈ ነው ። ስለዚህ የዓለምን ታሪክ ወይም ሳይንስ በትክክል ባይገልጽ እንኳን ዋናውን ዓላማ ሲያስተምር ትንሽ ነቁጥ ያህል ስሕተት የለበትም። ብሉይ ኪዳን ያንድ ሕዝብ ታሪክ ነው፣ አዲስ ኪዳን ያንድ ሰው ታሪክ ነው። ያ ሕዝብ ያንን ሰው ለማፍራት የተመረጠና ለዚሁም በቂ ሆኖ እንዲገኝ እግዚአብሔር በብዙ ሰዎችና መንገድ የመከረውና የተከባከበው ነው ።

የሙሴ መጻሕፍት ስለ ሕዝቡና ስለ ሕጋቸው ይነግሩናል። የሚቀጥሉት አሥራ ሁለት መጻሕፍት የሕዝቡን መንግሥትና አገዛዝ ይገልጻሉ። ከዚያ በኋላ ያሉት አምስት የቅኔ መጻሕፍት ያ ሕዝብ በተድላ የኖረበት ወርቃማ ዘመን መግለጫ ናቸው። የቀሩት አሥራ ሰባት የነቢያት መጻሕፍት ሕዝቡ በጨለማና በመጠቃት የኖረበት ዘመን ታሪክ ናቸው ። ስለዚህ ነቢያት የሕዝቡ ኀዘን ወደ ደስታ ልቅሶአቸው ወደ ሳቅ የሚለወጥበት ጊዜ ወደፊት እንዳለ እየተነበዩ ያጽናኑአቸው ነበር። ይህም የሚፈጸመው ያ ሰው (ክርስቶስ) ሲመጣ ነው ።

አራቱ ወንጌላውያን የዚያን ሰው መወለድ፣ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ያወራሉ ። እግዚአብሔር ራሱ ሰው ሆኖ በመካከላችን መመላለሱ እግዚአብሔር ምን እንደሆነና ምንስ ለማድረግ እንደሚችል ይገልጹልናል። ያም ሰው (ክርስቶስ) የተሟላና ጉድፍ የሌለበት እውነተኛ የፍቅር ሕይወት ነበረው። በችግር ያሉትን የሚወድና፣ ከለ ኃጢአት የሚጠላው የሌለው ነበር። የሐዋርያት ሥራ የዚያ ሰው መንግሥት እንደጀመረ ይተርካል። የሐዋርያት መልእክቶች የዚያን ሰው መንግሥት ሕግና ሥርዓት ያስተምራሉ። ራእይ ዮሐንስ ያ ሰው ለወደፊት ፍጹም በመሆኑ መላዋን የዓለም መንግሥት እንደሚገዛ ይተነብያል ።

ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ነው። በብሉይ ኪዳን የተዘጋጀው ፕሮግራም በአዲስ ኪዳን በሥራ ላይ ውሎአል። ያለ ብሉይ ኪዳን አዲስ ኪዳንን አናስተውልም። ያለ አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንም ተፈላጊነትን ያጣል። በተጨማሪም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ከሰው ጋር ያደርግ የነበረው ሁሉ በአዲስ ኪዳን ከሰው ጋር ለሚያደርገው ጥላው ነው። ከመጀመሪያው ለወደቀው የሰው ዘር ደኅንነት ሰው በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንዲሆን ታቅዶአል። ነገር ግን ከመምጣቱ፥ ከመሞቱና ከመነሣቱ አስቀድሞ ክርስቶስ በእነርሱ በኩል ከሚመጣው ሕዝብ ጋር እግዚአብሔር ይሠራ ነበር። እንደዚሁም ዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእያንዳንዱ ሰው ይሠራል።

አንድ ጊዜ ይህንን እውነት ከጨበጥን ብሉይ ኪዳን የደረቀ ታሪክና ፍች የሌለው መሥዋዕት መጽሐፍ ከመሆን የእግዚአብሔር መግለጫ ወደ መሆን ይለወጣል። ይህም ነገር አሁን ልናጠና ስላለው መጽሐፈ ኢያሱ እውነተኛ መሠረት ነው። እንደማምነው፥ ዛሬ ከክርስቲያን ኑሮ የጎደለውን ምሥጢር በመጽሐፈ ኢያሱ እናገኛለን።

ዛሬ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያስፈልጋቸው ታላቁ መንፈሳዊ መታደስ በአዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት የሚፈለግባቸው የክርስቲያንነት ኑሮ አቋም መሆኑ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ዋና እምነቴ ሆኖአል። በምናምነውና በአኗኗራችን መከከል ታላቅ ገደል ያለ ይመስላል፥ እንዲሁም በክርስቶስ በተሰጠን ሥፍራና በኑሮአችን መከከል ትልቅ ልዩነት አለ። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከልባስ እስከ ልባስ እንደምናምን ብዙ ጊዜ እናወጋለን። መጽሐፉ የሚጠይቀውን እውነተኛ ኑሮ ግን መኖር ያቅተናል። በዘመናችን ያለውን ዓለም የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲጎበኝና እንዲባርክ እንመኛለን። ነገር ግን ከዚህ የሚቀድመው የቤተ ክርስቲያን አዲስ ኪዳንን እንደ ገና መከተልና የእግዚአብሔር ቃልም የሚሰጠውን ሙሉውን መግለጫ ማመንና የሚጠይቀውንም የተቀደሰ ኑሮና ጠባይ መፈጸም ነው።

እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ ዛሬ እንደጊዜው መሆንንና ጸንቶ የቆየውን ግን ከቃሉ ውጪ የሆነውን ልማድ በማይቃወሙ ወንጌላውያን አከባቢ ብዙ ስብከትና ፕሮግራም፥ ብዙም ችሎታና ምስክርነት አለ። ነገር ግን ትውልዳችንን ወደ ጌታ ለማምጣት የተደረገው ድካም ውጤት እጅግ አነስተኛ ነው። የእውነተኛ በረከት መንገድ አድካሚ ሁልጊዜም የሚያደናግርና አብዛኛውን ጊዜ ግን ፍሬያማ ነው። ሰዎች የክርስቶስን ሥራዎችና እግዚአብሔርም ለእያንዳንዱ ነፍስ ያዘጋጀውን ደኅንነት እንዲያገኙበት፥ ጌታችንም እንዲጠቀምበት ይህ መጽሐፍ በብዙ ጸሎትና ምኞት የተደረሰ ነው። አሸናፊውም የክርስቲያን ኑሮ የሚመሰገንና የሚወደድ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ልንደሰትበት የሚገባን ሕይወት ነው።

በዚህ መጽሐፍ የሚገኙት ዋናዎቹ አርእስቶችና ቁም ነገሮች በሙዲ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቴን በጀመርሁበት በ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. የሰበክሁባቸው ናቸው። ብዙዎች ሰዎች እንዲታተም ስለጠየቁኝ ለንባብ እንዲመች በማድረግ ከስብከቱ አደ

ረጃጀት ቀና ሐሳብ ሳላዘንፍ ደረስኩት ። ስለዚህ ተመራማሪ አንባቢ ይህንን ስለሚያ ገኝበት ባይስማማው ይቅር ይበለኝ ።

በሕይወቴ ለሰጡኝ መንፈሳዊ ድጋፎች ብቻ ሳይሆን ይህንን መጽሐፍ ሳዘጋጅ በጽሑፎቻቸው ለረዱኝ ለዶክተር ኤፍ ቢ መዬርና ለዶክተር ግራሃም ስክሮጂ ባለ ውለታ ነኝ፤ እነዚህም ሰዎች አሸናፊውን የክርስቲያን ኑሮ የሚኖሩ፥ ያስተማሩና ስለ እርሱም የጻፉ ናቸው ። ሥራቸውም ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለማይቆጠሩ አእላፋት በረከ ትን አስገኝቶአል ። የእግዚአብሔር ቃልና የእነዚህ ሰዎች አድራጎት ያስገኘልኝ በረከት ለሌሎች እንዲደርስ እመኛለሁ ።

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጀትና በማረም ለረዱኝ ለወይዘሪት አርቢን ሃሪስ ምስጋ ናዬን አቀርባለሁ ።

ቸካን ኢሊኖይስ
አላን ሬድፓዝ

ለትዕግሥትዋ ፣ ለፍቅርዋና ለጸሎትዋ ባለዕዳ ለሆንሁ ለባለቤቴ

ለወይዘሮ ጌጤ አመንሲሳ እና

ለአዲስ አበባ መሀኒ ቤት አበረክታለሁ ።

# አስተዋጽዖ ።

## መጀመሪያ ክፍል ።


፩. የክርስቲያን ኑሮ ዓላማ ። ኢያሱ ፩ ፡ ፪
፪. እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው ። ኢያሱ ፩ ፡ ፱
፫. ትርፍና ጉዳቱን መገመት ። ኢያሱ ፩ ፡ ፲፩
፬. የበረከት ንጉሳዊ ጎዳና ። ኢያሱ ፫ ፡ ፲፩


## ሁለተኛ ክፍል ፤ ጠላትን ማሸነፍ ።


፭. መስቀልና ክርስቲያን ። ኢያሱ ፭ ፡ ፱
፮. ለጦርነት መዘጋጀት ። ኢያሱ ፭ ፡ ፲
፯. የመገናዘብ ዋጋ ። ኢያሱ ፭ ፡ ፲፪
፰. ድልን ማክበር ። ኢያሱ ፮ ፡ ፳፫
፱. መሰናክሎች ፡ ምክንያታቸውና ፈውሳቸው ። ኢያሱ ፯ ፡ ፲፫
፲. የክርስቲያን የነፃነት ሕግ ። ኢያሱ ፰ ፡ ፳
፲፩. የጠላት የጦር ስልትና ዓላማ ። ኢያሱ ፱ ፡ ፫
፲፪. የማያቋርጥ ድል ። ኢያሱ ፲ ፡ ፴፭
፲፫. የድል ፍሬ ። ኢያሱ ፲፩ ፡ ፳፫
፲፬. ርስታችንን መውረስ ። ኢያሱ ፲፫ ፡ ፩


## ሦስተኛ ክፍል ፤ ያንን ሕይወት መኖር ።


፲፭. የረካ ሕይወት ። ኢያሱ ፲፫ ፡ ፳፫
፲፮. የደቀ መዝሙር ዋጋ ። ኢያሱ ፲፬ ፡ ፲፬
፲፯. በሙላት መኖር ። ኢያሱ ፲፯ ፡ ፲፰
፲፰. የምንከላከል አደጋዎች ። ኢያሱ ፲፰ ፡ ፫
፲፱. የምንከተላቸው ሥርዓቶች ። ኢያሱ ፳፫ ፡ ፲፩
፳. የምናገለግልበት ኃይል ። ኢያሱ ፳፬ ፡ ፲፬

# መጀመሪያ ክፍል ።

# ዓላማን መመልከት ።

## ምዕራፍ ፩ ።

## የክርስቲያን ኑሮ ዓላማ ።

### ኢያሱ ፩ ፥ ፪ ።

«እንዲህም ሆነ ፥ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፦ ባሪያዬ ሙሴ ሞቶአል ፥ አሁንም አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሥታችሁ ለእስራኤል ልጆች ወደምሰጣቸው ምድር ይህን ዮርዳኖስን ተሻገሩ ። ለሙሴ እንደነገርሁት የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን በታ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቼአለሁ ። ከምድረ በዳው ፥ ከዚህም ከሊባኖስ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ የኬጢያውያን ምድር ሁሉ እስከ ፀሐይ መግቢያ እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ዳርቻችሁ ይሆናል ። በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ፥ ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ፥ አልጥልህም ፥ አልተውህም ። ለአባቶቻቸው ፦ እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና ጽና ፥ አይዞህ ። ነገር ግን ጽና ፥ እጅግ በርታ ፥ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ ፥ አድርገውም ፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል ። የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው ፥ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ፥ ይከናወንልሃልም ። በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና ፥ አይዞህ ፥ አትፍራ ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን ?»

### ኢያሱ ፩ ፥ ፩ — ፱ ።

የመጽሐፈ ኢያሱ የችኮላ አነባበብ ኢያሱና ሠራዊቱ የከነዓንን ምድር ለማሸነፍ ስላደረጉዋቸው ውጊያዎች የተጻፈው ታሪክ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ይህን ያህል ሰፊ በታ ለምን ተሰጠው ? የሚል ጥያቄ ሳይፈጥር አይቀርም ። ነገር ግን በቀላል ሊታወቅ የማይቻል ጥልቅ የሆነ ውስጣዊ ምሥጢር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዳለ የታመነ ነው ።

ይህንንም ውስጣዊ ምሥጢር ስንመረምር በብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን መዝሙራት ከመንገድ ሳንስት አንቀርም ። በብዙ የቤተ ክርስቲያን መዝሙራት ዮርዳኖስ በሞት ከነዓንም በሰማያዊ አገር ተመስለዋል ። በመጽሐፈ ኢያሱም ውስጥ በእነዚህ ትርጓሜዎች ብንመራ በገጾቹ ለተጻፉ ብዙ ነገሮች ምንም ዓይነት ፍች አይኖራቸ

ውም ። በመጽሐፈ ኢያሱ ከነዓን የጦር ሜዳ ነው ። በእውነቱ ይህ ወደ ዕረፍታቸው የገቡት ሰዎች ፈንታ አይደለም ። ክርስቲያን በምድራዊ ኑሮው ሁሉ የሚጋፈጠው ጠላት አለው ፤ ነገር ግን ጦርነቱ አልቆ ከጌታው ጋር የሚሆንበትን ዕረፍት በናፍቆት ይጠባበቃል ። እንግዲያውስ ይህ አይሆንም ። በእነዚህ ሃያ አራት ምዕራፎች የተጻፉትን ሁኔታዎች ትርጉም ማስተዋል ከፈለግን ጠለቅ አድርገን መመርመር ይገባናል ።

የዚህ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ትርጓሜ በአዲስ ኪዳን በሚገኙ በኤፌሶንና በዕብራውያን መልእክቶች እንደሚገኙ እገምታለሁ ። ለምሳሌ በዕብራውያን ምዕራፍ ሦስትና አራት የከነዓን ምድር እያንዳንዱ አማኝ በዚህ ምድር የሚከፈላቸው ዕረፍትና ድል እንዲሁም በክርስቶስ ሃይማኖት ያለ ዕረፍት ምሳሌ መሆኑን እናገኛለን ። ደግሞም ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተጻፈው መልእክት ስለ «ሰማያዊ ስፍራ» ሲናገር ስለ መንግሥተ ሰማያት አይደለም ። ነገር ግን ከሙታን የተነሣው ጌታችን ባደረገው ድል በዚህ ዓለም ሳለን ከእርሱ ጋር ስላለን አንድነት ነው ። ይህም የእግዚአብሔር በረከት ሙላት ያለበት ምድረ በረከት ነው ። የኤፌሶን መልእክት በአዲስ ኪዳን የሆነውን ሁሉ መጽሐፈ ኢያሱ ደግሞ በብሉይ ኪዳን እንደሆነ ብናስተውል ፤ የመጽሐፈ ኢያሱን እውነተኛ ምሥጢር እንደምንረዳ አምናለሁ ። ይህንንም በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ልንፈርድ እንችላለን ።

ስለዚህ በዚህ የመክፈቻ ምዕራፍ የመጽሐፈ ኢያሱን ጠቅላላ ትርጉም ስንመረምር በምድረ ከነዓንና በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእያንዳንዱ አማኝ በተሰጠው በምድረ ደኅንነት መካከል ያለውን ተመሳሳይነት እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ ።

ከነዓን እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደዚያ የሚመራበት ግብ መሆንዋን በመጀመሪያ እናስተውል ። በሚነድ የቁጥቋጦ እሳት ውስጥ እግዚአብሔር ለሙሴ በተገለጠ ጊዜ እስራኤላውያንን ከምስር ባርነት የሚያወጣቸው ብቻ ሳይሆን ወተትና ማር ወደ ምታፈስ ምድር እንደሚያገባቸው ቃል ኪዳን ገብቶአል ። «እግዚአብሔርም አለ ፦ በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም ጭቆና የተነሣ የሚያፈልቁትን ጩኸታቸውን ሰማሁ ፥ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ ፥ ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ ፥ ከዚያችም አገር ወተትና ማር ወደምታፈሰው አገር ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር ወደ ከነዓናውያንም ወደ ኬጢያውያንም ወደ ፌርዛውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳውያንም ስፍራ አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ» ዘጸአት ፫ ፥ ፯ ፥ ፰ ።

በሌላ አነጋገር ከግብፅ መውጣት በከነዓን ለሚያገኙት ተድላ መሰናዶ ነው ። ፋሲካው ፥ የደሙ መፍሰስ ፥ የቀይ ባሕር መሻገርና የፈርኦን ሠራዊት መደምሰስ በከነዓን ወደ አለው የዕረፍት ስፍራ የማይመሩ ከሆኑ ከንቱ ልፋት ናቸው ። ደግሞም እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ የሚፈጸመው ርስታቸው የሆነችውን ከነዓንን ሲወርሱ ብቻ ነው ።

መቼም ቤተ ክርስቲያን ወደ በረከት አገር (እውነተኛ መንፈሳዊ ኑሮ) የማትገፋበት ምክንያት አላት ። መጽሐፈ ኢያሱንና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ስናነጻጽር በከነዓን ኃያላት ጠላቶች እንደነበሩ እናስተውል ። የብረት ሰረገሎችና ጽኑ ምሽግ ያሉዋቸው ሰባት ነገሥታት በከነዓን ነበሩ ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለን ሙሉ በረከትን ደኅንነት ያለው አገራችን ማለት ለክርስቶስ የተሰጠ እውነተኛው የክርስቲያን ሕይወት እንዲሁ ከውጊያና ከጠላቶች ነፃ የሆነ አይደለም ። በኤፌሶን መልእክት ስድስተኛው ምዕራፍ የሚገኘው ያ ግሩምና ድንቅ ክፍል የምዕመናንን ጦርነት ሁኔታ አበጥሮ ያስረዳል ። «መጋደላችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለምና ፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ፡— ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ ።»

ለክርስቲያን ኑሮ አስፈላጊ የሆነው ሙሉ በረከት ፤ ለተራቡት ለሚመኙትና ሊያገኙትም ለሚለምኑ ብቻ ካልሆነ አይሰጥም ። እርግጥ ነው ፤ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በሰማያዊ ስፍራ (የተቀደሰ ኑሮ) ባርኮናል ። እነዚህም በረከቶች ያሉ በሰማያዊ ስፍራ ነው ። ወደዚያም ቦታ ሰይጣን ክፉውን ፍላጻ ሁሉ ይወረውራል ። ክርስቲያን በረከትን ካልፈለገና ካልተመኘ እግዚአብሔር አይበርከውም ። የምንፈልገው ጥቂት ከሆነ እግዚአብሔር ሙላቱን በገበታ አድርጎ እንድንመገብ አይጋብዘንም ። በምናደርገው መንፈሳዊ ውጊያ ሁሉ የሚገጥሙንን ጠላቶች ሁሉ የኛ ኢያሱ (ክርስቶስ) ድል እንዳደረገልን በማመን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለ እርስታችንን እንዳንረከብ ሰይጣን የሚያነሣብንን ሁሉ እንድንጋፈጥ እግዚአብሔር ለያንዳንዱ ልጁ ይመኛል ።

ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ያወሳሁአቸው በመጽሐፈ ኢያሱና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል ያሉ የሐሳብ መስማማት መጽሐፈ ኢያሱ ለኛና ለብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ለደኅንነታችን ባዘጋጀው እቅድ ብዙ ሰፊ ሥፍራ በመንፈስ ድል ማድረግ እንደሚቻል ወደ በረከትም የሚያደርሱ መንገዶች አዲስ ምሥጢሮች እንዳሉ ያብራሩልናል ። መጽሐፈ ኢያሱ ለብዙዎቹ ተራ የታሪክ መጽሐፍ ነው ፤ ነገር ግን ከላይ የተባለውን ብናስተውል ይህ መጽሐፍ የታሪክ መጽሐፍ መሆኑ ቀርቶ ነፍሱንና ሰውነቱን ለእርሱ በሰጠው ሰው በኩል እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደሚችል የሚገልጽ መጽሐፍ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፪ ።

# እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው ።

ኢያሱ ፩ ፡ ፱ ።

«ኢያሱም የሕዝቡን አለቆች ፦ በሰፈሩ መካከል እለፉ ፤ ሕዝቡንም ፦ አምላካችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ ምድር እስከ ሦስት ቀን ይህን ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ልትወርሱአት ትገቡባታላችሁና ስንቃችሁን አዘጋጁ ብላችሁ እዘዙአቸው ብሎ አዘዘ ።

ኢያሱም የሮቤልን ልጆች የጋድንም ልጆች የምናሴንም ነገድ እኩሌታ እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ፦ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዲህ ብሎ ያዘዛችሁን ቃል አስቡ ፦ አምላካችሁ እግዚአብሔር ያሳርፋችኋል ፤ ይህችን ምድር ይሰጣችኋል ። ሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁ ከብቶቻችሁም ሙሴ ከዮርዳኖስ ማዶ በሰጣችሁ ምድር ይቀመጡ ፤ ነገር ግን እናንተ ፤ ጽኑዓን ኃያላን ሁሉ ፤ ተሰልፋችሁ በወንድሞቻችሁ ፊት ተሻገሩ ፤ እርዱአቸውም ፤ እግዚአብሔር እናንተን እንዳሳረፋችሁ ወንድሞቻችሁን እስኪያሳርፍ ድረስ ፤ እነርሱም ደግሞ አምላካችሁ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ምድር እስኪወርሱ ድረስ ፤ ከዚያም በኋላ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ በፀሐይ መውጫ ወደሰጣችሁ ወደ ርስታችሁ ምድር ትመለሳላችሁ ትወርሱአትማላችሁ ። እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ብለው መለሱለት ፤ ያዘዝኸንን ነገር ሁሉ እናደርጋለን ወደምትልከንም ስፍራ እንሄዳለን ። በሁሉም ለሙሴ እንደታዘዝን እንዲሁ ለአንተ ደግሞ እንታዘዛለን ፤ ብቻ አምላክህ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደነበረ ከአንተ ጋር ይሁን ። በትእዛዝህ የሚያምፅ ሁሉ የምታዝዘውም ቃል ሁሉ የማይሰማ ፤ እርሱ ይገደል ፤ ብቻ ጽና ፤ አይዞህ ።»

ኢያሱ ፩ ፡ ፲ — ፲፰ ።

በመጽሐፈ ኢያሱ የሚገኘውን ውስጣዊና ጥልቅ ትርጉም አሁን መመርመር ጀምረናል ። የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዲህ ነበር ፤ «አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሥታችሁ ለእስራኤል ልጆች ወደምሰጣቸው ምድር ይህን ዮርዳኖስን ተሻገሩ» በጦርነትና በውጊያ ቢሆንም ይህ የተሻለ የኑሮ ደረጃና ሁልጊዜም ጥርጣሬና ድል መሆን ካለበት የምድረ በዳ ኑሮ የበለጠ የማሸነፍ ኑሮ እንዳለ ይገልጻል ።

እንደማምነው በሁላችን ልብ «እግዚአብሔር የሚጠቀምበትና ሊሠራበት የሚችል ሰው እንዴት አድርጌ እሆናለሁ ?» የሚል ጩኸት አለ ። እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ መሪነት የሚያምነው ሰው እንዴት ያለውን ነው ? እስቲ እግዚአብሔር ለመሪነት የመረጠውን ሰው ኢያሱን እናስብ ። ይህ አዲስና ከፍተኛ ኃላፊነት በተሰጠው

ወቅት ለኢያሱ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነበር፣ «በምትሄድበት ሁሉ አም ላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፣ አይዞህ፣ አትፍራ፣ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን ?»

የእግዚአብሔርን ሥራ ልንመራ ከፈለግን ሁላችን ጽኑዎች መሆን አለብን ማለት ነውን ? እንዲህ ከሆነስ ተስፋችን ጥቂት ነው። ብዙውን ጊዜ እንደ ጳውሎስ «ለዚህ የሚበቃ ማነው ?» እያልን እንጮሃለን፤ እግዚአብሔር ግን ኢያሱን እየደጋገመ ጽና፣ በርታ፣ አይዞህ ይለዋል። ይህ ለምንድን ነው ? በእውነት ኢያሱ የራሱን አለመብቃት ድካም ያውቅ ነበረ። እንዲህ ያለ ክብር እንደሚሰጠው ከቶ አላሰበም። የሙሴ ባሪያና አገልጋይ ሆኖ በምክትልነት መኖርን ፍጹም በቃኝ ብሎ ተቀብሎታል። ነገር ግን አንድ ቀን ጥሪ በመጣለት ጊዜ ልቡ ቀለጠ።

እግዚአብሔርም «ጽና» አለው። እግዚአብሔር ለአንድ ሰው እንዲህ ሲናገር ያ ሰው ደካማ መሆኑን ያስረዳል። «አትፍራ» ሲል ሰውዬው እንደሚፈራ ያስረዳል። «አይዞህ አትደንግጥ» ማለት እግዚአብሔር የሚናገረው ያ ሰው ተስፋ በመቁረጥ ሥራውን እንደሚያቋርጥ ያረጋግጣል። ለሰዎች እንዲህ ሲሰማቸው እግዚአብሔር መጥቶ ለመሪነትና ለኃላፊነት ያስነሣቸዋል።

እግዚአብሔር ይቅር ይበለን እንጂ ብዙዎቻችን እንዳይጠቀምብን ለእግዚአብሔር ትልቆች ነን። የምናደርገውን በመወጠንና ለአሠራሩም በራሳችን ውጥኖች ተሞልተናል። እግዚአብሔር ዝቅ ሊያደርገን፣ ሊሰብረንና ባዶዎች ሊያደርገን ይፈልጋል። ሥራውን ተቀብለን በእርሱ ፈቃድ ወደፊት መገሥገሥ እንድንችል አነስተኛዋን ማጽናናትና ድፍረት እንኳ ከላይ እንድንቀበል እግዚአብሔር እጅግ ዝቅ ሊያደርገንና አለመብቃታችንን ሊያስረዳን ይፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች ብርቱዎችና ኃያላን የሆኑ ሰዎች ብቻ ኑሮ ሊመቻቸው ይችላል ይላሉ፣ እግዚአብሔር ግን ለዛሉና ጉልበት ላጡ ደካሞች ኃይል ይሰጣል። በሰው ድካም የእግዚአብሔር ኃይል ይገለጣል። ያሉትን ነገሮች እንደሌሉ ለማድረግ በምናምን ነገሮች ይሠራል። እራሱ እንደመሰከረው ሐዋርያው ጳውሎስ በንግግር ችሎታው የተዋረደ በመሆን ፈንታ ሥልጡን ተናጋሪ ቢሆን ኖሮ ታላቅ ሐዋርያ ባልሆነም ነበር።

ኢያሱን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ያደረገው ኃይል የመነጨበትን ሦስት የኃይል ምንጮች ከኔ ጋር ሆነህ እይ። በመጀመሪያ እርሱ ታማኝ ሰው ነበረ። ኢያሱ ፩፣ ፩ ኢያሱ የሙሴ አገልጋይ (ሚኒስቴር) እንደነበረ ይገልጻል። ይህ «አገልጋይ» የተባለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት ያለ ክቡር ቃል ነው! በእንግሊዝ አገር «ቄስ» ወይም «ካህን» በማለት ፋንታ «አገልጋይ» ወይም «ሚኒስቴር» እንላለን። ሚኒስቴር ወይም አገልጋይ ሕዝብን ሊገዛ የተሾመ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ብሎ ሕዝብን የሚያገለግል ነው። በጥቂት ታማኝ መሆን በብዙዎች ነገሮች ገዥ መሆንን የሚያስችል ነገር ነው።

ታሪክ ጸሐፊው ኢዮሴፉስ ትክክለኛ ከሆነ ኢያሱ በግብፅ ባርነት አርባ ዓመት እንደተቀመጠ ያወጋል። አስገባሪዎቻቸው ያደረሱባቸውን ችግር፣ ማዋረድ፣ ጭካኔና ጭቆና ሁሉ ያውቃል። እንደገናም አርባ ዓመታት ሙሉ በምድረ በዳ መንከራተትን ቀምሶአል። በዚያም በረሃው ጉዞ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የነበሩትን አማሌቃውያንን ወግቶ ድል አደረገ። የተስፋን አገር ሰልለው መልካም ዜና ከመጡት ከጥቂቶቹ ኢያሱ አንዱ ነው። ጀግኖቹንና ብርቱዎቹን የከነዓንን ሰዎችና ጽኑ ቅጥሮቻቸውን አይቶአል፤ ነገር ግን አምላኩ ሁሉን ማድረግ እንደሚችል አመነ። ሰማንያ ዓመታት ሙሉ በእነዚህ ሁኔታዎች በታማኝነት ካገለገለ በኋላ እግዚአብሔር ጠራውና ለዚያ ብዙ ሠራዊት የመሪነት ሥልጣን እንዲይዝ አዘዘው።

እግዚአብሔር ዛሬ ለምን እንደሚያዘጋጀን ማን ያውቃል? በዙሪያችን ባለችው አነስተኛ ሥራችን በየቀኑ እናጉረመርማለን። ከዚህ የበለጠ ታላላቅ ሥራዎችን መሥራት እንደምንችል እንገምታለን። አነስተኛዋ የቀን ተግባራችንና ሥራችን በቂና ተስማሚአችን አይደለችም እንላለን። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሊጠቀምብህ ከተፈለገ አነስተኛዋን ተግባርህን የምትፈጽምበት አንዷ ሰዓት በፊቱ በጣም ጠቃሚ ናት።

ለመግዛት መገዛትንና ትዕግሥትን መማር አለብን። ወደ ላይ ለመውጣት መጀመሪያ መውረድ ያስፈልጋል። ለሰው ሕይወት ያለው የእግዚአብሔር ፈቃድ በከፍተኞች ነገሮች ሳይሆን በጥቃቅንና በተዋረደ ነገሮች በኩል ይመጣል። ትንሽዋን ኃላፊነት ተቀብለህ አነስተኛዋን ተግባርህን ከልብህና ከአእምሮህ ብታከብር እግዚአብሔር አነስተኛዋንና የተዋረደችውን ሥራ ከአንተ አንሥቶ ከፍ ያለ ኃላፊነት ያለበትን ትልቅ ሥራ የምትሰጥበት ቀን ይመጣል።

በለንደን ከተማ በመኖሪያ ክፍላቸው ወጥ ቤት ውስጥ በዕቃ ማጠቢያ ገንዳዋ ላይ ያንድ ጓደኛዬ ሚስት እንዲህ የሚል ጽሑፍ አላት። «የተቀደሰ አገልግሎት በቀን ሦስት ጊዜ እዚህ ይፈጸማል» በዚህ ሐሳብ የሰማይ መንፈስ ያለበት ይመስለኛል። እግዚአብሔር አንድ ቀን ለከፍተኛ ነገሮች እንደጠራንና እንዲያምነን የሚያደርጉት እነዚህን በመሳሰሉ ጥቃቅንና ዝቅተኛ ተግባሮች ታማኞች ሆነን መገኘት ነው።

ለመሪነት ለመመረጥ የሚያስችሉ ነገሮች እነዚህ ከሆኑስ አሁኑኑ ሥራችንን እናቁም። የእያንዳንዱ ሰው ዓይን አትኩሮ የሚመለከታቸውን ተግባሮች በጥንቃቄ የምንሠራውን ያህል አንድ ሰው እንኳ ሊያይ የማይችለውን በጥንቃቄ አልሠራንም። ለእግዚአብሔር ከማገልገል ስለምናገኛቸው ጥቅሞች ብቻ እንደጊዜው ሁኔታ ልናገለግለው ሳንሞክር አልቀረንም። ወዮልን እኛ ጎስቋሎች ሰዎች። እስከ አሁን ታማኞች ስላልሆንን የወደፊቱን በድፍረት ልንገጥመው እንችላለን ወይ? ወይስ እናቋርጥ? አ፣ አይሆንም ጥቂት ጊዜ ቀረኝ።

ኢያሱ ጥላ ነው ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን ግን እውነተኛው የጥላው አካል ነው ። ኢየሱስ ከለመታወቅ በተነሣ ጊዜ ለሦስት ዓመት ሥራ የሰላሣ ዓመት ዝግጅት አድርጓል ። ለወላጆቹ ታዘዘ ። የቤተሰቡን ሥርዓት ፈጸመ ፤ በናዝሬት ከተማ እናጢ ሆኖ በመሥራት ሞያተኝነትን አከበረ ። ከዚያ ሱቅ ያልተሟላ ዕቃ ተገኝቶ አይታወቅም ። በየሰንበቱም ወደ መስጊድ ሄዶአል ። በጊዜውም ያች መስጊድ የሞተች ነበረች ። የወደፊት ሥራው ምን እንደሆነ በማያውቁ ቤተ ሰብ መካከል ኖረ ።

አንድ ቀን ከለመታወቅ ወጣ ፣ ተጠመቀና ሥራውን ጀመረ ። ያንጊዜ ከሰማይ ድምፅ መጣና «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» አለ ። ሰላሣ ዓመት በውጪ ሳይታወቅ ከወላጆቹ ጋር የኖረበትን ጊዜ እግዚአብሔር ማንተሙን አኑሮ በታል ።

የናዝሬቱ ኢየሱስ ዛሬም አለ ፤ እርሱም የቤተ ክርስቲያን ራስና መሪዋ ነው ። የእርሱ ታማኝነት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በምዕመናን ገብቶ ኃይልና ክብር እንዲሰጣቸው ሊያደርግ ይችላል ። ቅንቅን የበላቸውን ያለፉ ዓመቶቻችንን ሊያድስ ይችላል ። ባለፉት ጊዜያት ወደ እርሱ በመራመድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደምናደርግ ሁሉ አሁንም ቢሆን የተውናቸው ኃጢአቶችና ውድቀቶች ከቶ አያደናቅፉን ። ይህን መጽሐፍ የሚያነብ ማንኛውም ሰው ልቡ የተዋረደና ተስፋ የቆረጠም የእግዚአብሔርን ሠራዊት ለመምራት ከተሰጠው ኃላፊነት ያለፈው ታሪኩና መጥፎ ስሙ የሚያግደው ቢመስለው በጌታዬ ስም የምመክረው ይህን ነው «በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና ፤ አይዞህ ፤ አትፍራ አትደንግጥ ።»

ሁለተኛ ፣ ለመሪነት ለመመረጥ የሚያስፈልገው «ግልፅ የሆነ ጥሪ» ነው ። «በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ፤ ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ፣ አልጥልህም ፣ አልተውህም ፤ ለአባቶቻቸው ፡— እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና ጽና ፡— አይዞህ» ኢያሱ ፩ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ለመንፈሳዊ መሪነት ግልፅ የሆነ ጥሪ ለሚያስፈልገው ኃይል ሁለተኛው ምንጭ ነው ።

ምድረ ከነዓን በማይቆጠሩ አእላፍ ባላጋራዎች እንደሞላች ኢያሱ ፈጽሞ አውቆአል ። እያንዳንዱ ስንዝር ጉዞ በጠላት እንደሚመከት ተረድቶአል ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር መጠራቱን ያረጋገጠ ሰው አይበገርም ደግሞም አያመነታም ። ኢያሱ የራሱን ድካምና አለመብቃት ያውቃል ። በምድሪቱም ትልቅ አምባና ጽኑ ምሽግ ያላቸው ከተሞች እንዳሉ አይቶአል ። ከሁሉም በላይ እዚያ ሳይደርስ ታላቅና ሰፊ የሆነውን የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር እንዳለበት ተገንዝቦአል ። ለእግዚአብሔር መቆምን የሚመርጡ ሰዎች የዘወትር ዋጋቸው በዓለማውያን ዘንድ ውርደት ፣ ትችት ፣ ወቀሳና ትዝብት መሆኑን ያውቃል ። ነገር ግን ዓይኖቹን ከእነዚህ ነቅሎ የተገለጠለትን የእግዚአብሔርን ዓላማ እየተመለከተ ራሱን ፣ ነፍሱንና ሥጋውን ያለውንም ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸምበት መሣሪያ አድርጎ ፈጽሞ ለእግዚአብሔር አስረከበ ።

ስለዚህ ለእግዚአብሔር ልታደርግ ስለጀመርከውም ማናቸውም ዓይነት ሥራ የምጠይቅህ ጥያቄ «የተገባህ ነህን ?» የሚል አይደለም ፣ ግን «የተጠራህ ነህን ?» የሚል ነው ። ለክብር ነውን ወይስ ስለተጠራህ ነው ? በእግዚአብሔር ፊት ለዚህ ጥያቄ ከምትሰጠው መልስ የበለጠ አንዳች ነገር የለም ።

በለንደን አንድ ካህን ዘመዱን ሊጎበኝ ሄደ ። ዘመዱም «በቤተ ክርስቲያንህ ትልቅ መንፈሳዊ መታደስ እንዳለ ሰምቻለሁ» አለ ። ካህኑም «አዎን ግሩም የሆነ ጊዜ ነበረን» አለው ። ዘመዱም «ለመሆኑ ስንት አዲስ ምዕመናን በተጨማሪ ተመ ዘገቡ» አለው ። ካህኑም «ወንድሜ ሆይ ፣ ተጨማሪ አልከኝ ? እንዲያውም የተባረከ መቀነስ ነበረን» አለው ።

ማንኛችሁም በቤተ ክርስቲያናችሁ ሥልጣን ፣ ስም ፣ ማዕረግና ክብር ቢፈልግ አሁኑኑ ሥራውን ያቁም ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቅ ። ዛሬ በቤተ ክርስቲ ያናችን የምንፈልጋቸው የእግዚአብሔር ሰዎች መንፈስ ሰብሮ ያደቀቃቸውንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን ክብር ብቻ የሚመኙትን ሰዎች ነው ።

ከተዋረዱና ልባቸው ከተሰበረ ሰዎች እርሱ ስለጠራቸው ብቻ ወደ ክብር የሚ ነሱትን ብርቱ ሠራዊት እንዲያስነሣ እግዚአብሔርን እንለምነዋለን ። ወንዙ በፊታ ችን ነው ፤ ነገር ግን ይህ ቢደረግ እግዚአብሔር ይመስገን እንሻገረዋለን ። የተመሸ ጉትን ከተሞች እንመታለን ፣ እግዚአብሔርም ተራሮችን ያርቃል ፣ ባሕሩ ይደርቃል ከተሞቹም ይወድቃሉ ። የእግዚአብሔር ሕዝብ ማድረግ ያለባቸው ተነሥተው ከጌታ ችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ፊት መገሥገሥ ነው ።

ሥራውን በትክክል ያወቀውን ጌታ ላስታውስህ ። ያለ ፍርሃት በቀጥታ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደበትን ኃይልና ድፍረት ከየት አገኘ ? ወደ ቀራንዮ ከረብታ ወጥቶ ኃያል ሳለ በድካም የተሰቀለበትን ኃይል ከየት አገኘ ? አስተውል ፤ «የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን ልፈጽም አልመጣሁም» አለ ። ደግሞም «አምላኬ ሆይ ፣ ፈቃድህን ማድረግ ደስ ይለኛል ፤ ምግቤ የላከኝን ፈቃድ ማድረግና መፈጸም ነው» አለ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወቱ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ተከራክሬ የእግዚአብ ሔርን ፈቃድ ከማድረግ እንዲያሳስተው አላደረገም ።

የኃይል ምሥጢር ይህ ነው ። እግዚአብሔር ከመረጠልህ መንገድ ሊያስወጣህ የሚስብህ ነገር በልብህ እንዳለ የምትመረምረውን ዛሬ ወስን ። በአንተና ለአንተ ከታ ቀደው ከመልካሙ ፤ ከፍጹሙና ደስ ከሚያሰኘው የእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል አንዳች ነገር እንዲቆም ከቶ አትፍቀድ ።

ሦስተኛው ለክርስቲያን መሪነት የሚያስፈልገው የኃይል ምንጭ የእግዚአብ ሔር ቃል በውስጣችን መኖር ነው ። ኢያሱ ምዕራፍ አንድ ቁጥር ስምንትን ተመ ልከት ፤ «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብ ቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው ፣ የዚያን ጊዜ መንገድህ ይቀናልሃል

ይከናወንልሃልም ፤» የእግዚአብሔር ቃል ቀንና ሌሊት ዘወትር በልባችን ቢኖር እግዚአብሔር ራሱ በመንፈሱ በውስጣችን ለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ነው ።

በቃሉ አማካይነት የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወትህን ይሞላና ልብህን ይወርሳል ። ለመሪነት የሚፈለገውም ኃይል ምሥጢር ይኸው ነው ። የልጁ ሀብት መሆን ፣ በውስጣችን በሚያድረው ኃይሉ ብርቱዎች መሆንና በመንፈሱ መሞላት ማለት ነው ። መንገዱም የሚከተለው ነው «በቀንና በሌሊትም አስበው» ለቅድስና ከዚህ የተሻለ አቋራጭ መንገድ የለም ።

ይህን ከግል ኑሮዬ ነገርኩህ ። በዘመን ሽግግሉ ከሆነው መጽሐፍ እንደማገኘውና እንደማምነው አንድ ሰው ቅዱስ መሆን ከፈለገ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ቃሉን ቀንና ሌሊት መከተል ነው ። ሰው አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አድርጎ የተቀደሰውን ኑሮ ሲኖር ስለ እግዚአብሔር ዝቅ ቢያደርገው አምላኩን በመቃወም የተሰጠውን ክብር ፣ ዕድልና ሥልጣን ቢያዋርድ «ለተዘጋ በር የሚከፍለውን ዕዳ ማወቅ ይገባዋል ፤» ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ከቤተ ሰቡ ከተዘጋው በር ውጪ የሆኑ ይገኛሉ ። ማንኛውም ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት ለብቻው በጉልበቱ ተንበርክኮ ካለበት ጊዜ ይልቅ መሪ ሊሆን አይችልም ።

ለማንኛችሁም ቅድስና የጥንቆላ ጥበብና የምሰጣችሁ ተአምራታዊ ችሎታ የለኝም ። ለመንፈሳዊ ኃይላችሁ የምሰጣችሁ ከዚህ የተሻለ አቋራጭ መንገድ የለም ። ላደርግላችሁ የምችለው አንድ ነገር ይህ ነው ፤ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ተመለሱና «ቀንና ሌሊት አስቡት» በእግዚአብሔርም ፊት በጸሎት በግምባራችሁ ተደፉ ። የክርስቲያን ንግዱና ትርፉ በቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለም ፤ ግን ከተዘጋው በር በስተውስጥ ነው ።

ጌታችንም የተራመደው ጐዳና ይኸው ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ መጽሐፉ (ብሉይ ኪዳን) ያለውን ሥልጣን አመነ ። ለጋብቻ ኪዳን ማሠሪያ መሠረት መሆን ጠቀሰ ። የራሱን ትንሣኤ ለማረጋገጥ የዮናስን ታሪክ አስተማረ ። ከሰይጣን በተጋፈጠና በፈተናው ወቅት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቀመ «ተጽፎአል» አለ ። የእርሱ ኃይል ሕይወቱን ከእግዚአብሔር ቃል ከማዋሃዱ መጣ ።

«እኔ የምነግራችሁ ቃል» አለ ፣ ጌታ ኢየሱስ «እርሱ መንፈስም ሕይወትም ነው ፤» በእግዚአብሔር ቃል መሞላት እርሱ ራሱ በእኛ ለማደሩ ማረጋገጫ ነው ። እንግዲህ እግዚአብሔርን አመስግኑ ፤ የሚሰነዘርብን መሣሪያ ሁሉ አይጸናም ። ለፍርድና ለትችት በሚሰነዘርብን ምላስ ሁሉ ይፈረድበታል ። የእሳት ማንደጃው እቶን ሰባት እጥፍ ቢሞቅም እርሱ ከእኛ ጋር ነው ፣ ወንዙ ሰፊና ትልቅ ቢሆንም ከቶ እንደማያሰጥመን ተስፋ ሰጥቶናል ። «አትፍራ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና» ያን ጊዜ ፈሪና ደካማው አሸናፊ ይሆናል ። ምክንያቱም የሰው ትምክህት ለማስቀረት እግዚአብሔር ፈቃዱን ሊገልጥ በደካሞች ሰዎችና ምንም በልሆኑ ነገሮች ይጠቀማል ። እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው እንዲህ ያለ ነው ።

የሚፈለገው የቀድሞው የታማኝነት አገልግሎት፣ አሁን የማይነቀፍ ሥራና በእግዚአብሔርም ቃል መሞላት ከሆነ እንዴት አድርገን ለእርሱ ብቁዎች እንሁን? ድካማችንን መርበትበታችንንና ፍርሃታችንን ወደ እርሱ እናምጣ፣ በውስጣችንም ለሚያድረው ብሩክና ቅዱስ መንፈሱ በመንበርከክ ራሳችንን እናስረክብ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የተገለጡ ብሩክ ጠባዮችና ባሕርዮች ሁሉ በኑሮዬና በኑሮህ ተገልጠው በሕይወታችንም እንዲዋሃዱ እንጸልይ።

የሚፈለግብህ ነገር አለ፣ ልትከፍለው ትፈቅዳለህን? ለአንተ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ከምታምን ውጪ የሆነውን ሌላውን ኃላፊነት ሁሉ ከሕይወትህ ሰርዝ። ቃሉን ያለማቋረጥ ከማሰብና ከመጠበቅ የሚከለክሉህን ክብርም ሆነ ሥራ ማናቸውንም ተግባር በሙሉ ኃይልህና ልብህ እምቢ በል፣ አትቀበል። የምንኖርበት ዘመናችን ሰዎች የተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ ከፊታቸው አድርገው ጸጥ ብለው እግዚአብሔርን እንዲናገር የመጠባበቅ ጥበብ የጠፋበት ዘመን መናፍቃን ነው።

ከዛሬ ጀምረህ ቅድስናን ለማድረግ ራስህን አስለምድ፣ ክብርንና ማዕረግን በመፈለግ በድለህ እንደሆነ አገልግሎትህን አቁም ወይም ለብቻህ ኃጢአትህን ለእግዚአብሔር ተናዝዘህ ከእርሱም ታረቅ። ያን ጊዜ በቤተ ክርስቲያንና በመሪነት አማካይነት የሰማይ ብርሃን፣ አምላካዊ ሥልጣንና ኃይል ይገለጣል፣ የእግዚአብሔርም የጸጋ ወንዝ በያንዳንዳችን ልብና በእኛም በኩል ለበረከት ወደ ሌሎች ይጎርፋል።

ምዕራፍ ፫ ።

# ትርፍና ጉዳቱን መገመት ።

ኢያሱ ፩ ፥ ፲፩ ።

«የነዌም ልጅ ኢያሱ ፥— ሄዳችሁ ምድሪቱንና ኢያሪኮን እዩ ብሎ ከሰጢም ሁለት ሰላዮች በስውር ላከ ። ሄዱም ረዓብም ወደሚሉአት ጋለሞታ ቤት ገቡ ፥ በዚያም አደሩ ። የኢያሪኮም ንጉሥ እነሆ ፥ ሰዎች ከእስራኤል ልጆች አገሩን ሊሰልሉ ወደዚህ በሌሊት ገቡ ሲባል ወሬ ሰማ ። የኢያሪኮም ንጉሥ አገሩን ሁሉ ሊሰልሉ መጥተዋልና ወደ አንቺ የመጡትን ወደ ቤትሽም የገቡትን ሰዎች አውጪ ብሎ ወደ ረዓብ ላከ ። ሴቲቱም ሁለቱን ሰዎች ወስዳ ሸሸገቻቸው ፥ እርስዋም ፥— አዎን ፥ ሰዎቹ ወደ እኔ መጡ ከወዴት እንደሆኑ ግን አላወቅሁም ፥ በሩም ሲዘጋ ሲጨልም ሰዎቹ ወጡ ፥ ወዴት እንደሄዱ አላውቅም ፥ ፈጥናችሁ አሳድዱአቸው ፥ ታገኙአቸውማላችሁ አለች ። እርስዋ ግን ወደ ሰገነቱ አውጥታቸው ነበር ፥ በዚያም በረበረበችው በተልባ እግር ውስጥ ሸሽጋቸው ነበር ። ሰዎቹም ወደ ዮርዳኖስ መሻገሪያ በሚወስደው መንገድ አሳደዱአቸው ፥ አሳዳጆችም ከወጡ በኋላ በሩ ተቆለፈ ።

እነዚህም ሳይተኙ ሴቲቱ ወደ እነርሱ ወደ ሰገነቱ ወጣች ። ሰዎቹንም እንዲህ አለቻቸው ፥ እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደ ሰጣችሁ ፥ እናንተንም መፍራት በላያችን እንደ ወደቀ ፥ በምድሪቱም የሚኖሩት ሁሉ በፊታችሁ እንደ ቀለጡ አወቅሁ ። ከግብፅ ምድር በወጣችሁ ጊዜ እግዚአብሔር የኤርትራን ባሕር በፊታችሁ እንዳደረቀ በዮርዳኖስም ማዶ በነበሩት እናንተም ፈጽማችሁ ባጠፋችኋቸው በሁለቱ በአሞራውያን ነገሥታት በሴዎንና በዐግ ያደረጋችሁትን ሰምተናል ። ይህንም ነገር ሰምተን ልባችን ቀለጠ ። አምላካችሁም እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነውና ከእናንተ የተነሣ ከዚያ ወዲያ ለማንም ነፍስ አልቀረለትም ። አሁንም እባካችሁ በእግዚአብሔር ማሉልኝ በእውነትም ምልክት ስጡኝ ፥ እኔ ለእናንተ ቸርነት እንደሠራሁ እናንተ ደግሞ ለአባቴ ቤት ቸርነት እንድትሠሩ አባቴንና እናቴንም ወንድሞቼንና እህቶቼንም ያላቸውንም ሁሉ እንድታድኑ ሰውነታችንንም ከሞት እንድታድኑ ። ሰዎቹም ይህን ነገራችንን ባትገልጪ ነፍሳችን በነፍሳችሁ ፋንታ ለሞት ይሆናል ፥ እግዚአብሔርም ምድሪቱን በሰጠን ጊዜ ከአንቺ ጋር ቸርነትንና እውነትን እናደርጋለን አሉአት ።

ቤትዋም በከተማ ቅጥር የተጠጋ ነበርና እርስዋም በቅጥሩ ላይ ተቀምጣ ነበርና ከመስኮቱ በገመድ አወረደቻቸው ። እርስዋም አሳዳጆቹ እንዳያገኙአችሁ ወደ ተራራው ሂዱ አሳዳጆቹም እስኪመለሱ ድረስ በዚያ ሦስት ቀን ተሰውራችሁ ተቀመጡ ፥ ኋላም መንገዳችሁን ትሄዳላችሁ አለቻቸው ። ሰዎቹም አሉአት ፥ እኛ ከዚህ ካማልሽን መሐላ ንጹሐን እንሆናለን ። እነሆ እኛ ወደ አገሩ በገባን ጊዜ ይህን ቀይ ፈትል

እኛን በወረድሽበት መስኮት በኩል እሰሪው ፥ አባትሽንም እናትሽንም ወንድሞችሽንም የአባትሽንም ቤተ ሰብ ሁሉ ወደ አንቺ ወደ ቤትሽ ሰብስቢ ። ከቤትሽም ደጅ ወደ ሜዳ የሚወጣ ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል ። ይህንን ነገራችንን ግን ብትገልጪ ከዚህ ከማልሽን መሐላ ንጹሐን እንሆናለን ። እርስዋም እንደቃላችሁ ይሁን አለች ፥ ሰደደቻቸውም እነርሱም ሄዱ ። ቀዩንም ፈትል በመስኮቱ በኩል አንጠለጠለችው ።

እነርሱም ሄደው ወደ ተራራው ደረሱ ፤ አሳዳጆቹም እስኪመለሱ ድረስ ሦስት ቀን በዚያ ተቀመጡ ። አሳዳጆቹም በመንገድ ሁሉ ፈልገው አላገኙአቸውም ። ሁለቱም ሰዎች ተመለሱ ፥ ከተራራውም ወርደው ተሻገሩ ፤ ወደ ነዌም ልጅ ወደ ኢያሱ መጡ ፥ የደረሰባቸውንም ሁሉ አወሩለት ። ኢያሱንም በእውነት እግዚአብሔር አገሩን ሁሉ በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶናል ። በአገሩም ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ በፊታችን ይቀልጣሉ አሉት ።

ኢያሱ ፪ ፥ ፩ — ፳፬ ።

በለፉት የመጽሐፈ ኢያሱ ጥናቶቻችን የብሉይ ኪዳን ምድረ ከነዓን በዚህ በምድር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በምንጠባበቀው የተሟላ ምድረ በረከት (መንፈሳዊ ኑሮ) እንደሚመሰል እንደተረዳን አምናለሁ ። የእግዚአብሔር ማዳን ዓላማ ይህ ነው ፥ ሊያስገባን አስወጣን ።

ወደዚህም የበረከት አገር በመልካም ጠባይ ፥ በትግል ፥ በደግነትና በምግባር መግባት አይቻልም ። የምድሪቱ በረከት በብሉይ ኪዳን ለኢያሱ በሐዲስ ኪዳን ለኢየሱስ አደራ ተሰጥቶአልና ፥ በባለአደራው አማካይነት በረከቱ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሊሰጥ ይችላል ። ደግሞም በሃይማኖት እንቀበለዋለን ፤ «የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቼአለሁ» ለእኛም ዛሬ እንደዚሁ ነው ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ባርከናል ፥ ነገር ግን እያንዳንዱን በረከት ተቀብለን የግላችን ሊሆን የሚቻለው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በሃይማኖት ብቻ ነው ።

ከታሪኩ ጉልህ ሆኖ እንደሚታየው የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ምድረ ከነዓን መሻገራቸው ሲደርስ ገና ሦስት ቀን መቆየት እንዳለባቸው ወደሚናገረው ክፍል መጣን «ኢያሱም የሕዝቡን አለቆች ፦— በሰፈሩ መከከል እለፉ ፥ ሕዝቡንም ፦— አምላካችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ ምድር እስከ ሦስት ቀን ይህን ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ልትወርሱአት ትገቡባታላችሁና ስንቃችሁን አዘጋጁ ብላችሁ እዘዙአቸው ብሎ አዘዘ» ኢያሱ ፩ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ።

ሁላችንም ማድረጉ የሚያቅተን ዓይነተኛውና ታላቁ ቁም ነገር ምንም ሳንሠራ ዝም ብለን ተቀምጠን ተስፋውን እስክንወርስ መጠባበቅን ነው ። እግዚአብሔር በመጠባበቅ ጊዜ ውስጥ የሚፈጽማቸው ታላላቅ ቁም ነገሮች ይኖራሉ ፥ ነገር ግን ሕዝቡ እነዚህን ቁም ነገሮች ለጊዜው ስለማያዩና ስለማይገነዘቡ ትዕግሥት ያጣሉ ።

በትዕግሥት ዝም ብለን ተቀምጠን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምንወርሰው በረከት ፍችና ጥቅም መገመቻ ስለሆነው የመጠባበቅና የመጠበቅ ጊዜ አብረን እናስብ ።

ሕዝቡ ሦስት ቀን እንዲቆዩና ከዚያ በኋላ ዮርዳኖስን እንደሚሻገሩ ለምን ተነገ ራቸው ? ከመጽሐፉ በዚህ ክፍል ለማስተዋል የማያስቸግሩ ሦስት መንፈሳዊ እውነ ቶችን እናገኛለን ፤ መንፈስ ቅዱስም በሕሊናችን ይቅረጽልን ።

በመጀመሪያ ፥ አንዲት የምትድን ነፍስ ነበረች ። ታሪኩ በመጽሐፈ ኢያሱ በሁለተኛው ምዕራፍ ይገኛል ። ኢያሱ ሁለት ሰላዮችን ወደ ኢያሪኮ ላከ ፥ እነርሱም ወደ ረዓብ ቤት መጡ ።

በኢያሪኮ ከተማ ኑሮ እንደ ወትሮው ይካሄዳል ፥ ተግባሮቹም እንደተለመው ይሠራሉ ። ከተማዋ ግን ከእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ነበረች ። የከተማዋ ነዋሪዎች በእነርሱና ከማዶ እየገፉ በመጣው ወራሪ ሠራዊት መካከል ባለው ታላቅ ወንዝ ተመኩ ። በከተማቸው በቅጥሮችዋና በምሽጎችዋ ኮሩ ። በእግዚአብሔር ፊት ግን የከፋታቸው ጽዋ ሞልቶአል ። ከኢያሪኮ ነዋሪዎች ጋር የሰላም ንግግርና ዕርቅ ማድ ረግ አያስፈልግም ፥ ከሁለት ሳምንታት በኋላ እግዚአብሔር በፍርድ ይመታታል ። ከተማዋም ፍራሽ ፥ ብናኝና ድብድብ ሆና ትቀራለች ።

ነገር ግን በሕያው እግዚአብሔር ያመነች አንዲት ነፍስ በከተማዋ ነበረች ። ጽኑና የተሟላ ሃይማኖት እንኳን አልነበረም ። ግን ረዓብ በሕያው እግዚአብሔር አምናለች ። ይህንም ለመግለጽ አላፈረችበትም ። በዕብራውያን መልእክት ምዕራፍ አሥራ አንድ የሃይማኖት አበቶች ሲጠቀሱ የሃይማኖትዋን ሁኔታ ለመግለጽ እርስ ቀም ተጠቅሳለች ። ሐዋርያው ያዕቆብም የረዓብ ሃይማኖት እንደሌሎች ሃይማኖት ሳይሆን በሥራዋ ተገለጠ ሲል ይመሰክርላታል ። ቀይ ፈትል በመስኮትዋ በማንጠል ጠል ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለመቆጠርና ከጥፋት ለመዳን በቂ እምነት ነበራት ።

ስለ ሃይማኖትዋና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሰላዮች ስለ ሰጠችው መጠለያ የም ድረ ከነዓን በረከት ሁሉ ተካፋይ ሆነች ። የዚህች ሴት ሃይማኖት በሥራዋ ተገለጠ ። ሥራዋም በረከትን አተረፈላት ።

አንዲት የምትድን ነፍስ ነበረች ፥ ያች ነፍስ እስከትድን የእግዚአብሔር ፍርድ ለጊዜው ታገደ ፥ እግዚአብሔር ዘወትር በዚሁ ዓይነት በሰዎች ይሠራል ። በሰዶም ከተማ አንድ ጻድቅ ሰው ነበረ ፥ እግዚአብሔር ከከተማዋ እንዲወጣ ያቀደለት ሰው እስኪወጣ ድረስ በዚያች ከተማ ምንም ሊያደርግ አልቻለም ፥ አንዲት ደካማ ኃጢአ ተኛና ርኩስ ሴት የኢየሱስን የልብሱን ጫፍ ነካች ። እርሷን እስኪያድን ድረስ ወደ ቀራንዮ ያደርግ የነበረ ጉዞው ለጊዜው ተቋረጠ ። አንድ ድሀና ዕውር ለማኝ ከመን ገድ ዳር ጮኸ ፥ «ኢየሱስ ሆይ ፥ ማረኝ» ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አዙሮ ስለነበረ ደቀ መዛሙርቱና ሌሎች ሰዎች ሊያቆሙትና ሊመልሱት ያልቻሉትን አንዲት የለ ማኝ ነፍስ አደረገች ። ያ ጩኸት ኢየሱስን አቆመው ። የጌታችን አደራረግ ሁልጊዜ ይኸው ነው ። አንድ ሰው እንኳ እንዲጠፋ ፈቃዱ አይደለም ።

ችና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ናቸው ። የእነዚህ ሁለት ተኩል ነገዶች ታሪክ በአሪት ዘኍልቁ ምዕራፍ ፴፪ ይገኛል ።

በምድረ በዳ ጉዞ ጊዜ የሮቤል የጋድና የምናሴ ነገዶች ወደ አንዲት በጣም ለምለም ምድር መጡ ። በምድሪቱም ለከብቶቻቸው መሰማሪያ ጥሩ ስፍራ አዩ ። ከፍጥረትዋ ሀብታምና ለምለም አገር ነበረች ። እነዚህም ነገዶች ብዙ የእንስሳ መንጋዎች ስለነበሩአቸው ሀብታሞች ነበሩ ። ስለዚህ ወደ ሙሴ መጡና «ይህን ምድር ለባሪያዎችህ ርስት አድርገህ ስጠን ፣ ወደ ዮርዳኖስም ማዶ አታሻግረን» አሉት ። ማንም ቢሆን የሚፈልገው ይህን ነው ። ወደ ከነዓን መግባት አንፈልግም ። እዚያ ስትደርሱ በሚገጥማችሁ መከራ መጨነቅ አንሻም ። ለእኛ እዚሁ ይሻለናል ።

አንድ ሰው ራሱ የሚኖርበትን የኑሮ ደረጃ ራሱ ለመምረጥ መብት ስላለው ሙሴ ምንም ሊያደርግ አልቻለም ። ሐሳባቸውንም ተቀበለ ። ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ያለችውን የምድረ በዳውን ለምለም ክፍል እንዲወርሱ ተፈቀደላቸው ። ሆኖም ይህን ከማግኘታቸው በፊት የቀሩት ወንድሞቻቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ ርስታቸውን ለመውረስ በሚያደርጉት ውጊያ ተካፋይ ለመሆን ስለተስማሙ አሁን ይህን ማድረግ ይገባቸዋል ። እንዲያውም ሙሴ የጦሩ ቀዳሚዎች እንዲሆኑ አዘዛቸው ፤ እነርሱም እንደቃልህ ይሁን አሉት ። የሮቤል የጋድና የምናሴ ነገዶች የጦሩ ፊታውራሪዎች ሆነው ወደ ምድረ ከነዓን መግባት አለባቸው ። ኢያሪኮንም ሲዞሩአት የመቀደም ስፍራ ተሰጣቸው ። የምድሪቱን ፍሬና ጣዕም የማሸነፍንም ደስታ ከቀመሱ በኋላ አሁንም የበረሃ ዳርቻ ወደሆነችው የምርጫቸው አገር መመለስ ይፈቅዱ እንደሆነ ኢያሱ ጠይቆ ከፈለጉ መቻላቸውን ያረጋግጥላቸዋል ።

አሁን ኢያሱ ፡— ምርጫችንን ከመውረሳችን በፊት እናደርጋለን ብለው የገቡት ቃል እየታወሳቸው እነዚህን ሁለት ተኩል ነገዶች ሲያነጋግርና የሚመርጡት ምን እንደሆነ ሲጠይቃቸው እንዴት ያለ ታሪካዊ ጊዜ ነው ? ፍላጎታቸውና ምኞታቸው እንዳጸደቀላቸው አስተውል ። የሰጡትን ተስፋ ሊፈጽሙ ፣ ሠራዊቱንም ቀድመው ሊመሩና ድልንም ሊያጣምሙ ፍጹም ፈቃደኞች ናቸው ። ነገር ግን አሁንም ወደ በረሃው ተመልሰው በኑሮው ሊደሰቱ እንደቆረጡ ናቸው ፤ «እዚሁ ይሻለናል» አሉ ።

ሃይማኖቱ እንደምንም ደካማ ወይም ጽኑ ቢሆንም እግዚአብሔር ሕዝቡን ሁሉ እያንዳንዱን የተዋጀ ነፍስ በተሰቀለው ኢየሱስ ጠልሎታል ። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በውስጥዋ ካሉት ከተመረጡ የእግዚአብሔር ምዕመናን ጋር ዓለም ሳይመሠረት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በደኅንነት ስፍራ ተደርገዋል ። እግዚአብሔር ደኅንነትን ያዘጋጀላቸውን ወንዶችና ሴቶች አንድ ባንድ አንሥቶ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ አኑሮአቸዋል ። እግዚአብሔር አለመብቃቱን የተገነዘበውንና እጅግ ደካማ የሆነው ክርስቲያን ከሴቶች ከተወለዱት ጽኑዎች የቤተ ክርስቲያን አዕማድ ከሆኑት ቅዱሳን ጋር በአንድነት ወስዶ ሙሉዋን ቤተ ክርስቲያን በደኅንነት

ምድር አድርጎአታል ። ደካማው ሆነ ብርቱው ክርስቲያን ወደ ድል ለመድረስ አይታገልም ፣ ነገር ግን በድል ሜዳ ቆሞአል ። ወይም በረከትን ለማግኘት አይፍጨረጨርም ፤ ግን ብድግ ብሎ እግዚአብሔር አዘጋጅቶ ያቀረበለትን ይቀበላል ። እኛም አሁን ያለንበት አቋም ይህ ነው ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመንክ ከሆንክ ምንም ያህል ደካማ ብትሆን ፣ ምንም ያህል ዓለማዊና ሥጋዊ ብትሆን ፣ ሃይማኖትህና ክርስቲያንነትህ ደካማ ቢሆኑ በእግዚአብሔር ፊት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በደኅንነት መሬት መሆንህን አረጋግጥልሃለሁ ። የእኛ አቋም አሁንም እርሱ ነው ።

ነገር ግን የክርስቲያንነት ሕይወታችንን የት እናሳልፈዋለን ወይም ምን ዓይነት የክርስቲያንነት የኑሮ ደረጃ እንኖራለን ለሚለው ጥያቄ መልሱን ራሳችን እንምረጥ ። በከነዓን በረከት ለትንሽ ጊዜ እደሰታለሁ ፣ ከበረሃውም ወጥቼ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ይህን ዮርዳኖስን እሻገራለሁ ። በኢየሱስ የግሌ የሆኑትን ድሎች እካፈላለሁ ። ግን በኃጢአት ልጠመድ እችላለሁ ። በዓለማዊነት ልማረክ እችላለሁ ። ዓለምንም በመምሰል እቀጥና በዲያብሎስ ወጥመድ ለጥፋት እጠመዳለሁ ።

አንድ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ በእውነት አዲስ ተወልዶ ልጁ ከሆነ ከቶ አይጠፋም ። አማኝ ዘላለማዊ ጥበቃና ደኅንነት እንዳለው አምናለሁ ። እንዲህም ስል እውነተኛው ምዕመን ማለቴ ነው ። እውነተኛ ምዕመንም ሕይወቱን ራሱንና ያለውን ሁሉ እንዳለ ያለ አንዳች ቅሬታ ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠ ነው ። በክርስቲያን ኑሮአችንም በማናቸውም ወቅት ረጋ ብለን በኢየሱስ ፊት ውስጥ እያየን «ጌታዬ ሆይ ፣ ካንተ በመራቅ ብዙ ሄጀአለሁና አሁን በቃኝ ፣ ይህም ጠርነት ብርቱ ውጊያውም ኃይለኛ ነውና አልችለውም ። ጌታዬ ሆይ ፣ ካንተ ብዙ ርቄአለሁና ይብቃኝ» እንለዋለን ።

«እግዚአብሔር አንደኛ የሆኑ ስጦታዎቹን ፈተናውን ለሚደፍሩ ይሰጣል ። አንደኛ የሆኑ ስጦታዎቹን ለማይቀበሉ ሁለተኛውን ይሰጣል ። ተስፋውንና በረከቱን የሚያስቀሩብን ሁልጊዜ ግልፅ የሆኑ ፈተናዎች አይደሉም ። ቀላልና የማይታወቁ ፈተናዎች ከላቀው በረከት የሚከለክሉን ናቸው ።»

እነዚህ ሁለት ተኩል ነገዶች ያደረጉት ምርጫ አሳዛኝ ፍጻሜ ምን እንደሆነ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ በምዕራፍ አምስት አንብብና አስተውል ። እስራውያን እስራኤልን በወጉ ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተማረኩት እነዚህ የእግዚአብሔርን ደግ ነገሮች የቀመሱ ፣ የእግዚአብሔርን ማሸነፍ ያዩና የእግዚአብሔርንም ሥራዊት ወደ በረከት አገር የመሩ ሁለት ተኩል ነገዶች ናቸው ። ተማርከውም ከቶ ወደ አገራቸው አልተመለሱም ። አንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ በረከት የመሩ ቢሆኑም ስንኳ ድል ሆነው በሪያዎች በመሆን ተዋረዱ ። መጽሐፈ መሳፍንት ፭ ፣ ፲፮ እንዲህ ይላል ፣ «በሮቤል ፈሳሾች አጠገብ ታላቅ የልብ ምርምር ነበረ» በእውነትም እንደነበረ አምናለሁ ። መረጡ ፣ በረከቱን ቀመሱ ፣ ወደ ተስፋው ምድር ገብተው ረገጡአት ፣ ነገር ግን ዓለምንና ደስታውን ፣ ርኩሰቱን ፣ ምኞቱንና ኃጢአቱን መረጡ ፣ በእርሱም ተያዙና ተጠመዱ ለዘላለምም ወደቁ ተመልሰው አልተነሡም ።

አንድ ሰው ክርስቲያንነቱን እንዴት እንደጀመረው ማሰብ ዋጋ የለውም። የሚ ጠቅመው ግን እንዴትና የት እንደሚጨርሰው ማወቅ ነው። በአንድ መንፈሳዊ ስብሰባ ውስጥ ክርስቶስን የግል አዳኝህ አድርገህ መቀበል አለመቀበልህን ሰባኪው ሲጠይቅህ በሺህ ሰው ፊት እጅህን አውጥተህ ንስሐ ለመግባትህ ማረጋገጫ መፈረም ወይም የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን መመዝገብ አንድ ነገር ነው። እውነት እንደ ሆን እግዚአብሔር ይብርክህ። ዳሩ ግን ዋናው ነገር አንድ ጊዜ ይህን ከወሰንህ በኋላ በምድረ በረከት መኖርን ትቀጥል እንደሆነ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ትራመዳለ ህን ? በሚቃወሙህ ሁሉ ፊትና በፈተና ሁሉ ባለመሰልቸት በትዕግሥት ትገፋበታለ ህን ? ባለመጠንቀቅ ተንሸራትተህ ብትወድቅ ተነሥተህ ጭቃውን አራግፈህ ጉዞህን ትቀጥላለህን ወይስ ወደኋላ ተመልሰህ ኑሮህን በርኩሰትና በኃጢአት ታሳልፋለህ ?

በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጊዜ በልጅነቴ በበልግ ወራት አንድ ቀን ከቀ ትር በኋላ ከአባቴ ጋር በእንግሊዝ አገር ኒውካስል በሚገኘው ታይኒማውስ ውስጥ በሚገኙ የምሰሶ ፍርስራሽ መካከል እንዋብ ነበርን። በዙሪያችን ብዙ ሰዎች በወደ ቡዋም ውስጥ ብዙ መርከቦች ነበሩ። ከሩቅ የጪስ ጉም ታየ፣ እያደገም ሄደ፣ ቀጥሎም ብዙ የጦር መርከቦች በታይኒ ወንዝ ገቡ። በመርከቦቹ መካከል አንዲት መርከብ እየተንጋደደች ትንሳፈፋለች። እኔም እንዴት ልትሰፍፍ እንደቻለች አደነ ቅሁ። የመርከብዋ ስም ኤች፣ ኤም፣ ኤስሊዮን ነበረ። በዚያን ጊዜ የጀርመንን ጦር ከእንግሊዝ አገር ከመለሰው ከጁትላንድ ጦርነት መመለሱ ነበረ። ወደ ወደቡ እየቀረበች በመጣች ጊዜ ብዙ ትልልቅ ቀዳዳዎችና ጠባሳዎች እንዳሉአት አየሁ። ምሰሶዎችን፣ የጪስ መውጫዋንና የጠመንጃ ክፍልዋን አራግፋለች። መሸጋገሪያ ድልድይዋ ጠፍቶአል። ወለሏ ደቅቆአል። በመርከቦች የክብር ዘብና በመሰቢያ እየተመራች ወደ አገሯ ስትመለስ ሳለች ውኃ ይገባባትና ከእርስዋም ይወጣ ነበር። በእውነቱ በመርከብ መልክ የተሠራ ወንፊት ትመስል ነበር። ለጊዜው በቀረላት ወለል ላይ ሃያ አምስት መርከበኞችና አንድ መኰንን ቆመው በስብርባሪዋም የመን ግሥትዋ ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልብ ያየሁትን ከቶ እረሣ ይሆን ? የቻለው አፍ ሁሉ እልል አለ። ጭብጨባው የማያቋርጥ ሆነ። ጥሩንባ የነበረው መርከብ ሁሉ ነፋ። የደስታ መግለጫ መድፎች ተተኰሱ። ይህ ሁሉ ሲጠቃለል እልፍ ነጎድጓዶች በአንድነት ያነጎዱ ይመስል ነበረ። እነዚያ ሃያ ስድስት ሰዎች ከአንድ ሺህ አንድ መቶ መርከበኞች የተረፉ አሳዛኝ ቅሬታዎች ናቸው። መርከቧ ግን ታገለች እስከ መጨረሻው ተዋግታ ድል አድርጋ አገርዋን ከምርኮ አትርፋ በብዙ ቆስላ ብዙ ሰዎ ችም ሞተውባት ተስፋ ሳትቆርጥ እየተንሳፈፈች መጣች።

በዚህ ምድር በክርስቲያንነት ሕይወታችን ሳለን ሰይጣን በብዙ ያቆስለናል። አንዳንድ ጊዜ የሚያቆስሉን ዘመዶቻችን ናቸው፤ አንድ ቀን ግን ወደ ሰማይ ወደብ ደርሰን ያች መርከብ ያገኘችውን የሚመስል የደስታ አቀባበል ብናገኝ ጌታችንም «መልካም፣ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» ቢለን ከዚህ የበለጠ አያሻንም። ኢየሱስን ስናይ የምድሩ ችግር ሁሉ ተገቢ እንደነበረ እንረዳለን።

ሦስተኛም፣ በወንዙ ዳር በሚቆዩበት ጊዜ ቅድስና ሊፈጸም ነው። (በመጽሐፍ ቅዱስ «ቅድስና» የሚባለው ቃል ብዙውን ጊዜ ለተቀደሰ አገልግሎት መለየትን ያመለክታል፤) «ነገ፣ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ» ኢያሱ ፫፡፭። ድንቅ አድራጊው የእግዚአብሔር ኃይል ድንቅ ነገር ለማድረግ ሁል ጊዜ የሕዝቡን መቀደስ ይጠይቃል። ምዕመን ከጌታው ፊት ለፊት በቅድስና እየሄደ ለማስተማር ከተዘጋጀው በላይ እግዚአብሔር አብልጦ ኃጢአተኛን ለማዳንና ከፍርድ በታች ለሆነችው ዓለማችን በቤተ ክርስቲያን በኩል የሚሰጠውን መልእክት እንደ ገናንነቱ አጋንኖ እንደ ታላቅነቱ በታላቅ ኃይል እንዳይሰጥ በእኛ ቅድስና ውሱንነት የእርሱም ኃይል የተወሰነ ሆነ። እግዚአብሔር የሚገናኝበት የክርስቲያንነት የኑሮ ደረጃ እኛ እርሱን ለመገናኘት ስንዘጋጅ ባለንበት ደረጃ ላይ ነው።

እግዚአብሔር ድንቅና ተአምራት እንዲወራ ሁላችንም እንመኛለን። በጠባያችንና በአኗኗራችን በእሾህና አሜከላ ፋንታ በለስና ወይን እንዲያድግ ከከፋትም ይልቅ ደግነት እንዲታይብን እንዴት በብዛት ጸልየናል? ቤታችንና ትዳራችን ምድረ በዳ መሆኑ ቀርቶ ጽጌ ረዳ እንዲያብብበት፣ በጌታችንም ፊት ጥሩ መዓዛ እንዳለው ያታክልት ስፍራ እንድንሆን እንዴት በብርቱ ጸልየናል?

እግዚአብሔርም ሌላ ጴንጤቆስጤ እንዲሰጠንና በዚህ መካከለኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን በመንፈሳዊ መታደስ እንዲጎበኘን ለቤተ ክርስቲያናችን በብርቱ ጸልየናል። ታዲያ ተስፋችንና መጠባበቃችን ለምን ከንቱ ሆነ? እስከ አሁን ለምን በሕይወትህ አሜከላና ኩርንችት፣ በቤትህና በትዳርህ ምድረ በዳነት ይኖራል? በቤተ ክርስቲያናችን ለምን ኪሣራና ጉድለት ይገኛል። እግዚአብሔር ንጹሕና ቅዱስ ሰውን እንጂ ሙሌና ብልህ ሰውን አይፈልግም። እግዚአብሔር እንዲጠቀምብንና እንዲሠራብን የበቃን ንጹሐንና ቅዱሳን ነን ወይ? እግዚአብሔር ለበረከቱ የታመንን አድርጎ እንዲቆጥረን እንደሚገባ ተዋርደናልን ወይስ ክብሩን ለራሳችን እንፈልጋለን?

መቀደስ የምንችለው በሰላም አምላክ ብቻ ነው። ቅድስና የእግዚአብሔር አድራጎት እንደመሆኑ መጠን መንፈስ ቅዱስ ሞልቶን በውስጣችን አድሮ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወትና ባሕርይ በሕይወታችንና በኑሮአችን ከመግለጽ የበለጠ ወይም ያነሰ ነገር አይደለም። በእኛ በኩል ደግሞ የምናውቀውን ኃጢአት ሁሉ መተውማለት ነው። ይህን አግኝተናልን? እግዚአብሔር መንፈሳዊ መታደስን እንደሰጠን የበቁ ቅዱሳን ሆነናልን? እግዚአብሔር እንዲጠቀምብን እንደሚገባ ተደቁሰን ተዋርደናልን? ወይስ በጎስቋላው የበረሃ ኑሮ ድካምና መጠራጠር እየኖርን አንዳች ነገር ሲፈጸምብን ሳናይ የምንኖር ነን?

እስቲ ለጥቂት ጊዜ ወደ መጀመሪያው የዓለም ጦርነት ልመለስ። እንደምታስታውሱት በፍላንደርስ የተደረገው የማርን ውጊያ አንድ አጠራጣሪ ጦርነት ነበረ። ጀኔራል ፎክ በጠባብ ስፍራ ነበረ። በጀርመኖችና በፓሪስ መካከል የመነመነች የወታደር መስመር ነበረው፣ ፓሪስ ብትጠፋበት ሁሉም እንደሚጠፋበት እወቁ፣ መኰን

## ምዕራፍ ፬ ።

# የበረከት ንጉሣዊ ጕዳና ።

### ኢያሱ ፫ ፣ ፲፯ ።

«ኢያሱም ማልዶ ተነሣ ፣ እርሱና የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ከሰጢም ተነሥተው ወደ ዮርዳኖስ መጡ ፣ ሳይሻገሩም በዚያ አደሩ ። ከሦስት ቀንም በኋላ አለቆች በሰፈሩ መካከል አለፉ ። ሕዝቡን ፡— የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦትና ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ፣ ከሰፈራችሁ ተነሥታችሁ ተከተሉት ። በእናንተና በታቦቱ መካከል ያለው ርቀት በስፍር ሁለት ሺህ ክንድ ያህል ይሁን ፣ በዚህ መንገድ በፊት አልሄዳችሁበትምና የምትሄዱበትን መንገድ እንድታውቁ ወደ ታቦቱ አትቅረቡ ብለው አዘዙ ።

ኢያሱም ሕዝቡን ፡— ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ አለ ። ኢያሱም ካህናቱን የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ በሕዝቡ ፊት እለፉ ብሎ ተናገራቸው ፣ የቃል ኪዳኑንም ታቦት ተሸክመው በሕዝቡ ፊት አለፉ ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር መሆኔን ያውቁ ዘንድ በዚህ ቀን በእስራኤል ሁሉ ዓይን ከፍ ከፍ አደርግህ ዘንድ እጀምራለሁ ። አንተም የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸከሙትን ካህናት በዮርዳኖስ ውኃ ዳር ስትደርሱ በዮርዳኖስ ውስጥ ቁሙ ብለህ እዘዝ አለው ።

ኢያሱም ለእስራኤል ልጆች ወደዚህ ቀርባችሁ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ አለ ። ኢያሱም አለ ፡— ሕያው አምላክ በመካከላችሁ እንደሆነ ፣ እርሱም ከፊታችሁ ከነዓናዊውን ኬጢያዊውንም ኤዊያዊውንም ፌርዛዊውንም ጌርጌሰዊውንም አሞራዊውንም ኢያቡሳዊውንም ፈጽሞ እንዲያወጣ በዚህ ታውቃላችሁ ፣ እነሆ ፣ የምድር ሁሉ ጌታ ቃል ኪዳን ታቦት በፊታችሁ ወደ ዮርዳኖስ ያልፋል ። አሁንም ከእስራኤል ነገዶች አሥራ ሁለት ሰዎች ምረጡ ። ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው ይሁን ። እንዲህም ይሆናል ፤ የምድር ሁሉ ጌታ የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙ ካህናት እግር ጫማ በዮርዳኖስ ውኃ ውስጥ ሲቆም ፣ ከላይ የሚወርደው የዮርዳኖስ ውኃ ይቋረጣል ፣ እንደ ክምርም ሆኖ ይቆማል ።

እንዲህም ሆነ ፣ ሕዝቡ ዮርዳኖስን ሊሻገሩ ከየድንኳናቸው በወጡ ጊዜ ፣ የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በሕዝቡ ፊት ይሄዱ ነበር ። እንደ መከር ወራት ሁሉ ዮርዳኖስ እጅግ ሞልቶ ነበርና ታቦት ተሸካሚዎቹ ወደ ዮርዳኖስ ሲደርሱ ፣ ታቦቱንም የተሸከሙት የካህናቱ እግሮች በውኃው ዳር ሲጠልቁ ፣ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ ፣ በጻርታን አጠገብ ባለችው አዳም በምትባል ከተማ በሩቅ ቆሞ በአንድ ክምር ተነሣ ። ወደ ዓረባ ባሕር ወደ ጨው ባሕር የሚወርደው ውኃ ፈጽሞ ተቋረጠ ። ሕዝቡም በኢያሪኮ ፊት ለፊት ተሻገሩ ። የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳን

ታቦት የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካከል በደረቅ መሬት ጸንተው ቆመው ነበር፣ ሕዝቡም ሁሉ ዮርዳኖስን ፈጽመው እስኪሻገሩ ድረስ እስራኤል ሁሉ በደረቅ መሬት ተሻገሩ ።»

ኢያሱ ፫ ፣ ፩ — ፲፯ ።

የብሉይ ኪዳን ድንቅ መጽሐፍ በሆነው በዚህ በመጽሐፈ ኢያሱ ጉዞአችንን ስንቀጥል፣ በእስራኤል ልጆች ታሪክ ውስጥ ከምድረ በዳ ወደ ምድረ ከነዓን ወደ ተሻገሩበት ታሪካዊ ወቅት ደረስን ። ዮርዳኖስን መሻገር ሞትና ወደ ዘለዓለማዊ መንግሥተ ሰማያት መድረስ አይደለም ። ነገር ግን የክርስቲያንን ከወራዳ ኑሮ ወደ ተሻለው የእንዋኑዋር ደረጃ መሻገርን ያስረዳል ። የግላዊ ኑሮን ማለቅና የክርስቶሳዊ ኑሮን መጀመር ያሳያል፣ በግል ድካም ሥራና ተግባር የተመሠረተ ኑሮን ማለቅና፣ በሃይማኖትና በመታዘዝ የተመሠረተ ኑሮን መጀመር ይገልጻል ። በእነዚህ ሁለቱ መካከል ኃይለኛው የዮርዳኖስ ወንዝ እየነጎደ ይንከባለላል ። ይኸውም የአይቻልም ነት ወንዝ ነው ።

በምትኖረው የክርስቲያንነት አንዋኑዋርህ ሁኔታ በብዙ ቅር ይልሃልን ? አሁንም እነዚህ ምዕራፎች የተሻለና ከፍ ያለ የአንዋኑዋር ደረጃ መኖሩንና ለማግኘትም የሚቻል መሆኑን መንገድ ከፍተውልሃልን ? ነገር ግን ይህን መጽሐፍ ለማንበብ እን ደጀመርህ አጥፈህ ልትወረውር ሳትፈተን አልቀረህም፣ እንዲህም ብለህ ይሆናል ፤ «ይህ ለእኔ አይደለም፣ አይጠቅመኝም፣ ያ ሰው ሕይወቴን አያውቀውም፣ የእኔን ችግርና ደካማነት እርሱ አያውቅም ።»

ወንድም ሆይ፣ እንዲህ አይደለም ። እርግጥ ነው ችግርህንና ደካማነት ምን እንደሆኑ አላውቅም ። ነገር ግን በእርሱ ዘንድ የማይቻል ነገር የሌለውን ጌታዬን አውቀዋለሁ ። ከእናንተ በማንኛችሁም የችግርና የመከራ የደካማነትም ተራራ ቢያፈ ጥባችሁ፣ በልባችሁም ከዚህ የተሻለ ኑሮ ለእኔ የለም ፤ አሸናፊው የክርስቲያን ኑሮም የበለጠ ልዩነት አያመጣልኝም ብትሉ እግዚአብሔር ከቃሉ ሊነግራችሁ የሚፈልግ ነገር እንዳለ አምናለሁ ። ይኸውም በደካማነት መሸነፋችሁና መጎሸማችሁ አልፎ በእግዚአብሔር ያላችሁ ዓለምን የምታሸንፉበት ሃይማኖታችሁን እንድታጸኑ ነው ።

ስለዚህም ይህ ሁለት ሚሊዮን ተኩል የነበረው ታላቅ ሕዝብና ሠራዊት የዮር ዳኖስን ወንዝ ሲሻገር ስናይ እንድትከተሉኝ በጥሞናና በጥንቃቄ እጠይቃችኋለሁ ፤ «እነሆ የምድር ሁሉ ጌታ ቃል ኪዳን ታቦት በፊታችሁ ወደ ዮርዳኖስ ያልፋል» ኢያሱ ፫ ፣ ፲፩ ።

በቁጥር አሥር እንዲህ ተጽፎአል «ኢያሱም አለ፣ ሕያው አምላክ በመካከላ ችሁ እንደሆነ፣ እርሱም ከፊታችሁ ከነዓናዊውን ኬጢያዊውንም ኤዊያዊውንም ፌር ዛዊውንም ጌርጌሳዊውንም አሞራዊውንም ኢያቡሳዊውንም ፈጽሞ እንዲያወጣ በዚህ ታውቃላችሁ» በዚያን ዘመን እስራኤላውያንን የገጠማቸው ነገር መጋደል ነበር ።

ደግሞም ማሽነፍ የእነርሱ ነበር። ምድረ ከነዓን በዚህ ቁጥር ስማቸው በተጠቀሱ ሰበት ኃያላን ነገሥታት ተይዛለች። እግዚአብሔርም እያንዳንዳቸው እንዲጠፉ አዘዘ።

የሰውን ሕይወት የሚያጠፋው የእግዚአብሔር ባሕርይ ምን እንደሆነ የምትጠይቁና «ይህን በሚያዝ እግዚአብሔር ከቶ አላምንም» በማለት የምትፈተኑ ስላላችሁ እዚህ ላይ ትንሽ ረጋ ልበል። እንደዚህ በለው አምላክ ልታምን አትችልምን? ይህችን ምድር ለአብርሃምና ለዘሩ ርስት አድርጎ እንደሚሰጥ እግዚአብሔር ከአራት መቶ ዓመት በፊት ለአብርሃም ተስፋ ሰጥቶ ነበር። በአራተኛው ትውልድ ሕዝቡ ወደ አገሩ ይመለሳል፣ የአሞራውያን ኃጢአትና ዓመፅ ገና አልሞላምና ብሎአል። ዘፍጥ. ፲፭፣ ፲፯።

አሁን ከአራት ትውልዶች በኋላ የእግዚአብሔር ሕዝብ በምድሪቱ ዳርቻ ላይ ናቸው። በእውነቱም የአገሪቱ ነዋሪዎች ኃጢአት ሞልቶአል። በብዙ ርኩሰትና ከርኩሳን መናፍስት ጋር በመቆራኘት በአያሌው በድለዋል። ከአሪት ዘዳግም ፲፰፣ ፲ እንደምታነቡት ከርኩሳን መናፍስት ከተቆራኙት ከምድሪቱ ነዋሪዎች ጋር ከሕዝቡ አንድ ሰው እንኳ እንዳይተባበር እግዚአብሔር አዘአል። ከእነዚያም የሚተባበር እስራኤላዊ ከሕዝቡ እንዲወገድ አስጠንቅቆአል። አሁን እግዚአብሔር እነዚያን ሰበት ነገሥታት ከሕዝቡ ፊት እንደሚያስወጣቸው የሰጠው ተስፋ ይፈጸማል። እስራኤልን የገጠመው መጋደል ከሥጋውያን ወንዶችና ሴቶች ጋር እንዳልነበረ አስተውል። ነገር ግን የከነዓንን ነዋሪዎች ልብና ባሕርይ ከሚገዙ አጋንንት ጋር ነበር።

ይህ መጋደል፣ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ከሚያደርገው መጋደልና ጦርነት ጋር ፍጹም ተመሳሳይነት አለው። «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፣ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር፣ በሰማያዊ ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» ኤፌሶን ፮፣ ፲፪ የእስራኤልን ልጆች የገጠማቸው መጋደል፣ እኔንና አንተን በየቀኑ ኑሮአችን የሚገጥሙን መጋደሎች ዓይነት ናቸው። የአንተ ባሕርይና አንዋኗር በመንግሥተ ሰማያትና በገሃነም እሳት መከከል ውጊያ የሚያንጉድበት የጦር ሜዳ መሆኑን ተገንዝበሃልን? በአንድ ወገን ሰይጣን በሌላ ወገን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ ሕይወትህን የግል ሊያደርጉ ይዋጋሉ። አንዱ ሊያጠፋህ ሌላው ሊያድንህ ነው። «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም» በምድረ ከነዓን የእስራኤልን ልጆች የገጠማቸውና እኛንም ዛሬ የሚገጥመን ውጊያ አንድ ዓይነት ነው።

እንድትገነዘብ የምፈልገው እነዚያን ሰዎች የገጠማቸው መጋደልና ውጊያ ብቻ ሳይሆን ድል መንሣትም ጭምር መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ለዚያች ምድር አንድ ዓላማ ነበረው። ዓላማው ምን ነበር? ይህ ነው፤ «አንድ ትንሽ ሕፃን በቤተ ልሔም በረት፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ፣ መቶ ሃያ ሰዎች በሰገነት ላይና የመንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መውረድ ነው።» ቤተ ልሔም፣ ቀራንዮና ጴንጤቆስጤ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋ መልበስ፣ የሰው ዘር ኃጢአት ፍርድን

በእርሱ መሟን ፣ የክርስቶስንም ሕይወትና ባሕርይ በምዕመን ልብ መቅረጽ ናቸው ። የወደቀውን የሰው ዘር ለማዳን ይህ ዓይነተኛውና ከሁሉ በፊት የነበረ የእግዚአብ ሔር ዓላማ ነው ። ማናቸውም ነገር ፣ ደግሜም ልናገር ፣ በምድርም ሆነ በገሃነም ካለው ሁሉ ማናቸውም ቢሆን የእግዚአብሔርን ዓላማ ሊያግድ ከፊቱ መቆም ከቶ አይገበም ። የምድሪቱ ሕዝብ መተላለፍና በዓመፅ መሞላት ! አሁን እግዚአብሔር እጁን ለፍርድ ያነሣና መሥራት ይጀምራል ።

እግዚአብሔር ዛሬ ለአንተ ሕይወት አንድ ዓላማ ወይም እቅድ አለው ። ይህ የተዘጋጀልህ እቅድ ምንድር ነው ? ቤተ ልሔም ፣ ቀራንዮና ጴንጤቆስጤ ናቸው ። ይህም ማለት ሥጋ የለበሰው ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ወደ ልብህና ባሕርይህ ገብቶ ፣ በመስቀሉም ላይ የኃጢአትህን ፍርድ ተሸክሞ ፣ አንተም ከክርስቶስ ጋር በኃጢአት ሁሉ ሞተህ የሥላሴ ሦስተኛ አካል የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከክርስቶስ ጋር ለመሞትና ተነሥተህ በአዲስ ሕይወት ለመኖር ፈቃደኛ ወደ ሆነው ሕይወትህ መጥቶ በውስጥህ መኖር ማለት ነው ። እግዚአብሔር ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች ለእያ ንዳንዳችን ያለው ዓላማ ቤተ ልሔም ፣ ቀራንዮና ጴንጤቆስጤ ናቸው ። እግዚአብ ሔር ይህን ዓላማውን እንዳይፈጽም የሚያሰናክል ሁሉ ይደመሰሳል ።

ነገር ግን በዓላማውና በፍጻሜው መካከል ዮርዳኖስ እያነገደ ይፈሳል ፣ እርሱ ንም መሻገር የማይቻል ይመስላል ። ለክርስቲያን አንዋንዋርህ እግዚአብሔር ያዘጋጀ ልህን ዓላማ እንድታውቅ አሁን ትንሽ መንገድ ስከፍትልህ በአእምሮህ እንዲህ ስትል ትጠይቅ ይሆናል ። «ነገር ግን ደካማነትን ወይም እንቅፋትን ምን ላድርግ ?» ችግ ርህና ደካማነትህ ምን ይሆን ? የዐመል ባርነት ነውን ? ምናልባትም እምነት ያለህ ሆነህ ሳለህ በስሜት ፣ በቁጣና በፍቅር ማዕበል ትነዳ ይሆን ? ሌሎችን የምታስተምር ሆነህ ሳለህ አንተ ራስህ ከእግዚአብሔር ያልተማርህ ነህን ? ለሌሎች ስለ ጌታ ኢየ ሱስ ክርስቶስ ትነግራለህ ፣ ዳሩ ግን ድል አድራጊው ኢየሱስ በኃይሉ በሕይወትህ ውስጥ አሸናፊ መሆኑን ያልቀመስክ ይሆንን ? የሰውን ልብ የሚያውቅ ፣ እግዚአብ ሔር ቢሆንም ምናልባት ያንተ ችግሮችና የደካማነት ወንዝ እነዚህ ግዙፎቹ አይደ ሉም ይሆናል ። ታዲያስ ጥቃቅን ብለን የምንጠራቸው ምሥጢራዊና የተደበቁ ነገ ሮች ናቸውን ? እነዚህም በይናችን ፊት የማይጎዱ ናቸው ፣ በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ግን ከግዙፎቹ እኩል የሚቆጠሩና የሚያሰጉ ናቸው ። በንዱ ዘንድ የማያፈቅር መንፈስ ይሆናል ፣ በሌላው ዘንድ ደግሞ ሰውን ማማት ፣ በሌሎቹ ደግሞ አትንኩኝ ባይነት ፣ በጥቂት መቆጣት ምኞታቸው ቢቃወስባቸው ለራሳቸው መከላከያ በሙሉ ኃይል መነሣት ፣ በማናቸውም ስፍራ ከፍ ከፍ ማለትንና ራሳቸውን ማመስገንና ማክ በርን የሚወዱ ናቸው ። አንዳንዶች ደግሞ በሌሎች ዕድል ይመቀኛሉ ። በረከትን እየጋረዱብን መንፈሳዊ መታደስን የሚከለክሉን እነዚህ ነገሮች ዛሬ በክርስቲያን ሕይ ወት እያደቡ ይኖራሉን ? ዛሬ የቤተ ክርስቲያናችንን ምስክርነት የሚያጨናግፉ ፣ በእኛና በበረከት አገራችንም መካከል እንደ ዮርዳኖስ እያነገዱ የሚንከባለሉ እነዚህ ነገሮች መሆናቸውን እንድናይና እንድንረዳ እግዚአብሔር ይርዳን ። የተፈለገው መጋደልና ማሸነፍም ነበር ። እስከ አሁን ያደረግነው ግን መዋጋትና መሸነፍ ነው ።

አሁን መንገዱን ማየት ጀመርህን ? መጋደላችን ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ነው እንጂ ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም ። ከታክልቱ ስፍራ፣ ከመስቀሉና ከመቃብሩ በኋላ አንድ ቀን ሊቀ ካህናታችን በድል አድራጊነት ከመቃብር ተነሥቶ ጠላቶቻችንን ገፈፈ ። የሰይጣንን ፈተና ሁሉ መለሰና ከሙታን ተነሣ ። አሸናፊው ፥ ድል አድራጊውና መጪው ንጉሣችን ፥ ሃሌ ሉያ ። በውኃ መከከል ለሚያልፉም «ከአንተ ጋር እሆናለሁ ፥ ወንዞችም አያሰጥሙህም» አለ ። የእግዚአብሔርን ልጅ ማለት ክርስቲያንን ለመቃወም የባሕሩ ሞገድ ፥ የአለቆችና የሥልጣናት ተቃዋሚነት አሸናፊው ጌታችን ኢየሱስ ስላሸነፋቸው አይበረቱም ።

ዮርዳኖስን መሻገር ድካምን ችግርንና እነዚህን ተቃዋሚዎች መጋፈጥ ማለት ነው ። ይህም የሞተውን የተነሣውንና ያረገውን ኢየሱስን ተከትለን ከአለቆችና ከሥልጣናት ሁሉ በላይ ወደ ሆነው ስፍራ መውጣት ማለት የው ። በፊትህ ወደሚንከባለለው ደካማነት ሳትደርስ ቀና ብለህ ኢየሱስን ደህና አድርገህ እየው ። እርሱም ራሱ ድካምህንና እንቅፋትህን ያስወግድልሃል ። በጌታ ኢየሱስ ስም የምነግርህ የሚከተለው ነው ። የእግዚአብሔርን ልጅ ማለት ክርስቲያንን ከሚያቆስሉት ከሰይጣን ፍላጻዎች ቀላልም ሆነ ጽኑ ፥ አስቀድሞ የጌታችንን ልብ ያልነካና ያላሳዘነው የለም ። እርሱም በመስቀሉና በትንሣኤው አሸንፎልናል እኛ ልጆቹ ከዚህ በፊት የታገልናቸውን ድካሞች እንደገና ገጥመን ዓይናችንን ወደ እርሱ ወደ ራሱ እንድናነሣ ይለምነናል ። እንዲህ በሉ ይለናል «ጌታ ሆይ ፥ አሁን ፥ እኔ እንደማልችል አምናለሁ ፥ አንተ ግን ሁሉን ትችላለህ» ያን ጊዜ የዮርዳኖስ ፉጨት ጸጥ ይላል ፥ ሞገዱና ኃይሉም ይወገዳሉ ። እኛም በደረቅ መሬት እንሻገራለን ። ከምድረ በዳ ወደ ከነዓን የሚመራው የክርስቲያን መንገድ አለመቻልነትን እየተጋፈጥን ከሙታን የተነሣውን ክርስቶስን አትኩረን በማየትና እርሱንም አጥብቀን በመያዝ ነው ። «ይህስ ደህና ነው ፥ ግን ይህ ሁሉ የአፍ ታሪክ አይደለምን ? የዚህ ነገር ሁሉ ኃይል እንዴት አድርጎ ወደ ልቤ ይመጣል ?» ትሉኝ ይሆናል ።

«የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካከል በደረቅ መሬት ቆመው ነበር ። ሕዝቡም ሁሉ ዮርዳኖስን ፈጽመው እስኪሻገሩ ድረስ እስራኤል ሁሉ በደረቅ መሬት ተሻገሩ» ኢያሱ ፫ ፥ ፲፯ ።

የምትልከኝ በግ ሆይ ፥ የአንተም ደም
ኃይል አለው የማይደክም
የተዋጁት ያምላክ ሕዝብም
እስኪጸኑ እንዳይበድሉህ ለዘላለም ።

የምንፈልገው ኃይል ሁሉ አነሰም በዛም ከእንግዲህ ወዲህ ያለው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። በእርሱ ያለን ኃይል የኃጢአትንና የፈተናን ነበልባል ይመከታል ፥ ድካምን ያግዳል ። የእስራኤል ልጆች የተናፈቀውን የተስፋ ምድር ቀርበው ከሩቅ አዩት ፤ ግን በእነርሱና በበረከቱ መከከል በድካም የተመሰለው ዮርዳኖስ አለ ። ይህ አሁን የአንተ ሁኔታ አይደለምን ? በረከት እንዳለ ታያለህ ፥ የተሻለ የክርስቲያንነት

የእንዋኑዋር ደረጃ እንዳለ ተገንዝበሃል፣ ሕይወትህ በኃጢአት እንደተሸነፈና የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንዳቃተህ ከእርሱም እንደራቅህ ታውቃለህ፣ ነገር ግን በአንተና በበረከት መካከል ደካማነት (ዮርዳኖስ) ይንጎራደዳል። በሃይማኖት ወደ ደካማነት ተራመድ።

ሕዝቡ በእግራቸው ጫማ የወንዙን ዳር እንደጠለቁ በቃል ኪዳን ታቦት እዚያ መኖር ወንዙ ደረቀ። ሲሻገሩም ዓይናቸውን ከታቦቱ እንዳይነቅሉ ተነግሮአቸዋል፤ እነርሱም ለጊዜው ዓይናቸውን ከበረከት አገር ነቅለው የቃል ኪዳኑን ታቦት አተኩረው ተመለከቱ። በዚህ ዓይነት ሲሻገሩ በእነርሱና በበረከት አገር መካከል የቃል ኪዳኑ ታቦት ቆሞ ነበር።

በመሸነፍ የምድረ በዳ ኑሮና በድል አገር መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነበር። በእኛና በበረከት መካከል ዮርዳኖስ ይንከባለላል። እርሱም ድካም ነው። ኃፍረት፣ ይሉኝታ፣ የተፈጥሮ ጠባይ፣ ክፉ ፀመልና ልማድ፣ ትዕቢትና ሥጋዊ በሕርይ በበረከት አገርና በክርስቲያን መካከል እንደ ዮርዳኖስ ያንጉዳል። የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ ዓይኖችህን አንሣና ወደ ጌታ ኢየሱስ ተመልከት፤ ይህን ስታደርግ በአንተና በደካማነትህ መካከል ክርስቶስ ራሱ አለ። ከዚህ በኋላ ክርስቲያን «ድልን ስለማግኘት» አያወራም። ድል አድራጊውን ራሱን እንጂ ድልን አይፈልግም። ድል አድራጊውንም ከአገኘ ድሉ የእርሱ ነው። «በረከትን ለማግኘት ስለ መጋደልና አዲስ እንዋኑዋርን ስለመፈለግ» አይናገርም። ዓይኖቹ በጌታ ኢየሱስ ላይ ናቸው። እርሱም ጌታ ኢየሱስን መከታ በማድረግ በትዕቢት የሚንጎራደደውን ዲያብሎስ ፈጥኖ ከእግሩ በታች በመቀጥቀጥ የአምላኩን ዓይን ያያል።

ንጉሣዊው የበረከት ጐዳናም እርሱ ነው። ራስን ወዳድነት፣ ለምን ተበደልኩ በይነት የሌለው የመሥዋዕትነት እንዋኑዋር ይህ ነው። የማይታወክ፣ የማይመቀኝ፣ የማይቀና በረከትንና ክብርን ለራሱ የማይመኝ፣ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስን ብቻ የሚፈልግ እንዋኑዋር ይህ ነው። ይህን ጐዳና ከእኔ ጋር አትራመድምን? ለብዙ ዓመታት ሲያሸንፍህ በኖረው ደካማነት ላይ በሃይማኖት ቆመህበት ወደ ኢየሱስ እያየህ በአንተና በደካማነት መካከል ኢየሱስን ለማየት ትፈቅዳለህን? ጌታ ኢየሱስንም እንዲህ በለው «ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ደካማነትን እጋጠመዋለሁ፤ በሃይማኖትም ረግጨው ፊትህን አያለሁ፤ ተሻግሬም ወደ በረከት አገር እስክደርስ ቆመህ ይህን ወንዝ አግድልኝ። ከእንግዲህ ወዲህ እኔ አይደለሁም ክርስቶስ እንጂ።»

# ሁለተኛ ክፍል ።

# ጠላትን ማሸነፍ ።

### ምዕራፍ ፩ ።

## መስቀልና ክርስቲያን ።

ኢያሱ ፫ ፡ ፱ ።

«እንዲህም ሆነ ፣ ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ፈጽመው በተሻገሩ ጊዜ እግዚአብሔርም ኢያሱን ከሕዝቡ ከየነገዱ አንድ ሰው ፣ አሥራ ሁለት ሰዎች ምረጥና በዮርዳኖስ መካከል የካህናት እግር ከቆመበት ስፍራ አሥራ ሁለት ድንጋዮች አንሡ ፣ ተሸክማችሁም በዚህ ሌሊት በምታድሩበት ስፍራ አኑሩአቸው ብለህ እዘዛቸው አለ ።

ኢያሱም ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው ከእስራኤል ልጆች ያዘጋጃቸውን አሥራ ሁለት ሰዎች ጠራ ። ኢያሱም አላቸው ፦ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ወደ ዮርዳኖስ መካከል እለፉ ፣ ከእናንተም ሰው ሁሉ በእስራኤል ልጆች ነገድ ቁጥር በጫንቃው ላይ አንድ አንድ ድንጋይ ከዚያ ይሸከም ። ይህም በመካከላችሁ ምልክት ይሆናል ፤ ልጆቻችሁም በሚመጣው ዘመን የእነዚህ ድንጋዮች ነገር ምንድር ነው ? ብለው ሲጠይቁአችሁ እናንተ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት የዮርዳኖስ ውኃ ስለተቋረጠ ነው ። ዮርዳኖስን በተሻገሩ ጊዜ የዮርዳኖስ ውኃ ተቋረጠ ፣ እነዚህም ድንጋዮች ለእስራኤል ልጆች ለዘላለም መታሰቢያ ይሆናሉ ትሉአቸዋላችሁ ።

የእስራኤልም ልጆች ኢያሱ እንዳዘዘ አደረጉ ፣ እግዚአብሔርም ኢያሱን እንደ ተናገረው በእስራኤል ነገድ ቁጥር ከዮርዳኖስ መካከል አሥራ ሁለት ድንጋዮች አንሥተው ወደሚያድሩበት ስፍራ ወሰዱ ፣ በዚያም አኖሩአቸው ። ኢያሱም የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት እግሮች በቆሙበት ስፍራ በዮርዳኖስ መካከል ሌሎችን አሥራ ሁለት ድንጋዮች ተከለ ። እስከ ዛሬም ድረስ በዚያ አሉ ። ሙሴም ኢያሱን እንዳዘዘው ሁሉ እግዚአብሔር ኢያሱን ለሕዝቡ እንዲነግር ያዘዘው ነገር ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ታቦቱን የተሸከሙ ካህናቱ በዮርዳኖስ መካከል ቆመው ነበርና ፣ ሕዝቡም ፈጥነው ተሻገሩ ። ሙሴም እንዳዘዛቸው የሮቤል ልጆች የጋድም ልጆች የምናሴም ነገድ እኩሌታ ተሰልፈው በእስራኤል ልጆች ፊት ተሻገሩ ። አርባ ሺህ ያህል ሰዎች ጋሻና ጦራቸውን ይዘው ለሰልፍ በእግዚአብሔር ፊት ወደ ኢያሪኮ ሜዳ ተሻገሩ ። በዚያም ቀን እግዚአብሔር ኢያሱን በእስራኤል ሁሉ ፊት ከፍ አደረገው ፣ ሙሴንም እንደፈሩ በዕድሜው ሁሉ ፈሩት ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን የምስክሩን ታቦት የሚሸከሙትን ካህናት ከዮርዳኖስ እንዲወጡ እዘዝ ብሎ ተናገረው ። ኢያሱም ካህናትን ከዮርዳኖስ ውጡ ብሎ

አዘዛቸው ። የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት ከዮርዳኖስ መካከል በወጡ ጊዜ ፣ የካህናቱም እግር ጫማ ደረቅ መሬት መርገጥ በጀመረ ጊዜ የዮርዳኖስ ውኃ ወደ ስፍራው ተመለሰ ፣ ቀድሞም እንደነበረ በዳሩ ሁሉ ላይ ሄደ ።

ሕዝቡም በመጀመሪያው ወር በአሥረኛው ቀን ከዮርዳኖስ ወጡ ፣ በኢያሪኮም ዳርቻ በምሥራቅ በኩል በጌልገላ ሰፈሩ ። ከዮርዳኖስም ውስጥ የወሰዱአቸውን እነ ዚያን አሥራ ሁለቱን ድንጋዮችን ኢያሱ በጌልገላ አቆማቸው ። ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ፦ በሚመጣው ዘመን ልጆቻችሁ አባቶቻቸውን ፣ እነዚህ ድንጋዮች ምንድር ናቸው ? ብለው ሲጠይቁ ፣ ለልጆቻችሁ እንዲህ ብላችሁ ታስታውቃላችሁ ፦ እስራኤል ይህን ዮርዳኖስን በደረቅ ተሻገረ ፤ እስክንሻገር ድረስ አምላካችሁ የኤርትራን ባሕር ከፊታችሁ እንዳደረቀ እንዲሁ እስክትሻገሩ ድረስ አም ላካችሁ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ውኃ ከፊታችሁ አደረቀ ። ይኸውም የእግዚአብ ሔር እጅ ጠንካራ እንደሆነች የምድር አሕዛብ ሁሉ እንዲያውቁ አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ለዘላለሙ እንድትፈሩ ነው ።» ኢያሱ ፬ ፣ ፩ — ፳፬ ።

በብሉይ ኪዳን በመጽሐፈ ኢያሱና በሐዲስ ኪዳንም በኤፌሶን መልእክት መካ ከል ያለውን የሐሳብ አንድነት ስናረጋግጥ እስከ አሁን ደርሰናል ። ወደ ድል የሚያ ደርሰው መንገድና እግዚአብሔር ለልጁ የሚመኝለት እንቅንቅር በዚህ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ግልጽና አንጊ በሆነ መልክ ተገልጾአል ። የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ምዕራፎች እነዚህ ሕዝቦች እንዴት ወደ ዮርዳኖስ እንደቀረቡ ይናገራሉ ፣ አሁን በአራተኛው ምዕራፍ ከወንዙ በሌላ በኩል እናገኛቸዋለን ። አሁን በከነዓን ምድር የባሕር ዳርቻ አምባ አግኝተዋል ።

በፊታቸው ሊያዙ የሚገቡ ኢያሪኮና ሌሎችም በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ተመሰ ሳይ ስፍራዎች አሉ ። በክርስቲያን ኑሮ ውጊያና ጦርነት አብረው ስለሚጓዙ አሁን ጦርነት ሊጀመር ነው ። በረከቱ በሚበዛው መጠን ከጨለማ ሥልጣናት ጋር የሚደ ረገውም ውጊያ ብርቱ ይሆናል ። የሚያሸንፍ ክርስቲያንም በእግዚአብሔር የሚማ ጠን ብቻ ነው ። እስራኤላውያን ግን ውጊያ ከመጀመራቸው በፊት ፣ ኢያሪኮን ለማ ጥቃት ከመሮጣቸው በፊት በጌልገላ በሚቆዩበት ጊዜ የሚማሩአቸው ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶች አሉ ። በትዕግሥት ረጋ ብሎ ጠብቆ ቆይቶ ተጠባብቆ ከእግዚአብሔር ትምህርትና መምሪያ መቀበል ለክርስቲያን በሕይወቱ ሁሉ የማይቻለው ከባድ ነገር ነው ።

በሃይማኖት ዮርዳኖስን ስለተሻገርን ጥቂቶቻችን በእግዚአብሔር ጸጋና አድራ ጎት በበረከት አገር የዳርቻ አምባ አግኝተናል ። ከዚህም የተነሣ በፍጥነት ተነሥተን በፊታችን ያለውን ሁሉ እየደመሰስን ማጥቃት እንፈልጋለን ። በምድረ በረከትም ለመቋቋም ስንፈልግ እጅግ የበረታ ጦርነት ይገጥመናል ፤ እግዚአብሔር ግን ለጦርነ ቱና ለማሸነፍም ታማኞች አድርጎን ከመቁጠሩ በፊት ጥሩ ውጤት የሚያስገኙ ትም ህርቶችን ሊሰጠን ይፈልጋል ።

ጌልገላ ለእስራኤላውያን የተቀደሰ ስፍራ ሆነ ። በሞላው መጽሐፈ ኢያሱ ጌልገላ ከጠላቶቻቸው ጋር ለሚያደርጉት ውጊያ ሁሉ የጦር ሰፈራቸው እንደሆነ እናገኛለን ። ኢያሱ በጦርነት ሳለ እያቋረጠ ብዙ ጊዜ ወደዚህ ስፍራ ይመለሳል ። ድል ካደረገ በኋላና አንዳንድ ጊዜም ሲሸነፍ እየደጋገመ ወደ ጌልገላ ይመላለሳል ።

የጦር ሰፈር ብቻም አልነበረም ፤ ግን የጎደለውንም የተበላሸባቸውንም የጦር ዕቃ ሁሉ ወደ ጌልገላ እየተመለሱ ያበጃሉ ። እንደዚሁም በጦር ሜዳና በጌልገላ መካከል የሚገኝ መገናኛ ሁሉ ዘወትር ክፍትና ነፃ መሆን አለበት ። ጌልገላ በመጀመሪያ ምድሪቱን የረገጡበት የጦር ሰፈራቸው ናት ። የእግዚአብሔር ሕዝብ በውጊያው ሁሉ ድል እንዲያደርጉ ከተፈለገ በጦር ሜዳውና በጦር ሰፈር መካከል ክፍት የመገናኛ መንገድ መኖርና መጠበቅም አለበት ። ይህም በጌልገላና በምድረ በረከት መካከል ማለት ነው ። ማናቸውም ነገር በምንም ዓይነት መንገድ ያንን መገናኛ መዝጋት የለበትም ።

ክርስቲያን በጌልገላ ሊማራቸው የሚገባ ስድስት ጠቃሚ ትምህርቶች አሉ ። ከእነዚህም በዚህ ምዕራፍ የምንማራቸው ሁለቱ የድልና የነፃነት ኑሮ ለሚፈልግ የእግዚአብሔር ልጅ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው ። ይህም ከድል መንገዶች አንድ አይደለም ፤ ነገር ግን አንድ የሆነ የድል መንገድ ነው ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሁለት የደኅንነት መንገዶች የሉም ። ይህ መንገድ በጠማማ ሐሳብ እያመኑ ከጠማማ ሐሳባቸውም በቂ ምክንያትና የሕሊና ፍርድ የማይመልሳቸው ወይም የጮሌ ሰዎች መንገድ ወይንም ከመጠን በላይ ጥብቅ የሆኑ ክርስቲያኖች መንገድ አይደለም ። የመስቀሉን አሸናፊነት በሕይወትህ ልትቀምስ ከተመኘህ የምትጓዝበትን የነፃነት መንገድ እንዳሳይህ ትልቅ ምኞቴና ፍላጎቴ ነው ።

በመጀመሪያ ፤ ጌልገላ ፤ «የመታሰቢያ» ስፍራ ነው ። በምዕራፍ አራት የመጀመሪያ ቁጥሮች ኢያሱ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን ከወንዙ መፍሰሻ ወለል ወስዶ በዚያን ቀን ለተፈጸመው ሁሉ ነዋሪ መታሰቢያ እንዲሆን ከዮርዳኖስ በድል ወገን እንዲያደርግ እግዚአብሔር ኢያሱን አዘዘ ። ኢያሱም የካህናቱ እግር ጸንቶ ከቆመበት ስፍራ ከዮርዳኖስ መካከል ድንጋዮቹን አነሣ ። ይህም ብቻ አይደለም ፤ ሌሎች አሥራ ሁለት ድንጋዮችንም ወስዶ በውኃው ወለል መካከል ካህናቱ ቆመው በነበሩበት ስፍራ እንደተከላቸው ከቁጥር ዘጠኝ እናነባለን ። እነዚህም ድንጋዮች ዮርዳኖስ በሚሞላበት ወራት ብቻ ካልሆነ እስከ ዛሬ ድረስ ዓመቱን ሙሉ በዓይን ሊታዩ ይችላሉ ። አስተውል ፡ ካህናቱ ጸንተው በቆሙበት ሕዝቡ በደረቅ መሬት በተሻገሩበት ስፍራ በዮርዳኖስ መካከል ነው ።

ኢያሱ ከጥቂቶቹ መሸነፍና ከአብዛኛዎቹ ማሸነፍ ወደዚያ በሚመለስበት ጊዜ ኢያሱም ብቻ ሳይሆን ተከታዩ ትውልድ ሁሉ ወደዚያ በሚመለሱበት ጊዜ «እነዚህ ድንጋዮች ምንድር ናቸው ?» ብለው ይጠይቃሉ ። በቁጥር አሥር የሚገኘውም የሚሰጣቸው መልስ ይህ ነው ፤ «ሙሴም ኢያሱን እንዳዘዘው ሁሉ ፤ እግዚአብሔር

ወደምትላክበት አገረ ስብከትዋ ከመሄድዋ በፊት አንዲት ጓደኛዋ እንዲህ ስትል እን ደመከረቻት ነገረችን «አሁን ለምን ብለሽ በቻይና ልትቀበሪ ትሄጃለሽ ? አየሩን ስለ ማትችይ በስድስት ወር ውስጥ ትሞቺአለሽ» ይህ ለወንጌል መልእክተኛ ሊሰጥ የሚ ገባ ጥሩ ምክር ነው ።

ሚሲዮናዊቱ ግን ለጓደኛዋ እንዲህ ብላ መለሰችላት ። «የተወደድሽ ጓደኛዬ ከአምስት ዓመት በፊት እንደሞትሁ እንድታውቂ እፈልጋለሁ ። ኢየሱስ ወደ ቻይና እንድሄድ በጠራኝ ጊዜ አንገቴን ከመስቀሉ ስር ደፍቼ ከእግዚአብሔርና ከቻይና ውጪ ለሆነው ሁሉ ሞትሁ» ይህች ልጃገረድ የሞተችው ለባል ፥ ለቤት ፥ ለልጆች ፥ ለትዳርና ለቤተ ሰብ ኑሮ ለምቾት ፥ ለደስታና ለተድላ መሆኑን አውቃለሁ ። እነዚህን ለማግኘት ይቻላት ነበር ።

በእግዚአብሔርና በሰማይ መላእክት ፊት ይህ ነገር እውነተኛውና ትክክለኛው የመስቀል ትርጉም ነው ። ለማንኛችንም ሌላ መንገድ የለም ። እግዚአብሔር በኢየ ሱስ ሲናገረን ፥ ልጁንም በመስቀል ተንጠልጥሎ ሲያሳየን እኛም ከእርሱ ጋር እንደ ሞትን በለመጠራጠር በአእምሮአችንና በልባችን ሁሉ እንድናምን ይጠይቀናል ።

አብዛኞቻችሁ ለእግዚአብሔር ትልቅ ሥራ ለመሥራት እንደምትመኙና ብዙ ውን ጊዜም እንደሚታያችሁ አምናለሁ ። ሁልጊዜም እቅድ ታወጡ ታወርዱና በምን መንገድ አንዲት ነፍስ ወደ ክርስቶስ እንደምታመጡ ትወጥናላችሁ ። በጣም ጥሩ ነው ። ነገር ግን ይህ ሁለተኛው እርምጃ ነው ። እግዚአብሔር ግን ከሁሉ በማስቀደም በአንደኛው ደረጃ ላይ ያዘጋጀልህ በመጀመሪያ ራስህ እንድትሞት ነው ። ምንም ያህል የተማርክ ፥ የረቀቅህ በሥራ ላይም ያለህ የከበርህ ሰው ብትሆን ወይ ንም የረከስክ ኃጢአተኛ ብትሆንም እግዚአብሔር ከመሞትህ የበለጠ ነገር የለውም ። ከክርስቶስ ውጪ እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ፍርድና ሞት ብቻ ነው ። «ክርስቶስ ብቻ» መሆን አለበት ። ለእርሱ ትልቅ ሥራ ለመሥራት ለሚፈልጉትና ራሱ ለሚጠ ራቸው ሰዎች እግዚአብሔር የሚመኘው አስቀድመው ከክርስቶስ ጋር እንዲሞቱ ነው ።

መስቀል ማለት ለአንተ ምንድር ነው ? ረጋ ብለን ይህን ጥያቄ ራሳችንን መጠ የቅ የሚገባ ነው ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ድልና ወደ መንግሥቱ ክብር ከፍ ከፍ ከማድረጉ በፊት ወደ ታች ወደ ዮርዳኖስ ጥልቅ ወለል ሊያወርዳቸው ይፈል ጋል ፥ ይወስዳቸውማል ። ለመሞት ፈቃደኞች መሆናቸውን ይጠይቃቸዋል ። ጌታ ችንም እንዲህ ብሎአል «እውነት እውነት እላችኋለሁ ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች ፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች» ዮሐ. ፲፪ ፥ ፳፬ ።

መንፈስ ቅዱስ የሚቀጥለውን ጥያቄ በልብህ ይቅረጽ «ከክርስቶስ ጋር ሞተሃ ልን ?» ለዝናህና ለጉራህ ሞተሃልን ? በዓይንህና በራስህ ግምት ደግ ቢመስልህም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ለሆነው ሁሉ ሞተሃልን ? ራስህን በትልቅ ነገር ከመ

ይህ በጣም አስገራሚ ታሪክ ነው፤ ግን ለእኔና ለአንተ ምን ይጠቅመናል ? ጥቅሙ ይህ ነው። «በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና፤ በሚመጡ ዘመናትም በኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን» ኤፌ. ፪፤ ፭ — ፯። ይህ ነገር ነፍሴን ይመስጣታል ያረካታልም። ትርጉሙ ገባህን ?

እስከ አሁን አሸንፊህ የድልን ጣዕም ያልቀመስህ ብትሆን፤ ክርስቶስ በወጣህ ነፃነት ውስጥም ያይደለህ እንደሆንክ ከኃጢአት ነፃ የመውጣት ትምህርትና ምሥጢር እዚህ ውስጥ ተጠቃልሎአል። ከክርስቶስ ጋር በመሞቱ ብቻ ተካፋዮች አልሆንም። ነገር ግን አብረን ተቀበርን፤ በዚህ በፋሲካ ዕለት ጧትም አብረን ከሙታን ተነሣን፤ ከእርሱም ጋር ወደ ሰማያዊ ስፍራ ወጣን ዛሬም ከአለቆችና ከሥልጣናት ሁሉ በላይ ነን።

ነገር ግን እንዲህ ትለኛለህ «ምን ማለትህ ነው ? እዚህ ቁጭ ብያለሁ፤ እግሬም መሬት ላይ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ታዲያ መሰንቆና በገና ይዘህ በክንፍ በሰማይ ትበራለህ የምትለኝ ምን ማለትህ ነው ? ወዳጄ ሆይ፤ እኔ ይህን አላልኩም፤ ነገር ግን ለአንተ መስሎህ ነው።

እስቲ ልግለጽልህ፤ ጳውሎስ እንዲህ ይላል «ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን» ሮሜ ፰፤ ፳፫። እንጠባበቀዋለን፤ በዚህ ዓለም በውርስ ኃጢአት በሚጠቃ በፍጥረታዊና በሥጋዊ ሰውነት እንኖራለን። በዚህ ዓለም እስካለን ድረስ በጠፊና በሚች ሥጋ እንደምንኖር እናውቃለን። ሁልጊዜ ከሥጋ ጋር ነን፤ የሥጋን በሕርይ ከምኞቱና ከፍጥረቱ ጋር ምን እንደሆነ እናውቀዋለን።

ክርስቶስ በሞተ ጊዜ እኔ ራሴና ለራሴ የሚባለው ግላዊ ኑሮ ሞተ፤ እርሱም አዲስ ሕይወት ወስዶ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አረገ፤ ከእርሱም ጋር ከአለቆችና ከሥልጣናት ሁሉ በላይ የሆነውን የራሱን ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአማኞቹ ልብ አፈሰሰ። እንግዲህ በሥጋ በዓለም፤ በመንፈስ ግን በሰማይ ነኝ፤ በሥጋ የዲያብሎስ ተገዢ ነኝ፤ በመንፈስ ግን ከጌታዬ ጋር በክብር ስፍራ ነኝ።

ታዲያ ሕይወቴን የሚገዛው ሥጋዬ ነውን ወይስ መንፈሴ ? የክርስቲያንነት ሥራዬንም የሚመራው ይህ የሚችና የድካም ሥጋ ነውን ወይስ ኢየሱስ በውስጤ ያደረገው የነፃነት መንፈስ ነው ? የኃጢአት፤ የፈተናና የምኞት ባሪያ በሆነው ሥጋ ተቆራኝቼ የክርስቲያንነት አንዋኑዋር ለጊዜው እኖራለሁን ? ወይስ በመንፈስ ከኢየሱስ ጋር ያለኝን ስፍራ በሃይማኖት እየጨበጥሁ ሰይጣንን «ውጣ፤ ከአንተ ክፍል የለኝም» እለዋለሁን ?

ይህን በምልበት ጊዜ ይህን እውነት ጨብጠው ወደ ክርስቶስ ሥራና አገልግሎት ለመግባት ለሚሰናዱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አስባለሁ። አዲስና የተሻለ ነገር

በፊታችሁ መሆኑን ታያላችሁን ? ወይስ ለሥጋ ባሪያ እንደምትሆኑ ወይም በመንፈ
ቅዱስ እንደምትሸነፉ ተረድታችኋልን ?

ሕልም ይመስላል ፣ ነገር ግን እምነት እውነተኛ ያደርገዋል ። የእግዚአብሔ
ቃል እውነት መሆን ሲነግርህ እንድትጠራጠርና ውሸት ነው እንድትል የሚያደርግ
ሰይጣን ነው ። በእምነት ስፍራውን በድል ሜዳ የሚያደርግ ማንኛውም ክርስቲያ
አይበገርም ። በእምነት ተነሥቶ ከአለቆችና ከሥልጣናት ሁሉ በላይ የሆነው ሕይ
ወት ከዲያብሎስ መድረሻ በላይ መሆኑን የሚቀበል ክርስቲያን አይሸነፍም ጌልገ
የትንሣኤ ስፍራ ነው ።

ማንኛውም እስራኤላዊ ወደ ምድረ በዳ ለመመለስ ዮርዳኖስን እንደገና ቢሻገር
በባሕር ውስጥ የተተከሉ እነዚያ ድንጋዮች በመቃወም ሊጮኹበት ይገባል ። በአን
ድነት ተዋጅተው በድል መሬት የተተከሉ ሕዝብ ወደ ምድረ በዳ ቢመለሱ በጌልገላ
የተቀለሉ ድንጋዮች በመቃወም ይጮኹባቸዋል ። የክርስቲያን አንዋኑዋርህ አቋም ፣
ዓለማዊነት ፣ ኃጢአተኛነትህና ከኃጢአተኞች ጋር መተባበርህ ሁሉ በዶ የቀረውን
የክርስቶስን መቃብር አንዋኑዋርህን በመቃወም እንዲጮህ ያደርጉታልን ?

የተተከልከው በድል ሜዳ ስለሆነ ወደዚያው ተመለስ እዚያም ኑር ።

ጌልገላ የትንሣኤ ስፍራ ነው ፣ ነገር መታሰቢያ ባይኖር ትንሣኤ ባልሆነም ፣
ሞት ባይሆን ሕይወት ባልነበረም ፣ መዋረድ ባይኖር ድል ማድረግ ባልተቻለም ፣
ከጌታ ኢየሱስ ጋር ወደ መቃብር ባልወርድ ኖሮ አሸናፊነት ባልተገኘም ነበር ።

ምዕራፍ ፯ ።

# ለጦርነት መዘጋጀት ።

ኢያሱ ፭ ፥ ፲ ።

«እንዲህም ሆነ ፥ በዮርዳኖስ ማዶ በምዕራብ በኩል የነበሩት የአሞራውያን ነገሥታት ሁሉ ፥ በባሕሩም አጠገብ የነበሩ የከነዓናውያን ነገሥታት ሁሉ እግዚአብሔር ከእስራኤል ልጆች ፊት የዮርዳኖስን ውኃ እስኪሻገሩት ድረስ እንደደረቀ በሰሙ ጊዜ ፥ ልባቸው ቀለጠ ከእስራኤልም ልጆች የተነሳ ነፍስ ከዚያ ወዲያ አልቀረላቸውም ።

በዚያን ጊዜም እግዚአብሔር ኢያሱን የባልጩት መቁረጫ ሠርተህ የእስራኤልን ልጆች ሁለተኛ ጊዜ ግረዛቸው አለው ። ኢያሱም የባልጩት መቁረጫ ሠርቶ የግርዛት ኮረብታ በተባለ ስፍራ የእስራኤልን ልጆች ገረዘ ። ኢያሱ የገረዘበትም ምክንያት ይህ ነው ። ከግብፅ የወጡት ሕዝብ ወንዶች ሰልፈኞች ሁሉ ከግብፅ ከወጡ በኋላ በመንገድ ላይ በምድረ በዳ ሞቱ ። የወጡት ሕዝብ ሁሉ ተገርዘው ነበር ፥ ነገር ግን ከግብፅ በወጡበት መንገድ በምድረ በዳ የተወለዱት ሕዝብ ሁሉ አልተገረዙም ነበር ። እግዚአብሔርም ወተትና ማር የምታፈሰውን ምድር ለእኛ ይሰጠን ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር እንዳያሳያቸው የማለላቸው ከግብፅ የወጡ የእግዚአብሔርንም ቃል ያልሰሙ እነዚያ ሰልፈኞች ሁሉ እስኪጠፉ ድረስ የእስራኤል ልጆች አርባ ዓመት በምድረ በዳ ይሄዱ ነበር ። ልጆቻቸውን በእነርሱ ፋንታ አስነሣ ፥ እነዚህንም ኢያሱ ገረዛቸው ፥ በመንገድ ሳሉ ስላልገረዙአቸው ሸለፈታሞች ነበሩና ። ሕዝቡም ሁሉ ፈጽመው በተገረዙ ጊዜ እስኪድኑ ድረስ በሰፈር ውስጥ በየስፍራቸው ተቀመጡ ። እግዚአብሔርም ኢያሱን ዛሬ የግብፅን ነውር ከእናንተ አንከባልያለሁ አለው ፤ ስለዚህ የዚያ ስፍራ ስም እስከ ዛሬ ድረስ ጌልገላ ተብሎ ተጠራ ።

የእስራኤልም ልጆች በጌልገላ ሰፈሩ ከወሩም በአሥራ አራተኛው ቀን በመሸ ጊዜ በኢያሪኮ ሜዳ ፋሲካ አደረጉ ።»

ኢያሱ ፭ ፥ ፩ — ፲ ።

መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ ፭ የመክፈቻ ቁጥሮቹን ብትመለከት በእስራኤል ልጆች ታሪክ አንድ አስገራሚ ነገር እንደተፈጠረ ታገኛለህ ። ከምድረ በዳ ወደ አገሪቱ ተሻገሩ ። የጠላቶቻቸውም ልብ ቀለጠ ፥ መንቀጥቀጥም ያዛቸው ። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል በወቂ ጊዜ የጠላትን ሰፈር ድንጋጤ ያዘው ።

ከነገሬ ሳልዘነፍ የምፈልገውን ልንገራችሁ ፥ ዛሬ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የጎደላት ሌላ ነገር ሳይሆን እውነተኛና ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል በውስጥዋ

ለመኖሩ ማስረጃ ወይም መግለጫ ማጣትዋ ነው ። የእግዚአብሔር ሕዝብ ማለት እስራኤላውያን ፥ ሕያው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ለመኖሩ የማያሳስት መግለጫና ማስረጃ ነበራቸው ። ይኸውም ከምድረ በዳ ወደ ምድረ በረከት በተአምራት አገባ ቸው ። ጠላቶቻቸውንም ፍርሃት ያዛቸው ።

ይህ የተመቸ የአደጋ መጣያ ጊዜ ነበረ ። በእውነቱ በሙሉ ኃይልና መሣሪያ የሚያጠቁበት ጊዜ ነው ። ግን እንዲህ አይደለም ፥ እግዚአብሔር ከቶ አይቸኩልም ። ከእኛ ችኮላ የእግዚአብሔር መዘግየት ይሻላል ። ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድ ረግ ሁልጊዜ እንጣደፋለን ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አንዳች ነገር ለእርሱ ከማድረጋ ችን በፊት እኛ ራሳችን ለእርሱ አንድ ነገር እንድንሆንለት እንደሚፈልግብን እንረሣ ለን ። ለወደፊቱ ጦርነታቸው መንገዳቸውን የሚያቃኑላቸውን ብዙ ነገሮች በጌልገላ በሚቆዩበት ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያስተምር ይፈልጋል ።

በጌልገላ ከሚማሩአቸው ስድስት ትምህርቶች ሁለቱን ባለፈው ምዕራፍ ገልጩ አለሁ ። ይኸውም ጌልገላ የመታሰቢያና የትንሣኤ ስፍራ መሆኑን አየን ። አሁንም በዚህ ምዕራፍ አራቱን ልጨርስ ስለማልችል ሁለቱን እዚሁ እንማርና የቀሩትን ሁለት ትምህርቶች ለሚቀጥለው ምዕራፍ እንተዋቸዋለን ። ትዕግሥት አትጣ ። እግዚአብሔር በጌልገላ ሊያስተምረን የሚፈልገውን ትምህርት ሳንቀበል ኢያሪኮን ለማጥቃት አትቸኩል ።

እኔ እንደማምነው የወደፊት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ፥ ጠበይና ምስክ ርነት ዋጋ የሚያገኘው በከፊል ሳይሆን በሙሉ ፥ መንፈስ ቅዱስ የቃሉን ትምህርት በልባችን ጽላት በማይፋቅ ፊደልና ቀለም ቢጽፍልን ነው ። ሥራዬ ማወጅ ብቻ ነው ። ነገር ግን ልብህንና ሕሊናህን ማርከ ይህን እውነት ገልጾልህ ፥ በሕይወትህም ውስጥ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል እንዲሰጥህ የምታምነው በእግዚአብሔር መን ፈስ ብቻ ነው ።

ጌልገላ የመታሰቢያና የትንሣኤ ስፍራ ነው ማለት ሕዝቡ ወደ ዮርዳኖስ ወር ደው ወደ ትንሣኤ ምድር የወጡበት ስፍራ ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሙሉ ከበረሃ ወደ ምድረ ከነዓን የገቡበት ስፍራ መሆኑን አየን ። በምድረ ከነዓንና በምድረ በዳው መካከል ዮርዳኖስ አለ ። አሁን ሁላቸውም በምድረ ተስፋ ናቸው ።

በሐዲስ ኪዳን አተረጓጎም ፥ ጌልገላ የተባለው ቃል የሚያመለክተው ፥ የክርስ ቶስ ቤተ ክርስቲያን በሞላዋ በቀራንዮና በሞት አድርጋ ወደ ምድረ ትንሣኤ መወሰ ድዋንና እያንዳንዱም የእግዚአብሔር ልጅ ምንም ያህል ደካማ ቢሆን በጌታችን በኢየሱስ በኩል በክብርና በአለቅነት ስፍራ መሆኑን ነው ። በዓለምና በክርስቲያን መካከል የክርስቶስ መስቀል ተተክሎአል ። ከክርስቲያንና ከኃጢአት መካከል ቀራ ንዮ ቆሞአል ፤ ስለዚህ በደሙ ተዋጅቶ ወደ ምድረ በረከት የተወሰደ ማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድረ በዳ ለመመለስ ቢፈልግ (እንደሚያደርግም እርግጥ ነው) መስቀሉን ከእግሩ በታች ረግጦ የቃል ኪዳኑንም ደም ጥቅመ ቢስና እንደ ርኩስ ነገር ይቆጥረዋል ።

አሁን ስለ ጌልገላ ሌሎች ሁለት አስገራሚ ትምህርቶችን እንድታውቅ እፈልጋ ለሁ ። እነዚህ በጣም ልብን መርማሪና የተከበሩ ናቸው ። በመጀመሪያ ይህ ነው ፥ ጌልገላ «የማስወገጃ ስፍራ» ነው ። በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አምስት መጀመሪያ ላይ በአርባ ዓመት የምድረ በዳ ጉዞ ጊዜ ቀርቶ የነበረው የግርዘት ሥርዓት እንደገና በሥራ ላይ ሲውል ታገኛለህ ። እግዚአብሔርም ሕዝቡን እንዲገርዝ ኢያሱን አዘ ዘው ። ግርዘት ምን እንደሆነ ለማስተዋል ብትፈልግ ዘፍ. ፲፯ ፥ ፲ — ፲፬ አንብብና ግርዘት እግዚአብሔር ከአብራም ጋር ላደረገው ኪዳን ማኅተም መሆኑን ታገኛለህ ። አብራምና ዘሩ ከነዓንን እንደሚወርሱ የተሰጠውን ተስፋ የሚያረጋግጥ ማኅተም ነው ።

የግርዘት ሥርዓት አገሪቱ በሥጋ ድከምና ተጋድሎ የምትወረስ ለመሆንዋ በሥጋ የሚደረግ ምስክርነት ነው ። አገሪቱን የሚወርሱአት ያለ መጠራጠር በታላቁ የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ለመሆኑ የሚገልጽ ምልክት ነው ። ሕዝቡ የማያምን እን ቢተኛ በመሆኑ ይህ ሥርዓት ለአርባ ዓመት ታግዶ ነበር ። አሁን ግን ወደ አገሪቱ ተወስዶአል ። ስለዚህ ምድረ ደኅንነትን ሲረግጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዚህ ለሚያምና ለሚያዋርድ ሥርዓት ራሳቸውን መስጠት አለባቸው ።

አሁን ሕዝቡን ምድረ ደኅንነት ከአደረሰን በኋላ ወደ መስቀል ፥ ሞትና ውር ደት እንደገና የምንወስዳቸው ስለሚመስል ይህ ነገር ሳያደናግረን አይቀርም ። ቢሆ ንም የክርስቲያንነት ኑሮ በየቀኑ ይኸው ነው ። ሐዲስ ኪዳን «በእጅ ስላልተደረገች ግርዘት» ይናገራል ። ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች የሚጽፍበትን አነጋገር ስማ «ለአለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነ በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል ። የሥጋ ንም ሰውነት በመገፈፍ ፥ በክርስቶስም መገረዝ ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ» ቆላ. ፪ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ።

በእርሱ የተሟላን እንደሆንን ማስተዋል አለብን ፥ ሁላችንም በምድረ ደኅንነት ነን ። የእኛ ምድረ ደኅንነት በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ ያለን እንዋኑዋር ነው ። የምንፈልገው ሁሉ «በኢየሱስ» ነው ። መንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በርከናልና ደከማም ሆነች ብርቱም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ ከመስቀሉ በድል ወገን ተተክላለች ።

ይህ ግን የትምህርቱ አንድ መልክ ቢሆንም ሌላ መልክ ደግሞ አለው ። በእግ ዚአብሔር ጸጋና በክርስቶስ ሞት ምክንያት በድል አገር ብንተከልም እያንዳንዳችን ማድረግ የሚገባን ነገር አለ ። ሁላችንም በመጠቃለል በድል ስፍራና በበረከት ምድር ብንደረግም ቅሉ እያንዳንዳችን ለየራሳችን ተነሥተን በፍጹም እምነት ፥ እሺ ታና ግልጽነት ለታላቁ የነፍስ ሐኪም ቢለዋ ራሳችንን መስጠት አለብን ። ይህ ነገር በጥልቅ ማለት በወል ልናደርገው የማንችል ነገር ነው ። እያንዳንዱ ሰው በየራሱ ማድረግ አለበት ። ወደ ታላቁ ሐኪም ቅረብና ልብህንና ፈቃድህንም ሁሉ ያለማመ ንታት ስጠው ። ወደ ቀራንዮ ተመልከትና የክርስቶስ መስቀል በእያንዳንዱ ባሕር ይህ ፥ ጠባይህና እንዋኑዋርህ ሁሉ እንዲታተም ፍቀድ ።

ለዚህ ሁሉ ምክንያት ምን እንደሆነ አይገባህ ይሆናል። በሙሉ እምነት የም ዋሰው የጳውሎስ አነጋገር ይህ ነው «እኔ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቼ ነበርና» ገላ ፪ ፣ ፲፱። ምን ማለቱ ነው ? ይህ ነው ፣ ምትኬ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን በትክክል በመፈጸሙ ፣ የእግዚአብሔርንም ፍላጎት በሙሉ በማጥገቡ ፣ ሕግ በኃጢአተኛ የሚፈርደውን የሞት ፍርድ ራሱ ሞቶ በመክ ፈሉ እኔ ለሕግ የሞትሁ ነኝ። በሌላ አነጋገር ሕግ በፍርዱ በኩል በእኔ ላይ ሥል ጣን የለውም ማለት ነው።

በክርስቶስ በእውነት ያመንኩት በእንግሊዝ አገር ግሬይ ቡል በምትባል ቤት ነበር። ከዚያ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን በብዛት አላነብም ነበር። ያን ቀን አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አሳየኝና ከሮሜ ፰ ፣ ፩ አስረዳኝ። «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም ።»

ያ ቁጥር እንዴት ያለ ክቡር ነገር ሆነልኝ። ደግ ሰው ለመሆን ብትፍጨረጨር ቤተ ክርስቲያን በየእሁዱ ብትሄድ ፣ ብትጸልይና ብትጾም መጽሐፍ ቅዱስንም ዘወ ትር ብታነብ አንድ ቀን የምትድንበት ጊዜ ይመጣል አይልም። እንዲህ ይላል «እን ግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» ያችን «አሁን» የምትለ ውን ትንሽ ቃል በኃይል ከሥርዋ አስመርኩአትና እስከ ፊልጵስዩስ መልእክት አጋ ማሽ ድረስ መጽሐፍ ቅዱሴን በዚያን ቀን አበላሽሁት። መበላሸቱ ግን ዋጋ ነበረው «እኔ ግን በሕግ በኩል ለሕግ ፈጽሜ ሞትሁ» ሕግ በእኔ ላይ ፍርድ የለውም ፤ የሕግ ፍላጎትና ፍርድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት ተፈጽሞአል።

ይህ በጸጋው ስለ ተተከልንበት ስፍራና አቋማችን ትክክለኛ ነው። ነገር ግን በእያንዳንዱ ሰው ሕይወትና እንዋኑዋር መፈጸም አለበት። ዛሬ በእኔና በእግዚአብ ሔር መካከል ያለው ይህ ነው። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን አቋም በእውነት ተቀብሎ እንደሆነ የሚመረመርበት ስፍራ በኑሮው ያጋጥመዋል። ይህን ማለቴም እያንዳንዱን ኃጢአትና መተላለፍ አንድ በአንድ ወስጄ በመስቀል እንድቸነክረው አይደለም። ይህን ላደርገው ከቶ አልችልም። እስከ ሞት ድረስ ቀኑን ሁሉ በሥራ ላይ አውላለሁ ፣ ይህም ባይሆን ስንኳ ዐመጼን ሁሉ ሰቅዬው አልጨርስም ወይም ደግሞ ይህን ኃጢአተኛ ሥጋ ወስጄ በመስቀል እንዳንጠለጥለውና እንድቸነክረው አይደለም። ትርጉሙ እንዲህ ነው። ኢየሱስ ሁሉንም እንዳደረገልኝ ማመን ነው። እርሱ ያልከፈለለት ኃጢአት ፣ ዐመልና ድካም በሕይወቴ እንደሌለ ማመን ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ አድራጎት ኃጢአቴና ውድቀቴ ሁሉ ለዘላለም እንደተረታ ማመን ነው። ይህም እውነተኛ ነገር መሆኑን ለልቤ እንዲገልጽልኝ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲያደርብኝ መፍቀድ እንደሚገባኝ ማመን ነው።

ክርስቲያን ጓደኛ ሆይ ፣ ስለ ክርስቲያንነት አንዋኑዋርህና ጠበይህ ይህ ነገር እው ነትና በኑሮህም ልትቀምስና ልታውቅ የሚገባህ ከሁሉ የበለጠ ታላቁ ቁም ነገር ነው። ስለ አንተ ድካምና ስለ ዲያብሎስ ኃይል በትክክል አበጥሮ የሚያውቅ

የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው። ስለዚህም በዚህ ነገር በልብህ ውስጥ የሚያስፈልገውን እንደሚገባ ሊሠራ የሚችል እርሱ ብቻ ነው። የሕይወትህን መሥዋዕት በቀራንዮ መሠዊያ ሊያስር የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነው። እርሱ ብቻ በውስጥህ ቢኖር ሥጋን እንደሞተ በሞት ስፍራ ጨቁኖ ሊይዘው ይችላል። ይህን ለማድረግም እርሱ ሁሉን ያያል፣ ሁሉን ያውቃል ሁሉንም ይችላል። ሥጋን ከምኞቱ፣ ከውሸታምነቱና ከአምሮቱ ጋር በሞት ስፍራ እንዲቆይ በሚያደርገው በመስቀሉ ነበልባል በልብህ ሊሠራ የሚችል የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው።

ክርስቲያን ማለት ኃጢአት የማይሠራ፣ የመተላለፍም አምሮት ከአንዋኑዋሩ የተፋቀ ነው የሚል ሰው ቢኖር ከእርሱ ጋር አልስማማም፣ ደግሞም እንዲህ ያለ ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አለ ብዬ አላምንም። ይህ አይደለም፣ ኃጢአት የመሥራት አምሮት ፍላጎትና በቀላሉም መበደል አብሮን ይኖራል። በኃጢአት ሥጋ እንኖራለን። እስከንሞት ድረስም ከእርሱ ጋር ነን። ነገር ግን በውስጣችን ከዚህ የሚበረታ ኃይል አለ። እርሱም የሥጋን ኃይል የሚያሸንፍ የክርስቶስ መንፈስ ራሱ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር እኔን ልጁን ደግሞም ከእኛ እያንዳንዱ ለየግሉ ወደ ነገሥታት ንጉሥ አዳራሽ ገብቶ ለማጥራት ለሚቀነጥብበት የማጥሪያ ሰይፍ ሰውነቱን በግልጽ እንዲሰጥ ይጠይቃል። ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ ብሎአል «ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል» ዮሐ. ፲፭፣ ፪።

እግዚአብሔር ለክርስቲያን አገልግሎትህ በረከት አልሰጠህምን? እግዚአብሔር ንስሐ የሚገቡና የሚድኑ ሰዎች አልሰጠህምን? ለልጆች ወይም ለአዋቂዎች የሰንበት ትምህርት ታስተምራለህ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ታስረዳለህ፣ ስለ ክርስቶስ በየቀኑ ትመሰክራለህ ወይም ለመመስከር ትሞክራለህ፤ ዳሩ ግን አንዳች ነገር ሲፈጸም አታይም። ስለዚህ ነገር በበኩልህ ምን ታስባለህ? ምናልባትም «እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነውና ውጤቱን እንዲያሳምር ለእርሱ እተዋለሁ» ትላለህ። የእግዚአብሔርን ከሃሊነት ሁሉን ቻይነትና ሥልጣን ለራስህ የኃጢአተኝነት አንዋኑዋር ማመከኛ ታደርጋለህን?

የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አንድነት ሲባል በውስጥዋ የሚገኙ ጥቂቶች አገልጋዮችና የሥራ ኀደኞቻቸው ሆኖ ሥራውንም የሚሠሩ እነርሱ ብቻ ናቸውን? ሌሎች ምዕመናን ተመልካቾች ናቸው የሚል እምነት ተፈጥሮብህ ይሆን? የክርስቲያን ኃላፊነት ይኸው እንደሆነ ትገምታለህን? እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የዋጀህ በአንተ በኩል ደግሞ ወደ ሌሎች እንዲደርስ መሆኑን አላስተዋልክምን?

አምላክ እጅ የለውም ያንተ የእርሱ ናቸው።
ዛሬ ሥራውን ሁሉ የሚሠራባቸው።
እግዜር እግር የለውም ያንተ የእርሱ ናቸው።
ሰውን በመንገዱ የሚመራቸው።

ምናልባት አሁን ይህን የምታነብ ሆይ ፣ ለብዙ ዓመታት ክርስቲያን ሆነህ ሳለህ ከአንድ ሌጣ ሰው ጎን ተቀምጠህ ወደ ክርስቶስ ያልመራህ ይሆናል ። ይህ ነገር እውነት ከሆነ በኑሮህ ውስጥ በአንድ ስፍራ ስሕተት አለ ። ምናልባት የክርስቶስ መስቀል በኑሮህ በጠባይህና በሰውነትህ ክፍሎች ሁሉ እንዳይሠራ አድርገህ ይሆናል ። ከእያንዳንዱ አማኝ ጋር በደኅንነት ስፍራ ቆመሃል ። በምድረ በረከት ነህ ፤ ነገር ግን በአንዋኑዋርህ በምድረ በዳ ትገኛለህ ። በጌልገላ ትንሽ ሰንብተህ ደህና ሥር ሰደህ እግዚአብሔርም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሕይወትህ ላዘጋጀው ሁሉ ራስህን እስክታስረክብ ድረስ እንድትቆይ እለምንሃለሁ ።

ለጌታ ተግሣፅ መገዛትን እንቢ ብለህ ይሆን ? ምናልባት ሰውነትህ በሥቃይ ደቅቆ አንተም የእግዚአብሔርን አስታማሚነት አልቀበልም በማለት ታግለህ ይሆን ? በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ አምፀህ ከአንተ በቀር ሌላ ሰው ስለ እርሱ አንዳች ነገር የማያውቅ የልብ ችግርና ሥቃይ ትሸከም ይሆናል ። የቅርብ ጓደኛህና ወዳጅህ ስለ እርሱ የማያውቁት ያ የልብህ ችግር በእግዚአብሔር ዓይን ፊት የአመፅ ምልክት መሆኑን አምላክ የሚፈርደው ይሆን ?

ምናልባት ይህ የልብህ መራራ ስሜት እግዚአብሔር ወደ ባዕድ አገር የወንጌል መልእክተኛ ሆነህ እንድትሄድ ጠራህ ፣ አንተ ግን ይህንን ማድረግ በጣም ከምትወዳቸው ቤተ ሰብ መለየትን የሚጠይቅ መሆኑን ስለተገነዘብክ ችላ አልክ ወይ ? በየሳምንቱ በእግዚአብሔር ፊት ትቆማለህ ፣ ከሕዝቡም ትገናኛለህ ፣ እግዚአብሔርም ተናገረህና ለአንተ ያዘጋጀውን ዓላማ ገለጸልህ ። ሰይፉንም መዝዞ ወደ ልብህ ሊጠልቅና ከዐመፅ ሁሉ ሊያጠራህ ፈለገ ፣ አንተ ግን «የለም አይሆንም ፣ አልችልም» አልክ ይህ ነውን ?

ክርስቲያን ጓዴ ፣ ከሰይፉ አትፍራ ፣ ሰይፉ ያለው የነፍስህ ወዳጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ነው ። ሊያድንህ የሞተው ሊጎዳህ የሚቃጣ አይደለም ። ምንም ያህል ቢጎዳህም እንኳ ጌልገላ ለአንተ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነውንና መንፈስ ቅዱስ የገለጠልህን ኃጢአት ሁሉ የምታስወግድበት የምትተውበትና የምትክድበት «የማስወገጃ ስፍራ» ይሁንልህ ። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማስረዳት ብቻ ሳይሆን የክርስቲያንነት አንዋኑዋር የሆነው የኑሮ አቋም ይህ ነው ። እውነትን ማስተዋል ብቻ አይበቃም ፣ ነገር ግን በጌታህ ፊት ውስጥ በሃይማኖት እያየህ የቀራንዮን ምሥጢር ለነፍስህ እንዲገልጥ መጠየቅ ነው ። ይህም የሚያጎድልብህ ቢመስልህ አትጨነቅ ፤ ታዲያ ይህን ማስወገጃ ልትገናኝ ትፈቅዳለህን ?

የነገሩን ሌላ መልክ ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ ስለምገልጽልህ ደስ ይለኛል ። ስለ እርሱም ማሰቡ ብቻ ነፍሴን በደስታ ይመስጣታል ። ኢያሱ ፭ ፣ ፲ ሕዝቡ በጌልገላ ሰፈሩ ብሎ አያቆምም ። ነገር ግን «ከወሩም በአሥራ አራተኛው ቀን በመሸ ጊዜ በኢያሪኮ ሜዳ ፋሲካ አደረጉ» ይላል ። ደግሞም ጌልገላ «የማደሻ ስፍራ» ነው ።

ከዚያ በፊት ፋሲካ ሁለት ጊዜ ብቻ ተከበረ ፣ አንዱ እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡ ቀን ሲሆን ሁለተኛው በሲና ተራራ ነው ። ከዚያ በኋላ እስከ አሁን ጊዜ

ድረስ ፋሲካ አልነበረም። ይህ የስግደት፣ የመታሰቢያና የአንድነት በዓል ጨርሶ ተቋረጠ። የተቋረጠውም በሕዝቡ ፍላጎትና ምርጫ ሳይሆን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ነበር። ማንም ያልተገረዘ ሰው ከፋሲካው በዓል እንዳይካፈል አዘአል። ዘጸ. ፲፪፣ ፵፰። በፋሲካው ሌሊት የተደረገላቸውን አርነት በማስታወስ እግዚአብሔር ባስገኘላቸው ድል እንዲደሰቱ አልተፈቀደላቸውም። ለዚህ የነበራቸውን መብት አቃለሉ፣ ክብሩንም በእንቢተኝነትና በአለማመን በመኖር ለወጡት። ስለዚህ ፋሲካ አልነበረላቸውም።

ከልቤ ምኞት፣ ናፍቆትና አምሮት ልነግርህ የምወደው ይህ ነው። በአንዋኑ ዋርህ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ እስከለ ድረስ፣ በጌታ ልትደሰት፣ በልብህ በዓል ልታደርግና ለእግዚአብሔርም እውነተኛ የልብ ስግደት ሊኖርህ አትችልም። አንድ አንድ ጊዜ እሁድ በቤተ ክርስቲያን የምታደርገው ስግደት ስሜት ባይሰጥህና ጥቅመ ቢስ ቢመስልህ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስም ጥቅም የማታገኝ ብትሆን ይህ ሁሉ ለተዘጋጀ ልህ በረከት ያለህን መብት በማቃለልህ እንደሆነ ልብህን ጠይቅ። በእንቢተኝነትና በለመታዘዝ በመኖር ለሚደሰቱ ሰዎች እግዚአብሔር በረከቱን ደስታውንና አንድነቱን አይሰጥም። ስለ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን «ስፍራው ጨርሶ ሞቶአል» ሲባል ብዙ ጊዜ እሰማለሁ። ይህም የሆነው በዚያ የሚሰበሰቡት ምዕመናን በፍጹም ለእግ ዚአብሔር ቃል የማይታዘዙ ሳይሆን አይቀርም።

የግርዛት ሥርዓት ሲታደስ ያን ጊዜውኑ ፋሲካን አከበሩ ፈነጠዙም። በታዘዙ ባት ወቅት ሰማይ ተከፈተላቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው አንድነት በዓል አደ ረጉ፣ ተደሰቱም። ፈቃደኞች ሆነው ለሞት ሕግ ማለት ለግርዛት በተገረዙበት ወቅት ያን ጊዜ እግዚአብሔርም እውነተኛነቱን ገለጠ።

ልቤ ከሳምንት ወደ ሳምንት ከእግዚአብሔር ጋር እልከኛ ወደ ሆነውና ራሱን ፈጽሞ ለክርስቶስ ወዶ ላስረከበ ሰው ነው። ወዳጄ ሆይ፣ ጌታ ሊባርክህ አጠገብህ ነው። አንተ ብትፈቅድ ስለራሱና ስለራስህ እውነቱን ሊገልጥልህ አጠገብህ ቆሞ አል። ለግርዛት ሥርዓት በታዘዙበት ወቅት ፋሲካ አደረጉ።

እርግጥ ነው የፋሲካው በግ ደም አንድ ጊዜ ፈሰሰ ሕዝቡም አንድ ጊዜ ከግ ብፅ በርነት ነፃ ወጡ፣ ዳሩ ግን ለዚያ ቀን ማስታወሻ በየዓመቱ በዓሉን ያከብራሉ፣ ሐሴትና ደስታም ያደርጋሉ።

ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ የፋሲካችን በግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥቂት ደቀ መዛሙርትን በዙሪያው ሰብስቦ በሰገነት ላይ እንጀራ ቆርሶ በርከ በሰጣቸውና ለመሞቱ መታሰቢያ እንዲያደርጉ በዘዛቸው ጊዜ አሮጌው የፋሲካ ኪዳንና በዓል ከእ ርሱ ለሚበልጠው ለሐዲስ ኪዳን ስፍራ ለቀቀ።

ሃይማኖት ወደ ማየት ተለውጦ ሕዝቡ ሁሉ በበጉ ሠርግ የእራት ገበታ ዙሪያ በሚሰበሰቡበት ያ ታላቅ ቀን ይህ ሐዲሱም ይቀራል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማ ድረግ ስንታገል ለደረሰብን የሞላው ዕድሜ ሥቃይ፣ ጣርና ውጊያ፣ በሰማይ የአምስት

ደቂቃ ጊዜ ይከሰዋል ። ነገር ግን እስከዚያ ቀን ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በዓል እያደረግን ሐሴትና ደስታ እንድናገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ።

በየቀኑ የሰማይን እንጀራ ካልበላህ የሰማይን ሥራ ልትሠራ አትችልም ። በልብህ ሥር በኢየሱስ የምትደሰት ካልሆንክ በከንፈርህ ስለ ኢየሱስ ልትመሰክር አትችልም ። ሕያው የሆነ ክርስቶስን ለማወጅ ራሱ በውስጥህ በመኖሩ መደሰት የሚቀድም ዓይነተኛ ተግባር ነው ። ራስህ ዘጠኝ አሥረኛ በመንፈስ የሞትህ ስትሆን እንዴት አድርገህ ሌላውን ነፍስ ወደ ሕይወት ልታመጣ ትችላለህ ? ከቶ ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነው ። በከንፈርህ መጽሐፍ ቅዱስን አሳምረህ እንደምታስተምር አውቃለሁ ስለ እርሱም ለጓደኛህ ትነግራለህ ትጠቅስለታለህ በመከራከርም ልታሸንፈው ትሞክራለህ ፣ የአማረና አስደሳች በሆነ በወንጌላዊ አነጋገር ትናገራለህ ፣ ነገር ግን ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ ምንም ውጤት ያላስገኘህ ሆኖ ታገኘዋለህ ።

ምክንያቱን ታውቀዋለህን ? ትንሽ አረፍ ብለህ በልብህ ሥር በክርስቶስ እንዳትደሰት ሁልጊዜ ችኩል ነህ ፣ ትጣደፋለህም ። ለሌሎች የምትነግረው ሳይሆን ራስህ እውነትን ለማወቅ ምን ያህል እንደምትመኝ ብትገምት ባለፈው ሳምንት ከእግዚአብሔር ጋር ሆነህ ለብቻህ ምን ያህል ጊዜ አሳለፍህን ? መጽሐፍ ቅዱስን በፊትህ ዘርግተህ ለብቻህ በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ እግዚአብሔር እንዲናገር የጠበቅኸው ምን ያህል ጊዜ ነው ? በዚያ ስፍራ ድካምህ ኃይሉን ይመጥጣል ፣ ጥድፊያህ ችኩልነትህ ፣ መቃተትና ብስጭትህ በእርሱ ኃይልና ሰላም ጸጥ ይደረጋል ። አለመታገስህም የእግዚአብሔርን ጸጋና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ትዕግሥት ይቀበላል ። ይህ ደርሶብሃልን ? ይህን መዝሙር ስማ ።

የሰላም ጤዛን አውርድልን  
ጸጥ እስኪል መከራችን ።  
ትግልና ጣርን አንሣ ከነፍሳችን  
ይተርክ የተመራው ሕይወታችን  
ቁንጅናና ታላቅነት ሰላምህን ።  
ተናገር በምኞታችን ሙቀት  
መዓዛ ጸጥታና በራድነት  
ሥጋ ይርጋ ፣ ይደንቁር ስሜት  
ተናገር በምድር መናወጥ በነፋስ በእሳት  
ለብ ያልክ ድምፅ የተሰጠህ ለደኅንነት ።

እኛ ግን ይህን እንዲያደርግ የአምስት ደቂቃ ጊዜ እንኳ አልሰጠነውም ።

ጌልገላ የመተውና የማደሻ ስፍራ ነበር ። አሁንም ለአንተ የማስወገጃና የማደሻ ስፍራ ሊሆን ይችላል ። ወንዙን ተሻግረው በጌልገላ ሰፈሩ ፣ ወንዙን በተሻገሩ በአራተኛው ቀን ማለት በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን በመሸ ጊዜ ፋሲካን አከበሩ ። እንዴት ፈጥነው ታዘዙ ። በኢያሪኮ ሜዳ በዓል አደረጉ ፣ ፈነጠዙም ። ልክ በዲያብሎስ ዓይን ሥር የእግዚአብሔርን በረከት ልናገኝ የምንችለው እንደዚህ

ባለ ስፍራ ነው ። ሰይጣንንም ድል የምናደርገው በዚያ ስፍራ ነው ። በጥርሱ ተን ክል ሥር ሳለን የሰማዩን አበታችንን ድል እናገኛለን ።

በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በገዳምና በደብር እየኖሩ የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበልና ከእርሱ ለመገናኘት ተስፋ ማድረግ ይገበል የሚል ነገር መሠረት የለ ውም ። አስቀድሜ እንደተናገርኩ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻችን የምንሆንበት ጊዜ መኖር አለበት ። ነገር ግን «በጠላቶቼ ፊት ማዕድ ታሰናዳልኛለህ» የሚባለውን እነ ጋገር እውነተኛነትና ቡሩክነት ተረድቼአለሁ ። በዲያብሎስ ዓይን ሥር በምታደርገው ውጊያ በጌታ በኢየሱስ በዓል አድርግና ኢየሱስ አሸናፊ መሆኑን ግለጽለት ፣ ጌልገላ ይህ ነው ።

መጥፎ ልማድና ጠባይ መተውና ማስወገድ ፈቃድህ ከሆነ የማደሻ ስፍራ አለ ልህ ። ኢየሱስ አሁን ወደ ልብህ ሊቀርብ ይጠብቃል ። ነገር ግን በልብህ ዙፋን እንዲት አነስተኛና የማትረባ ጣዖት ስለምታስቀምጥ ለኃይሉና በውስጥህ ለመኖሩ ያለህን መብት ታቃልላለህ ። አሁንም ፍጹምን ማስወገጃ ማለት የሥጋን ምኞትና አምሮት መካድን የገበሬውም ቢለዋ የበሰበሰውንና የደረቀውን የጠመመውንና የተበ ላሸውን የአሮጌ ኑሮን ቅርስ እንዲቆርጥና እንዲያጠራህ ትፈቅዳለህን ?

ታማኞች ግልጽ መሆን ከፈለግንና ከታዘዝን ወዲያውኑ ፋሲካን እናከብራለን ። «የሚቃጠለውም መሥዋዕት ማድረግ በተጀመረ ጊዜ የእግዚአብሔር መዝሙር ደግሞ ተጀመረ ፣ መለከቱም ተነፋ ፣ የእስራኤልም ንጉሥ የዳዊት ዜማ ዕቃ ተመታ» ዜና መዋዕል ካልዕ ፳፱ ፣ ፳፯ ። የእግዚአብሔር ልጅ በእውነት ወደ አምላኩ መጥቶ የክርስቶስ መስቀል በጠባዩ በዐመሉና በሰውነቱ አካል ክፍሎች ሁሉ እንዲ ሠራ ከፈለገ ምንም ጥቅመ ቢስ ቢመስለውም ያን ጊዜ ሰማይ ተከፍቶ የጌታችን ሰላምና ደስታ ነፍሱን የበረከት ሁሉ ወንዝ ምንጭ ያደርገዋል ፣ ከማስተዋልም ሁሉ የበለጠ ሰላም ልቡን ይሞላል ። ይኸውም ጠላቶቹ ባሉበት ስፍራ እነርሱ እያዩ በዓ ይናቸው ፊት ይደረጋል ።

ምዕራፍ ፯።

# የመገናዘብ ዋጋ ።

ኢያሱ ፭ ፥ ፲፪ ።

«የእስራኤልም ልጆች በጌልገላ ሰፈሩ ፥ ከወሩም በአሥራ አራተኛው ቀን በመሸ ጊዜ በኢያሪኮ ሜዳ ፋሲካ አደረጉ ። ከፋሲካውም በኋላ በነጋው የምድሪቱን ፍሬ የቂጣ እንጎቻ ቆሎም በዚያው ቀን በሉ ። በነጋውም ከምድሪቱ ፍሬ ከበሉ በኋላ መናው ቀረ ። ከዚያም በኋላ ለእስራኤል ልጆች መና አልመጣላቸውም ። ነገር ግን በዚያው ዓመት የከነዓንን ምድር ፍሬ በሉ ።

እንዲህም ሆነ ፥ ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዓይኑን አንሥቶ ተመለከተ ፥ እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር ። ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን ? አለው ። እርሱም አይደለሁም ፥ እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ አለ ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው ? አለው ። የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ ኢያሱን አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው ። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ ።» ኢያሱ ፭ ፥ ፲ — ፲፭ ።

የሚገጥሙንን መንፈሳዊ ውጊያዎች ለመጋጠም ስንዘጋጅ ባለፉት ሁለት ምዕራፎች ከእስራኤል ልጆች ጋር በዮርዳኖስ ዳርቻ ነበርን ።

ከዚህ በፊት እንደተናገርኩት ጌልገላ ለሁሉም ነገር የመክፈቻ ቁልፍ ስፍራ ሆኖላቸዋል ። እንደማምነው ለእኛም የልብ ምርምር ስፍራ ሳይሆን አልቀረም ። ለመማር ቀላል ያልሆኑ ትምህርቶችን እዚያ ተምረናል ። ነገር ግን ከጴንጠቆስጤ ቀራንዮ መቅደም እንደነበረበት አስተውለናል ። የሕይወት ውኃ ወንዝ ደግሞ ከእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ወደ አማኞች ልብ ከመፍሰሱ በፊት እኛ ምዕመናን ሕዝቡ ለራሳችን በፍጹም የሞትንና ለእግዚአብሔር ፈቃድ የተሰጠን መሆን አለብን ።

ጥቂቶቻችሁ እንዲህ ሳትሉ አልቀራችሁም ፥ ይህ ሁሉ አስፈላጊ ነውን ? እንዲህ ያለ ታላቅ መሥዋዕትነት ይፈለግብኛልን ? ሥጋዬን ልጨቁንና ስለ እግዚአብሔር ብዬም የሚደርስብኝን ሁሉ እታገሳለሁ ። ታዲያ ይህን ያህል ረጅም ጉዳና መጓዝ ይኖርብኛልን ? በእውነቱ በብዙው መጨነቅ ፥ መጠበብና መቃተት የሌለበት የክርስቲያንነት አንዋኑዋር መኖር አልችልምን ?»

እርግጥ ነው ፥ ለዚህ ጥያቄ መልሱ «አዎን» ነው ። «አዎን ፥ እርግጥ ነው ይቻላል» ሰዎች ዛሬ በሁለተኛ ማዕረግ በረከት በቃን ብለው የሚኖሩ መሆናቸው የማይካድ ነገር ነው ። ስለዚህ ነው ፥ ዛሬ በአስጊው ሰዓትዋ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ከሰማያዊ ምንጮችና ከሰማያዊ ሥልጣን ጋር ጎን ለጎን ልትራመድ ያልቻለችው ።

አንድ ክርስቲያን ፥ ክርስቶስ በውስጡ እንዳደረ ማመን ሲጀምር ፤ ድሉንም ማሰብ ከኃይሉም ምንጭ መቅዳት ሲጀምር በሙሉ አዲስ የሆነውን አገር እንደረገጠ ይሆናል ። ሃይማኖቱ በክርስቶስ መስቀል የተተከለ የእግዚአብሔር ልጅ ከእግዚአብ ሔር ዙፋን ጋር ግንኙነት ስላለው አሁን ይኸው ሃይማኖቱ ሲያፈራ ያገኘዋል ። ወደ ቀራንዮ መስቀል ብቻ ሳይሆን በሰማይ ዙፋን ወደ ተቀመጠው ወደ ክርስቶስ መመ ልከት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አዲስ የኑሮ ጣዕምና የልብ ተመስጦ አይደለምን ? በየቀኑና በየደቂቃው ፍጹም የሆነ የተሟላ የሰማይ ኃይል ከእርሱ እያገኘን የሞተልን ክርስቶስ እርሱ ራሱ ሕይወታችንም መሆኑን እንገነዘባለን ። የፍላጎታችን አምሮታ ችንና ምኞታችን ሁሉ ምንጭ በእርሱ ነው ። እርሱም ከሙታን የተነሣና «የሙታን ሁሉ በኩር» የሆነው ነው ።

መና የምድረ በዳ ምግብ ነበረ ፤ ለምድረ በዳ ጉዞ ምቹ ነበር ። እህል እስኪያ ገኙ ድረስ በምድረ በዳ ለፍላጎታቸው በቂ ነበረ ። እግዚአብሔር ለልጆቹ በሚሰጣ ቸው ስጦታዎች መካከል ማቋረጥ አይገኝም ። በአካባቢያችን ሁኔታዎች ተደናግረን በመገረም እንግዲህ ምን ሊያደርግብን ያስብ ይሆን ? ብለን እንድናስብ የሚያደርግበት ጊዜ አይጠፋም ፤ ልባችንም በሥቃይና በኀዘን የሚሞላበት ጊዜም አለ ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚሰጠን የሰማይ ብርሃን ምን ጊዜም አያቋርጥም ።

ይህ ልዩነት ግን አለ ፤ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ልጆቹን በመድኃኒታችን በኢየ ሱስ ክርስቶስ ከተሰጠን የደኅንነት እንዋኑዋር ወደአልተገለጡና አዲስ ወደ ሆኑ ስፍ ራዎች ይመራናል ። የተለየና ያልተለመደ ከሆነው ከበረሃ መና ለይቶን ከትንሣኤው ኃይል የሚመነጩትን የጸጋ ስጦታዎች ሊሰጠን ይፈልጋል ፤ ክርስቲያኖች ግን መሻሻ ልና ወደ ፊት መገሥገሥ የሚቻል መሆኑን የማይገነዘቡ እንዴት ያሉ አመንቺዎች ናቸው ? እግዚአብሔር እንደሚለውጠው የምንጠራጠር እንዴት ያለን አመንቺዎችና ወላዋዮች ነን ?

በማናቸውም የኑሮ ክፍሎች እንደሚደረገው ሁሉ ፥ በዕድሜ እየገፋን በሄድን ቁጥር መለወጥ ወይም መሻሻል የሚባለውን ሐሳብ እንደምንጠላና እንደምንጠራጠረ ውም እርግጥ መሆኑን አውቃለሁ ። የዱሮዋ ቤት ፤ የዱሮው እንዋኑዋር ፤ የዱሮዎቹ በመሉች ፥ ጠባዮችና ጨዋታዎች ፤ የዱሮዎቹ ወዳጆች ሁልጊዜም የተሻሉ ናቸው ። እነርሱንም መተው አስቸጋሪ ነው ። እግዚአብሔር ለልጁ በሚሰጠው ማሰልጠኛ ውስጥ አንድ የመተሳሰብ ቀን ይደርሳል ። እስከዚያች ቀን ድረስ የዱሮዎቹ መንገ ዶች ፥ ሥራዎችና እንዋኑዋሮች ለእግዚአብሔር ሥራ መንገድ ሲያዘጋጁ ኖረዋል ። ከዚያ በኋላ ግን ለክርስቲያን ውጊያዎች ሥነ ሥርዓትና በቂ ትምህርት መሆናቸው ቀርቶአል ። የተወደድክ ክርስቲያን ሆይ ፤ ለእርሱ ከምትሠራው አገልግሎት አንተ ራስህ ለእግዚአብሔር ከሁሉ የበለጥህ ክቡር ዕንቁ መሆንህን ሁልጊዜ አስታውስ ፤ እንድትፈጽመው እርሱ የሚሰጥህ ማናቸውም ሥራና መከራ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሙሉ ሰው ወደ መሆን ወደ ክርስቶስም ፍጹም አካል የሚያደርስህ መሆኑን ተገን

ዘብ ። ስለዚህም እግዚአብሔር ሁልጊዜ ልጆቹን ሊመራቸው ሊለውጣቸው ሊያዘጋጃቸው ለጸጋውና ለሥልጣኑም በለጠግነት ሊያሰናዳቸው ይፈልጋል ።

ወዳጄ ሆይ ፣ እስቲ አንዋኑዋርህን መርምር ፤ በጊዜያዊ የመንፈስ ሞቅታ ፣ በመንፈሳዊ ተመስጦና በስሜታዊ ስብሰባዎች አትመካ ። እነዚህ ሁሉ የክርስቲያን አለመብሰል ምልክቶች ናቸው ፤ እነዚህ በሕፃናት መደሰቻ ስፍራ መሆን የሚገባቸው ናቸው ። ይህ ምን ማለት እንደሆነ አስተውለሃልን ? እንዲህ ነው ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ የተመራ ሰባኪ በቤተ ክርስቲያናችሁ ወይም መንደራችሁ መጥቶ ሲሰብክ ስትሰሙ ስለ ኃጢአታችሁ ታለቅሳላችሁ ፣ ለወደፊቱም ደህና ክርስቲያኖች ለመሆን ትወስናላችሁ ። ለሁለት ወይም ሦስት ቀን መጥፎ ጨዋታ አነጋገርን ሁሉ ትጠላላችሁ ። ነገር ግን ሳምንት ሳይሞላ ወደ ዱሮው ሥራችሁ ትመለሳላችሁ ። ለእግዚአብሔር ኀበዝና ብርቱ ሰው ልትሆን ትፈቅዳለህን ? ሰይጣን እየፈረጠጠ ሲሸሽ ልታይ ትመኛለህን ? እንግዲያውስ የምድሪቱን ፍሬ ብላ ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተራቡትን በበጎ ነገር ይሞላቸዋል ፣ የሚጓጓውንም ነፍስ ያረካል ፤ ዛሬም ሊመራህ ፣ መንፈሳዊ ዓላማዎችን ለማየትና የክፉውን ኃይል በስሙ እንድትደመስስ ክርስቶስ ራሱ የአንተ ነው ። በመስቀሉ ኃይል የክርስቲያንነት አንዋኑዋርህ የማፍራቱ ወራት ይድረስ ፣ ከእግዚአብሔርም ዘሩን ይመገብ ። የክርስቲያንን ሃይማኖት ሀ ፣ ሁ ፣ ማለት የመጀመሪያ ትምህርት ተውና ከሙታን በተነሣው በክርስቶስ በዓል እያደረግህ እግዚአብሔር ኃይሉንና ችሎቱን ሰጥቶህ በእርሱም ከክፋት ጋር በምታደርገው መጋደል ታላቅ አርበኛ እስኪያደርግህ ድረስ በእርሱ ጽና ።

ጌልገላ የመገናዘቢያ ስፍራ ሆነ ። የምድረ በዳ ጉዞ አለቀ ፣ የኃጢአተኝነት ኑሮው ተወገደ ፣ ለበረሃ የሚመቸው ምግብም ተቋረጠ ፣ ሕዝቡ ከበረከት አገር አዲስ ሕይወት ይቀበላሉ ። እኛም ከሙታን በተነሣው ክርስቶስ የበጎን ነገር ሁሉ ምንጭ አግኝተናል ።

ነገር ግን ጌልገላ ሌላ ተጨማሪ ነገር እንደነበረ ላሳይህ እወዳለሁ ። ጌልገላ «የገለጻ ስፍራ» ነበረ ።

አሁን እስራኤላውያን ለጦርነት ተዘጋጅተዋል ። በአገሪቱ የሚገኘውን ባላጋራ ለማሸነፍ በአገሪቱ ፍሬ በዓል አደረጉ ። አሁን ኢያሱ ከተማይቱን ሊሰልልና የሚያስፈልጉትን ለመገመት ይወጣል ። ኢያሪኮ የማትበገር መስላ በፊቱ ተደቅናለች ፣ ነገር ግን ሳትማረክ ወደ ኋላ መቅረት የለባትም ። ያ በምድረ በዳ ጉዞና ጦርነቶች የሰለጠነ ጀኔራል ራሱን እንዲህ ሲል እንደሚጠይቅ አምናለሁ ። «እነዚህን ቅጥሮች ለመውጣት ስንት መሰላሎች ያስፈልጉኝ ይሆን ? እነዚህንም ታላላቅ መዝጊያዎች ለማድቀቅና ገፍቶ ለመጣል ስንት መስበሪያዎች ያስፈልጉኝ ይሆን ?»

አንድ ሰይፍ የመዘዘ ሰው ድንገት ከፊቱ ቆመና አፈጠጠበት ። ኢያሱ ግን በድፍረት እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል ። «ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን ?» ለኢያሱ የተሰጠው ምላሽ እንደ ቀን ብርሃን የጠራ ነበር ። «እኔ የእግዚአ

ብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ አለ» ኢያሱም ያለ አንዳች ማመን ታት በዚህ ታላቅ የጦር አዛዥ እግር ሥር በግንባሩ ተደፋ። ይህ ታላቅ የጦር አዛዥ ከአርባ ዓመታት በፊት ለሙሴ በተናገረው ቃል አሁንም ለኢያሱ ይናገራል። «አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን አውልቅ»አለው። ዘጸ. ፫ ፥ ፭ ።

ለምጻሙ ስለነፃ በእግሩ ወድቆ የሰገደለት ሰው ይህ የጦር አዛዥ ነበር። ጴጥ ሮስ በጀልባይቱ ውስጥ በግምባሩ ተደፍቶ ጌታ መሆኑን የመሰከረለት አዳኝ ይህ እንጂ ሌላ አይደለም። ዮሐንስ ስለ እርሱ በራእይ «የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ» ብሎ የሚናገርለት እርሱ ነው። በዚያን ጊዜ ኢያሱን ለመገናኘት የመጣው መድኃ ኒታችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነበር።

ለምን መጣ ? በኢያሱ ፋንታ አዛዥ ሊሆን ነውን ? የኢያሱን ሥልጣን ሊወ ርስ ነውን ? የመጣሁት ይላል ራሱ «የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ» የእግዚአብሔር ሠራዊት የተባለው በጌልገላ ሰፍሮ ያለ ሕዝብ አይደ ለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ዘወትር የሚኖሩና ለመታዘዝ ዝግጁ ሆነው በሰማያት ስፍራ ከሰይጣን ሥልጣን ጋር የሚዋጉ በሰው ዓይን የማይታዩ መን ፈሳውያን ሠራዊት ናቸው።

ስለዚህ ሠራዊት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በብዙ ስፍራ እናነባለን። ያዕቆብ ከስደት ሲመለስ ያንን ሠራዊት አየ። የኤልሳዕ ሎሌ በሶርያ ወታደሮች በተከበቡ ጊዜ በእነርሱ ፋንታ ሊወጉ የመጡትን የሰማይ ሠራዊት በዙሪያው አየ። ኢየሱስ ከጌቴሴማኒ ሲወጣ ሳለ ስለዚህ ሠራዊት ተናገረ፥ ከአፉ በምትወጣው አንዲት ፉጨት አሥራ ሁለት ጭፍሮች መላእክት ሰማይን ቀድደው ሊወርዱና ጠላቶቹን ከመቅጽበት ሊያወድሙ ይችሉ ነበር። ሞላው መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ዓለም አሁን እየገዙ ስለሚ ኖሩ የክፋትና የጨለማ መናፍስት፥ በኋላም ኢየሱስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ እነ ዚህን የክፋትና የጨለማ መላእክት ድል አድርገው ወደ ገሃነም ስለሚጥሉአቸው የብርሃን መላእክት ይናገር የለምን ?

ኢያሱ በዚህ ታላቅ የጦር አዛዥ እግር ወድቆ ሲሰግድለት፥ ራሱን ከታላቁ የጦር አዛዥ ስለ አስተሳሰረ በጠላት ላይ ለሚያደርጉትም ውጊያ ከታላቁ መሪ መሪነ ትን ተቀብሎአልና የኢያሪኮ ከተማ ያለ ውጊያ መውደቋ ምን የሚያስገርም ነገር አለበት ? የተሟላ ሠራዊት ከኢያሱ ፊት እየፈረጠጠ ሲሸሽ፥ እርሱም ሰባት ኃያላን ነገሥታትን በሰባት ዓመት አሸንፎ አገሪቱን ሲወስድ ምን የሚደነቅ ነገር አለበት ? ይህ በሰማያት መላእክት ሲዋጉ ለተደረገው ማሸነፍ መግለጫ የሆነ ምድራዊ ውጤት ነው። ኢያሱ ለእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ራሱን በመስጠት ከእርሱ ስለተሻረከ የኢያሪኮ ቅጥር ያለ አንዳች ተኩስ ወደቀች።

ጌልገላ የገለጸ ስፍራ ነበር። የመጋደላችንን ምንጭና ሁኔታ ምን እንደሆነ፥ የማሸነፋችንንም ምሥጢር እንድናውቅ ምነው መንፈስ ቅዱስ ይህን ቃል በልብህና በልቤ ጽፎ ቢገልጽልን ?

በዘመናችን ዓለም በሚገዙ ፣ በእግዚአብሔር በማያምኑ ኃያላን መንግሥታትና ገዥዎች በስተጀርባ በኰሚኒዝም ኃይል ለሞት በተወሰኑ ስምንት መቶ ሚሊዮን ሕዝብ በስተጀርባ ሆኖ የሚገፋፋ የሰይጣን ኃይል አለ ። እውነትን ለማጣመምና ለመቃወም ከሚደረገው ደንዳንነትና የልብ ጨከኝነት በስተጀርባ ወንዶችና ሴቶችም ወጣቶችም ስለ ክርስቶስ ወንጌል ግድ የለሽ እንዲሆኑ ከሚያደፋፍር ትምህርት ነገር ሁሉ በስተጀርባ የዚህ ዓለም አምላክ አለ ፣ እርሱ የማያምኑትን አእምሮና ማስተዋል ልቡናቸውንም አሳወረ ። ሚስት ፣ ባል ፣ ወይም ልጆቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይቀበሉ ከሚያደርገው ማናቸውም ሐሳብ በስተጀርባ ፣ ከተበላሸ አንዋኑዋርና ሕይወት ከተሰባበረው የወንጌል ምስክርነት በስተጀርባ ሰይጣን ቆሞአል ። እርሱም ፍርዱን የሚቀበልበት ቀን እንደተቃረበ ስለሚያውቅ በዚህ በመጨረሻው የጸጋ ዘመን ባለው ጥበብ ፣ አቅም ፣ የጦር ስልት ፣ ጉልበትና ኃይል ይጠቀማል ።

ለወንጌል መልእክተኞች እየተዘጋ በሚሄደው በር በስተጀርባ መልእክተኞቹም የጤና መታወክና ፈተናን ለመቋቋም ካለመቻላቸው በስተጀርባ የሚሲዮናውያን ጣቢያዎችም እየተከታተሉ እንዲዘጉ ከሚያደርገው በስተጀርባ ፣ ሚሲዮናውያንን ማለት የወንጌል መልእክተኞችን እንዳንደግፍ ከሚያደርገን የገንዘብ እጦት በስተጀርባ ሰይጣን ቆሞ ይስቃል ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ልጆች ልብና ኪስ እንደ ጉጠት አጥብቆ ይዘአል ።

ይህን በእግዚአብሔር ፊት እንናዘዝ ፣ ከእንግዲህ የቀረን ለሁላችንም ወይ መታደስ ወይም መጥፋት ነው ።

በዚህ ዓይነት ለሚመጣው ጥሪና የጊዜ ሁኔታ መልሳችን ምንድር ነው ? ምን ማድረግ እንሞክራለን ? ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የሚስቡ ስለሚመስሉ ልዩ ልዩ ከባድና አዳጋች የሆኑ ሙከራዎችን እንወጥናለን እንሠራብትማለን ። የሚያጓጉ ማስታወቂያና ሽልማቶች እናቀርባለን ። ሰዎችን ከወንጌል ድምፅ ሥር ለማድረግ ብዙ ገንዘብ እናጠፋለን ። ይህ ሁሉ ተደርጎ ተሠርቶበት ሲያበቃ ፣ ደቅቀን ፣ ተጎስመን ፣ ተነሳቅለን እግዚአብሔር አልረዳንም እያልን ተስፋ ቆርጠንና ተደናግረን ውጊያውን ፣ ጦርነቱንና መጋደሉን እናቋርጣለን ።

ምን ማድረግ ይቻላል ? ደግሞስ ምን ጎደለ ? ከሰማይ በታች ባለው አቅምና ዘዴ ሁሉ ሠርተንበታል ። ከተሞቻችንን በወንጌል ማስታወቂያዎች ጽሑፎች አጊጠናል ፣ ታላላቅ መንፈሳዊ ስብሰባዎችና ዘመቻዎች አድርገናል ። ነገር ግን አልፎ አልፎ ከሚገኙት ከጥቂቶች በቀር ውጤቱ ፍሬ ቢስና ባዶ ሆኖ ተገኘ ። በዚህ ዘመን ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ የሚመጡት በመቶ ሲቆጠሩ ሰይጣን የሚማርካቸው በሚሊዮን ይቆጠራሉ ።

ነገር ግን «የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው» ፪ኛ ቆሮ. ፲ ፣ ፬ ። ይህን ቃል እንድታስተውልና ልብህን እንዲይዝ መንፈስ ቅዱስ ልቡናህን ያብራ ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም

በነበረበት ጊዜ ሁሉ ከእነዚህ ጠላቶች ብዙ ጊዜ ተጋፍጦ ነበር። በበረሃ ተጋፋት፥ በጌቴሴማኒ በሙሉ ኃይል ተነሡበትና አባቴ ሆይ፥ ይህችን ጽዋ ሳልጠጣት ትለፍ እንዲል አደረጉት፥ ግን አምላኬ ሆይ፥ አንተ እንደምትፈቅድ እንጂ እኔ እንደምወደው አይሁን በማለት አሸነፋቸው። በመስቀል ላይ ሳለም ሰይጣን በለው መሣሪያና ጉልበት ተዋጋውና «የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ ከመስቀል ውረድ» አለው። በመሞቱ ግን ተቃወማቸውና አሸነፋቸው። እነርሱ እንዳይሞት ታግለው ነበር። ከሙታንም ተነሥቶ ከባለ ሥልጣኖቻቸው ከአለቅነት፥ ከዙፋናት፥ ከጌትነትና ከባለ ማዕረጎቻቸው በላይ ወጥቶ ሥልጣናቸውን ደመሰሰ። ወደ ሰማይም ሲያርግ እነርሱን አራገፈና ከሁላቸው በላይ ራስ ሆነ፤ «ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት (አስተውል፥ አስገዛለት ይላል እንጂ ያስገዛለታል አይልም) ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው፥ እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት» ኤፌ. ፩፥፳፪፥፳፫።

መንፈሳውያን ጠላቶቻችንን በሥጋዊ ዕቃ ጦር ለመውጋት ስለምንሞክር እግዚአብሔር ይቅር ይበለን። ሊደረግ አይቻልም። በማቀድ፥ በማስታወቂያ፥ በመንፈሳዊ ዘመቻ አንድ ውጤት እናስገኛለን ብለን ስንታገል፥ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ምንም ስለማናስገኝ እግዚአብሔር ይማረን። የመጋደላችን ዕቃ ጦር ሥጋዊ ነገሮች መሆን እንደማይገባቸው አላስተዋልንምን ?

የተቀደሰ ሕይወትና አንዋኑዋር እንድትኖር ለክርስቶስ መቶ በመቶ ተሰጥተሃልን ? የተገለጡልህን ኃጢአቶች ሁሉ ለመተውና ለማስወገድ ወስነሃልን ? የተሟላና ፍጹም የሆነ ሥልጣንና ኃይል ካለው ከኢየሱስ ጋር በሃይማኖት ለመሻረክ በሙሉ ልብህ ወስነሃልን ? ይህን አድርገህ እንደ ሆነ፥ የጌታችን ቤተ ክርስቲያን እንደ ገና ሰይፋዋን መዝዛ እያምዘገዘገች በብሉይ ኪዳን አነጋገር እንዲህ ትላለች «የእግዚአብብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ» «በዚችም ዓለት ላይ» አለ ጌታ ኢየሱስ «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም» ማቴ. ፲፮፥፲፰።

በመሥሪያ ቤት ከጽሕፈት መኪና በስተኋላ ተቀምጣ፥ ለጌታዋ ምንም ማድረግ እንደማትችል የምታስብ ተራ ሰው የሆነች ልጃገረድ፥ ከሰማይ ጌታችን ጋር ብትሻረክ፥ ማንም ሊቃወመው የማይችል ምስክርነት ልትሰጥ ትችላለች። ክርኩሳንና ሴሰኞች ተሳዳቢ ጓደኞች ጋር በፋብሪካም ሆነ በማናቸውም መሥሪያ ቤት በሳምንት አምስት ቀን እየሠራ በእነዚህ ጓደኞች መካከል ለጌታ የሚደረግ ነገር የለም ብሎ ተስፋ በመቁረጥ የሚኖር ሰው፥ ሃይማኖት ማለት ወደ ቀራንዮ መመልከት ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አቅንቶ ማየት መሆኑን ቢረዳ ለእግዚአብሔር ለማገልገል ሰማያዊ ጉልበት፥ ኃይልና ሥልጣን ማግኘት ይጀምራል።

ለራሳቸው መሃይማን ቢሆኑም በሕፃናት የሰንበት ትምህርት ቤት ለሚያስተምሩ ወንድና ሴት ልጆች ዘዴውንም ለማያውቁበት በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ካለው ከክርስቶስ ጋር የሚተሳሰሩበት ቀን ይመጣል፥ ያን ቀን እግዚአብሔር መሥራት፥ ኢያሪኮዎችም መውደቅ ይጀምራሉ።

ባልዋ ክርስቶስን አልቀበልም ብሎ ቤትዋ ንብረትዋና ትዳርዋ ለተከፋፈለ ተራ የቤት እመቤት ሃይማኖትዋ ሁሉን በሚችል ጌታ መሆን የምትገነዘብበት ጊዜ ይመጣል፣ ሁሉን በሚችል ጌታ የተደረገ ሃይማኖትም ኃያልና ብርቱ ይሆናል። በዚህን ጊዜ ሰውዬው በሞላ ሕይወቱ ያቃተውን እግዚአብሔር ሊያደርግ ይጀምርና ሰውዬው ይድናል።

እግዚአብሔር የሚፈልግብን፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ቤተ ክርስቲያን ልብ በማስገባት እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያኒቷ አባል ከእግዚአብሔር ዙፋን እንዲታሠር እንድናደርግ ነው። በሕያው ክርስቶስ ተማርከን ራሳችንንና የአለንን ሁሉ ለእርሱ ብናስረክብ እግዚአብሔር መሥራት ይጀምራል፣ የቤተ ክርስቲያን መቃደስ ይመጣልናል፤ ነፍሳትም ይበረከሉ ይድናሉም። ቤተ ክርስቲያንም እንደ ብርቱና ጽኑ ሠራዊት እንደገና መጓዝና መገመት ትጀምራለች።

ምዕራፍ ፲ ።

# ድልን ማክበር ።

## ኢያሱ ፮ ፡ ፩-፳ ።

«ኢያሪኮም ከእስራኤል ልጆች የተነሣ ፈጽማ ተዘግታ ነበር ፣ ወደ እርስዋ የሚገባ ከእርስዋም የሚወጣ ማንም አልነበረም ። እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው ፤ ተመልከት ፣ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን ጽኑዓን ኃያላንዋንም በእጅህ ሰጥቼአለሁ ። ሰልፈኞቻችሁ ሁሉ ከተማይቱን አንድ ጊዜ ይዙሩአት ፣ እንዲሁም ስድስት ቀን አድርጉ ። ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት በታቦቱ ፊት ይሸከሙ ፣ በሰባተኛውም ቀን ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዙሩ ፣ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ይንፉ ። ቀንደ መለከቱም ባለማቋረጥ ሲነፋ የመለከቱንም ድምፅ ስትሰሙ ፣ ሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይጩኹ ፤ የከተማይቱም ቅጥር ይወድቃል ፣ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ይገባበታል ። የነዌም ልጅ ኢያሱ ካህናቱን ጠርቶ ፣ የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸከሙ ፣ ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ወስደው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሂዱ አላቸው ። ሕዝቡንም ፡— ሂዱ ፣ ከተማይቱንም ዙሩ ፣ ሰልፈኞችም በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሂዱ አለ ።

ኢያሱም ለሕዝቡ በተናገረ ጊዜ ፣ ሰባቱ ካህናት ሰባቱን ቀንደ መለከት ይዘው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ሄዱ ፣ ቀንደ መለከቱንም ነፉ ፣ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ይከተላቸው ነበር ። ሰልፈኞቹም ቀንደ መለከቱን በሚነፉ በካህናቱ ፊት ይሄዱ ነበር ፣ የቀረውም ሕዝብ ከታቦቱ በኋላ ይሄድ ነበር ። ካህናቱም እየሄዱ ቀንደ መለከቱን ይነፉ ነበር ። ኢያሱም ሕዝቡን ፣ እኔ ጩኹ እስከምልበት ቀን ድረስ አትጩኹ ፣ ድምፃችሁንም አታንሡ ፣ ከአፋችሁም አንድ ቃል አይውጣ ፣ በዚያን ጊዜ ትጮሃላችሁ ብሎ አዘዛቸው ። እንዲሁ የእግዚአብሔርን ታቦት አንድ ጊዜ ከተማይቱን አዞረው ፣ እነርሱም ወደ ሰፈሩ ተመልሰው አደሩ ።

ኢያሱም ማለዳ ተነሣ ፣ ካህናቱም የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸከሙ ። ሰባቱም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሄዱ ነበር ። ቀንደ መለከቱንም ይነፉ ነበር ። ሰልፈኞቹም በፊታቸው ይሄዱ ነበር ። የቀሩትም ሕዝብ ከእግዚአብሔር ታቦት በኋላ ይመጡ ነበር ፣ ካህናቱም እየሄዱ ቀንደ መለከቱን ይነፉ ነበር ። በሁለተኛውም ቀን ከተማይቱን አንድ ጊዜ ዞረው ወደ ሰፈር ተመለሱ ፤ ስድስት ቀንም እንዲህ አደረጉ ።

በሰባተኛውም ቀን በነጋ ጊዜ ማልደው ተነሡ ፣ እንደዚህም ሥርዓት ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ ፣ በዚያ ቀን ብቻ ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ ። በሰባተኛው ጊዜ ካህናቱ ቀንደ መለከቱን ሲነፉ ኢያሱ ሕዝቡን አለ ፣ እግዚአብሔር ከተማይቱን ሰጥቶአችኋልና ጩኹ ። ከተማይቱም በእርስዋም ያለው ሁሉ ለእግዚአብሔር እርም

ይሆናሉ ፤ የላክናቸውን መልእክተኞች ስለሸሸገች ጋለሞታይቱ ረዓብ ከእርስዋም ጋር በቤትዋ ውስጥ ያሉ ሁሉ ብቻ በሕይወት ይኖራሉ ። እናንተ ግን እርም ከደረጋችሁት በኋላ እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ ፤ እርም ከሆነው አንዳች የወሰዳችሁ እንደሆነ የእስራኤልን ሰፈር የተረገመ ታደርጉታላችሁ ፤ ታስጨንቁትማላችሁ ። ነገር ግን ብርና ወርቅ ሁሉ የናስና የብረትም ዕቃ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን ፤ ወደ እግዚአብሔርም ግምጃ ቤት ይግባ ። ሕዝቡም ጮኸ ፤ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ነፉ ፤ ሕዝቡም የቀንደ መለከቱን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ታላቅ ጩኸት ጮኹ ፤ ቅጥሩም ወደቀ ፤ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ወደ ፊቱ ወደ ከተማይቱ ወጣ ፤ ከተማይቱንም ወሰዱ ።» ኢያሱ ፮ ፥ ፩ — ፳ ።

ከሰይጣን መንግሥት ባርነት ነፃ የመውጣትን አኳኋኖችና መሠረቶች ስናጠና ቆየን ። ከሕግ ፍርድና ከሰይጣን መንግሥት ነፃ መውጣት ሁልጊዜ በመስቀሉ ደምና በታረደው በግ በኩል ብቻ ነው ። እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ እንደወጡ እኛም ከሰይጣን መንግሥት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ልንገባ ወጣን ።

እንደምናውቀው ሁሉ በክርስቲያን ሕይወታችን ውስጥ ብዙ ምድረ በዳዎችን አቋርጠናል ፤ ረጅም ጎዳናዎችም ተጉዘናል ፤ በእነርሱም የእግዚአብሔርን በእኛ አድሮ ከእኛ ጋር መኖርንና የማሸነፍንም መጠን ፤ እንደዚሁም ብዙ የራሳችንን መሸነፍና ውድቀቶች ሁሉ አይተናል ። በመሞቱና በትንሣኤው ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆንንበትን እርሱም ሕይወታችንና ድላችን ሊሆን በውስጣችን እንደ አደረና ፍላጎታችንን አምሮታችንንም ሁሉ እንደሚያረክ ወደ ማስተዋል የደረስንበትን ዮርዳኖስን ጥቂቶች ተሻግረናል ። በምድረ ደኅንነት ቆመናል ። ነገር ግን ምድረ በዳውን አቋርጦ ፤ ፈተናውንም አልፎ ሙሉ በረከት ወዳለው ምድረ በረከት የገባ ክርስቲያን እስኪደነቅ ድረስ ከመቅጽበት ኢያሪኮ በፊቱ ይደቀናል ። እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች ስንት ክርስቲያኖች ወደ ኋላቸው የተመለሱና የተሸነፉ ይመስላችኋል ?

የሰይጣን ተንኮልና ሽንገላ የሌለበት ፤ ከኃጢአትና ከፈተና በሙሉ ነፃ የሚሆንበት የጸጋ አቋም የሚያገኝ ማንም አይምሰለው ። እንዲህ የሚያስብ ማንም ቢኖር ፤ የእግዚአብሔር ቃልና የሰው የተፈጥሮ ባሕርይ ይህን አስተያየት እንደሚቃወሙ ይረዳ ። በዚህ ዓይነት ሐሳብ ላይ ተስፋውን የመሠረተ ማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ የሚኖረው ለውድቀትና ለመንፈሳዊ መታወር ብቻ ነው ። ምክንያቱም ፤ ከክርስቶስ ጋር በመሞቱና በትንሣኤው ስፍራውን ቢይዝም ፤ ክርስቶስም ድሉ መሆኑን በየቀኑ ቢያምንም ቅሉ ኢያሪኮን ከፊቱ ተደቅኖ ያገኛል ።

በምድረ ግብፅ ባሪያ ያደረገው ፤ በበረሃም የሸነገለውና የታገለው ሰይጣን ፤ የእግዚአብሔር ልጅ በምድረ በረከት ሲደርስ በተጨማሪ ኃይልና በበለጠ ተንኮል ተከታትሎ ይመጣል ። ለራስህ በመስቀሉ በመሞትና ከሙታን በተነሣውም መድኃኒት ሕይወትህን አግኝተህ በክቡር ጌታ ስፍራህን ተረክበህ ፥ ዛሬም ርስትህን እየወረስክ ድልህ በሆነው በክርስቶስ ስትደሰት ሳለህ ፤ በመንገድህ ላይ ኢያሪኮ ተንጀርግጎ ስለምታገኝ ትደናገራለህን ?

ለጥቂቶች፥ ኢያሪኮ ከውስጣቸው የሚገነፍል ራስን አለመግዛትና መንፈስ ደካማነት ነው። በጠባያችን ውስጥ አንድ ደካማ ነጥብ መኖሩን እናውቃለን፤ ምናልባት በሕፃንነት ጊዜ ተምረነው፥ በልጅነት፥ በጎልማስነትና በወጣትነት ወራትም ተከትሎን ያሸነፈንና ሙሉ ሰውም ስንሆን ያልለቀቀን ነገር ይሆናል። እያንዳንዱ ሰው በተለይ አተኩሮ የሚመለከተውና የሚጠነቀቅበት የተለየ ነጥብ በሕይወቱ፥ በሰውነቱና በጠባዩ እንደአለ ያውቃል፤ ያችም በሕይወቱ ያለችው ሁልጊዜ የምትከነክነው የራሱ ኢያሪኮ ናት።

በሕይወትህ ያለው ኢያሪኮ ምናልባት ከባሕርይህ፥ ከጠባይህና ከራስህ ውጪ የሆነ ነገር ይሆናል። ለምሳሌ በቤተሰብህና በትዳርህ ውስጥ የገጠመህ አስቸጋሪ ሁኔታ ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን የምታውቀውን እንዳታደርግ የሚከለክልህ መሰናክል ይኖር ይሆን? ምናልባት፥ የወንጌል መልእክተኛ ሆነህ በሌላ አገር እንድታገለግለው፥ ወይም በሌላ ዓይነት ተግባር እንድትሠራለት እግዚአብሔር በየጊዜው ተናግሮህ ይሆናል፤ ነገር ግን በአንተና በእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል ኢያሪኮ አለ። ለመሆን የምትመኙትን ሙሉ ሰው እንዳትሆኑ እንደሚከለክሉአችሁ ራሳችሁ ስለምታውቁ ኢያሪኮዎቻችሁ ከሳምንት ወደ ሳምንት እዚያ ቆመው ይሙዋገትዋችኋል ያሸፉባችኋልም።

ይህ ከተማ እንዴት ይሸነፍ ይሆን? የእስራኤል ልጆች ታላቁን ቅጥራቸውን ሲዞሩ ማየት ለኢያሪኮ ነዋሪዎች እንዴት ያለ አደናጋሪ ትርዕይት ይሆን? የቃል ኪዳኑ ታቦት በመካከል ሆኖ የእግዚአብሔርም ሕዝብ ከኋላ ሲከተሉ፥ ከቅጥሩ ድረስ የሚሰማው ስልፉን የሚመሩ ካህናት የሚነፉት የቀንደ መለከት ድምፅ ብቻ ነበር። የሠራዊቱም ጸጥታ ከቅጥሩ በስተ ውስጥ በሚገኙ ሰዎች ማሾፍ ሳይታወክ እንዳል ቀረ አስባለሁ።

የኢያሪኮ ሰዎች ምንም በእስራኤላውያን ቢያፌጡባቸው እንኳ ፍርሃት ይዞአቸው እንደ ነበረ በምዕራፍ ስድስት የመክፈቻ ቁጥሮች ይነግሩናል። ቅጥሩን በዝምታ መዞር ፍች የሌለው ቂልነትና ስንፍና ቢመስላቸውም የእነዚህ ወራሪዎች ኃይል መለኮታዊ ምንጭ በፍርሃትና በመርበድበድ ሞላቸው። በማሾፋቸውና በማሽሟጠጣቸው ውስጥ ቅጥሩን በዝምታ የሚዞሩትን ወራሪዎች መፍራት ተቀላቅሎበታል።

በየቀኑ ቅጥሩን ዞረው ሲመሽ ወደ ሰፈራቸው ሲመለሱና፥ በሰባተኛውም ቀን ሰባተኛ ጊዜ እስኪዞሩ ድረስ ለእስራኤላውያን ኢያሪኮ የማትሸነፍ ጽኑ ሆና ታየቻቸው። ከዚያ በኋላ በኢያሪኮ ቅጥር ዙሪያ አሥራ ሦስተኛውን ዙር ሊፈጽሙ አቅራቢያ በኢያሱ ትእዛዝ ቀንደ መለከቶቹ ተነፉ፥ ሕዝቡም በታላቅ ቃል ጮኹ። የኢያሪኮም ቅጥሮች ወደቁ፥ እያንዳንዱም ሰው በቀጥታ ወደ ፊቱ ተራመደ፥ በመካከል ከተማም ተሰበሰቡ። በዛሬው ዘመን አነጋገር ቢሆን፥ ኢያሪኮ አንዲት ጥይት ሳትተኰስ ተማረከች ይባላል።

በክርስቲያን ኑሮ ውስጥ ይህ ተመሳሳይነት አለውን ? እግዚአብሔር ሕዝቡን ሁሉ ከባርነት ቢያስወጣም በግል ኑሮህ ያለውን ኢያሪኮ ስለምታሸንፍበት መንገድ ይህ ምን ያስተምርሃል ?

ይህ ከተማ እንዴት ተማረከ ? በጉልበትና በሰው ጥበብ አልተሸነፈም ። «በሃይማኖት የኢያሪኮ ቅጥሮች ወደቁ ሰባት ቀን በከበቡዋቸው ጊዜ» ዕብ· ፲፩ ፥ ፴ ።

እነዚህ ቅጥሮች እንዲወድቁ ስለአደረገው ሃይማኖት ሁለት ወይም ሦስት ነገሮችን ከእኔ ጋር በጥንቃቄ እይ ። የእስራኤላውያን ሃይማኖት እንዴት እንደተፈተነ አስተውል ። ለምን በዝምታ ቅጥሩን እንደሚዞሩ መግለጫ ባይሰጣቸውም አሥራ ሦስት ጊዜ ዞሩ ። ለኢያሱ ሁሉም ተነግሮታል ፥ እርሱም እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራ ያውቅ ነበር ፥ ሕዝቡ ግን አያውቁም ። ኢያሱ ሁሉንም ገለጸላቸው ። በሰባተኛው ቀን በአሥራ ሦስተኛው ዙር ጊዜ በዚያን ቀን ብቻ ነበር ። ለሕዝቡ አስቸጋሪና ከበድ የነበረው ነገር በዝምታ ቅጥሩን መዞር እንደነበረ አምናለሁ ። በመጨረሻው ግን ኢያሱ እንዲጮኹ አዘዛቸው ። በድል አድራጊነት ጩኸታቸውም ቅጥሮቹ ወደቁ ።

የሰልፉ መካከለኛ ትርዕይት የቃል ኪዳን ታቦት እንደ ነበረ አስተውል ። በዚህ ምዕራፍ ታቦቱ አሥራ አንድ ጊዜ ተጠቅሶአል ። ይህ የእስራኤላውያን ሃይማኖት ምልክት ነው ። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለጊዜው ባያውቁም በቃል ኪዳኑ ታቦት ምልክትነት እግዚአብሔር ራሱ በመካከላቸው መሆኑን ስለአመኑ በዝምታና በጸጥታ ቅጥሮቹን መዞር ቻሉ ። ባለፈው ሕይወታቸው በገጠማቸው ሁሉ የታላቁ አምላክ ከእነርሱ ጋር መሆን ምልክት ሆኖ አሁንም ዮርዳኖስን አሻገራቸው ። ምዕራፉን ብታነብ አሥራ አንደኛው ቁጥር «የእግዚአብሔር ታቦት ከተማውን አንድ ጊዜ ዞረ» ብሎ ይነግረናል ። ከአዛዦቻቸው አንዳች ቃል ከመነገሩ በፊትም እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ሆኖ ከተማውን አሥራ ሦስት ጊዜ ዞረ ። ኢያሱም እንዲህ አለ ፥ «እግዚአብሔር ከተማይቱን ሰጥቶአችኋልና ጩኹ» ከዚያ ጩኸትና ለቀንደ መለከቶቹ መነፋት መልስ ቅጥሩ ወደቀ ፥ ሕዝቡም በድል አድራጊነት ወደ ፊት ተጓዙ ።

ያንን ስፍራ በዝምታ አሥራ ሦስት ጊዜ የዞሩት ለምንድር ነው ? ጠላቶቻቸውን አሥራ ሦስት ጊዜ አትኩረው በማየት ፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ካልሆነ በቀር በቅጥሩ ውስጥ ከአሉት ሊወዳደሩና ኢያሪኮንም ለመማረክ የማይችሉ መሆናቸውን እያንዳንዳቸው እስኪረዱና እስኪያምኑ ድረስ ያንን ረጅም ጊዜ የወሰደ ይመስለኛል ። በውጊያው እግዚአብሔር ተካፋይ ካልሆነ ለማሸነፍ ላላቸው ተስፋና ትምክህት ሁሉ ፈጽመው እንዲሞቱ እግዚአብሔር በዚያ ጽኑ ቅጥር ዙሪያ አሥራ ሦስት ጊዜ አዞራቸው ።

የአንተ ሕይወትና አንዋኑዋር ከዚህ ተመሳሳይነት የለውምን ? እግዚአብሔር ወደ ክርስቲያንነት ኑሮ እንደ አመጣህና በሰጠህም በረከት ራሱን እንደ ገለጠልህ ታውቃለህ ፥ ነገር ግን የሚያሰናክልህ ኢያሪኮ በፊትህ ተደቅኖአል ። ይኸውም ከውስጥህ ወይም ከውጪ የሚመጣ ኢያሪኮ ነው ።

በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እንደ ብረት ግድግዳ ጸንቶ የቆመው ታላቁ ችግር፣ ሁሉ ነገር ከአቅሙ በላይ መሆኑን፣ የጠላትም ኃይል ለእርሱ ብርቱ መሆኑንና የራሱ ኢያሪኮ እንዲወድቅ ከተፈለገ እግዚአብሔር መሥራት እንዳለበት ተረድቶ ማመን እንደሚገባው አለማስተዋል ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ማናቸውንም ሰዎች ለመንፈሳዊ ኃይል ስጦታና መሪነት፣ ለድልና ለበረከት የታመኑ እንዲሆኑ ከማድረጉ በፊት ኢያሪኮን ደህና አድርገው ጎብኝተው፣ በራሳቸው ኃይልና ጥበብ ማሸነፍ የማይቻል መሆኑን ወደሚያምኑበት ስፍራ እንደሚወስዳቸው አምናለሁ። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው አቅመ ቢስነታችንን ከመገንዘብ የበለጠ ነገር የለም። እኛ ግን ከአቅመ ቢስነታችን ብርቱ ሰው ለመፍጠር ለብዙ ዘመን ተፍጨርጭረናል። ራሳችን ማናቸውንም ነገር በጉልበታችንና ጥበባችን ብቻ ማሸነፍ እንደምንችል ማሰባችንን እስክንተው ድረስ ከሙታን በተነሣው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚሰጠን የኃይል ምንጭና የኃያሉ እግዚአብሔር ኃይል ሊረዳን አይችልም። ትምክህትና በራስ መታመን ካለበት እግዚአብሔር ፈቀቅ፣ ገለል ይላል።

ሌላው ታላቁ ፈተና ዝምታ ነው። ችግራችንን ለሌሎች ለመንገር፣ ክርስቲያኖች በጸሎት እንዲረዱን ጭንቀታችንንም ለወዳጆች ማወያየት ስንወድ መቼስ አይጣል ነው። ነገር ግን የምንፈልገው ሁሉ ከእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እንጂ በመፍጨርጨሬና በጉልበቴ አለመሆኑን እውነቱ ለልቤ ሲነጋልኝ፣ የማሸንፈውም ድልን ሊሰጠኝ በሞተውና በተነሣው በክርስቶስ ብቻ መሆኑን ተረድቼ በግምባሬ ተደፍቼ በፊቱ ልቤን የማፈስበት ጊዜ ከሁሉ ይልቅ የተባረከ መሆኑን ስረዳው ነው።

ኢያሪኮን ክርስቶስ ለትምህርት እንደሰጠህ የምታምንበት ቀን እስኪመጣልህ ድረስ በፊትህ ቆሞ ያፈጥብሃል። እርሱንም የምታሸንፍበት ማሸነፍ ተሰጥቶሃልና በሃይማኖት ተቀበል። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህን ድል የሚያስረክብህ ራስህ ተቀብለህም ልታሸንፍ የማትችል መሆንህን በፊቱ የምትረዳበትና የምትናዘዝበት የክርስቲያንነት የአንዋኑዋር ደረጃ ላይ ስትደርስ ብቻ ነው።

ነገር ግን ስለ እነዚህ አነስተኞች ውጊያዎችና ማሸነፍ ስናስብ፣ ከመጽሐፍ ይኸኛው ክፍል ተገቢ ስፍራውን እንዲይዝ ማድረግ እፈልጋለሁ። ከግላዊና ውሱን ስፍራ ዘልዬ ዛሬ በጠቅላላው የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚጋፈጡአቸውን አእላፍ ኢያሪኮዎች ላሳይህ እፈልጋለሁ። የአመፅ፣ የኃጢአትና የመተላለፍ ኢያሪኮ አለ፣ የግድ የለሽነትና የንዝህላልነት ኢያሪኮ አለ፣ የምድራዊነትና ዓለማዊነት ኢያሪኮ አለ፣ የአሕዛብነትና አረመኔነት ኢያሪኮ አለ፣ ትልቁና ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ደግሞ ክርስቲያኖች በአንዋኑዋራቸው ያልታመኑ፣ ያልተቀደሱ ኑሮዎች፣ ከኃጢአትም ጋር በጣም ስለ ተዋሐዱ ወይ. ገሃነም መኳዛቸው የማይሰማቸው ክርስቲያኖች ኢያሪኮዎች አሉ። ዛሬ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ውስጥና አካባቢ የማይበገሩና የማይሸነፉ መስለው የሚታዩ አእላፍ ኢያሪኮዎች አሉ።

በሕይወታችን እነዚህን ኢያሪኮዎች ብዙ ጊዜ ሳንዞራቸው አልቀረንም ። ተዋ ግተናቸዋል ፣ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ሞክረናል ፣ በስብከቶቻችን ፣ በማስታወቂያዎቻችን በራዲዮ አዋጃችን ፣ በጉልበታችንና በአነጋገር ችሎታችን ልናወድማቸው በብርቱ ሞክረናል ፣ ኢያሪኮዎቹ ግን እዚያው ቆመዋል ። በመጨረሻም ተስፋ በመቁረጥ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚያፈጡ ኢያሪኮዎች መወገድ እንደሚገባቸውና የሚ ጠቁትም በእግዚአብሔር ኃይልና መንፈስ ቅዱስም በመንፈሳዊ መታደስ የነበኘን እንደሆነ ብቻ መሆኑን ወደ መገንዘብ እንመለሳለን ። በጉባኤዎቻችን ተቀምጠን እነዚህን ቅጥሮች በመቀየስና የሚወድቁበትን አዳዲስ ዘዴዎች በማቅረብ ስንት ጊዜ አባክነናል ? እግዚአብሔር አዲስ ሰውን እንጂ አዲስ ዘዴን የማይፈልግ መሆኑን እንረሳለን ።

የልቤ ሸክም ይህ ነው ፣ በመላው ዓለም ፣ በአከባቢያችን ኢያሪኮዎች ቆመው በትግላችን በጉልበታችንና በመጣጣራችን ያፌዛሉ ። ንጉሣችን በቶሎ እንዲመጣ ወንጌልን ለዓለም ለማዳረስና ሥራውን ለመፈጸም በምናደርጋቸው የማይከናወኑ ሙከራዎች እየሳቁ ይንከተከታሉ ። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በአስጊ ሁኔታ ላይ ነች ፣ በፍጥነት እየደከመች መሄድ ጀምራለች ። አልፎ አልፎ አንዳንዶች በወንጌል ስለ ተጠቃለሉ አልጨነቅም ። እስቲ የራስህን እንዋኑዋር መርምር ፣ በአካባቢህ ያሉትን ጓደኞችህን አስተውለህ እይ ። ወደ ሰማይም አሻቅበህ «ጌታ ሆይ ፣ እኛ በፍ ጹም ደካሞች ነን» በል ።

በዓለም ላይ ከዳኑት ሰዎች ይልቅ ያልዳኑት እንደሚበዙ ታውቃለህን ? ወንጌ ልን በጭራሽ ያልሰሙ ሺህ አምስት መቶ ሚሊዮን ሰዎች እንዳሉ ታውቃለህን ? ከብረቱ መጋረጃ በስተኋላ ዛሬ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ ስላላቸው እምነት በብዛት እንደሚታረዱ ታውቃለህን ? በዓመት ሰላሳ ሚሊዮን ሰዎች እንደሚሞቱና ፣ በሰዓት ሦስት ሺህ አራት መቶ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት እንደሚለዩ ታውቃለህን ? ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር በታላቅ ኃይሉ በመንፈሳዊ መታደስ ከልጎበኘን ዛሬ ቤተ ክርስቲ ያን ተስፋ የላትም በማለት አናፈግፍግ ።

እነዚህን ኢያሪኮዎች በምን መንገድ እናጥቃቸው ? መናገር ቢቻላቸውም እንኳ እስራኤላውያን በዝምታ ኢያሪኮን አሥራ ሦስት ጊዜ ዞሩ ። ለምን ? የኢያሪኮ ነዋሪ ዎች ስለፈሩአቸው ነው ። የኢያሪኮ ትምህርት በልባችን ሲደውል ይኑር ። እስራኤ ላውያን እግዚአብሔር በመካከላቸው መኖሩንና ከቅጥሩም ውስጥ ያሉትን የፍርሃት ጣር እንደያዛቸው ስለ አወቁ በዝምታ ቅጥሮቹን ሊዞሩና እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሊያደርጉ ቻሉ ።

በመንፈሳዊ አእምሮ ለሚመረምሩ ወንዶችና ሴቶች ፣ በእነዚህ ዓረፍተ ነገሮች የሃያኛው መቶኛ ክፍለ ዘመንን ክርስቲያንነት አሳዛኝና አስቃቂ ሁኔታ ገለጽኩ ። በቤተ ክርስቲያናችን መለኮታዊ ኃይልና ሥራ ለመኖሩ መግለጫና ማስረጃ ስለሌለን ዝም ልንል አንችልም ፣ እንጮኻለን ፣ እንቀባጥራለንም ። አብልጦ ጩቀዋሂ የበለጠ ሰሚ ያገኛል ስለተባለ መልክታችንን ለማወጅ የጥርስ ሳሙናና ማስቲካ ከረሜላ

ለማስታወቅ ከሚሰለፉ ነጋዴዎች ጎን እንቆማለን። እግዚአብሔር በአውሎ ነፋስ፣ በምድር መናወጥና በእሳት አልነበረም፣ ነገር ግን ለዘብ ባለች ታናሽ ድምፅ ውስጥ ነበረ። በእውነቱ ቤተ ክርስቲያን በስህተት እግር ቆማለች፣ እኛም መንፈሳውያን ጠላቶቻችንን በሥጋዊ መሣሪያ ለመውጋት መሞከር ከሥር መሠረቱ የተሳሳተ ዘዴ ነው። በሆሊውድ ጥበብ የሰማይን ጉዳይ መፈጸም አይቻልም። መነሻ የሌለው ውድቀት እንወድቃለን።

የጉባኤ ወይም የኮሚቴ አባል ሆይ፣ ለወገንህ የቀረበውን እቅድ እንደገና መርምረህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነ ልትፍቀው ተዘጋጅተሃልን? እግዚአብሔር አረማመድህንና ምስክርነትህን እንዲመራ፣ ልትፈቅድለት፣ ከሌሎችም ጋር በንጽህናና በቅድስና ጸንተህ ለመቆም ተዘጋጅተሃልን? እግዚአብሔር እንዲለውጥህ ተዘጋጅተሃልን? ወይስ የቀድሞ መንገዶችንና አንዋኑዋርህን ከመውደድ የተነሣ ልትተዋቸው አትፈቅድም? ለአንተ ኢያሪኮዎች መልሱ የሚገኘው በጉልበትህ ተንበርክከህ ነው እንጂ፣ የትም አይገኝም። ይህ ታካችነት ወይም ስንፍና አይደለም፣ ነገር ግን በድካምህና በአለመቻልህ ከኃያሉ እግዚአብሔር ኃይል ጋር መቆራኘት ነው።

ሰዎች እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ድምፁን እየሰሙ፣ በጸሎት ቢታገሉ ጠላት መንቀጥቀጥ ይጀምራል። ያን ጊዜ ሽማግሌው መጽሐፍ ስለ ኃጢአት መዝለፍ ብሎ የሚጠራው በያለበት ይታያል። ዛሬ የጎደለው ይህ ነው። በዘመናችን ሃይማኖታችን አንድ ዓይነት ፈንጠዝያ፣ አሻንጉሊት ወይም መደሰቻ ነው ብለን እንገምታለን።

እውነተኛውን ስለ ኃጢአት መዘለፍን ምን ያህል እናውቃለን? ስለ ኃጢአት መዘለፍ በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ጠልቆ በመስመጥ ሰውዬው በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ምን እንደሚመስልና ምን እንደሆነ ሁኔታውን ቢገልጽለት፣ በሕይወቱ ውስጥ በእርሱና በአምላኩ መከከል ያለው ግንኙነት ከማናቸውም ነገር በላይ ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን እንደሚገነዘብ አስተውል። በዚያን ጊዜ ሁሉም ነገር ዋጋ ቢስ ሆኖ ይታየዋል፣ እኛም በእግዚአብሔር ፊት የተሰበርንና የደቀቅን ሆነን የእርሱን ማንጻት፣ ቤዛነትና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ብቻ እንጠባበቃለን፣ አለበለዚያ አገልግሎታችን ሁሉ ይቋረጣል።

በወንድማማችና በጓደኞች መከከል መራራቅን የሚዘሩስ? በዓለማዊነት የሚኖሩስ? ገድ የለሾችና እንደ ልቡዎችስ? ወደ ጸሎት መምጣት የማይፈልጉስ? በጸሎት ታካች መሆን ለእግዚአብሔር ልጆች አደገኛና አሰቃቂ ኃጢአት መሆኑን ለማሰብ ጥቂት ጊዜ ሰጥተህ ታውቃለህን? ከእግዚአብሔር የሚላክ የኃጢአት ዘለፋና ወቀሳ ካልሆነ በቀር የዚህን ዓለም ልብ ሊነካ የሚችል ነገር የለም። እግዚአብሔርም ዓለምን የሚዘልፈውና የሚወቅሰው፣ ቤተ ክርስቲያንን አስቀድሞ ቢዘልፋትና ቢወቅሳት፣ እርሷም ብትቀበለውና ብትነቃ ነው። ስለ ኃጢአታችን ተዘልፈናልን?

አሁን ወደ ድል ልመለስ። በዓለም ያሉ ኢያሪኮዎች ሁሉ እያንዳንዳቸው አንድ በአንድ ሊወድቁ ነው። ይህንንም በሙሉ ልቤ አምናለሁ።

የኢየሪኮ ከተማ እንዴት ወደቀች ? ጩኸትና የመለከት ድምፅ ነበረ ። እነዚህ ግሩም ቃላት የሚሉትን አዳምጥ ። «ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና» ፩ኛ ተሰ ፬ ፡ ፲፮ ። በጌታችንና መድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መገለጥ ይህች ዓለም ከኃጢአትዋ ፡ ከርኩሰትዋና ከተንኮልዋ ሁሉ ጋር ከፊቱ ትፈረከከሳለች ፡ እንዳልነበረችም ትሆናለች ። «ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ፡ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ ። እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል» ራእይ ፳፩ ፡ ፪ ፬ ። ይህ ግርማዊ ቀን ከምናስበው ይልቅ ወደ እኛ ቀርቦ ይሆን ? ሕዝቡ ለንጉሡ መምጫ እልል እንዲሉና እንዲጮኹ ልባቸው እንዲሰበር ፣ ንስሐ እንዲገቡና ራሳቸውን እንዲያዋርዱ እግዚአብሔር በደጅ ቆሞ ይለምን ይሆን ?

ሲነጋጋ ቀኑ ጧት ይሆን ?
ጎህ ሲቀድ ጨለማና ጥላን
የሱስ የሚመጣው በግርማና ሥልጣን
ከዓለም ሊያወጣ ለእርሱ የሆኑትን ።
በቀትር ነው ይሆን ወይስ እኩል ሌት ?
የሌሊት ጨለማ ምናልባት በድንገት
በግርማው ፀዳል የሚያንጸባርቅበት ?
የሱስ የእርሱን ሊወስድ ወደ ሰማያት ።
ኦ የሱስ መቼ ነው መቼ ነው በዚያ
በደስታ መዝሙር በአንተ አምሳያ
አሜን እንደሰት ሃሌ ሉያ ።
ክርስቶስ ቶሎ ና ፣ ና ሃሌ ሉያ ።

ምዕራፍ ፱ ።

# መሰናክሎች ፣ ምክንያታቸውና ፈውሳቸው ።

ኢያሱ ፯ ፣ ፲፫ ።

«የእስራኤል ልጆች ግን እርም በሆነው ነገር በደሉ ፣ ከይሁዳ ነገድ የሆነ አካን ፣ እርሱም የከርሚ ልጅ ፣ የዘንበሬ ልጅ የዛራ ልጅ እርም ከሆነው ነገር ወሰደ ፣ የእግዚአብሔርም ቁጣ በእስራኤል ልጆች ላይ ነደደ ።

ኢያሱም ከቤቴል በምሥራቅ በኩል በቤት አዌን አጠገብ ወዳለችው ወደ ጋይ ሰዎችን ከኢያሪኮ ልኮ ፦ ውጡ ምድሪቱንም ሰልሉ ብሎ ተናገራቸው ፣ ሰዎቹም ወጡ ፣ ጋይንም ሰለሉ ። ወደ ኢያሪኮም ተመልሰው ሁለት ወይም ሦስት ሺህ ያህል ሰው ወጥተው ጋይን ይምቱ እንጂ ሕዝቡ ሁሉ አይውጣ ፣ ጥቂቶች ናቸውና ሕዝቡ ሁሉ ወደዚያ ለመሄድ አይድከም አሉት ። ሦስት ሺህ ያህል ሰዎችም ወደዚያ መጡ ፣ ከጋይም ሰዎች ፊት ሸሹ ። የጋይም ሰዎች ከእነርሱ ሠላሳ ስድስት ያህል ሰዎችን መቱ ፣ ከበሩ እስከ ሸባሪም ድረስ አባረሩአቸው በቁልቁለቱም መቱአቸው ፣ የሕዝቡም ልብ ቀለጠ ፣ እንደ ውኃም ሆነ ።

ኢያሱም ልብሱን ቀደደ ፣ እርሱና የእስራኤልም ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግምባራቸው ተደፉ ፣ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ ። ኢያሱም አለ ፣ ዋይ ! ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፣ በአሞራውያን እጅ አሳልፈህ ትሰጠን ታጠፋንም ዘንድ ይህን ሕዝብ ዮርዳኖስን ለምን አሻገርኸው ? በዮርዳኖስ ማዶ መቀመጥን በወደድን ነበር እኮ ! ጌታ ሆይ ፣ እስራኤል በጠላቶቻቸው ፊት ከሸሹ ምን እላለሁ ? ከነዓናውያንም በምድሪቱም የሚኖሩ ሁሉ ሰምተው ይከቡናል ፣ ስማችንንም ከምድር ያጠፉሉ ፣ ለታላቁ ስምህም የምታደርገው ምንድር ነው ?

እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው ፦ ለምን በግምባርህ ተደፍተሃል ? ቁም ፤ እስራኤል በድሎአል ፤ ያዘዝኋቸውንም ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋል ፤ እርም የሆነውንም ነገር ወሰዱ ፣ ሰረቁም ፣ ዋሹም ፤ በዕቃቸውም ውስጥ ሸሸጉት ። ስለዚህም የእስራኤል ልጆች በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም ፤ የተረገሙ ስለሆኑ በጠላቶቻቸው ፊት ይሸሻሉ ፤ እርም የሆነውንም ነገር ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም ። ተነሣና ሕዝቡን ቀድስ ፣ እንዲህም በላቸው ፣ እስራኤል ሆይ ፣ እርም የሆነ ነገር በመካከልህ አለ ፣ እርምም የሆነውን ነገር ከመካከላችሁ እስከታጠፉ ድረስ በጠላቶቻችሁ ፊት መቆም አትችሉም ብሎ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ተናግሮአልና እስከ ነገ ተቀደሱ ። ነገም በየነገዳችሁ ትቀርባላችሁ ፣ እግዚአብሔርም የሚለየው ነገድ በየወገኖቹ ይቀርባል ። እግዚአብሔርም የሚለየው ወገን በየቤተ ሰቦቹ ይቀርባል ፣ እግዚአብሔርም የሚለየው ቤተሰብ በየሰው ይቀርባል ። እርም የሆነውም ነገር የተገኘበት ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አፍርሶአልና ፣ በእስራኤልም ዘንድ በደል አድርጎአልና ፣ እርሱና ያለው ሁሉ በእሳት ይቃጠላሉ ።

ኢያሱም ማልዶ ተነሣ፤ እስራኤልንም በየነገዶቻቸው አቀረበ፤ የይሁዳም ነገድ ተለየ፤ የይሁዳንም ወገን አቀረበ የዛራንም ወገን ለየ፤ የዛራንም ወገን ሰዎች አቀረበ፤ ዘንበሪም ተለየ፤ የቤቱንም ሰዎች አቀረበ፤ ከይሁዳም ነገድ የሆነ የከርሚ ልጅ የዘንበሪ ልጅ የዛራ ልጅ አካን ተለየ። ኢያሱም አካንን፦ ልጄ ሆይ፥ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፥ ለእርሱም ተናዘዝ፤ ያደረግኸውንም ንገረኝ፤ አትሸሽገኝ አለው። አካንም መልሶ ኢያሱን በእውነት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በድያለሁ እንዲህና እንዲህም አድርጌአለሁ። በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰነዖር ካባ፥ ሁለት መቶም ሰቅል ብር፥ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኘኋቸው፤ ወሰድኋቸውም፤ እነሆም፥ በድንኳኔ ውስጥ በመሬት ተሸሽገዋል፥ ብሩም ከሁሉ በታች ነው አለው።

ኢያሱም መልእክተኞች ሰደደ ወደ ድንኳኑም ሮጡ፤ እነሆም፥ በድንኳኑ ውስጥ ተሸሽጎ ነበር፥ ብሩም በበታቹ ነበረ። ከድንኳኑም ውስጥ ወሰደው ወደ ኢያሱና ወደ እስራኤል ልጆች ሁሉ አመጡት፤ በእግዚአብሔርም ፊት አኖሩት። ኢያሱና እስራኤል ሁሉ የዛራን ልጅ አካንን፥ ብሩንም፥ ካባውንም ወርቁንም፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹንም፥ በሬዎቹንም፥ አህዮቹንም፥ በጎቹንም፥ ድንኳኑንም፥ ያለውንም ሁሉ ወስደው ወደ አኮር ሸለቆ አመጡአቸው። ኢያሱም ለምን አስጨነቅኸን? እግዚአብሔር ዛሬ ያስጨንቅሃል አለው፤ እስራኤልም ሁሉ በድንጋይ ወገሩት፤ በእሳትም አቃጠሉአቸው፥ በድንጋይ ወገሩአቸው። በላዩም እስከ ዛሬ ድረስ ያለ ታላቅ የድንጋይ ክምር ከመሩ፤ እግዚአብሔርም ከቁጣው ትኩሳት ተመለሰ። ስለዚህም የዚያ ስፍራ ስም እስከ ዛሬ ድረስ የአኮር ሸለቆ ተብሎ ተጠራ።» ኢያሱ ፯፥ ፩ — ፳፮።

በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ ሰባት በመጀመሪያው ቁጥር «ግን» የተባለች አፍራሽ ቃል ትገኛለች።

የእግዚአብሔር ሕዝብ እስከ አሁን ድረስ ዮርዳኖስን በመሻገር፥ አገሪቱ በመግባት፥ በጌልገላና በኢያሪኮም ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም አሸናፊዎች ነበሩ። እስከ አሁን ድረስ ታሪኩ የቀና ነው። ዳሩ ግን በዚህ ስፍራ፥ የእስራኤል ልጆች ወደ ኋላቸው ሲያፈገፍጉ እናገኛቸዋለን። ኢያሱም በመራራ ኀዘን ተሞልቶ በእግዚአብሔር ፊት በግምባሩ ተደፍቶ እናየዋለን።

ኢያሱ፥ ድል አድራጊነቱ የማይቋረጥ መስሎት ነበር፤ ከእንግዲህ ወዲህ መሸነፍ እንደሌለና የእስራኤልም ሕዝብ እንደማይወድቅ አምኖ ነበር። አሁንም እግዚአብሔር ራሱ የተዋቸውም ወይም ከከነዓናውያን ኃያላን ነገሥታት ጋር ሊዋጋላቸው ያልቻለ ይመስላል። እስራኤልም በአስጊና አስቸኳይ ሁኔታ ላይ ያለች ትመስላለች። የከነዓንን ሠራዊት ለመውጋት ኃይላቸው፥ ጉልበታቸው፥ ቁጥራቸውና ጥበባቸው የማይበቃ መሆኑ ግልጽ ነው። በአገሪቱ የባሕር ዳርቻ አምባ ሠርተዋል፤ አሁን ግን ወደ ኋላቸው ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ጥልቀት የሚወረወሩበት ጊዜ የቀረበ ይመስላል።

ብሔር የሰማው ወቀሳ ነበረ። አሁን የጸሎት ጊዜ አይደለም ፤ የሥራ የኃጢአት ማስወገጃ ጊዜ ነው። ኢያሱ ድል በደረገ ጊዜ ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ቢያደርግ ኖሮ ፣ በሕዝቡ ልብ ያለውን በደል ከላስወገደ ወደ ጥፋት የሚጓዝ መሆኑ ይገለጽለት ነበር።

እግዚአብሔር ድልን ከጎናጸፈህ በኋላ የሚመጣብህ ታላቁ ፈተና በጸሎት መታ ከት ነው። ጎበዝና ብርቱ ስለሆንክ ከእንግዲህ ወዲህ ጸሎት የማያስፈልግህ ሲመስ ልህ ኃጢአት እንዳይሰማህ ልብህንና ስሜትህን አደነዘዝህ ማለት ነው። ከጌታ ኢየ ሱስ ጋር አንድነቱና ግንኙነቱ ከልቀጠለ እንደሚሸነፍ ለእግዚአብሔር ሰው ሊገልጽ ለት የሚችለው በድል ጊዜ የሚደረግ ጸሎት ነው። የማሸነፍ ጊዜ የመዋረድና የት ህትና ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ከኃጢአት ስለ አነጻው ልቡ በደስታ የተመሰጠ ሰው ያች ጊዜ ለእርሱ የመዋረድና የትህትና እንጂ የኩራት ፣ የትምክህትና የትዕቢት ጊዜ አይደለችም።

የእስራኤል ልጆች በጋይ እንዲሸነፉ ያደረገው ሦስተኛው ምክንያት አለመታ ዘዝ ነበረ። በቁጥር ፲፩ የሚያሳዝን ንግግር እናገኛለን። እግዚአብሔር ለኢያሱ ሲናገር እንዲህ ይላል «እስራኤል በድሎአል፤ . . . እርም የሆነውን ነገር ወሰዱ ፣ ሰረቁ ፣ ዋሹም በዕቃቸውም ውስጥ ሸሸጉት» በእንግሊዝኛ ቋንቋ የዱሮው ትርጉም ፣ እርም ይላል አዲሱ ትርጉም የተቀደሰ ይላል ፣ የተቀደሰ ማለትም ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲለይ ማለት ነው።

አሁን ፣ ለሁል ጊዜ የሚሆን ትምህርት እዚህ እንዳለ አስተውል። በእስራኤል መካከል ምን ተደረገ ? አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ከተለየ ማለት ከተቀደሰ የዘረፋ ዕቃዎች ሰርቆ ለራሱ ወሰደ። ከሰፈሩ አንድ ሰው ብቻ ለእግዚአብሔር አልታመ ነም ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ ግን «አካን በድሎአል» የሚል አልነበረም ፤ ነገር ግን «እስራኤል በድሎአል» የሚል ነበረ። በአንድ ሰው በደል መላው ሠራዊት ድል ሆነ። የእስራኤል ልጆች አንድ ሕዝብ እንደ ነበሩ አስተውል። ደካማውና ኃይ ለኛው ከእነርሱ ሳይለይ በመጠቃለል እንደ አንድ ሰው ወደ ምድረ ደኅንነት ተወሰ ደዋል። የተጠቃለለ አንድ ነዋሪ ነገር ናቸው። እግዚአብሔር ለሰው ዘር ያዘጋ ጀው ዓላማው በእነርሱ በኩል እንዲፈጸም ከእነርሱ ጋር የሚሠራው በማጠቃለል አንድ አድርጎአቸው ነው። ስለዚህ አሁን በአንድ ሰው በደል በሰፈሩ ላይ የመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ «እስራኤል በድሎአል» የሚል ነበረ።

መንፈስ ቅዱስ ይህን ትምህርት በልብህ ሥር እንደሚጽፍልህ እተማመናለሁ። በአንድነት ከሚኖሩት ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ አንዱ አባል ቢበድል እግዚአብሔር «ሕዝቤ በድሎአል» ይላል። አንድ ሰው በገዛ እጁ ከበረከት ወጥቶ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የሆነውን ሥራ ፣ ሁሉን የሚያየው የጌታችን ዓይን ፍርድ እንዲህ ይላል «ሕዝቤ በድሎአል።»

«አየሁ ፣ ተመኘሁ ፣ ወሰድሁ ፣ ሸሸግሁትም» ክርስቲያን ሆይ ፣ የአንተ በደልና መተላለፍ ይህ ነውን ? የሰውን እንዋኑዋር ወይም ሕይወት በእጅህ ፣ በአነጋገርህ ፣ በሥራህ ፣ በእንዋኑዋርህ ስሜት ጎድተህ ፣ ወይም አጎድፈህና አዋርደህ አጎሳቁለህም ማንም እንዳያውቅብህ ትሠውራለህን ? የአካን ኃጢአትም ይኸው ነበረ ። አካን የሠራው ልክ ይህንኑ ነው ። እያንዳንዳችን የምንፈራው ፣ የምንንቀጠቀጠውና የምንርበተበተው ስሕተታችን ፣ በደላችንና ነውራችን እንዳይገለጥብን ነው እንጂ በልባችን ከተሸሸገው ኃጢአት ፍርሃት የተነሣ አይደለም ። ሕሊናችን ቢወቅሰን የመጀመሪያው ዓላማችን ኃጢአታችን እንዳይገለጥ በሚቻል ሁሉ መታገል ነው ። ምናልባትም በኃይልና በገንዘብ መሸፈን እንፈልጋለን ፤ ደግሞ እናደርጋለን ። አንድ ቀን ግን መረቡ ያጠምደናል ፣ ማምለጫ ይጠፋል ፣ ኃጢአታችን በቀን ብርሃን በሰው ፊት ይገለጣል ፤ መንፈስ ቅዱስም «በድለሃል ፣ ኃጢአተኛ ነህ» ይለናል ። በዚያን ጊዜ በመዋረድና ራሳችንን በማዘቅዘቅ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት በግምባራችን ተደፍተን «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ፣ አየሁ ፣ ተመኘሁ ፣ አደረግሁ ፣ ወሰድሁ ፣ ሸሸግሁም» እንላለን ።

አካን ፣ ቤተ ሰቡና ያለው ሁሉ ስለ ታላቁ በደሉ ጠፉ ፣ ወደሙ ። እንዴት ያለ ከባድ ፍርድ ነው ! ይህ ቁጥር ብዙ ጊዜ በብዙ ሰዎች ተጠቅሶልኛል ፤ እነርሱም የሚሉት እንዲህ ነው ፣ «የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር አንድ አምላክ አይደሉም ፣ ልዩ ናቸው ፤ ስለዚህ አካንና ቤተ ሰቡ በዚች በደል ምክንያት እንዲጠፉ በፈረደው እግዚአብሔር አናምንም» ይላሉ ። እግዚአብሔርና መድኃኒቴ ኃጢአት የሆነውን ሁሉ የሚጠላበትን ጥልና ፣ ከፈቃዱ ውጪ የሆነውንም ከጠባዩና ከእንዋኑዋሬ የሚያስወግድበትን መራርና አሰቃቂ ሁኔታ ሳስብ ልቤ በሰቀቀን ይሞላል ።

እስራኤል እንዲሸነፍ ምክንያት በሆነውና በእግዚአብሔርም ስም ላይ ትዝብት ፣ ትችትና ውርደት ለማምጣት በሚሞክረው ዲያብሎስ ሊደረግ የሚገባው ጨርሶ መደምሰስ ነው ። በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ገላጭነት እንደምንረዳው ኃጢአትን ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም ። ለአንዲት ሰዓት እንኳ ረጋ ብለህ እነዚህን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቀሃልን ? «ለምን ይህ ሁሉ ሆነ ? ምን አመጣው ? መሆን ይገባው ነበረ ወይ ? ለምንስ ይህ ሁሉ እንዲደርስብኝ አደረግሁ ? በጸሎት ታካች ሆንሁ ፣ ትምክህት ሞላብኝ ፣ እምቢተኛ ነኝ» ድካምህን ወደምትረዳበት ወደ ወደቅህበት ስፍራ ተመለስ ። የድካምህን መሠረት ስታገኝ ራስህን ወደ ላይ ወደ ኢየሱስ አሻቅበህ እንዲህ በል «አየሁ ፣ ተመኘሁ ፣ አደረግሁ ፣ ወሰድሁም» ከዚህ በኋላ «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ፣ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ስለተባለ ታመሰግነዋለህ ። ፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፣ ፱ ።

ክርስቲያኖች ራሳቸውን ከኃጢአት እንዲያነጹ ይጠየቃሉ ማለት በኃጢአታቸው እንዲናዘዙና እንዲተውትም ነው ። «ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ»

ኤፌሶን ፯ ፣ ፲፫ ። የእግዚአብሔር ቃል ግን በተጨማሪ እንዲህ ይላል ፣ «እርምም የሆነውን ነገር ከመካከላችሁ እስክታጠፉ ድረስ በጠላቶቻችሁ ፊት መቆም አትች ሉም» ኢያሱ ፯ ፣ ፲፫ ።

በክርስቶስ ወዳጆቼ የሆናችሁ ምዕመናን ሆይ ፣ ከልቤ ፍቅርና ምኞት ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የምለምናችሁ ይህ ነው ፤ ወይ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁና አንድ ሁኑ ወይም ከቤቱና ከማኅበሩ ውጡ ። ለማሸነፍና ድል ለመን ሣት ከተፈለገ የመጀመሪያው እርምጃ በብዙ ቤተ ክርስቲያናት መዝገብ ላይ ከሚገ ኙት ምዕመናን ጥቂቶችን መቀነስ ሳይሻል አይቀርም ። በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በጣም ቢያዋርድህም ቅሉ በልብህ ያለውን አከንን መርምረህ እንድታስ ወጣ እግዚአብሔርን እለምናለሁ ፣ ይሉኝታና እፍረትን ትተህ ከእግዚአብሔር ታረቅ ። በጌታ በኢየሱስ ፊት በኃጢአትህ ተናዘዝና ተወው ፤ በደሙ የተሰጠህንም ማንጻት ተቀበል ።

ምዕራፍ ፲ ።

# የክርስቲያን የነፃነት ሕግ ።

ኢያሱ ፰ ፥ ፴ ።

«የእስራኤልም ልጆች ሲያዩ በዚያ ስፍራ በድንጋዮቹ ላይ የሙሴን ሕግ ጻፈበቸው ። የእስራኤልንም ሕዝብ አስቀድሞ ይባርኩ ዘንድ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዳዘዘ ፥ እስራኤል ሁሉ ፥ ሽማግሌዎቻቸው ፥ አለቆቻቸውም ፥ ፈራጆቻቸውም ፥ የአገሩ ልጆችም ፥ መጻተኞችም ፥ እኩሌቶቹ በገሪዛን ተራራ ፊት እኩሌቶቹም በጌባል ተራራ ፊት ሆነው ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት በተሸከሙት በሌዋውያን ካህናት ፊት ለፊት ፥ በታቦቱም ፊት በወዲህና በወዲያ ቆመው ነበር ። ከዚህም በኋላ በሕጉ መጽሐፍ እንደ ተጻፈ ሁሉ ፥ የሕጉን ቃሎች ሁሉ በረከቱንና እርግማኑን አነበበ ። ኢያሱም በእስራኤል ጉባኤ ሁሉ በሴቶቹም በሕፃናቱም በመካከላቸውም በሚኖሩት መጻተኞች ፊት ሁሉን አነበበ እንጂ ሙሴ ካዘዘው አንዲት ቃል አላስቀረም ።» ኢያሱ ፰ ፥ ፴፪ — ፴፭ ።

መጽሐፈ ኢያሱ ስምንተኛው ምዕራፍ የሚያወራው በመጨረሻ በጋይ ላይ ስለ ተደረገው ውጊያና ድል ነው ። ይኸውም ከመዋረድ በኋላ ወደ ክብር መነሣት ነው ። የአመለጣቸውን ስፍራ መልሰው ለመያዝ ኢያሱ የወሰደውን እርምጃና የጦር ስልት እንድታነብ ሳላሳስብህ አላልፍም ። በዚያ ስለ ደፈጣ ፥ በምክንያት ስለተደረገ ሽሽትና በመጨረሻም ድል ስለማድረጋቸው ታነባለህ ፤ ጠላቶች ግን እስራኤላውያን ሲሸሹ ድል የአደረጉዋቸው መሰላቸው ። ጋይ በመጨረሻው እንድትሸነፍ ከእስራኤል ኃያላንና ጽኑዓን ሰዎች የጦሩ ፊት አውራሪዎች እንደተደረጉ በብዙ ታነባለህ ። ጋይ ከኢያሪኮ የአነሰች ከተማ ነበረች ፤ ነገር ግን እስራኤላውያን በመጀመሪያው ውጊያ ድል ስለሆኑ አሁን ጋይን ማሸነፍ አስቸጋሪ ይመስላል ።

በቤትህ ለብቻህ ቁጭ ብለህ ፥ የተዘረጋ መጽሐፍ ቅዱስ በፊትህ አድርገህ በዚህ ክፍል የተጻፈውን ሁኔታ ብትመረምር ፥ የአመለጠንን ፥ የጠፋብንን ወይም ለቀቅን የሸሸነውን ስፍራና አቋም መልሰን መያዝ በክርስቲያን ኑሮ ውስጥ ከሁሉ በላይ እጅግ በጣም አስቸጋሪ መሆኑን እንደምትገነዘብና ልብህንም እንደሚነካ አምናለሁ ። በእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት ውስጥ የሰላሳ ደቂቃ አለመታዘዝ ወይም ስሕተት ብዙውን ጊዜ አያሌ ሰዎችን ከሰላሳ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ከበረከት ውጪ አድርጎ አቸዋል ። አንድ ሰው አሥራ ሁለት ወራት ሙሉ የማያቋርጥ ጠንካራ የክርስቲያን አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ ፥ ለጥቂት ጊዜ ወደ እረፍት ይሄዳል ፤ እዚያም ከእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ውጪ በሆነ ጓደኝነትና ወዳጅነት ይጠመዳል ፥ ከዚህ የተነሣ ያለፈውና የሚመጣውም የክርስቲያን ሥራው ይፈርሳል ። የተለቀቀውን ስፍራና አቋም መልሶ መያዝ እጅግ በጣም አዳጋች ነው ። ይህ ትምህርት በልብህ ውስጥ በጋለ ብረት ቢቀረጽ በገዛ ፈቃድህ በኃጢአት ብትወድቅ መነሣት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ታገኛለህ ።

ታሪካዊና ልብን ማራኪ ነገሮች መፈጸሚያ ስፍራ ነች ። ነገር ግን አሁን ከምነግራ ችሁ የበለጠ ልብን የሚቀሰቅስ ሁኔታ በማናቸውም ታሪክ ውስጥ እንዳልነበረ ላሳስ ባችሁ እፈልጋለሁ ።

ከሴኬም ሽለቆ ግራና ቀኝ ሁለት ተራሮች ሲኖሩ ሽለቆው ሁለት ማይል ስፋት አለው ። በአንድ ወገን የተመላለጠ ፣ ባድማ ፣ ምድረ በዳና ዓለታማ የሆነው የጌባል ተራራ ቆሞአል ። በሌላው ወገን በጫካ የተሸፈነና ያሸበረቀ ለምለሙ የጌሪዛን ተራራ ነው ። ዛሬ ወደ ፓለስቲን አገር ጉዞ አድርጎ እነዚህን ስፍራዎች የጎበኘ ሰው ከእነዚህ ተራሮች በአንዱ ላይ የቆመ ሰው ምንም ድምፁን ከፍ ሳያደርግ በሁለተ ኛው ተራራ ላይ ከቆመው ጋር በደንብ ሊነጋገር እንደሚችል ይተርክልሃል ። የዚ ህች ሸለቆ ድምፅ ማጉላትና እንዲሰማም ማድረግ አንድ ድንቅ ነገር ነው ። የሸለ ቆው ስፋት ማለት ተራሮቹ የሚራራቁት ሁለት ማይል እንደሆነ አስተውል ፤ ይኸ ውም ሦስት ኪሎሜትር ከሩብ ነው ! ሸለቆዋ እንደ ቲያትር አዳራሽ የተሸለመችና በተፈጥሮዋ የተሟላች ስለሆነች ድምፅ ከአንዱ ተራራ ጫፍ ወደ ሁለተኛው ጫፍ ከመቅጽበት በጉልህ ይበራል ።

እስራኤላውያን በጌባል ተራራ ግርጌ በደረሱ ጊዜ መሠዊያ ከልነከውና በሰው እጅ ሥራ ካልረከሱ ድንጋዮች መሠዊያ ሠሩ ። በኖራም አለበሱት ፤ በእርሱም ላይ በሁለቱ የድንጋይ ገበታ ተቀርጸው ያሉ አሥርቱ ቃላተ ኦሪት ተጻፉበት ። እስራኤላ ውያን ዮርዳኖስን ከተሻገሩ ወዲህ ከእግዚአብሔር ጋር ወደሚገናኙበት የስግደት ስፍራ ልባቸው ሲሳብ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ ነው ። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ሕግ ወደ ተጻፈበት የሕግ ፣ የሥነ ሥርዓትና የመታዘዝ ኑሮ የቀረቡበት ቀን ነው ።

ከዚያ በኋላ ከሕዝቡ እኩሌቶቹ ወደ ጌባል ፣ እኩሌቶቹም ወደ ጌሪዛን ተራራ ወጡ ። ከጌባል ተራራ የአለመታዘዝ ፍርድና እርግማን ይታወጃል ። ከጌሪዛን ተራራ መታዘዝንና ለእግዚአብሔር መሰጠትን የሚከተሉ በረከት ፣ ደስታና ክብር ይታወ ጃሉ ፤ የሮቤል ፣ የጋድ ፣ የአሴር ፣ የዛብሎን ፣ የዳንና የንፍታሌም ነገዶች ወደ ጌባል ተራራ ወጡ ፤ ከእነዚህም ሁለቱ ነገዶች ከከነዓን ምድር ወደ በረሃው ዳርቻ ሊመለሱ ያደረጉትን ቁርጥ ሐሳብ ገልጸዋል ። የከነዓን ምድር የሚወረሰው በብዙ ድካም ነው ፤ ከዚህም ሌላ ቤተ ሰቦቻቸውንና ከብቶቻቸውን ከዮርዳኖስ ማዶ ትተዋል ። በጌባል ተራራም የአለመታዘዝን እርግማን ሰሙ ። ከዚህ ጀምሮ የአለውን የሮቤል ንና የጋድን ታሪክ ብትከታተል መጨረሻው ጥፋትና መደምሰስ እንደሆነ ታገኛለህ ። ከእነርሱም ታሪክ ትምህርት ውሰድ ። የስምዖን የሌዊ ፣ የይሁዳ ፣ የይሳኮር ፣ የዮሴፍና የብንያም ነገዶች ወደ ጌሪዛን ተራራ ወጡ ። የመታዘዝንም በረከት ሰሙ ። በእነዚህ ተራሮች መካከል ኢያሱና ካህናቱ ከቃል ኪዳን ታቦት አጠገብ ቆመዋል ። ይህም እግዚአብሔር እዚያ ቆሞ እንደሚሰማቸው የሚገልጽ ምልክት ነው ።

ኢያሱ መናገር ጀመረ ፣ ድምጹም በዚያ የተፈጥሮ አዳራሽ ውስጥ ያስተጋ ባል ። ለሕዝቡም በረከትና እርግማንን ፣ ሕይወትና ሞትን ፣ ገነትና ገሃነምን አወጀ ። አለመታዘዝ የሚያስከትለውን እርግማን ሞትና ገሃነም ፣ እንዲሁም መታዘዝ የሚያስ

ከትለውን በረከት ፥ ሕይወትና ገነት አስታወቃቸው ። በሁለቱ ተራሮች ላይ የሚገ ኙም ሰዎች «አሜን» ሲሉ በሸለቆው ውስጥ ያስተጋባ ነበር ። የተባበረው ሠራዊት ተከፍሎ እኩሌቶቹ በአንዱ ተራራ ጫፍ ፥ እኩሌቶቹም በሌላው ተራራ ጫፍ ሆነው የእግዚአብሔርን ፍርድ አሜን ብለው ተቀበሉ ፥ ብንታዘዝ እንኖራለን ፥ ባንታዘዝ እንሞታለን ። ከእርሱ ፈቀቅ ብንል እንጠፋለን ፤ ብንከተለው እንባረካለን ። እንዴት ያለስ የሕዝብ ብዛት ፥ እንዴት ያለ ታሪካዊ ወቅት ነው ።

ታዲያ ይህ ነገር ከጊዜአችን ሰዎች ጋር ምን ግንኙነት አለው ? ይህ መልእክት ልቤንና ልብህን ሲወቅስና ሲዘልፍ ሳለ እስቲ ልመርምረው ። በመጀመሪያ የእግዚአ ብሔር ሕግ በፍርድና በእርግማን ተራራ ግርጌ ላይ እንደተጻፈ አስተውል ። ሰውን ሃይማኖተኛ መሆኑ ከእግዚአብሔር ሕግ እርነት አያወጣውም ፥ ነፃም አያደርገውም ። ከሕግ ፍርድ በአንድ በሌላ ሰው ሞትና መሥዋዕትነት ነፃ መሆኑ ግልጽ ነው ። እውነትም ነው ። ሕግ ከሚፈልገውና ከሚጠይቀው ምግባርና ኃላፊነት እንዲህም የተቀደሰ አንዋኑዋር ግን ነፃ አይደለም ።

እኔ እንደምገምተው በሰው ልጆች መካከል ከተወለዱት አስተማሪዎች ታላቁ ሰባኪ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚለውን ሰማ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» ሮሜ ፰ ፥ ፩ ። ይህ ቡሩክ እውነት ነው ። ንስሐ በገባ ሰው ፥ በአመነ ሰው ፥ ከሙታን የተነሣውን አሸናፊ ጌታ በሕይወቱ ውስጥ በተቀበለ ሰው ፥ በየቀኑም የተገለጸለትን ኃጢአት ለመተው በሚጥር ሰው አሁን ኩነኔ የለበ ትም ። የሕግ ፍርድ እርሱም ሞት ፥ በምትኩ በክርስቶስ ላይ ተደርጎአል ። ወዳጆቼ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ስፍራችን ፥ አቋማችንና መብታችን ይህ ነው ።

ይህ እንዴት እንደሆነ ለማወቅ ብትፈልግ ጳውሎስ በጥርጣሬ ውስጥ አይተወ ንም ፤ እንዲህ ይላል «በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ፥ ከኃጢአ ትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛል» ሮሜ ፰ ፥ ፪ ። ምን ማለቱ ነው ? እንዲህ ነው ፥ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ፍላጎት ሲፈጽም ፥ ፍርዱንም አሜን ብሎ ሲቀበ ልና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ፥ በዚያች ወቅት ሌላ ሕግ በሰማይ መሥራት ይጀምራል ። ንስሐ ገብተው ለሚያምኑ ሕይወትን ሊሰጣቸው ፥ በውስጣችንም ለአ ዲስ ሥርዓትና ሕግ የሚሆን የሕይወት መንፈስ ሕግ እንዲሰጠን መንፈስ ቅዱስን ሊሰጠን እግዚአብሔር ከልጁ ከኢየሱስና ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል ፤ ቃል ኪዳኑም በመስቀሉ ደም ታትሞአል ። አንድ ሰው ባመነ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ አዲስ ይወለዳል ፤ የሥላሴ ሦስተኛ አካል የሆነውም የእግዚአብሔር መንፈስ ገብቶ በት በውስጡ ያድራል ። ስለዚህም «በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ፥ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛል»

ይህ ተአምራታዊ አድራጎት እንዴት እንደሚፈጸም ብንጠራጠር ጳውሎስ ይነግ ረናል «ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን ፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና .... ኃጢአትን

በሥጋ ኰነነ» ሮሜ ፰፥፫ና ፬። ከድካማችን፥ ከጉስቁልናችንና ሥጋዊነታችን የተነሣ ሕግ ሊሠራብን እንዳልቻለ አስተውል።

አዎን፥ ክርስቲያን በሆነ ሰው ሕይወት ውስጥ አሁን የሚሠራ ሌላ አዲስ ሥርዓት አለ። የትንሣኤን ሕይወት ወደ ልቡ ወስዶአል። ፍጹም ያለ ነውር ንጹሕም ወደ ሆነው ወደ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት እንዲለወጥ በእግዚአብሔር መንፈስ ተጠመቀ፤ ክርስቶስም የማይነቀፍ፥ ቅዱስና ፍጹም የሆነ አንዋኗዋር ኖረ፤ የማስተሰረያ ሞት ሞተ፥ ከመቃብርም ተነሥቶ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አረገ፤ በተለይ ለሚያፈቅራቸው ብቻ ሳይሆን አዲስ ለተወለዱ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ አዲስ የሕይወት ሥርዓትና በክርስቶስ ያለውን የሕይወት መንፈስ ሕግ ይሰጣል።

ይህ ሁሉ ለምን እንደተደረገ ትጠይቃለህን? ይህን ስማ «እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ» ሮሜ ፰፥፬። ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ሕግ አልተለየበትም። ከሕግ ፍርድ ነፃ ወጥቶአል፤ ነገር ግን ሕግ የሚጠይቀውን አንዋኗዋር እንዳይኖር ነፃነት የለውም። በግልጽ ቋንቋ ልንገርህ፥ ቅድስና ብትፈልግ ተቀብለህ ሳትፈልግ የምትተወው ምርጫ አይደለም። ያለ ቅድስና ማንም ቢሆን እግዚአብሔርን ሊያይ አይችልም።

ዛሬ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኘው ታላቁ ችግር ይህ ነው። ብዙዎች ክርስቲያን በመሆን ይጫወታሉ፤ ይቀልዳሉ። ክርስቲያንነት የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት ስለሚፈሩ ለተቀደሰና ለአሸናፊው የክርስቲያን ኑሮ ራሳቸውን በእውነት ለማስረከብ አይፈቅዱም። ሃይማኖታቸው በሥራ ስላልተገለጠ፥ መጽሐፍ ቅዱሳቸው በሥራ ላይ ስላልዋለ፥ ሕይወታቸውም ስላልተቀደሰ፥ በጌታችን ፊት ሲቀርቡ የአመኑት ሃይማኖት፥ ያፈቀሩትና ያቀፉት ትምህርተ ሃይማኖት፥ እናምነዋለን የሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ለታላቅ አድናቆታቸው ብዙዎችን ወደ ገሃነም አሽቀንጥሮ እንደሚወረውራቸው ሳሰላስል ነፍሴ በውስጤ ይንቀጠቀጣል፤ በፍርድ ተራራ ግርጌ የተጻፈውን ሕግ መጠበቅና መፈጸም ይገባል። ይህም የሚደረገው፥ እግዚአብሔር ይመስገን በእኛ ጉልበትና መፍጨርጨር አይደለም። ነገር ግን በውስጣችን ባለው በመንፈስ ቅዱስ ነው።

ደግሞም ሌላ ነገር ላሳይህ፤ ይኸውም በዝርዝር ተገልጾአል፥ ይህ ነው፤ ሕጉ በመሠዊያ ላይ ተጻፈ። መሠዊያውም በጌሪዛን ተራራ ውበት ላይ አልተሠራም፤ ነገር ግን በባዶውና በባድማው፥ ፍርድ ከሚነበብበት ከጌባል ተራራ ሥር ተሠራ። በሰዎቹ የተፈረደባቸው ስፍራ መሆኑን አስተውል።

ሕግ ካልፈረደበትና ያልፈረደበት አንድ ክርስቲያን እንኳ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም አይችልም። በክርስቶስ ደም ከተዋጁት አንድ ስንኳ ወደ እግዚአብሔር እያየ «ከኩነኔና ሞት ነፃ ነኝ፥ ከሕግ ፍርድ ነፃ ነኝ፥ ነገር ግን ጌታ ሆይ፥ በአርሱ ኃይል ብቻ መታዘዝ ለሚቻለኝ ለመንፈስ ቅዱስ ራሴን ያለ ቅሬታና ማመንታት

መስጠት ተስኖኛል ፤ የክርስቲያን ኑሮዬም እውነተኛ ታሪክ የማያቋርጥ ውድቀት ፣ መሸነፍ ፣ ኃጢአተኝነትና እንቢተኝነት ነው ፤ እኔ በራሴ አፍራለሁ» የማይል የለም ።

የሆነ ሆኖ ሕጉ የተጻፈው በመሠዊያ ላይ ነው ። መሠዊያውም ደም የሚፈስበት ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነትና አንድነት የሚታደስበትና ለእግዚአብሔርም የሚሰገድበት ስፍራ ነው ። ስለዚህ ጌታዬን በልቤ እያመሰገንሁ የሚቀጥለውን ልነግርህ እችላለሁ ። «እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ» ማለት ፣ ከመሰወር ፣ ከማስመሰል ፣ ከልማዳዊ ወግና ሥርዓት ምቾት ብቅ ብለን ድካማችንንና ኃጢአተኛነታችንን በሙሉ ልባችን አምነን ፣ እንዳለ ከነኃጢአታችን በእግዚአብሔር ፊት ብንቆም ፣ ይህንንም ለማድረግ ብንደፍር «ለእያንዳንዳችን ሕብረት አለን» ማለት ፣ እግዚአብሔርና እኛ «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል» ፩ኛ ዮሐ. ፩ ፣ ፯ ። ምክንያቱም ፣ «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃ ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው» ፩ኛ ዮሐ. ፩ ፣ ፱ ።

ዛሬ በክርስቲያን ፊት ሕግና የሕግ ፍላጎቶች እንዳሉ አትረዳምን ? ሕግ ከነፍላጎቱ ያለ ምሕረት ቆሞ እንደሚያፈጥበት አታስተውልምን ? ነገር ግን አንድ ድምፅ ከልቤ እንዲህ ይላል «ብትወዱኝ ትእዛዛቴን ጠብቁ» ዮሐንስ ፲፬ ፣ ፲፭ ። ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቲያን ሕግን እንደ አንድ አስገዳጅ ነገር አይቆጥረውም ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽም ስለሚመራው ይደሰትበታል ፣ ከውስጡም የእግዚአብሔር ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ ወደ ውጪ ይጎርፋል ። ከላይ ስለተወለደ እግዚአብሔር የሚጠላውን ይጠላል ፤ እግዚአብሔር የሚወደውንም ይወዳል ። ስለ ራሱ ጥቅም ሳይሆን ስለ ኢየሱስ ብሎ በሠራው ኃጢአት ያዝናል ፣ ይጨነቃል ፣ ይናዘዛል ፣ ይተዋታልም ። የልቡም ጸሎት እንዲህ ነው ፣ «አቤቱ ፣ እግዚአብሔር ሆይ ፣ ቀድሰኝ» የእግዚአብሔር ልጅ መልካም እንዲሠራ ከውስጡ የሚመራው ፣ የሚቀድሰው ፣ መልካምንም ሁሉ የሚያስተምረው ነገር በውስጡ እንዳለ ያውቃል ። ከውስጡም የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር እየነደደ ስለሚንበገበግ መልካምን ሥራ ማለት ምግባርን ሳያውቅ እንዲሠራና እንዲፈጽም ይገፋል ፣ ይገደዳል ፣ ይደፋፈራልም ።

ኢየሱስ ሆይ ፣ አሸናፊው ፍቅርህ በልቤ ፈሷል ።
ልቤም አይታገል ከእንግዲህ ወዲህ በአምላክ ጸንቶ እንዲተከል ።
አሁንም ያ ቅዱስ እሳት ይጋል ይንደድም በልቤ
ያቃጥል ወራዳውን የልቤን ምኞት ተራሮቼን ያቅልጥ እንደ ቀቤ ።

ሕግ በመሠዊያ ላይ ነበረ ። የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ ፣ ሕጉን መተላለፍህን ብትገነዘብ ለጌታ ኢየሱስ ያለህ ፍቅር ፣ ምኞትና ቅድስና መቀነሱ ቢሰማህ ፣ ወደ ሕብረት መሠዊያ ተመልሰህ የሕጉን ፍላጎት እንደገና እንድትመለከት እለምንሃለሁ ። ሰዎች ይመጡና እንዲህ ብለው ይጠይቁኛል ፤ «ክርስቲያን ይህን ፣ ያንን ፣ ማድረግ ይገባዋልን ?» እነዚህ ጥያቄዎች አሳሳችና ጅልነት ናቸው ። ክርስቲያን እንዲድን ምን ማድረግ ፣ ምንስ ያህል መራቆት አለበት ? የሚሄደውስ የት ድረስ ነው ? እስከ

መስቀሉ ድረስ ብቻ ነው ። ነገር ግን በአንዋኑዋሬ ለእግዚአብሔር የማልታዘዝ ፣ ሕጉንም ችላ ያልኩ እንደሆንኩኝ በመስቀሉ ሥር እንድሰግድ ያለብኝን ግዴታ እንደ ከድሁ የሚገልጽ አዋጅ ነው ።

ለጌታችን ሥራ የሞቀ ምኞት ከሌለህ ፣ ለሚጠፉ ነፍሳትም ርኅራኄ ባይኖርህ ፣ ለቃሉም እውነተኛ ፍቅር የሌለህ እንደሆን ፣ የዚህ ሁሉ ጠንቅ በቀራንዮ የሚገባውን ስግደት ስለተውክ ነው ። ምክንያቱም ለራሱና ለዓለም በመስቀሉ የሞተ ሰው በዓለም ስለሚደረገው ሥርዓትና ማናቸውም ነገር ፣ እንደዚሁም ማድረግ ስለሚገባውና ስለማይገባው ነገሮች ማሰብ አይጨነቅም ፤ የሞተ ሰው ስለ ትዳር ይጨነቃል ወይ ? ለዓለምና በዓለምም ላለው ሁሉ የሞተ ሰው አትንካ ፣ አትቅረብ ፣ አትቅመስ ስለሚበሉና ስለሌሎችም ዓለማዊና ሥጋዊ ሥርዓቶች እንዴት መጨነቅ ይገባዋል ? ጩኸቱ እንዲህ ብቻ ነው ፣ «አቤቱ ፈቃድህን ማድረግ ደስ ይለኛል ፣ ሕግህንም እንዴት ወደድሁ አምላኬ ሆይ !»

ይህን ምዕራፍ በመደምደም ላይ ሳለሁ ፣ ልነግርህ የምፈልገው ፣ በፍርድ ተራራና በበረከት ተራራ መከከል ታቦቱ እንደነበረ ነው ። እነዚህን ሁለት ተራሮች በለየው ሸለቆ ውስጥ የቅዱስ እግዚአብሔር መኖር ምልክትና ማረጋገጫ አለ ። ለማንኛችንም ቢሆን አማካይ ስፍራ መያዝ ከቶ አይቻልም ። ከእግዚአብሔር ጥሪ ግምባር ለግምባር ሲገናኙ ፣ አንዳንዶች ይሞቃሉ ፣ ጥቂቶቹ ከእግዚአብሔር ይታረቃሉ ። ጥቂቶቹ ወደ ክርስቶስ ይቀርባሉ ፤ ንስሐ ይገቡና ራሳቸውንም ያዋርዳሉ ። ሌሎች ግን ጎዳናው ስለሚፈጃቸው ይሸሻሉ ።

ቀኖቹ አጭር ስለሆኑ ምርጫህንና ውሳኔህን በፍጥነት እንድታደርግ በእግዚአብሔር ስም እለምንሃለሁ ። ቃሉ በደረገልህ አድራጎት ተንሰራፍፈህ ቁጭ ብለህ በእግዚአብሔር አትቀልድ ፣ በሐዲስ ኪዳንም ቅድስና አትጫወት ። የሞቀ ምኞትና ፍቅር በልብህ ከሌለ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለአንተ ተገቢ ስፍራ አይደለም ። ጌታችን በቅርብ ጊዜ ስለሚመጣ የሚሠራ ብዙ ሥራ አለን ፣ የምንገዳደረው ታላቅ ጥሪ አለን ። ጌዴዎን ሰላሳ ሺህ ሰዎች ከነበረው ጊዜ ይልቅ ሦስት መቶ ሰዎች ብቻ በነበረው ጊዜ የበለጠ ሥራ እንደሠራ አስተውል ። የተወደድህ ዓለማዊ ክርስቲያን ሆይ ፣ በዓለማዊ ኅብረትና በዘመኑ መንፈስ መኖር ብርቅ የሚመስልህ ወዳጄ ሆይ ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሌለህና በአንድ ሐሳብ ያልሆንክ ወንድሜ ሆይ ፣ ወደ መስቀሉ ሄደህ ከእግዚአብሔር ጋር እንድትስማማ በጌታችን በኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ ።

ሌላ ምርጫ የለም ። አማካይ ስፍራም የለም ። ያሉት ሁለት ምርጫዎች ብቻ ናቸው ። እነዚህም ሕይወት ወይም ሞት ብቻ ናቸው ። በዚህ በጌሪዛንና በጌባል ተራሮች ትርዕይት ፣ ጌታችን ዳግመኛ በሚመጣበት ቀን ሕዝብ ሁሉ በፊቱ ተሰብስበው ፣ እርሱም እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ ይለያቸዋል ያለውን ትንቢታዊ ቃል የሚያስረዳ መግለጫ ይገኝበታል ። አንድ ሰው ሕይወት ወይም ሞት በረከት

ወይም እርግማንን ይመርጣል። የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች በጌታዬ በኢየሱስ ስም «በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን፥ በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ። እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ» ዘዳግም ፴ ፥ ፲፱ ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

# የጠላት የጦር ስልትና ዓላማ ።

ኢያሱ ፱ ፡ ፫ ።

የገባዖን ሰዎች ግን በኢያሪኮና በጋይ ያደረገውን በሰሙ ጊዜ ፣ እነርሱ ደግሞ ተንኰል አደረጉ ፣ ለራሳቸውም ስንቅ ያዙ ፣ በአህዮቻቸው ላይ አሮጌ ዓይበትና ያረጀና የተቀደደ የተጠቀመም የጠጅ አቁማዳ ጫኑ ። ያረጀ የተጠቀመም ጫማ በእግራቸው አደረጉ ፣ አሮጌም ልብስ ለበሱ ፤ ለስንቅም የያዙት እንጀራ ሁሉ የደረቀና የሻገተ ነበረ ። ኢያሱም ወደ ሰፈረበት ወደ ጌልገላ ሄደው ለእርሱና ለእስራኤል ሰዎች ከሩቅ አገር መጥተናል ፣ አሁንም ከእኛ ጋር ኪዳን አድርጉ አሉ ። የእስራኤልም ሰዎች ኤዊያውያንን ምናልባት በመካከላችን የምትቀመጡ እንደ ሆነ እንዴትስ ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን እናደርጋለን ? አሉአቸው ። ኢያሱንም እኛ ባሪያዎችህ ነን አሉት ። ኢያሱም፣— እናንተ እነማን ናችሁ ? ከወዴትስ መጣችሁ ? አላቸው ። እነርሱም አሉት ፦— ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ስም የተነሣ እጅግ ከሩቅ አገር ባሪያዎችህ መጥተናል ፣ ዝናውንም ፣ በግብፅም ያደረገውን ሁሉ ፣ በዮርዳኖስ ማዶም በነበሩት በሁለቱ በአሞራውያን ነገሥታት በሐሴቦን ንጉሥ በሴዎን በአስታሮትም በነበረው በባሳን ንጉሥ በዐግ ያደረገውን ሁሉ ሰምተናል ። ሽማግሌዎቻችንም በምድራችንም የሚኖሩት ሁሉ ፦— ለመንገድ ስንቅ በእጃችሁ ያዙ ፣ ልትገናኙአቸውም ሂዱ ፣ እኛ ባሪያዎቻችሁ ነን ፤ አሁንም ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አድርጉ በሉአቸው አሉን ። ወደ እናንተ ለመምጣት በተነሣንበት ቀን ይህን እንጀራ ትኩሱን ለስንቅ ከቤታችን ወሰድነው ፤ አሁን እነሆ ፣ ደርቆአል ፤ ሻግቶአልም ። እነዚህም የጠጅ አቁማዳዎች አዲስ ሳሉ ሞላንባቸው ፤ እነሆም ተቀድደዋል ፣ መንገዳችንም እጅግ ስለራቀብን እነዚህ ልብሶቻችንና ጫማዎቻችን አርጅተዋል ። ሰዎቹም ከስንቃቸው ወሰዱ ፤ እግዚአብሔርንም አልጠየቁም ። ኢያሱም ከእነርሱ ጋር ሰላም አደረገ ፤ በሕይወት እንዲተዋቸውም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ ፤ የማኅበሩም አለቆች ማሉላቸው ።» ኢያሱ ፱ ፡ ፫ — ፲፭ ።

ክርስቲያኖች ስለሆንን የሚደርሱብን መጋደሎች ሁሉ አንድ ምክንያትና ዓላማ አላቸው ። ይኸውም የተሟላ ደኅንነትና ፍጹም ከሆነው የኃጢአት ባርነት ነፃ መውጣትን ለማስገኘት ነው ። በአንድ ውጊያ ብናሸንፍ ጦርነት ሁሉ አለቀ ማለት አይደለም ፤ እንዲሁም በአንዱ ውጊያ ብንሸነፍ በቀረው ጦርነት ሁሉ ለማሸነፍ መጣር ተስፋ የሌለው ነው ማለት አይደለም ። ኃጢአት እስከለ ድረስ ውጊያ ይቀጥላል ። እኔና አንተ ሙሉ ደኅንነቱ ወደፊት በሆነው ሥጋ እስካላን ድረስ መፈተን ምን እንደሆነ በየቀኑ እንማራለን ። ማናቸውም ኃጢአት ወይም ክፉት ትልቅ ነው ፤ ወይም ትንሽ ነው ማለት አይገባም ፤ ከሰይጣን መተሻሸት ከክፉት መዛመድ ነው ።

የመሸነፍና የመውደቅ ጠንቅ ሁልጊዜ በጸሎት ይገለጣል ፤ ነገር ግን የተለቀቀ ጭንና የአመለጠውን ስፍራና አቋም መልሶ መያዝ ከጸሎት የበለጠ ነገር ይጠይቃል ። የነፍሳችንን ጠላት በአንድ ምትና በአንድ ወቅት ልንጥለው አንችልም ፣ አርነት የመውጣት ድርጊቶች ቀስ በቀስ ይሠራሉ ፣ ይፈጸማሉም ። ለታላቁ የጦር አዛዣችን መታዘዝ ፣ በእርሱም መታመን የአሸናፊው እንዋኑዋራችን እውነተኛ ምሥጢር ነው ።

እግዚአብሔር ሕጉን ለክርስቲያን የሰጠው እንዲያሞግሰውና እንዲያወድሰው ሳይሆን እንዲታዘዝለት ነው ። በክርስቲያን ውስጥ በሚያድረው በእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ የዚያ ሕግ ፍላጎት በክርስቲያኑ ሕይወት ፣ እንዋኑዋርና አካሄድ መፈጸም ለምንኖርበት የነፃነት ሕግ ጽኑ ማኅተም ነው ። በዚያ ነፃነት ስንኖር ሳለን በአሸናፊነት የመኖርን ትርጉም እንረዳለን ።

እስከ አሁን ስንማራቸው ከቆየናቸው ትምህርቶች ዋቂቶቹ እነዚህ ናቸው ። የድል ምሥጢር በጦር ስልትና በዓላማ መሆኑን ልነግርህ እወዳለሁ ። በከነዓናውያን ላይ የሚደረገው ወረራ እንዴት ባለ ጥንቃቄና ጥበብ በኢያሱ እንደታቀደ ተመልከት ። በመጀመሪያ ከኢያሪኮ በቀጥታ ወደ ምዕራብ አጠቃ ። በዚህም በምድሪቱ አማካይ ስፍራ ላይ በመድረሱ የጠላትን የጦር ኃይል ከሁለት ከፈለ ። ከዚያ በኋላ በደቡብ ያሉትን ለማጥፋት ወደ እነርሱ ዞረ ፣ ቀጥሎም ወደ ሰሜን ተመልሶ ጠላቶቹን ሁሉ ጠረገ ። ይህ ፣ የጦር ስልትና ልምምድ ባለው ታላቅ መሪ የታቀደ ዘመቻ ነው ።

በእኛ በብዙዎቻችን ክርስቲያኖች የሚገኘው አንዱ ችግር ለየቀኑ ተግባራችን የተቀደሰ ዓላማና ስሌት ስለማናደርግ ነው ። የክርስቲያን ኑሮአችን ዓይነን ጨፍኖ ድንጋይ በመወርወር ብታገኝ ምታ ባታገኝ ተው እንደሚባል ጨዋታ ያለ ዋዛ ፈዛዛ ነገር አይደለም ። ይህ ከሆነማ ከምንመታው ይልቅ የምንስተው ስለሚበዛ መደነቅም አያሻም ። ክርስቲያን በዕለታዊ እንዋኑዋሩ ከጠላቱ ጋር በሚያደርገው መጋደል ፣ አስቀድሞ በታቀደ ዓላማና ሥነ ሥርዓት የሚጠቀምበት አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። ስለዚህ ሰይጣን ከግንባችን አሽቀንጥሮ ይወረውረናል ። ሰይጣን ራሱ ዝነኛ የሆነ የጦር ስልትና ዓላማ አዋቂ ነው ። ዲያብሎስ የሚጮህ አንበሳ ብቻ አለመሆኑን አስተውል ። ተንኰለኛ ጠቢብና አሾክሿኪ እባብ መሆኑንም እወቅ ። ከእባብ ሹክሹክታ ይልቅ የአንበሳ ግሣት እንደሚሻል አስተውል ። የአንበሳን ግሣት ከሩቅ ሳለምትሰማ ልታመልጥ ትችላለህ ፤ ነገር ግን ከእግርህ ሥር የሚያንሾካሹከው እባብ ሳትሰማና ሳታይ ይነክስሃል ።

በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ ዘጠኝ ውስጥ የጠላታችንን ዘዴኛነት ፣ እንዲሁም የማታለል ጥበብና የእኛን በቀላሉ ተታላይነት አሳምሮ የሚያሳይ መግለጫ እናገኛን ። ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገንና ፣ በዚሁም ምዕራፍ ደግሞ ስሕተታችንንና መተላለፋችንን ለክብሩ የሚለውጠውን የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት እናገኛለን ።

ስለዚህ ከእኔ ጋር ሆነህ የነፍሳችን ጠላት ያለውን የማታለል ጥበብና ዘዴውን እንድ ንመረምር እጠይቅሃለሁ ።

የእስራኤላውያን ድሎች የተባበረ የጠላት ውጊያ እንደቀሰቀሰባቸው ተረዳ ። የዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ቁጥር በከነዓናውያን መካከል የነበረው የጎሳ ንትርክና የወገን ግጭት እንደተቋረጠ ይናገራል ። ጥቃቅን ንትርኮች ተረሱና ከእነዚህ ዳግማዊ ከሆኑ ነገሮች ቀዳሚና ዋነኛ በሆነው ፥ ወራሪውን የእስራኤልን ሠራዊት ለመደምሰስ በተደረገው መተባበር ተዋጡ ።

እዚህ ላይ ከዋናው ዓላማዬ መዛነፍ የለብኝም ፥ ሆኖም ሳላልፍ ይህን ልንገርህ ፥ አንድ ክርስቲያን በኑሮው የአገኘው እያንዳንዱ ድል የነፍሱ ጠላት በሙሉ መሣር ያና ኃይል እንዲነሣበት ያደርጋል ። ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር በሚያደርገው መሸሸልና በእያንዳንዱ ጥሩ እርምጃ ሁሉ በጠላቱ አደጋ ዳርቻ ላይ ነው ። በረከትና መጋደላችን ጎን ለጎን ይራመዳሉ ። በሁሉም በኩል ብትከበብና በተፋፋመ መጋደል ላይ ብትሆን እግዚአብሔርን አመስግን ። ፈተናው ከአቅምህ በላይ ቢከብድብህ ፥ ትግሉም የማትገፋበት ብርቱ ቢመስልህ ፥ እኔን እጅግ በጣም ደስ እንደሚለኝ እንድ ታውቅ እወዳለሁ ። ለአንተ የተጣልህ መሰለህ ፤ እኔ ግን በአንተ ፋንታ በጣም ተደ ሰትኩ ። ወዳጄ ሆይ ፥ ይህ ጥሩ ምልክት ነው ። በቀኝህና በግራህ ብትፈተን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ በረከት የምትጓዝ ስለሆንክ ነው ።

ለራስህ ግን እንዲህ ብትል «ይህ ሰው የሚያወራው አይገባኝም ፥ ከብዙ ዓመ ታት ወዲህ ተፈትኜ አላውቅም ፤ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አላውቅም» ወደ ጌታችን ሂድና ፥ ከሕይወትህ ውስጥ ደንዝዞ በትክክል የማይሠራው ብልሽት ምን እንደሆነ ጠይቀው ።

እኛ ክርስቲያኖች ባለን መሣሪያና ኃይል በጠላታችን ላይ አደጋ ለመጣል ሌሎ ችን ንትርኮችና ትርኪ ምርኪ ነገሮች ምነው በተውነ ? ዳሩ ግን በወገን መካከል ባለው መወቃቀስና መተቻቸታችን በጥቃቅን ንትርኮቻችንና በሃይማኖት ትምህርትም ባለመግባባታችን ዘወትር ጠጉራችንን እንነጫለን ፤ እነዚህም ከማይረቡ ግሳንግሦች ጥቂቶቹ ናቸው ። ልዩ ልዩ ችግሮችን ለማቃለል ሁልጊዜ እንለፋለን ፤ ለቁም ነገሩ ግን ጊዜ የለንም ። የእግዚአብሔርን አብያተ ክርስቲያናት በጥቃቅን መሰናክሎች ወደ ረግረግ ስለጣሉአት በገሃነም ሦስት ጊዜ እልል ይላሉ ።

በዚህ በሃያኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የቀራት ተስፋ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያደርጉት ሰፊ የሆነ የመተባበር ውጊያ መሆኑን እንገንዘብ ፤ ሰይጣንም በዚህ ዘዴ ትንሽ እንደ ቀደመንና እኛም ከእርሱ እንደተማርን ያውቃል ።

ነገር ግን ከዚህ ምዕራፍ እንድታስተውል የምፈልገው የከነዓን ነዋሪዎች በእስ ራኤላውያን ላይ ሰፊ የሆነ የተባበረ ውጊያ ከማድረጋቸው በፊት ከእነርሱ ጋር የተስ ማሙና የተባበሩ በማስመሰል ሊያታልሉአቸው እንደ ሞከሩ ነው ። በከነዓናውያን አስተያየት ትግሉ ብዙ ተስፋ አልነበረላቸውም ፤ እስከ አሁን ድረስ የተገኘው

እንዳትለፋ እያለ ሊጫወትብህና ሊዘብትብህም ሞክር ይሆናል ፤ ምናልባት ፥ በሕይወ ትህ ውስጥ የክርስቶስ የገዥነት ሥልጣን የማይመለከተው ነገር አለ ብሎ ሊያግባባህ ይሞክራልን ? ሰይጣን በንግግሩ ሁሉ በእግዚአብሔር እንደሚያምን እንደ ጭላን ጭል እንደሚያሳይ አስተውል ። ራሱ ሃይማኖተኛ እንደሆነ ያሳስብሃል ። ራሱ ፍጹም የሆነ መሠረታዊ እንደሆነ ያውጃል ። ዲያብሎስ ይህ ሁሉ ነው ። እርሱ ፍጹም አርቶዶክስ (መሠረታዊ) ነው ። ለአንዲት ደቂቃ እንኳ መጽሐፍ ቅዱስን አይክድም ። ከሙታን የተነሣውን ጌታና ዳግመኛ ስለ መምጣቱም አይክድም ።

ራሱንና ዘዴውን በመሸፋፈን ስለመጣብህ በቀላሉ ሳያጠምድህ አልቀረም ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይሉኝታና የራስህ ግምት ተገቢ ነው ሳይልህ አልቀረም ። በግል ጉዳይህ በተለይም በገንዘብ በኩል እንደ ሌሎች ሁን ብሎሃል ። ሃይማኖት የተባለው ነገር ለአእምሮህ ፍርድ የማይመች ነውና ሁልጊዜ ልቡናህ በሚነግርህ የተሻለ ነው ይልሃል ። እንደዚህ እያስመሰለ በማሳሳት ስለ መጣ ሰይጣንን ማወቅ በጣም አዳጋች ነው ። በማናቸውም ነገር ባለው ኃይል እንደሚረዳህ ተስፋ አስደፈ ገህ ። እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ ግን በተንኰሉ ጥበብ ለጥፋትህና መደምሰስህ ይሠራል ። «መንፈስን ሁሉ አትመኑ ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ» ፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፥ ፩ ይላል የእግዚአብሔር ቃል ።

ከይሁዳ ቀያፋ ይሻላል ፤ ከሰይጣንም ሽፍንፍን የተንኰል ፈተና ይልቅ ፊት ለፊት ከሚመጣ ብርቱ ጠላት ጋር መጋጠም በጣም የተሻለ ነው ። በእግዚአብሔር (እስራኤል) ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ቀን የእስራኤል ጠላቶች በተቀደሰችው በጌልገላ መሬትና በሕዝቡ ሰፈር ውስጥ ቆሙ ። ለእግዚአብሔር የተለዩና የተቀደሱ እስራኤላውያን እንዲያጠፉአቸው እንጂ እንዳይቀላቀሉአቸው እግዚአብሔር ካዘዛቸው ሕዝብ ተቀላቀሉ ።

ገባዖናውያን ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ፥ በእያንዳንዱ ክርስቲያን አንዋኑ ዋር ፥ በእያንዳንዱ ክርስቲያን የዕለት ተግባርና የቤተ ሰብ ኑሮ ውስጥ በመግባታቸው የመጣብንንና የሚመጣብንንም አሳዛኝ ሁኔታ ምነው ባየን ? ሰይጣን በሽፍንፍን ገብ ቶብን የምስክርነታችንን ኃይልና መረቅ ሁሉ ይመጥጣል ። አወይ የጠላታችን የተ ንኰል ጥበብ ።

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ልጆች ደደብነት ላሳይህ ። በዚሁ ምዕራፍ በአሥራ አራተኛው ቁጥር ያለው አነጋገር የወደፊት ዕድላቸውን በጣም የሚገልጽ ነው ። «እግዚአብሔርንም አልጠየቁም»

በጸሎት መታከት ወደ መከራ እንደሚመራና የሚመጣውን ክፉ ነገር የምናይ በት የመንፈስ አርቆ ተመልካችን እንደሚያጠፋብን እስክናውቅ ድረስ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ይመስላል ። ጸሎትን ችላ ማለት ሁልጊዜ ወደ ሞት የሚመራ የሆነው የራሳችን ግምትና የሕሊና ፍርድ ትምክህት ነው ። ሰይጣን እንደ ብርሃን መልአክ ስለሚገለጽ ራሱ ፥ ትምህርቱን አገልጋዮቹ እውነትን ይመስላሉ ። ስነሮቹ ቀንጃጅት ልባሞቹን ይመስሉ ነበር ። በእርሻው የተዘራው እንክርዳድ ስንዴውን ይመስላል ።

መልሱ ምንድር ነው ? ሰይጣንንና የተንኰሉን ጥበብ እንዴት አድርገን እናወዳድረው ? ስማኝ፣ በማናቸውም የራስህ የሕሊና ፍርድ ከቶ፣ ከቶ፣ አትተማመን። ልብህ አንዳንድ ንግግርና ስድብ ተገቢ ነው ቢልህ፣ የሃይማኖትና የበረከት ጉዳና ከሕሊናና ከልማድ ጉዳና በሌላ አቀጣጫ ስለሆነ ልብህን ወደ እግዚአብሔር አንሣ። በምትሠራው እንድትቸኩል የልብህ ድምፅ ሲያፋጥንህ ሁሉንም ነገር ወደ እግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ውሰድ። እስከ አሁንም ብትጠራጠር በድፍረትና በእምነት ጸንተህ ቁም። አንድ ነገር እንድታደርግ በሚያስቸኩል ብትጠራና ለጸሎት ጊዜ ብታጣ ያንን ነገር አታድርገው። ለአንድ ነገር ወይም የጊዜ ሁኔታ አቀጣጫ ለመንዝ ብትጠራና ከእግዚአብሔር ሰላምና ማረጋገጫ እስከታገኝ መቆየት ቢያቅትህ ጉዞውን ተው። እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉና በእርሱ የሚታመኑ ከቶ ስለማያፍሩ በርታ፣ ጽና፣ አይዞህ። በእግዚአብሔር ታመን። ከዲያብሎስ የምንበልጠውና ከእርሱም ይልቅ የምናይለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

አንዳንድ ሰው እንዲህ ሲል ይመልስልኛል፤ «የተናገርከው ሁሉ እንደ ሰይፍ በልቤ ገብቶአል። ተሳስቻለሁ፣ በሥራዬ የማይገባ መተሳሰር አደረግሁ፤ በጋብቻ የማይገባ መቆራኘት አደረግሁ፤ ዓመታቱም እንዳለፉ ስለ እነዚህ ሁሉ ምን ያህል እንደ ተሠቃየሁ ተምሬሐለሁ። በእኔ የደረሰብኝ በሌሎች እንዳይደርስ ብቻ እጸልያለሁ። የእኔ ጊዜም አልፎአል።»

ወዳጄ ሆይ፣ ይህ የዲያብሎስ ተላላ ነው። ዓይነተኛው የሰይጣን የተንኰል ወረራ እንዲህ ይላል «ክርስቲያንን አሰናክልና በገመዴ አገባሁ» ብለህ በጆሮው አሾክሹክ።

በዚህ ምዕራፍ ቁጥር ሃያ አንድን አንብብ «አለቆቹም በሕይወት ይኑሩ አሉአቸው። አለቆቹም እንደተናገሩአቸው ለማኅበሩ ሁሉ እንጨት ቆራጮች ውኃም ቀጂዎች ሆኑ» ይህ ልብን ይመስጣል። ስለ ሰይጣን ጥበብና ዘዴ ብነግርህም እግዚአብሔር ደግሞ ለጥበቡና ለተንኰሉ ሁሉ ያለውን መልስ ስነግርህ በጣም ደስ ይለኛል። እንሳሳታለን፣ የማይሳሳት ማን ነው ? በውጊያው እንሸነፋለን፣ ሁላችንም እንወድቃለን፣ የማይሸነፍ የማይወድቅስ ማን ነው ? ነገር ግን የተዋረድህ፣ ተስፋ የቆረጥህና የዛልህ ክርስቲያን ሆይ፣ ስማኝ፣ በውጊያው እንደ ገና ልናሸንፍ እንችላለን። ኃጢአታችንን መተላለፋችንንና በደላችንን የሚያስወግድ፣ እርግማንንም ወደ በረከት ለሚለውጥልን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው። እነዚህ ገባዖናውያን ለእግዚአብሔር ቤት እንጨት ቆራጮችና ውኃ ቀጂዎች ሆኑ። ይህ ድንቅ አይደለምን ? ለመሠዊያው እሳት ማገዶ እንዲቆርጡና ለማደሪያው መቅደስ ጽዳቶች ውኃ እንዲቀዱ ተደረጉ። እስራኤላውያን ተሰናክለውበት የወደቁና በምክንያቱም በኋላ ሥቃይ የደረሰባቸው ይህ ኅብረት ወደ መልካም ነገር ተለወጠ። ያታለሉአቸው ሰዎች የመሠዊያውን እሳት እንዲነድድ እንዲያደርጉና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የስግደት ስፍራ ጽዳት እንዲጠብቁ ተዋረዱ።

ከገበያናውያን ጋር ያለውን ኅብረት ማፍረስ ይገባልን ወይስ አይገባም ? የሚል ጥያቄ እንደሌለ አስተውል ። የእስራኤላውያን የኋለኛው ታሪካቸው ይህንን ኅብረት ለማፍረስ በሞከሩበት ጊዜ ብዙ ችግር እንደ ደረሰባቸው ይነግረናል ። ሳኦል ከገባዖናውያን ጋር የነበረውን ኅብረት ሰበረና መከራ ደረሰበት ።

የተወደድክ ክርስቲያን ሆይ ፣ ተሳስተህም ተሸንፈህም ፣ ወድቀህም እንደሆነ ፣ አሁንም በመከራና በጭንቅ ብትሆን የገባኸውን ኪዳን እንድታፈርስ ይህ ምክንያት አይሆንህም ። ክርስቲያን በሥርዓት ፣ የሚኖር የታመነ ፣ ያለ ነውር የሚኖር የማይናወጥ መሆን አለበት ። ነገር ግን ጸንተው ከመኖራቸው ማፍረሳቸው የሚበጅ ቃል ኪዳኖች አሉ ። ለምሳሌ በዘፈንዋ ስላስደሰተችው ሄሮድስ የማለው መሐላ ነፍስ እንዲገድል ስላደረገው ትክክለኛ ነገር አልነበረም ። ኃጢአትን እንድትሠራ ከሚያጋልጥህ ነገር ጋር ያደረግኸውን ኪዳን ዛሬውኑ ስለ እግዚአብሔር ብለህ አፍርስ ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች በሥራና በጋብቻም ለቀረው ሕይወታቸው ሁሉ ከገባዖናውያን ጋር ተሳስረዋል ። እንዲህ ያለው ምን ይሁን ? መልሱ ቃሉ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም «ከወንድሞች ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርስዋም ከእርሱ ጋር ልትቀመጥ ብትስማማ አይተዋት ፣ ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርስዋ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ ፣ አትተወው ። ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና ያላመነች ሚስት በባልዋ ተቀድሳለች ። አንቺ ሴት ባልሽን ታድኚ እንደሆንሽ ምን ታውቂአለሽ ? ወይስ አንተ ሰው ሚስትህን ታድን እንደሆንህ ምን ታውቃለህ ?» ፩ኛ ቆሮ. ፯ ፣ ፲፪ — ፲፬ ፣ ፲፮ ። የተወደዳችሁ ክርስቲያን ወጣቶች ካላመኑ ጋር እንድትጋቡ ይህ ምክንያት አይሁናችሁ ። እንዲያማ ከሆነ ካላመኑ ጋር አትተባበሩ የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር አፈረሳችሁ ።

ነገር ግን ባለማወቅ ወይም ባለመጠንቀቅ አንተን ወይም አንቺን ለማግኘት ብቻ ክርስቲያን ነኝ ካለች ወይም ካለው ጋር በዚህ ዓይነት ጋብቻ ተሳስራችሁ ከዚያ በኋላም ኑሮአችሁና ትዳራችሁ የምድር ላይ ገሃነም ሆኖ እንደሆነ እንኳ እንዲህ ያለውን መተባበር ልታፈርሱትና ልትሰብሩት እንደማትችሉ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያስተምራል ። ነገር ግን ራስህን በማዋረድ ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርበህ መተላለፍህንና በደልህን ብትናዘዝና ብታዝን ያገባሃት ገባዖናዊት በጸሎት ወደ እርሱ እንድትቀርብ የምታደርግህ ታላቅ በረከት እንደምታመጣልህ የእግዚአብሔር ቃል ይነግርሃል ። ለኢየሱስ ባለህ የፍቅር መሠዊያ ላይ ያለው እሳት የበለጠውን ይነዳል ያበራል አያቋርጥምም ። በአንተ በኩልም ብዙ ነፍሳት እንዲድኑ ይደረጋል ።

ይህ ነገር በዮሐንስ ዊስሊ ደርሶአል ፤ ከዚያም ወዲህ በብዙ ሴቶችና ወንዶች ደርሶአል ። ለእነርሱ መርገም የመሰለውን ፣ ሊላቀቁት የማይቻል ስሕተት የመሰላቸውን ፣ ለእውነት የሚያደርጉትንም ምስክርነት የሚያፈርሱ የመሰሉት እነዚህ ስሕተቶች ብርቱ ጸሎተኞችና እርሱም የተቀደሱ እንዲያደርጋቸው እግዚአብሔር የሠራባቸው መሣሪያዎች ሆኑ ። እግዚአብሔር እርጉሙን ወደ በረከት ለወጠው ።

አ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ጥልቅ ምሥጢር አ፣ ተወዳዳሪ የሌለው የክርስቶስ ጸጋ ከስሕተታችን ከውድቀታችንና ከኃጢአታችንም ሁሉ ጋር ወስዶን እነዚህን ሁሉ ለክብሩና ለምስጋናው የሚለውጥ የእግዚአብሔር ጥበብና ሥራ ግሩም ድንቅ ነው። እርሱ አተኩሮ አየን፣ እኛም አየነውና እንዲህ አልን «ጌታ ሆይ፣ ስለበደልኩህ አዝናለሁ፣ ነገር ግን ጌታዬ ሆይ፣ ደጎብያ (ቅንቅን) የበላቸውን ዓመታት ልታ ድስ እንደምትችል አምናለሁ። ዲያብሎስ ወደ ታች ጎትቶ እዚያም ጨቁኖ እንዳይዘኝ እምቢ እለዋለሁ። ከኋላዬ ያሉትን ነገሮች እየተውኩ በፊቴ ወዳሉት ነገሮች አጥብቄ እያለሁ እሮጣለሁ።»

የተሳሳትሁትንና የበደልኩትን በደል፣ የሠራሁትን ኃጢአት፣ ያደረግሁትን ክፋትና ግፍ ማስታወስ እየተመላለሰ ነፍሴን ቢወተውታት እንኳ፣ ለንጽህና፣ ለይቅ ርታና ለኃይል በየቀኑ ወደ መስቀሉ እንደሚነዱኝ ገብቶኛል። አንድ ጊዜ በኃጢ አት ገመድ የፍጥኝ የታሠረ ጎስቋላ ኃጢአተኛ፣ ያ የሠራው ኃጢአት አሁን ለጌታው ወደ ተቀደሰ አገልግሎት የወሰደው ከሁሉ የበለጠ በረከት እንደነበረ ይገነዘባል። እንዴት ያለ ግሩም ድንቅ አዳኝ አለን።

ምዕራፍ ፲፪ ።

# የማያቋርጥ ድል ።

ኢያሱ ፲ ፣ ፳፰ ።

«እንዲህም ሆነ ፣ የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒጼዴቅ ኢያሱ ጋይን እንደ ያዘ ፈጽሞም እንዳጠፋት ፣ በኢያሪኮና በንጉሥዋም ያደረገውን እንዲሁ በጋይና በንጉሥዋ እንዳደረገ ፣ የገባዖንም ሰዎች ከእስራኤል ጋር ሰላም እንዳደረጉ በመካከላቸውም እንደሆኑ በሰማ ጊዜ ፣ ገባዖን ከመንግሥታት ከተሞች እንደ አንዲቱ ታላቅ ከተማ ስለ ሆነች ፣ ከጋይም ስለ በለጠች ፣ ሰዎችዋም ሁሉ ኃያላን ስለ ነበሩ ፣ እጅግ ፈራ ። ስለዚህም የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒጼዴቅ ወደ ኬብሮን ንጉሥ ወደ ሆሃም ፣ ወደ የርሙት ንጉሥም ወደ ፒርአም ፣ ወደ ለኪሶ ንጉሥም ወደ ያፊዓ ፣ ወደ አዶላም ንጉሥም ወደ ዳቤር ልኮ ፡— ወደ እኔ ውጡ ፣ ከኢያሱና ከእስራኤልም ልጆች ጋር ሰላም አድርገዋልና ገባዖንን ለመምታት አግዙኝ አለ ። አምስቱም የአሞራውያን ነገሥታት ፣ የኢየሩሳሌም ንጉሥ ፣ የኬብሮን ንጉሥ ፣ የርሙት ንጉሥ ፣ የለኪሶ ንጉሥ ፣ የአዶላም ንጉሥ ፣ ከሠራዊቶቻቸው ሁሉ ጋር ተሰብስበው ወጡ ፣ ከገባዖንም ጋር ሊጋጠሙ ከበቡአት ።

የገባዖንም ሰዎች ኢያሱ ወደ ሰፈረበት ወደ ጌልገላ ልከው በሪያዎችህን ለመርዳት እጅህን አትመልስ ፤ በተራራማው አገር የሚኖሩ የአሞራውያን ነገሥታት ሁሉ ተሰብስበውብናልና ፈጥነህ ወደ እኛ ውጣ አድነንም እርዳንም አሉት ። ኢያሱም ከእርሱም ጋር የነበሩ ሰልፈኞች ሁሉ ጽኑዓን ኃያላኑም ሁሉ ከጌልገላ ወጡ ። እግዚአብሔርም ኢያሱን በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼአቸዋለሁና አትፍራቸው ። ከእነርሱም አንድ ሰው የሚቋቋምህ የለም አለው ። ኢያሱም ከጌልገላ ሌሊቱን ሁሉ ገሥግሶ በድንገት መጣባቸው ። እግዚአብሔርም በእስራኤል ፊት አስደነገጣቸው ፤ በገባዖንም ታላቅ መምታት መታቸው ፣ በቤትሆሮንም አቀበት በመንገድ አሳደዳቸው ፣ እስከ ዓዜቃና እስከ መቄዳ ድረስ መታቸው ። ከእስራኤልም ልጆች ፊት እየሸሹ በቤትሆሮን ቁልቁለት ሲወርዱ ፣ ወደ ዓዜቃ እስኪደርሱ ድረስ እግዚአብሔር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸውና ሞቱ ፣ የእስራኤል ልጆች በሰይፍ ከገደሉአቸው ይልቅ በበረዶ ድንጋይ የሞቱት በለጡ ።

እግዚአብሔርም በእስራኤል ልጆች እጅ አሞራውያንን አሳልፎ በሰጠ ቀን ኢያሱ እግዚአብሔርን ተናገረ ፣ በእስራኤልም ፊት እንዲህ አለ ፣ በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቆም ፣ በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ ፣ ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ ፣ ጨረቃም ዘገየ ። ይህስ በያሻር መጽሐፍ የተጻፈ አይደለምን ? ፀሐይም በሰማይ መካከል ዘገየ ፣ አንድ ቀንም ሙሉ ያህል ለመግባት አልቸኰለም ። እግዚአብሔር ለእስራኤል ይዋጋ ነበርና እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ ቀን ከዚያም በፊት ከዚያም በኋላ አልነበረም ።

ኢያሱም ከእርሱም ጋር እስራኤል ሁሉ ወደ ሰፈራቸው ወደ ጌልገላ ተመ ለሱ ።

እነዚህም አምስት ነገሥታት ሸሽተው በመቄዳ ዋሻ ተሸሸጉ። ለኢያሱም አምስቱ ነገሥታት በመቄዳ ዋሻ ተሸሽገው ተገኙ ብለው ነገሩት ። ኢያሱም እንዲህ አለ፤ ወደ ዋሻው አፍ ታላላቅ ድንጋይ አንከባልላችሁ ይጠብቁአቸው ዘንድ ሰዎችን በዚያ አኑሩ፤ እናንተ ግን አትዘግዩ፤ ጠላቶቻችሁንም አባርሩአቸው፤ በኋላም ያሉ ትን ግደሉ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር በእጃችሁ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋልና ወደ ከተሞቻቸው እንዳይገቡ ከልክሉአቸው አለ። እስኪጠፉም ድረስ ኢያሱና የእስራ ኤል ልጆች በታላቅ መምታት መምታታቸውን በፈጸሙ ጊዜ፤ ከእነርሱም ያመለ ጡት ወደ ተመሸገ ከተማ በገቡ ጊዜ፤ ሕዝቡ ሁሉ ኢያሱ ወደ ሰፈረበት ወደ መቄዳ በደህና ተመለሱ፤ በእስራኤል ልጆች ላይ ምላሱን ማንቀሳቀስ የደፈረ ማንም ሰው የለም ።

ኢያሱም፤ የዋሻውን አፍ ክፈቱ፤ እነዚያንም አምስት ነገሥታት ከዋሻው ወደ እኔ አውጡአቸው አለ። እንዲህም አደረጉ፤ አምስቱንም ነገሥታት፤ የኢየሩሳሌ ምን ንጉሥ የኬብሮንንም ንጉሥ፤ የየርሙትንም ንጉሥ፤ የለኪሶንም ንጉሥ፤ የኤዶ ላምንም ንጉሥ፤ ከዋሻው ወደ እርሱ አወጡአቸው። እነዚያንም ነገሥታት ወደ ኢያሱ በወጡአቸው ጊዜ ኢያሱ የእስራኤልን ሰዎች ሁሉ ጠራ፤ ከእርሱም ጋር የሄዱትን የሰልፈኞች አለቆች ፡— ቅረቡ፤ በእነዚህም ነገሥታት አንገት ላይ እግራች ሁን አኑሩ አላቸው። ቀረቡም በአንገታቸውም ላይ እግራቸውን አኖሩ። ኢያ ሱም ፡— እግዚአብሔር በምትወጉአቸው በጠላቶቻችሁ ሁሉ ላይ እንዲሁ ያደርጋልና አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤ ጽኑ፤ አይዞአችሁ አላቸው። ከዚህም በኋላ መትተው ገደሉአቸው፤ በአምስቱም ዛፎች ላይ ሰቀሉአቸው ፤ እስከ ማታም ድረስ በዛፎቹ ተሰቅለው ቆዩ ።» ኢያሱ ፲፡፩—፳፮።

እውነትን አዝሎ ሳለ ውሸት የመሰለ እንግዳ ነገር ቢሆንም የተሟላ ርስተ በረ ከት ያለው መንፈሳዊ ኑሮ የከበድ ውጊያ ጦር ሜዳ መሆኑ ዘላለማዊ እውነት ነው ። መጀመሪያ ውጊያና ማሸነፍን መማር አለብን። በኋላም ከሙታን በተነሣው ጌታ ርስታችንን መከፈልና መውረስ እንማራለን ።

ወደ ምድረ ከነዓን መግባትን ወደ ምድረ በረከት ከመግባት ጋር በማስተባበር ተምረናል ። አገሪቱም የተሸነፈችው ሦስት መልክ ባላቸው ዘመቻዎች መሆኑን አስገነዘብኩአችሁ ። በመጀመሪያ ኢያሱና ሠራዊቱ የተቃዋሚዎቹን የጦር ኃይል በሁለት በመከፈል ያዳከሙአቸው የግምበር ዘመቻ ነበር ። ሁለተኛው በደቡብ በኩል የነበረውን የጠላት ጦር ያሸነፈበት የደቡብ ዘመቻ ነው ። ሦስተኛ ዓላማውና ጦርነቱ ሁሉ ፍጻሜ ያገኘበት ወደ ሰሜን የተደረገው ዘመቻ ነው ። ይህ ሁሉ በጥሩ አቅድና የጦር ስልት የተወጠነ መሆኑን አስተውል ። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጆች የሚዋጋበት የማጥቂያ ዘዴዎች በጥንቃቄና በታላቅ ጥበብ የተወጠኑ ናቸው ። ለዚ ህም ዓይነተኛው ምሳሌ በምድረ በዳ በጌታችን ላይ ያደረገው የማወናበድ ተንኰል

ነው ። ሰይጣንን የምንቃወምበት የራሳችን የጦር ስልት በጥበብና በማስተዋል የታቀደ አይደለም ። የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎቻችንም ማመንታት ፥ ማወላወልና ግልፍተኝነት ናቸው ። እነዚህም በመሸነፋችንና በታላቅ ጸጸት ተውጠው ያልቃሉ ።

በመካከለኛው ማለት በግምባሩዊው ዘመቻ ጊዜ ከበደቹ ውጊያዎች በኢያሪኮና በጋይ ነበሩ ። በደቡቡ ጊዜ ገባዖንና ቤትሆሮን ነበሩ ፤ (ኢያሱ ፲) በሰሜናዊ ዘመቻ ጊዜ በማራን ውኃዎች ነበሩ ። (ኢያሱ ፲፩) ምናልባት ሌሎች ብዙዎች ውጊያዎችም ሳይደረጉ አልቀሩም ። የጠቀስኩአቸው ግን የሦስቱ ዘመቻዎች ፍሬ ነገር ናቸው ።

በክርስቲያን ኑሮ ውስጥ በአንድ ትግል መሸነፍ ለሁልጊዜ ድል መሆንን የሚገልጽ እንዳልነበረ አስታውቄሃለሁ ። ነገር ግን አጨራጣሪና አደገኛ በሆኑ ጠባብ ስፍራዎችና ጊዜዎች የምናደርገውና የምንወስደው እርምጃ ለኑሮአችን ሰፊና ከባድ በሆኑ ሁኔታዎች ለምንፈጽመው ሁሉ ማረጋገጫ ነው ።

ኢያሱ በመካከለኛ ከነዓን ያደረገውን የመጀመሪያውን ዘመቻ አየን ። ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶችንም እንደ ተማርን አምናለሁ ። ይኸውም አለመታዘዝና በጸሎት መታከት የማይቀር መሸነፍን እንደሚያመጡ ነው ። መታዘዝ ፥ ትጋትና በጌታ ኢየሱስ መደገፍ የድል ዋስትና ናቸው ። የተወደድክ ወጣቱ ክርስቲያን ሆይ ፥ ለወደፊቱ ሕይወትህ ዓይነተኛ መሣሪያ የሚሆኑህን እነዚህን ትምህርቶች ከመጀመሪያው ተማርና መልክም አጀማመር ይሆኑልሃል ።

አሁን ግን በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አሥር ታሪኩ ወደ ተጻፈበት የኢያሱ ደቡባዊ ዘመቻ እንመለስ ። በዚያም አዲስ ሁኔታዎችና አደጋዎች በሃይማኖት ፥ በትግል ፥ በጭከኔ ፥ ከዓለማውያንም በለመተባበር በደፋር ጦርነት እንደ ተመከቱና በመጨረሻም ድልን እንዳስገኙ እንመለከታለን ።

የዚህን ረጅም ምዕራፍ ታሪክ እስቲ በአጭሩ ልተርክ ። ኢያሱ ከገባዖን ሰዎች ጋር ስላደረገው ኪዳን አምስት የከነዓን ነገሥታት ተሰቀሉ ። ስለዚህ ተባብረው በገባዖን ላይ ዘመቱ ። ገባዖንም ከቃል ኪዳን ጓደኛዋ ከኢያሱ እርዳታ ጠየቀች ። ኢያሱም ድል እንደሚያደርግ እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ ተዝናንቶ ከሰፈሩ ከጌልገላ ተነሣ ። ጠላትንም ወግቶ አሸንፎ አበረራቸው ። ያን ቀን እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ተከፋይ የሆነበት በዓለም ታሪክ ታላላቅ ጦርነቶች ከተባሉት አንዱ ውጊያ ተደረገ ። ውጊያው እስኪያልቅና ድሉ እስኪረጋገጥ ምሽትን አዘገየና ቀኑን አስረዘመ ። አምስቱም ነገሥታት ተማርከው ታሠሩ ።

ጦርነቱ ሲያልቅ እነዚያን ነገሥታት ከተደበቁበት እንዲያመጡአቸው ኢያሱ የጦር አለቆቹን አዘዘ ። አለቆቹም እግሮቻቸውን በነገሥታቱ ጠላቶቻቸው አንገት ላይ እንዲያቆሙ ተናገራቸው ። ይህ አደራረግ ጠላት ለሆነ ንጉሥ በጣም የከበደ ውርደት ነው ። ኢያሱም ሠራዊቱን ሲያይ በልቡ እሳት የነደደ መሰለ ። «ኢያሱም እግዚአብሔር በምትወጉአቸው በጠላቶቻችሁ ሁሉ ላይ እንዲሁ ያደርጋልና አትፍሩ ፥ አትደንግጡ ፥ ጽኑ ፥ አይዞአችሁ አላቸው» ኢያሱ ፲ ፥ ፳፭ ። አንዳንድ ሰዎች

ይህን ያህል ማዋረድ ብቻ ይበቃል ይላሉ ፤ ነገር ግን ይህ የማዋረድና የማሳፈር ትዕይንት ኢየሱን አላረካውም ። ስለዚህ አምስቱንም ነገሥታት አረደና እያንዳንዳቸውን በተለያዩ ዛፎች ሰቀላቸው ። ኢየሱ እንዴት ጨካኝ ነው ! ይመስልሃል ?

የዚህ ውጊያ ውጤት በሥዕላዊነት መልክ በቁጥር ሃያ አንድ እንዲህ ይነግረናል ። «በእስራኤል ልጆች ላይ ምላሱን ማንቀሳቀስ የደፈረ ማንም የለም» ከዚያ ቀን ጀምሮ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚፈራ ወገን ሆነው በአገሪቱ ተቋቋሙ ። እንዲህ ያለ ደምሳሽና ጠራጊ ውጊያ ኢያሪኮና ጋይ በእድል የተሸነፉ እንዳልነበሩ ይገልጻል ። እንዲህ ያለ ማሸነፍ እስራኤላውያን ተራ ሕዝብ እንዳልነበሩ ያረጋግጣል ። ይህ ከግብፅ ኃይል የወጣ ፣ በሕረ ኤርትራን በደረቅ መሬት የተሻገረ ፣ ምድረ በዳውን ያቋረጠ ዮርዳኖስን በደረቅ መሬት ተሻግሮ ከሁሉ የምትፈራውንና የማትደፈረውን ኢያሪኮን የማረከ ሕዝብ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ የሚያጸናቸው ኃይል ስለ አለው መፈራት ይገባዋል ።

እግዚአብሔር ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን ያለው ዓላማ የዚሁ ዓይነት መሆኑን አምናለሁ ። የማትደፈር የምትከበርና የምትፈራ ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን ይፈልጋል ። ቤተ ክርስቲያን ስንል ስለ ሕንፃው ብቻ ያሰብን እንደ ሆነ ሰዎች የማይጸጸቱ ፣ ንስሐ የማይገቡና ከክፉ ሥራቸው ፈጽመው የማይመለሱ ከሆነ ወደ ቤቱ መቅረብ የሚፈሩት ስፍራ መሆን አለበት ። ቤተ ክርስቲያን ማለት ግን በመላው ዓለም የሚገኙ ምዕመናን አንድነት ወይም በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ያሉ ማኅበርተኞች ኅብረት ማለት ናት ። በውስጥዋ ያሉ ምዕመናንም በምስክርነታቸው ዓለማውያንና የአፍ ክርስቲያኖች ስሜት አንንካ በማለት የማይመሩ ፣ ትምህርታችንም ከዘመኑ መንፈስ ጋር መስማማትና ጎን ለጎን መራመድ አለበት የማይሉ ፣ በሃይማኖት ደፋሮች በሕይወታቸው የተቀደሱ የሆኑ መሆን አለባቸው ። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ስግደትና ጸሎት በሚደረግበት ጊዜ እግዚአብሔር እዚያ ቆሞ ተገልጾ ቢታይ የምንሰጠውን ክብርና ስግደት ያህል መጠንቀቅ አለብን ።

ለሕንፃዋ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር መንፈስ በእውነት የተወለዱ ልጆቹ ሁሉ ወንዶች ሆኑ ሴቶችም እንዲፈሩትና እንዲያከብሩት የእግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ ነው ። ክርስቲያን ማለት በኑሮው ጻድቅ ፣ በአንዋኑዋሩ ሥርዓት ከጊዜውና ከአካባቢው መንፈስ ጋር የማይተባበር ፣ ለጌታው በሚኖረው የተቀደሰ ኑሮ የሚግል ፣ የመሥዋዕትነት ተግባር የሚፈጽምና አንዋኑዋሩ ለማንም ግልጽ የሆነ ሰው ነው ። ሌሎች ክርስቲያኖች ባሉበት ቢሠራ የሚያፍርበት ፣ ለብቻው ሲሆን ግን የሚፈነድቅበትና የሚረክስበት ከመጋረጃ በስተውስጥ የሆነ ሌላ የኑሮ ምሥጢር የለውም ። ክፉም ሆነ ደግ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በሚደርሱበት ሁኔታዎች አንዋኑዋሩ በቅርብና በጥልቅ የተመሠረተ ፣ የተፈተነና የነጠረ ስለሆነ በእነዚህ ሳይጎዳ ሁል ጊዜ የተቀደሰ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ ከማቅለጫው ኩስኩስት ይወጣል ።

ይህ የእግዚአብሔር ዓላማ ከሆነ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ደምም የተገኘው ደኅንነት በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን መሠረት ይህ መሆኑን ለሚጠይቀኝ የምመልሰው

ይህ በየራሳችንና በቤተ ክርስቲያናችን እንዴት አድርጎ ይፈጸማል ብለን እራሳችንን እንጠይቅ። የእግዚአብሔር ፍርሃትና ክብር ምነው በሰባኪውና በአድማጮች ልብ በሆነ። ሰዎችም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ ስፍራ ስለ ሰማይና ስለ እግዚአብሔር የሚነግራቸው ነገር በኖረው።

እንዴት እናገኘዋለን ? በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ ኢያሱ ከልተነካና ጦርነቱን ከልተቆራቆሰ ማጥቃትም ከልጀመረ አንዳች ጦርነት እንደማይደረግ አስተውል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገሃነም ደጆች ቤተ ክርስቲያኔን አይችሉአትም ብሎአል። የገሃነም ደጆች ሳይታሰብ በድንገት ተነድለው በዚህ ዓለም ወደ ሕዝቤና ቤተ ክርስቲያኔ ይዘምታሉ ያለበት ጊዜ እንደሌለ አስተውል። እርሱ ያለው ይህ ነው ፣ በመንፈስ የተሞሉ ሕዝቤ ወደ እርስዋ ዘምተው የሚወጉአትን ውጊያ ፣ የሚመቱአትን አመታት ፣ የሚጥሉበትን አደጋና ወረራ የገሃነም ደጆች አይችሉአትም። በእግዚአብሔር ቃል ባውዛ ብናይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ዘወትር ወራሪዎችና አጥቂዎች እንዲሆኑ እንጂ አወላዋዮችና ተከላካዮች እንዲሆኑ ምኞቱ አይደለም። ብዙ ጊዜ እናመነታለን ፣ እናፈገፍጋለን ፣ እንሸሻለን ፣ ከዲያብሎስም እንሸሸጋለን ፣ ይህን በማድረግ ፋንታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና ኃይል የተባበረ ሰፊ አደጋ እንጣልበት።

ስለዚህ አሸናፊ እምነት ጥያቄ እንዳለን መልሱን የምናገኘው እነዚያ አምስት ነገሥታት ወደ ቤትሆሮን ያደረጉትን ሽሽት በመመርመር ነው። ስለ ሦስት ሁኔታዎች ደህና አድርገህ እንድትገነዘባቸው እጠይቅሃለሁ።

በመጀመሪያ ይህ ምዕራፍ በአሥራ ሰባተኛው ቁጥር በዋሻ እንደተደበቁ ይነግረናል። እንዴት እንደተደበቁ ራሳችንን እንጠይቅ። ኃያል ሠራዊትና ብርቱ ሥልጣን ነበሩአቸው ፣ ታዲያ ኢያሱ ምን ቢያደርግ ነው ፈርተውት እንዲደበቁ የተገደዱት ? መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አሥርን በሞላ ለማንበብ ጥቂት ጊዜ ማሳለፍ ፈቃድህ ቢሆን አንዲት ቃል አምስት ጊዜ ተጠቅሳ ታገኛታለህ ፣ ያች ቃል የማሸነፍ ቁልፍ መክፈቻ ናት ፣ እርስዋ «ጌልገላ» ናት።

ኢያሱ ጠላትን ለመግጠም ከጌልገላ ወጣ ፤ በውጊያው መካከል ጦርነቱ በረድ ሲል ወደ ጌልገላ ሄደ ፣ ድሉ ሲረጋገጥ ወደ ጌልገላ ተመለሰ። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በዘመቻዎቹ ሁሉ ከጌልገላ ጋር ክፍት የሆነ ግንኙነት ነበረው። የጌልገላን ትምህርቶች እኛም እንደተረዳን እተማመናለሁ።

ሥራቸውና ግንዳቸው በጌልገላ የተተከሉትን የሐዲስ ኪዳንን የእውነትና የደኅንነት ታላላቅ ቃላት ላስታውስህ። እነዚህ ናቸው ፣ ማስታወስህን አድስ። ጌልገላ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ወደ ሞት የወረዱበት የመታሰቢያ ስፍራ ነበረ። ከመሪአቸው ጋር ወደ አዲስና የተሻለ የኑሮ ደረጃ የተሸገሩበት የትንሣኤ ስፍራ ነበረ። የምድረ በዳን የሥጋዊ ልማድና አንዋኑዋር የተላቀቁበት የመተው ወይም የማስወገጃ ስፍራ ነበረ። ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ወደ ኅብረት ፣ አንድነትና ስምምነት

የመጡበት የማደሽ ስፍራ ነበር። የአገሪቱ ጣፋጭና ጉልበት ሰጪ ጠንካራ ምግብ የቀመሱበት የመገናዘቢያ ስፍራ ነበረ። የተመዘዘ ሰይፍ የያዘ የጦር አለቃቸውን ያዩበት የገለጻ ስፍራ ነበረ።

የክርስቲያን ሕይወት ሥርና ግንዶች በቀራንዮ ተተክለዋል። እዚያ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ሞትንና ከሙታን ተነሣን፣ እዚያም ሥጋዊነትንና ዓለማዊነትን ክደንና አስወግደን ከጌታ ጋር አንድነትን፣ ኅብረትንና ስምምነትን አገኘን፣ እዚያም የቃሉን ጣፋጭ ጉልበት ተካፈልንና ጠንካራ ምግብ መመገብ ጀመርን፤ እዚያም የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ በየደቂቃው ከእኛ ጋር መሆኑን ተገነዘብንና እርሱም ተገለጸልን።

ጌልገላ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻ የተያዘችና በኋላ የምትለቀቅ ስፍራ አይደለችም። ዳሩ ግን በውጊያዎቹ ሁሉ የማያቋርጥ ሰፈርና መሠረታቸው ነበረች። ስለዚህ ቤትሖሮን ለተደረገው የጠረጋ ውጊያና የተረጋገጠ ድል ምሥጢር የሆነች ይህች የማትለቀቅ ሰፈር ነበረች።

ዛሬ በአንተ ሕይወትና በሰማይ ዙፋን መካከል ክፍት የሆነ መገናኛና ግንኙነት አለ ወይ ? ይህ እስኪኖርህ ድረስ ከቶ ድል አታደርግም። በጌታችን ዓይን ውስጥ ቀና ብለህ ብትመለከት ፈገግታውን የሚያሳይህ ይመስልሃልን ? ምናልበት ራስህን ለክርስቶስ መስጠት ለአንድ ጊዜ ብቻ ተደርጎ የተፈጸመ ሥራ ይመስልህ ይሆናል። ሥራ አለመሆኑን ልንገርህ። ነገር ግን የማይለቀቅ የማይለወጥ ዘላለማዊ የሆነ የልቡናህ ዝንባሌ ሁኔታ ነው። የኃይል ምሥጢርም በእርሱ ነው።

ሁለተኛ፣ ነገሥታቱ በጣም እንደ ተዋረዱ አስተውል፤ ቁጥር ሃያ አራት አምስቱ ነገሥታት በመሬት ተዘርረው ሲጋደሙ ኢያሱ ከጦሩ አለቆች አምስት ሰዎች በእያንዳንዱ ንጉሥ አንገት ላይ እግሮቻቸውን እንዲያኖሩ አዘዘ። በሕዝብ ፊት ለምን ይህን ያህል ይዋረዳሉ ? ለምን እንደሆነ ልንገርህ፣ ድሉን ያደረገው እግዚአብሔር መሆኑን የእስራኤል ሠራዊት ሁሉ እንዲረዱ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ዓይን ፊት ተዋረዱ። «እግዚአብሔር በጠላቶቻችሁ ሁሉ እንዲሁ ያደርጋል»

የተወደዳችሁ ወዳጆቼ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናንተና ለእኔ በቀራንዮ ተዋግቶ አሸነፈ። በነፃ አውጪውና ፈዋሽ የክርስቶስ ደም ሥልጣን ሥር የማይደረግ የሕይወትህ ክፍል ሥር የሰደደ ኃጢአት ወይም ፀመል የለህም። የክርስቶስ ማዳን ለአንተ በቂና የተሟላ ነው። ወዳጆቼ ሆይ፣ ጌታ እግዚአብሔር ራሱ ተዋግቶላችኋል፣ ደግሞም አመስግኑት ድል ነስቶአል።

እግዚአብሔር ድል እንዳደረገላቸው እንዲያውቁ ብቻም አልነበረም። እበክህን ይህን በጥንቃቄ ተመልከት፣ እግዚአብሔር ያደረገላቸው ድል ልክ የራሳቸው ማሸነፍ መሆኑን እንዲረዱ ሊያሳያቸው ነው። «እግዚአብሔር በምትወጉአቸው በጠላቶቻችሁ ሁሉ ላይ እንዲሁ ያደርጋል»

«ነገር ግን የክርስቲያን ሕይወት የውጊያ ኑሮ አይደለም፥ የሃይማኖት አንዋኑዋር ነው» ትለኝ ይሆናል። እውነትክን ነው ወይ? ለክርስቶስ ራስን መስጠት ብቻ በቂ አይደለም። ለክርስቶስ ጌትነትና የበላይነት መቀደስ ብቻ በቂ አይደለም። በሕይወትህ ውስጥ ያለውንና ኃጢአት መሆኑን በምታውቀው ሁሉ ላይ ጦርነት ካላደረግህ በክርስቶስ ስም ድል ልታደርግ ከቶ አትችልም። እግርህና እግሬ በቅንዓት፥ በትዕቢት፥ በኩራት፥ በክርክር መንፈስና በቁጣ አንገት ላይ ስለ ተደረጉ ደስ ይበልህ። የክርስቲያን ምስክርነታችንን በሚያሰናክለው ነገር ሁሉ አንገት ላይ እግሮቻችንን ስለ አኖርን እንዝናና።

የሕይወቴ ዘመን እስኪያልቅ ድረስ የማደርገውን እያንዳንዱን መሻሻል ዲያብሎስ በሙሉ ኃይሉ ይቃወማል። በኃጢአት ላይም ዘመቻ ቀስቃሽ ካልሆንሁና ውጊያውን ካልጀመርኩ የኢየሱስ ክርስቶስን የአሸናፊነት ኃይል በኑሮዬ ላገኘው አልችልም። በእግዚአብሔር ስም ልጠይቅህ፥ በሁሉም ግምባር ትዋጋለህን? በጌታ ኢየሱስ ስም ልትወጋና ልታሸንፍ በኩራት፥ በትዕቢት፥ በአንተ በራስህ፥ በመጥፎ አነጋገርህ፥ በክርክር በትችት ላይ ጦርነት በመቆራቆስ ራስህን ከሌሎች ለይተህ አስታውቀሃልን? የማያቋርጥ አቋምና የምትቀበለው ድል አለልህ።

ሦስተኛ፥ ስለዚህ ታሪክ ላሳስብህ የምፈልገው ነገር አለ፥ ይኸውም ፍች የሌለውን የአምስቱን ነገሥታት ሬሳ በአምስት የተለያዩ ዛፎች መሰቀል ነው። ይህ የጭካኔ ሥራ አይደለምን? ያልታደሉ ሰዎች መጀመሪያ በዋሻ ተሸሸጉ፥ ከዚያ ታድነው ተይዘው መጡና በመሬት ተዘርረው እንዲተኙና የኢያሱ የጦር አለቆች እግሮቻቸውን በአንገቶቻቸው እንዲያኖሩ ተደረገ፤ ለአንድ ቀን ይህ ብቻ ይበቃ አልነበረምን? ወደ ዋሻቸው መልሰውአቸው እዚያ ቢቆዩ ይሻላቸዋል። ግን ከዚያ ወጥተው እንደገና እንዳይወጉአቸው ያሰጋሉ። ኢያሱ እንዴት ያለ ጨካኝ ሰው ነው!

ከዚህ በፊት ያልኩትን አንድ ነገር አስታውሳለሁ። የእግዚአብሔር ዓላማ ለዚያች ምድር፥ ቤተ ልሔም፥ ቀራንዮና ጴንጠቆስጤ ነበረ። የአገሪቱም ነዋሪዎች ኃጢአት፥ በደል፥ ግፍና ርኩሰት ሞልቶ ተትረፍርፎአል። እግዚአብሔር ለሰው ደኅንነት ድል ባዘጋጀው ጐዳና ውስጥ እንቅፋትና ማሰናከያ ሊሆን ማናቸውም ነገር ሊደቀን አይፈቀድም። ይህን ለማድረግ የደፈረ ወይም በአደራረጉ የሚተባበር ሁሉ ይደመሰሳል።

አምስት ነገሥታት በዋሻ ውስጥ እያደቡ እንዲኖሩ ማድረግ አይገባም፤ መታረድ ይገባቸዋል።

ይህን የቃሉን ዋነኛ እውነት መንፈስ ቅዱስ በልብህ እንዲጽፍልህ ብዙ ጸልዩ አለሁ። ክርስቲያኖች ሆይ፥ አሁን የምነግራችሁ ጽድቅን ነው እንጂ ቅድስናን አይደለም። በእያንዳንዳችን አሮጌው ሰው አለ በራሱ ሊቀደስ የማይቻለው ሥጋ አለ፤ እርሱም በመስቀል ላይ በስቅላት እንዲሞት ተፈርዶበታል። በእያንዳንዳችንም

ሌላ አዲስ ሰው አለ ከራሱም ኃጢአት ሊሠራ አይችልም ፤ እርሱም በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለን ሃይማኖት የተሰጠን ነው ። በክርስቶስ ድል ልደሰት የምች ለው ግን ለቁስሎቹ ለችንካሮችና ራሴንም በመስቀሉ ላይ ለመስቀል ፈቃደኛ ስሆን ብቻ ነው ። ሳይፈረድበትና ሳይገደል በልቤ ዋሻዎች ኃጢአትና ዐመል እያደባ እን ዲኖር መፍቀድ አልደፍርም ።

ይቅር ተብለህ ምሕረትን ያገኘህ ኃጢአተኛ ስለሆንህ ትደሰታለህን ? በኢየሱስ ደም ተሸፍነህ ወደ ሰማይ ስለምትጓዝ ትደሰታለህን ? እኔም እንዲሁ ነኝ ። እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለህ አንተ አሁን ኩነኔ ስለ ሌለብህ ትደሰታለህን ? ስለ እነዚህ ሁሉ ደስ ይልሃል ። የጽዮንንም መዝሙር ትዘምራለህ ። ነገር ግን በስውር የሚኖር ያልተገለጠ የምሥጢር ኃጢአት ፣ ያልተናዘዝኸውና ያልተውከው ፣ በአንተም ያልተ ፈረደበትና ያልተኰነነ ኃጢአት በውስጥህ እያደባ ይኖር ይሆናል ። አንተም ምስክር ነትህ ስለማይሰምር ማስተማርህም ፍሬ ስለሌለው ታደንቃለህ ።

ይህ ለምን ሆነ ? ምናልባት ሰዎችን የሚያማ ፣ የሚተችና የሚወቅስ የሚንቅም ምላስ በውስጥህ ያደባል ። ያልሞተ ምላስ ፣ ወይም ያልተሰቀለ ኩራትና ትዕቢት ፣ ወይም ለእግዚአብሔር ያልተናዘዝከው ክፉ ምኞት ምናልባትም ለራስህ ክብር የሆነ ስስታም ምኞት በልብህ ዋሻ ገና በሕይወቱ እያደባ ይኖራል ። አዎን ይቅር ተብሎ አል ፤ አዎን ፣ ከደሙ ሥር ተደርጎአል ፤ አዎን ፣ ኩነኔ የለም ፣ ለዚህ ሁሉ ሃሌ ሉያ ። ነገር ግን ራስህ በረጅሙ ኑሮህ ልምድ እንዳየኸው እዚያ ዋሻ ውስጥ ያሉ ወደረኞች በየጊዜው ሾልከው እየወጡ ምን እንደሆነ ምንስ እንዳደረግህ ሳታውቅ ትጨክና ለህ ፣ በሌሎች ትፈርዳለህ ፣ ራስህን መግዛት ያቅትሃል ፣ ትቆጣለህ ፣ ትበሳጫለህ ። ሰይጣን ከተሸሸገበት ዋሻው ወጥቶ ጨበጠህ ።

ወደ ድል የሚያደርስ ንጉሣዊ ጐዳና አንድ ብቻ ነው ። ይኸውም የማያቋርጥ አቋም ፣ የምንከፈል ድልና የምናስወግድ አደጋ አለ ። ከመስቀሉ ደም ሥር መጠጊ ያህን አድርግ ። መሸሸጊያህም የክርስቶስ ቁስሎች ይሁኑ ። ከኃጢአት ጎን አትጠጋ ። ነገር ግን በልብህ በሚያደበው አባብ ላይ ጠቅላላ ውጊያ አድርግ ። ያ አባብ እንደ ምን ተደርጎ ይታረዳል ? ኢየሱስ አርዶልሃል ።

ወደ ድል አንዋኑዋር ለመሸገር ቁርጥ ሐሳብ ያደረገ ፣ በሃይማኖት ማጥቃት የጀመረ ክርስቲያን ባለፉት ዘመናትና ጊዜያት ባደረገው በደል ትዝታ ሊጎሰምና ሊከረከም አይፈቅድም ። ነገር ግን ወደ አሸናፊነት አንዋኑዋር አቋም ሊገባ ቆርጦ አል ። እርሱ የሚያደርገው እንዲህ ነው ፤ ወደ በደለው ወይም ወደ በደላት እህት ሄዶ ይቅርታ ይጠይቃል ። በጌታው እግር ሥር ተደፍቶ ታሪኩን ሁሉ ይናዘዛል ፤ ሁሉም በቀራንዮ ስለተፈጸመለት ጌታ ኢየሱስን ያመሰግናል ። በእርጅናው ዘመን እንኳ ቢሆን ስስትን ፣ ንፍገትን ፣ ምላሱን ፣ ሐሜትን ፣ ክርክርን ፣ ወቀሳንና ንቀትን ፣ ሌሎችንም ሁሉ ለማሸነፍ ስለሚችል ክርስቶስን ያመሰግናል ።

ከዚህ በኋላ ምን ያደርጋል ? ዓይኑን አቅንቶ በሃይማኖት በሕያው ጌታው ዓይን ውስጥ እያየ በእምነትም እግሮቹን በጠላቶቹ አንገት ላይ አኑሮ «በምወጋቸው በጠላቶቼ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር እንዲሁ ያደርጋል» ይላል ። ከዚህ በኋላ በሕይወቱ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በሁሉም ግምባር እያጠቃ ወደ ፊት ይገሠግሣል ። እስከ አሁን ያልተፈረደበት ፣ ያልተኰነነ ፣ ያልሞተና በእግዚአብሔር ፊት ያልተናዘዘ ነገሮች በሕይወቱና በነፍሱ እንዳሉ ጠቅላላ ውጊያ ያነሳባቸዋል ።

በመልካም ተጋደል በሙሉ ጉልበትህ
ክርስቶስ ኃይልህ ነው ክርስቶስም ቀኝህ
ሕይወትን ጨብጥ ደግሞም ትሁንልህ
የዘላለም ደስታ ደግሞም አክሊልህ ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

# የድል ፍሬ ።

ኢያሱ ፲፩ ፥ ፳፫ ።

«እግዚአብሔርም ባሪያውን ሙሴን እንዳዘዘው እንዲሁ ሙሴ ኢያሱን አዝዞት ነበር፥ ኢያሱም እንዲሁ አደረገ፥ እግዚአብሔር ሙሴን ካዘዘው ሁሉ ምንም አላስ ቀረም ።

ኢያሱም ያን ምድር ሁሉ ተራራማውን ፥ ደቡቡንም ሁሉ ፥ የጎሰምንም ምድር ሁሉ ፥ ቆላውንም ፥ ዓረባንም ፥ የእስራኤልንም ተራራማውንና ቆላውን ያዘ ፥ እስከ ሴይርም ከሚያወጣው ወና ከሆነው ተራራ ጀምሮ ከአርሞንዔም ተራራ በታች በሊ ባኖስም ሸለቆ ውስጥ እስካለው እስከ በአልጋድ ድረስ ፥ ነገሥታቶቻቸውንም ሁሉ ይዞ መታቸው ፥ ገደላቸውም ። ኢያሱም ብዙ ዘመን ከእነዚህ ነገሥታት ሁሉ ጋር ይዋጋ ነበር ። በገባዖን ከሚኖሩ ከኤዊያውያን በቀር ከእስራኤል ልጆች ጋር ዕርቅ ያደረገች አንዲት ከተማ አልነበረችም ፤ ሁሉን በሰልፍ ያዙ ። እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘ ፥ ያጠፉቸው ዘንድ ሞገስንም እንዳያገኙ ፈጽመውም እንዲያጠፉአቸው ፥ ከእስራኤል ጋር ይጋጠሙ ዘንድ ልባቸውን እንዲያደነድኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነ ።

በዚያን ጊዜም ኢያሱ መጣ ፥ ከተራራማውም አገር ከኬብሮንም ከዳቤርም ከአ ናብም ከእስራኤልም ከተራራማ ሁሉ ከይሁዳም ተራራማ ሁሉ የዔናቅን ልጆች ገደለ ። ኢያሱም ከከተሞቻቸው ጋር ፈጽሞ አጠፋቸው ። በጋዛ በጌትም በአዛጦ ንም ጥቂቶች ቀሩ እንጂ በእስራኤል ልጆች ምድር ከዔናቅ ልጆች ማንም አልቀ ረም ። እግዚአብሔርም ለሙሴ እንደ ነገረው ሁሉ ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ ። ኢያሱም ለእስራኤል እንደ ክፍላቸውና እንደ ነገዳቸው ርስት አድርጎ ምድሪቱን ሰጣቸው ፤ ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች ።» ኢያሱ ፲፩ ፥ ፲፭ — ፳፫ ።

መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አሥራ አንድ በምድረ ከነዓን የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድነት ሆነው መዋጋት ያቋረጠበትን ጊዜ ይነግረናል ። ድሎቻቸው ደምሳሾችና አውዳሚዎች ነበሩ ። ጠላቶችም ምንም እስከ አሁን በምድሪቱ ቢኖሩም እንኳ ተመትተው ተበታትነዋል ። እግዚአብሔርም መላዋን ምድር ለራሱ ሕዝብ ሰጠ ።

ብዙ ገና የሚያዙ ክፍለ ሀገሮች ቀርተዋል ። ነገር ግን ከወንአቸውና ከአበረ ሩአቸው ሕዝቦች የአገኙትን ምድር እያንዳንዱ ነገድ እንዲወርስ ተሰጥቶአል ። እያን ዳንዱ ነገድ ርስቱን ለመውረስ በኅብረት ተዋግቶ በተማረው የጦር ስልት ለየቅሉ መሥራት አለበት ። ሕዝቡም ይህን ለማድረግ አለመቻላቸው የእግዚአብሔርን ኃይል ጉድለት አያሳይም ፤ ነገር ግን ኢያሱ በመከከላቸው ያካፈለውን ሊረከቡና ሊጠብቁት ባለመቻላቸው ነው ።

እጅግ በጣም ጠቃሚ ነገር እንድነግራችሁ ትንሽ ረጋ ልበል (ስንቶቻችሁ ልታስተውሉት እንደምትችሉ አላውቅም) የምንማረው እያንዳንዱ የከበረ እውነት ሁሉ በሃይማኖት በልባችንና በሕይወታችን መሥራት አለበት። አለበለዚያ የምናደርገው ሁሉ ፍሬ ቢስ ይሆናል። ለልባችን የምንቀበላቸው በረከት፣ የመንፈስ ግለትና ሞቅታ ይህን መጽሐፍ ከዘጋን ከአምስት ደቂቃ በኋላ ተረስተው እንዳልነበሩ ይሆናሉ። ከእግዚአብሔር ጋር የሚራመድ መናኝ፣ ጌታውንም ፊት ለፊት እስኪያይ በክርስቶስ አሸናፊነትና ኃይል የሚራመድ ሰው ሁሉ፣ ጸጥ ያለ ስፍራ ይፈልግና እግዚአብሔር እዚያ የሚነግረውን ያሰላስል። ለተቀበለውም እውነት ሁሉ እዚያው ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቀርባል። እግዚአብሔርም በኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያናቱ ሁሉ በማጠቃለል አንድ አካል አድርጎ የሠራላትን እዚያ ሆኖ በግል ሕይወቱ ይቀበላል።

የመስቀሉ ድል ሁሉን ደራሽና ደምሳሽ መሆኑ የማይካድ እውነት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ከዚያ ድል በግል ኑሮው ሊረዳውና ሊያገኘው የሚችለው በሃይማኖት የተቀበለውን ያህል ብቻ ነው። በዚህ ዘመን ለቤተ ክርስቲያኑና ለሕዝቡ ከእርሱ ጋር በአንድ ሐሳብ የሆኑትንና ያለ ጸጋውም በራሳቸውና በሚሠሩት ሁሉ ጎዶሎ መሆናቸውን የተገነዘቡትን ሰዎች እግዚአብሔር ያስነሣልን።

የድል ፍሬ ምን እንደሆነ እንዳሳይህ እፈልጋለሁ። እርሱንም በኢያሱ ፲፩፣ ፳፫ ታገኛለህ። «ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ፤ ኢያሱም ለእስራኤል እንደ ክፍላቸውና እንደ ነገዳቸው ርስት አድርጎ ምድሪቱን ሰጣቸው። ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች» «ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ» ውጊያው ተፈጸመና ድሉ ተረጋገጠ። «ኢያሱም ... ርስት አድርጎ ምድሪቱን ሰጣቸው» ወስደው እንደሆን ወይም አልወሰዱ እንደሆነ በሃይማኖት ወጥተው ሄደው የዕጣ ርስታቸውን መረከብ የሕዝቡ የራሳቸው ፋንታ ነው «ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች»

በአንድ ክርስቲያን ኑሮ ውስጥ የሚደረጉ መጋደሎች ምንጮቻቸው የሚከተሉት ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር በንድ ሐሳብ አለመሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር አለመታረቅና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የሆኑትን ነገሮች በውስጣችን እንዲኖሩ ማድረግ ናቸው። እንዲህ ማድረግ ከሰማይ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መታገልና መዋጋት ነው። አንድ ሰው መታዘዝ ሲጀምር በዚያኑ ጊዜ ከውጊያ ያርፋል።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የነበረውን የድል ፍሬ እስቲ ተመልከት። «ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች» የአንድነት፣ የሽርክናና የመተባበር ሥራ አበቃ። ድል ተገኝቶአል። ይህ የምንናገረው ሁሉ በመጽሐፈ ኢያሱ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ያለውን የሐሳብ የትርጉም ኅብረት ለመግለጽ ያህል ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተሰራጭተው ያሉትንና እያንዳንዱን አምሮት ለማጥገብ የሚችሉትን መግለጫዎች እንከተላለን እንጂ የአፍ ታሪክ ወይም ልብ ወለድ ወሬ የምናጠና አይደለም። ምድረ ከነዓንን መውረር፣ መውጋትና ማሸነፍ በክርስቶስ

ሞት ፥ ትንሣኤና እርገት የሚመስል የብሉይ ኪዳን ታሪክ ነው ። ስለ እርሱም ወደ ዕብራውያን ሰዎች የጻፈው የሚለው እንዲህ ነበር «ኃጢአታችንን በራሱ ከነፃ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» ዕብ. ፩ ፥ ፫ ።

በመላው መጽሐፈ ኢያሱ ምድረ ከነዓን በሐዲስ ኪዳን ትምህርት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ በራሱ የምናገኘው ርስት ምሳሌ መሆኑን እንረዳለን ። ምድሪቱ ለእስራኤል የነበረችውን ሁሉ ክርስቶስ እራሱ ለአንተና ለእኔ ነው ። ምድሪቱም ከውጊያ ዐረፈች ፥ ኢየሱስም በሰማያት በግርማው ቀኝ በከፍታ ተቀመጠ ። ድሉ ተገኝቶአል ። ምድሪቱንም ሁሉ ያዘ ። በዓለምም ሆነ በሰማያት ስፍራዎች እንኳ ቢሆን የመስቀሉ ድል በመጨረሻው ያልገለበጣቸው የዲያብሎስ ግዛቶች የሉም ። በተፈጠረው ጠቅላላ ዓለም (ዩኒቨርስ) ውስጥ በቀራንዮ ምክንያት ክርስቶስ ጌታና ንጉሥ ነው ።

በሚታይና በሚጨበጥ ነገር ብቻ የሚያምኑ (የማቴሪያሊስት) የኰሚኒዝም ግሥጋሴ ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ አንዲት ስንዝር ሊራመድ አይችልም ። እርሱ የሁሉ ጌታ ነው ። የተወደዳችሁ ክርስቲያን ጓደኞቼ ሆይ ፥ በድል ወገን መሆናችሁን ማወቅ እንዴት ያለ ሃሴ ቱያ ለልባችሁ ያመጣ ይሆን ? ኢየሱስ ድል ከደረገ በኋላ ለሚያምን ለእያንዳንዱና ስጦታውንም በሃይማኖት ለመቀበል ለተዘጋጀ የእግዚአብ ሔር ልጅ የመስቀሉን ድል ሊያከፍልና ሊሰጥ ወደ ሰማይ ዐረገ ። «ኃጢአታችንን በራሱ ከነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» ንጉሣዊ ዕረፍት ነው ።

ስለዚህ ስለ ጌታ ኢየሱስ «ዕረፍት» ለጥቂት ጊዜ እንድታስብ እፈልጋለሁ ። ምን ዓይነት ዕረፍት ነው ? በእውነቱ ከድካም የተነሣ የተደረገ ዕረፍት አይደለም ። አንተና እኔ የምንቀመጠው ሲደክመን ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለራሱ አልሰለተም ደግሞም አልፈራም ። የእርሱ አንዋኑዋር የማያቋርጥ ትግል ፥ እንቅልፍ ነሺ ትጋት ፥ የመሪር ኀዘን ፥ የጌቴሰማኒ ጣርና የሰው ኃጢአት ፍዳና ከበድ ሸክም የተሞላ ኑሮ ነበረ ። ነገር ግን ከእነዚህ ነገሮች ያደከመው አንዳች ስንኳ አልነበረም ። የስንፍና የታካችነት ወይም የሥራ ፈትነት ዕረፍትም አይደለም ። ምክንያቱም የማርቆስ ወን ጌል የመጨረሻ ቁጥሮች እንዲህ ይላሉ «እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር» ማር. ፲፮ ፥ ፳ ።

የእርሱ ዕረፍት የመርካት ፥ የማሟላትና የመጥገብ ዕረፍት ነው ። ዙፋኑን ትቶ ፥ ክብሩን አውልቆ አስቀምጦ ራሱን ስለ ኃጢአታችን መሥዋዕት አድርጎ በማ ቅረብ ኃጢአትን አልደመሰሰምን ? «ተፈጸመ» ብሎ አልጮኸምን ? አሁንም ክቡር ጌታችን ከድካም ወይም ከሥራ ፈትነት ሳይሆን በቀራንዮ በፈጸመው ሥራ መንፈ ሱና ልቡናው ረክቶ የመሟላት ዕረፍት አርፎአል ። የመስቀሉ ፍሬ የሚሰበሰብበትን ያን ቀን እየተጠባበቀ በሰላምና በጸጥታ የተረጋገጠ ዕረፍት ያደርጋል ። በተፈጸመው የደኅንነታችን ሥራ ላይ አንዳች ነገር መጨመር ከቶ አይቻልም ። የመስቀሉ መሥ ዋዕት ለዓለም ደኅንነት ፍጹም በቂ መሆኑን ስላረጋገጠ ጌታችን በሰማያዊ ስፍራ ተቀመጠ ። ዕብራውያን ፲ ፥ ፲፪ እንዲህ ይላል «እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን

መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፤» እግዚአብሔር ለጽድቅ የሚጠይቃቸው ነገሮች ሁሉ እርሱ በሚፈልገው ዓይነት ተሟልተው ተፈጸሙ። እግዚአብሔር ለኃጢአት ፍርድ የመዘዘው ሰይፍ ወደ አፎቱ ተከተተ። እንግዲህ ዛሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑና ለሚከተሉ አሁን ኩነኔ የለባቸውም። የኃጢአታችን ዕዳ የተከፈለው አሁንም የሚከፈለው በምግባራችን ወይም በቅዱሳን ሰማዕታትና መላእክት በኩል አይደለም። ክርስቶስ አንድ ጊዜ አሟልቶ ከፍሎአል።

የመድኃኒታችን ዕረፍት የሰላምና የጸጥታ ዕረፍት የትክክለኛ ሚዛን ዕረፍት፣ የተከናወነና የተፈጸመው በቂና አጥጋቢ ስለሆነ የማረጋገጫ ዕረፍት፣ የመርካት ዕረፍትና የተፈጸመ ሥራ ዕረፍት ነው። ለእያንዳንዱ ሰው የነፍስ ደኅንነት የሚያስፈልገው ሁሉ ተደርጎ ተፈጽሞአል። የሚጨመርበት፣ ወይም እንድንቀበለውም የሚፈለግብን ችሮታ የለም፤ ስለዚህ ጌታችን በዕረፍት ተቀመጠ።

ጌታችን ኢየሱስ አሁን በተቀመጠበት ስፍራ ሆኖ ተፈጥሮአችንን እንደሚሸከም መገንዘብ አለብን። ወዳጆቹ ለሆኑ የሰው ልጆች ሲል እንደ ሰው ሆኖ እዚያ ተቀምጦአል። እኔና አንተም በእርሱ ሆነን ከእርሱ ጋር ያንን ዕረፍት እንድንከፈል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ለኤፌሶን ሰዎች በምዕራፍ ፪፣፮ ሲጽፍ የሐዋርያው ጳውሎስ ሐሳብ ይህ ነበረ «ከእርሱም ጋር አስነሣን፣ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።»

የተወደዳችሁ ክርስቲያን ወዳጆቼ ሆይ፣ የደኅንነታችን ዓላማና ፍሬ ነገር የሆነ የክርስቲያን ኑሮ ደስታና የልብ ተመስጦ፣ በሞቱ በትንሣኤውና በዕርገቱ «ከክርስቶስ ጋር» መሆናችን እንደሆነ እንድትረዱ እፈልጋለሁ። ስለዚህ አንተና እኔ በየቀኑ ኑሮአችን አቋም ወደዚያ ዕረፍት እንድንገባ ኢየሱስ ይመኝልናል። ለክርስቶስ ያደረግነው የድል ፍሬ ዕረፍት ነው። ከክርስቶስ ጋር ያንን ድል የመከፈላችን ጥቅም አንድ ነው፤ እርሱም ዕረፍት ነው።

ዛሬ ያ ዕረፍት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ምን ውጤት ወይም ስሜት አለው? ሁልጊዜ እንደጋልህ ብትሮጥ ከሥራህ ፍሬ ልታገኝ አትችልም። እንደ ፈለገው በሚፈቅደው ዓይነት እንደገና ፈጭቶ አቡክቶና ጠፍጥፎ እንዲሠራን በእርሱ ኃይል ማረፍ እስከንማር ድረስ ትኩሳቱና ሞቅታው፣ ጥድፊያውና ትካዜው፣ መርበድበዱና ግልፍተኝነት በክርስቶስ ዕረፍት እስኪዋጡ ድረስ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሚገባ ሊሠራና ፍሬ ሊሰጥ አይችልም።

ከአንድ ወይም ሁለት ዓመት በፊት አንዱን ወዳጄን በለንደን ያለውን የቅዱስ ጳውሎስን ካቴድራል አስጎበኘሁ ነበር። ያስደነቀኝ ነገር ተፈጠረ። ወዳጄ ወደ ካቴድራሉ ሕንፃ ጉልላት ወይም ሞገስ ሊወጣ ፈለገ፣ እስከ ጉልላቱም አራት መቶ ደረጃዎች ነበሩ። ሰውየው ደግ ክርስቲያንና የኢንተርናሽናል የእግር ኳስ ተጫዋች ነው። እርሱም የውፉሬን ጉዳት አስረዳኝ። በእውነቱ እኔ ገና ከደረጃዎቹ እኩሌታ ላይ ስደርስ እርሱ አራቱን መቶ ደረጃዎች ፈጽሞ በጉልላቱ ጫፍ ላይ ነበረ። እኔም

ቁና ቁና እየተነፈስኩና እየፈራሁ እርሱ ወዳለበት የታላቁ ካቴድራል ጉልላት ላይ ስደርስ ብሩህ የሆነ የጥቢ ወራት እኩለ ቀን ይመስላል ። እንደዚህ ያሉ ቀኖች በለን ደን አንዳንድ ጊዜ ብቻ ይደርሳሉ ። ጀምበርዋም ደመና ከሌለበት ሰማያዊ ጠፈር ከጉልላቱ ላይ በቆመው መስቀል ላይ ታበራለች ። ወደ ላይ ስናይ ያ መስቀል በብ ሩሁ ሰማይ ወርቃማ ቀለሙ ያብረቀርቃል ። ወደ ታች ስንመለከት አንዳች ነገር አይታይም ። ለንደን በጉም ፣ በጭጋግ ፣ በጭስና በአዋራ ውስጥ ተደብቃለች ። በእኔ ግምት ይህ የክርስቲያን ሕይወት ምሳሌ ነው ። በየቀኑ ሕይወታችን ከዘወትሩ አዋራ ፣ ጭጋግና ትግል አስወጥቶን ወደ እግዚአብሔር ሰማያዊ ፍቅርና የክርስቶስ ዕረፍት ከፍ ሊያደርገን በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው ። እኔና አንተ በዚህ ፍቅርና ዕረፍት እንደሰት እንደሆነ ይገርመኛል ።

ያረፈ ክርስቲያን ማለት ሕይወቱን ከክርስቶስ ጋር ከማዕበል በላይ ከፍ ካለ ስፍራ የሚያኖር ነው ። የሌሎች ኀዘንና ችግር ይሰማዋል ። ሁልጊዜም የእግዚአብ ሔርን ጥበብ ሊያይ ይችላል ። የአፍቃሪውን እግዚአብሔር ልብ ስለሚተማመን በትግሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ እስኪገለጥለት ድረስ በትዕግሥት ይጠ ብቃል ። ከዘወትር ችግርና ሁከት በላይ የሚኖርና ከሰማይ ዙፋን የማያቋርጥ ግንኙ ነት ያለው ክርስቲያን በኢየሱስ አርፎአል ። ከሥራው ከትጋቱና ከፈጣንነቱ የተነሣ በለመድከሙና በአጭር በለመቀጨቱ የምታደንቅለት ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ሥራ የሚ በዛበት ትጉህ አገልጋይ ነው ። ለዚህ ሁሉ ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ብትጠይቀው ሊሰጥህ የሚችለው አንዲት መልስ ጌታውን ተስፋ እያደረገ ሲኖር እንከፍ የሆነች የራሱን ኃይል ሁሉን ቻይ በሆነ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደ ለወጠው ነው ። አረፌ ክርስቲያን ፣ እንዲህ ነህን ? ሰነፍ ክርስቲያን አላልኩም ፤ ግን አረፌ ክርስቲያን ነው ያልኩኝ ። አረፌ ክርስቲያን ሁልጊዜ ሥራ የሚበዛበት ፣ አስተዋይ ፣ ሁልጊዜ የጌታው ትጉህ ሠራተኛ ፣ በልቡ ውስጥ ጠለቅ ብሎ ግን ድንገተኛ ማዕበል እንኳ የማያውከው ፣ መሬር ፣ ከባድና ጽኑ ኀዘን እንኳ የማያናውጠው ሰላም አለው ።

ይህ ዕረፍት በምን ዓይነት ለአንተና ለእኔ ሊሆን ይችላል ? እኔ ለልቤና ለሕይ ወቴ ይህን ዕረፍት ያለማቋረጥ እንደምመኘው አንተም እንደምትመኝ እርግጠኛ ነኝ ። በመጀመሪያ ፣ ይህ ዕረፍት የኃጢአት ስርየትን ማረጋገጫ ዕረፍት ነው ። አየህ ወዳጄ ፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓይነት የሚያርፍ ሰው ከእንግዲህ ወዲህ የኃጢአትን ስርየት ለማግኘት ወደ መስቀሉ ለመድረስ የሚሠራ አይደለም ፤ ነገር ግን ከመስቀሉ ሥር ቆሞ ድሉን ይከፈላል ። የሰማይ ብርሃን በመስቀሉ ላይ ሲያበራና ሲያብረቀርቅ ይመለከታል ፣ እርሱንም ለማዳን የሚያስፈልገን ሁሉ ክርስ ቶስ አንድ በአንድ እንደ ፈጸመው ያውቃል ። «ተፈጸመ» የተባለውን ጩኸት ሰምቶአል ። «እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል ?» ሮሜ ፰ ፣ ፴፫ ። የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ያደምጣል ። እንዲህ ያለ ሰው ከክርስቶስ ጋር አብሮ መሞቱን በእርግጥ ስለሚያውቅ የኃጢአቱ ፍርድ ተፈጽሞአል ። የራሱን ነጎሎነትና ራቁትነት ቢያውቅም ቀሉ የክብር መድኃኒቱን ጽድቅና ቁንጅና ለብሶ

አጊጦ በአምላኩ ፊት ያለ ነውር ሆኖ ይቆማል ። ኢየሱስ ምን እንደሆነ አውቆ በእርሱ ስለሚያፍር ክርኩሰት ፣ ከጉምና ከጭጋግ በላይ ከፍ ባለ ስፍራ በዕረፍት ይቀመጣል ።

ወዳጄ ሆይ ፣ ያለፈ ኃጢአትህን እያስታወስክ ትጨነቅበታለህን ? ሁልጊዜም ከተረሳበት እያወጣህ ለሌሎች ታወራለህን ? ዘወትር እንዲያስቃይህ ታደርገዋለህን ? ሁልጊዜ ለጓደኞችህ ትነግራለህ ፣ ለሌሎችም ትናዘዘዋለህን ? የተወደድክ ወዳጄ ሆይ ፣ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ደም ሥር የቀበረውን ረስቶታል ፤ አንተም እርሳውና በቀራንዮ ሥር አርፈህ ተቀመጥ ። እግዚአብሔር የረሳውን አንተ እያስታወስክ እግዚአብሔርን በየጊዜው ለማስታወስና ለመወትወት አትድፈር ።

ይህ የክርስቲያን ዕረፍት ከኃጢአት ስርየት የተነሣ ዕረፍት ብቻ አይደለም ። ነገር ግን ከድል የሚገኝ ዕረፍት ጭምር ነው ። በራሳችን ጉልበትና ቆራጥነት ብቻ ሰይጣንን ለመቃወም ስንት ጊዜ ለፍተናል ? ተዋግተናል ፣ ታግለናል ሲያቅተንም እንደገና ጀምረናል ። ነገር ግን እንደገና ወድቀናል ። የእግዚአብሔር ልጅ ግን ክርስቶስ ሁሉን እንዳደረገለትና እንደፈጸመለት ማየት ሲጀምርና ሰይጣንም ድል የሆነ ጠላት መሆኑን ሲረዳ የድል ዕረፍት ያገኛል ። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ሕይወቱ ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ውስጥ ስለተሰወረ ዲያብሎስ ሕይወቱን ሊነካ እንደማይችል መረዳት ይጀምራል ። በተጨማሪም ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አንድ መሆኑን ይገነዘባል ።

መጀመሪያ እግዚአብሔርንና ክርስቶስን ነክቶ ፣ ወግቶ ፣ አቁስሎና በስቶ የመጣ ካልሆነ የጊዜ ሁኔታም ፣ መከራም ፣ ፈተናም ፣ ሊነካኝ አይችልም ። ይህን ሁሉ ዘልቆ አልፎ መጥቶብኝ ከሆነ አሁን ለጊዜው የማይገባኝ ቢሆንም ለታላቅ ጉዳይ የመጣ መሆኑን አውቃለሁ ። ስለዚህ ባልደናበር ፣ ይህ የመጣውም ለልቤ በረከት ለታላቅ ጉዳይ ከእግዚአብሔር ዙፋን ፊት መምጣቱን አውቄ ዓይኔን ወደ ሰማይ አሻቅቤ ብቀበለው ኀዘን አያውከኝም ፣ ፈተና አይማርከኝም ፣ የጊዜ ሁኔታም አያስደ ነብረኝም ። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ በሆነልኝና በሠራልኝ ደስታ አርፋለሁ ። ይህ ነው የድል ዕረፍት ።

በተጨማሪም ፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ያረፈ) ክርስቲያን በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ ጭምትና ጸጥተኛ ነው ፤ ለማገልገልም ቅዱስ ጉልበት ይሰጠዋል ። እንከፍ የሆነው የራሱ ጉልበት በነበረበት ስፍራ አሁን የታላቁ እግዚአብሔር ኃይል ስለተ ተካ በዚህ ዓይነት ሰው ወይም ሴት ዘንድ መንፈሳዊ ሙላትና ከኃይል ሁሉ የሚበ ልጥ ኃይልና ሥልጣን እንዳለ የሚያስረዳ ነገር አለ ። በኃጢአቱ ስርየት መረጋገጥ ስለሚያርፍ ፣ በድል ስለሚዝናና ከሁሉም በላይ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጽሞ ስላስረከበ ይህ ታላቅ ኃይልና መንፈስ በውስጡ ይሠራል ።

ወዳጆቼ ሆይ ፣ የራሱ ፈቃድ የገዛ ምኞቱን ለመፈጸም የሚጠቀምበት መሣሪያ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ መጠቀሚያ መሆኑን የሚያውቅ ዛሬ ከእኛ ስንታችን ነን ?

ይህን ዕረፍት ለማግኘት ዘወትር ወደ ልቤ ብመለከት ምን ይሆን ? ስለ መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈውን መፈለጌ ነው ። ሰዎች «እውነተኛ ጥምቀት» ብለው የሚጠሩትን ስላየሁና በልዩ ልዩ ቋንቋም ስለማልናገር ያልዳንሁ ይመስለኝ ይሆናል ። ወደ ራሴ ያየሁ እንደሆን መናፍቅ እሆናለሁ ። የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ ጋር መሆኑን ሳልረዳ ዓይኔን ከራሴ አንስቼ ወደ ክርስቶስ ባይ ፣ እሩቅ መሆኑንና ተስፋ ቢስ መሆኔን አያለሁ ። የምፈልገው በጣም ከፍ ስላለ ልደርስበት አልችልም ። ነገር ግን ወደ ሰማያዊው ጠፈር ወደ ላይ ወደ መስቀሉ ያየሁ እንደሆነ ጠፈሩ ባዶ ነው ። ምክንያቱም በመስቀል የተሰቀለው ርስተ በረከቴን በእጁ እንደያዘ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል ። የራሱንም ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልቤ ውስጥ እንዳፈሰሰና በዚህ ምድራዊ ኑሮዬ ሳለሁ የክርስቶስን የራሱን ሕይወት እንድኖር እንዳደረገኝ ብገነዘብና ባምን በዚያኑ ጊዜ ነፍሴ ከሰልፍ ታርፋለች ። ከጫጫታ ፣ ከኡኡታ ፣ ከዋይታ ፣ ከሁከት ፣ ከችከላ ፣ ከርኩሰትና ከኃጢአት ሁሉ በላይ ከፍ ባለ ስፍራ እኖራለሁ ። በክርስቶስ አርፋለሁ ። ከእኔ ጋርና በእኔ ውስጥ መሆኑን እውነተኛ ለማድረግ መንፈስ ቅዱስን ስለላከልን አመሰግነዋለሁ ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

# ርስታችንን መውረስ ።

ኢያሱ ፲፫ ፥ ፩ ።

«የእስራኤልም ልጆች የመቱአቸው ከአርኖንም ሸለቆ ጀምሮ እስከ አርሞንዔም ተራራ ድረስ በምሥራቅ ያለውን ዓረባ ሁሉ በዮርዳኖስም ማዶ በፀሐይ መውጫ ያለውን አገራቸውን የወረሱአቸው ነገሥታት እነዚህ ናቸው ። በሐሴቦን የተቀመጠው ፥ በአርኖንም ሸለቆ አጠገብ ካለችው ከአሮዔር ፥ ከሸለቆውም መካከል ጀምሮ የገለዓድን እኩሌታ እስከ ያቦቅ ወንዝ እስከ አሞን ልጆች ዳርቻ ድረስ ፥ በምሥራቅም በኩል ያለውን ዓረባ እስከ ኪኔሬት ባሕር ድረስ ፥ በቤትየሺሞት መንገድ አጠገብ እስካለው እስከ ዓረባ ባሕር እስከ ጨው ባሕር ድረስ ፥ በደቡብም በኩል ከፈስጋ ተራራ አፋፍ በታች ያለውን ምድር የገዛው የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎን ፥ ከራፋይም ወገን የቀረ ፥ በአስታሮትና በኤድራይ የተቀመጠው ፥ የአርሞንዔምንም ተራራ ፥ ስልካን ፥ ባሳንንም ሁሉ እስከ ጌሹራውያንና እስከ ማዕካታውያን ዳርቻ ፥ የገለዓድንም እኩሌታ እስከ ሐሴቦን ንጉሥ እስከ ሴዎን ዳርቻ ድረስ የገዛው የባሳን ንጉሥ ዐግ ፥ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴና የእስራኤል ልጆች መቱአቸው ፤ የእግዚአብሔርም ባሪያ ሙሴ ርስት አድርጎ ለሮቤል ልጆች ለጋድም ልጆች ለምናሴም ነገድ እኩሌታ ምድሪቱን ሰጣቸው ።»

«ኢያሱም ሸመገለ በዕድሜም አረጀ ፥ እግዚአብሔርም አለው ፦ አንተ ሸመገልህ ፥ በዕድሜህም አረጀህ ፥ ያልተወረሰች እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርታለች ፤ የቀረችውም ምድር ይህች ናት ፥ የፍልስጥኤማውያንና የጌሹራውያን አገር ሁሉ ፥ በግብፅ ፊት ካለው ከሺሖር ወንዝ ጀምሮ በሰሜን በኩል እስካለችው የከነዓናውያን ሆና እስከ ተቆጠረችው እስከ አቃሮን ዳርቻ ድረስ ፥ የጋዛ ፥ የአዛጦን ፥ የአስቀሎና ፥ የጌት ፥ የአቃሮን ፥ አምስቱ የፍልስጥኤማውያን መኳንንት ፥ በደቡብም በኩል የኤዋውያን ፥ የከነዓናውያንም ምድር ሁሉ ፥ ለሲዶናውያንም የምትሆን መዓራ እስከ አሞራውያን ዳርቻ እስከ አፌቅ ድረስ ፥ የጌባላውያንም ምድር ፥ በምሥራቅም በኩል ከአርሞንዔም ተራራ በታች ካለችው በአልጋድ ጀምሮ እስከ ሐማት መግቢያ ድረስ ያለችው ሊባኖስ ሁሉ ፥ በተራራማውም አገር የሚኖሩትን ሁሉ ከሊባኖስ ጀምሮ እስከ ማሴሮን ድረስ ሲዶናውያን ሁሉ ፥ እነዚህን ሁሉ ከእስራኤል ልጆች ፊት አባርራቸዋለሁ ፤ እንዳዘዝሁህም ምድራቸውን ለእስራኤል ርስት አድርገህ አካፍላቸው ።» ኢያሱ ፲፪ ፥ ፩ — ፯ ፤ ፲፫ ፥ ፩ — ፯ ።

መጽሐፈ ኢያሱን የግብር ይውጣ የሚያነብ ሰው ምዕራፍ ፲፪ እና ፲፫ን በትክላ አንብቦ ለማለፍ ሳይቃጣ አይቀርም ። ምክንያቱም ያለ ጥንቃቄ ለሚያነብብ እነዚህ ምዕራፎች በከነዓን አገር ስለሚገኙ ልዩ ልዩ አገሮች ይናገራሉ ። ብዙ ስሞችና ስፍራዎች ተመዝግበዋል ፤ እነዚህንም በትክክል ማንበብና ማስተዋል ያስቸግራል ።

አንተም በዚሁ ምክንያት የተሸነፍህ ብትሆንና እነዚህን ሁለት ምዕራፎች በጥንቃቄ ሳታነብ ብታልፍ በጣም ትልቅ የሆኑ ቁም ነገሮች ያመልጡሃል። የእግዚአብሔር ቃል ዋነኛ ሀብትና በረከት በቀላሉ እንድንለቅማቸው በቃሉ ፊት ላይ፣ ላይ ላዩን የተነጠፉ ወይም የተሰራጩ አይደሉም።

ስለዚህ የከነዓንን ውጊያዎችና ድሎች ዋና ዋና ውጤቶች በማሳጠር የሚተርከውን ይህን አሥራ ሁለተኛውን ምዕራፍ በጭሩ እንመልከት። የመጀመሪያዎቹ ስድስት ቁጥሮች በሙሴ መሪነት የተደረጉትን ድሎች ይነግሩናል። ከቁጥር ሰባት እስከ ቁጥር ሃያ አራት ያሉት በኢያሱ መሪነት የተፈጸሙትን ድሎች ይነግሩናል።

በሙሴ መሪነት የተገኙ ድሎች ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በምድረ በዳው ጉዞ ጊዜ የተደረጉ ናቸው። በኢያሱ መሪነት የተፈጸሙ ድሎች በአገሪቱ ውስጥ የተደረጉ ውጊያዎች ናቸው። በሙሴ ሥር በራሳቸው ምኞት አምሮትና ምርጫ መሠረት ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ የሚገኘውን ክፍለ ሀገር የሮቤል፣ የጋድ ነገዶችና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት ሆነ። ኢያሱና ሠራዊቱ ከምድረ ከነዓን ምን ያህል አሸንፈው እንደወረሱ ይህ ምዕራፍ ይነግረናል። ምድሪቱን ተከፋፍለው ይገዙ የነበሩ የሰላሣ አንድ ኃያላን ነገሥታት ዝርዝር ተሰጥቶአል። እነዚህ ሁሉ አሁን የተገለበጡና ከእግዚአብሔር ሕዝብ ሥልጣን ሥር የተገዙ ሆነዋል።

በሰው ታሪክ ውስጥ በእግዚአብሔር ጸጋ ምን ያህልና ስንት ነገሮች እንደተሸነፉ ተቀምጦ ማስታወስ አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ ነው። ይህም ሲሆን በትምክህት አይደለም። ነገር ግን በትህትናና ምስጋና በተሞላ ልብና መንፈስ ያለፉት ዘመናትን ትዝታና የማስታወስ ገጾች በጥንቃቄ በመመርመር የእግዚአብሔር ጸጋ ስንቱን ነገር እንዳሸነፈልን በማስታወስ ፊት ለፊት እያየነው «ኃጢአት በበዛበት ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፣ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፣ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ» ሮሜ ፭፥ ፳ ና ፳፩ «ኃጢአት በበዛበት .... ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ» ለማለት እንችላለን።

ለጥቂቶች ሰዎች አብዛኛው የኑሮ ትግል ተፈጽሞአል። የሚዋጉአቸው ጥቂቶች ብቻ ቀርተዋል። ለብዙዎቹ ግን የኑሮ ውጊያዎች ገና ናቸው። ውጊያም ከዚህ በፊት ተፈጽሞም ሆነ ወይም ገና የሚመጣ ቢሆን ጉዞአችን ሲያልቅ «መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፣ ሩጫውንም ጨርሼአለሁ፣ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤» ፪ኛ ጢሞ. ፬፥ ፯ ለማለት እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን።

ይህን ምዕራፍ ከመተዋችን በፊት ወደ ስድስተኛው ቁጥር አመለክታችኋለሁ። እንዲህ ይላል «የእግዚአብሔርም ባሪያ ሙሴ ርስት አድርጎ .... ምድሪቱን (ሙሴ ያሸነፋቸውን ምድር) ሰጣቸው፤» እነዚህ ቃላት በምዕራፍ ፲፩ ቁጥር ፳፫ ካሉት ቃላት ጋር በጣም ይቀራረባሉ። ይኸውም ኢያሱ በሚለው ስፍራ ሙሴ ብለን ያነበብን እንደሆን ነው። ነገር ግን በመካከላቸው ትልቅ ልዩነት አለ።

መንፈስ ቅዱስ ለተመረጠው ሕዝብ የመደበላቸውን ርስት ማለት የምድሪቱን ስፋትና ትልቅነት ብንመረምር ይጠቅማል። በሰሜን በኩል ከፍልስጥኤማውያን አገር ጀምሮ በደቡብ እስከለው ለምለም ምድር ይደርሳል። እግዚአብሔር እንዲወር ሱአት ድምበርና ወሰን አድርጎ የወሰነላቸውን ግዛትና እስራኤል ለመውረስ የቻለች ውን ግዛት ብናመዛዝን በሁለቱ መካከል የሚያሳዝን ልዩነት እናገኛለን። እስራኤላ ውያን በመላው ታሪካቸው ውስጥ በማናቸውም ጊዜ እግዚአብሔር ያሰበላቸውን አሟልተው ተቀብለው አያውቁም።

አሁን የታሪኩን ሐተታ ልተውና ታሪኩ ለሕይወታችን ያለውን መንፈሳዊ ትም ህርት ልግለፅ። እያንዳንዳችን እንድንወርስና እንድንደሰትበት እግዚአብሔር ያቀደ ልን ርስተ በረከት ሁሉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ተቀምጦልናል። ምድረ ከነዓን ለእስራኤላውያን የነበረውን ሁሉ ክርስቶስ ዳግም ለእኛ ነው። የምንወርሰው መንፈ ሳዊ ግዛት ሁሉ ከርታው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተነድፎልናል። የሰማያዊ ተራ ራዎች ራእይ፥ ሸለቆዎቹም በመጀመሪያ የመጠራጠር ሸለቆዎች ይመስላሉ። በኋላ ግን ወሰን የለሽ በረከት ያለባቸው ሸለቆዎች ሆነው ይገኛሉ። የዕረፍትና የመዝናናት የጸጥታም መስክ፥ የሚሸነፉና የሚወረሱ ከተማዎች፥ የሚገለበጡ ጠላቶች ናቸው። እያንዳንዳቸውንም ገና የምንወርስ እጅግ ብዙ ስፍራ እንደቀረ እርግጠኛ ነገር ነው። በክርስቶስ ያለን ርስታችን በእርሱ ከራሱ የተከፈለ ቁራጭ ክፍል አይደለም። ነገር ግን ሞላው ክርስቶስ የታሰበልንና የታቀደልን ርስታችን ነው። በኢየሱስ ያለውን ሁሉ እንድንወርስ እግዚአብሔር መድቦልናል። የወረስነው ርስታችን ግን በሃይማ ኖት ከክርስቶስ በከፊል የጨበጥነውን ብቻ ነው። የተሰጠንን በሙሉ ተቀብያለሁ የሚል ሰው ከእኛ አንድ ስንኳ አይገኝም።

እግዚአብሔር በፈቃዱ ከቀደለን በከፊል ብቻ በማግኘት እንዴት በቃን ብለን ልንኖር እንችላለን? በኢየሱስ ያለውን ራሱ «ክርስቶስ የሆነውን» ሕይወት መኖር የሚቻል መሆኑን አውቀን ያን ሕይወት ለመኖር ሙሉ ወደ ሆነው የክርስቲያን ኑሮ አቋም ላይ ሳንደርስ እንቀራለን። ክርስቶስ ከተዋጋቸው ውጊያዎች አንዳችም አላሸ ነፍንም። ወደኋላ መለስ ብለን ያለፈውን ብናስታውስ ሕይወታችንና ሰውነታችን ድል በሆኑባቸው ውጊያዎች የደረሱባቸውን ብዙ ጠባሳዎችና ጎዳንሰ አዝለዋል። በሕይወታችንም ብዙ ጊዜ ከሰይጣን ሾልከን እያመለጥን ቀላሉን መንገድ የመረጥንባ ቸው አያሌ ጊዜያት ስላሉ ልንዋጋ ይገባን ከነበሩ ውጊያዎች ብዙዎቹን እንደሚገባ አልተዋጋንም። ዳሩ ግን እነዚህ ነገሮች መንፈሰ ደካማነት መስለው አይታዩኝም። እንዲህ እያልኩ እንድጮህ የሚያስገድደኝ መንፈስ አገኝባቸዋለሁ። «ጌታ ሆይ፥ ከፍ ወዳለ ምድር ምራኝ» ወደ ግባችን እንድንደርስ የሚያደርጉን ከኑሮ ልምምድ የምንማራቸው ከውድቀት የሚከተል መነሣትና፥ የክርስቶስ ደም እንደሚያነፃ ከማ ወቅ የሚመነጭ የልብ ተመስጦ፥ ጌታችንም በቅርባችን፥ በጎናችን፥ በውስጣችንና በልባችንም ሆኖ ከእርሱ ጋር እንደሚመራን ማወቅ ናቸው። ክርስቶስ ከቶ አይተ ወንም፥ አይከደንም። ነገር ግን ገና ያልተያዘች እጅግ ብዙ ምድር ቀርታለች።

ከሕይወትህና ከሕይወቴ ገና ስለሚያዙ ስፍራዎች እስቲ ጥቂት እናስብ። እንዴት እንደምንወርሳቸው እንጠያየቅ። በመጨረሻም እስከ አሁን ለምን እንዳልያዝንና እንዳልወረስን እንረዳለን።

ከእውቀት ግዛት ገና ያሚያዙ ብዙ ስፍራዎች አሉ። የምነግርህ እውቀት ግን የተፈጥሮ ዝንባሌ አይደለም። ከአእምሮ የመነጩ ሥነ ሥርዓት ማስተዋል፣ ተመል ክቶ መረዳት፤ እነዚህ ሁሉ የተፈጥሮ ዝንባሌን ያዳብራሉ። ስለዚህ ከእውቀት በጣም የተለዩ ናቸው። አንድ ሰው ጥቂት የተፈጥሮ ዝንባሌ ሊኖረው ይችላል። ግን ከተፈጥሮ ዝንባሌ ወሰን አልፎ ጠልቆ መንፈሳዊ እውነቶችን ለማየትና ለመረ ዳት የሚያስችል ነገር ይኖረዋል። የእግዚአብሔርን ደግነት የሚገልጹ ዕፁብ ድንቅ የሆኑ ማረጋገጫዎችን ያገኘሁ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ትንሽ ጉብል ልጅ ሲናገር በሰማሁ ጊዜ ነው። ይህ ልጅ የትምህርት እውቀት አልነበረውም፤ ነገር ግን ክርስ ቶስ በውስጡ እንዳደረና የክርስቶስንም ኃይል በእርግጥ አውቆአል። ስለዚህ በእርሱ ማለት በክርስቶስ ከተፈጥሮ ዝንባሌ ሁሉ ይልቅ በጣም በላቀ ጥበብ ሊናገር ቻለ። በሌላም በኩል አንድ ሰው በጣም አዋቂና ብልህ የተራቀቀ፣ ብዙ ነገሮችንም የሚያ ውቅ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በፍጹም እውቀት የለውም። በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ስለሆኑ ነገሮች የሞኞች ሞኝ ሊሆን ይችላል።

እውነተኛውን አንዱን አምላክ እንድናውቅ ጌታ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ይሰጠናል። በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በየቀኑ ወደ ቀራንዮ መጥተን ጸጥ ባለ መን ፈስና በአክብሮት ልብ እንድንድን ስለ እኛ የደማውንና የሞተልንን እንድናይ ይጋብ ዘናል። እርሱን ከየን አብን አየን፤ ምክንያቱም የተሰቀለውን፣ የሞተውንና ከሙታ ንም የተነሣውን ጌታ ካላየ ማንም እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ልብ ሊያስተውል አይችልም። እኛስ እናውቀዋለን ወይ ? ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር እንዲህ ልንል እንችላለን ወይ ? «አዎን፣ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንደሆነ እቆጥራለሁ። ስለ እርሱ ሁሉን ተጎ ዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ ... በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቆጥ ራለሁ፤ እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ» ፊልጵ. ፫፥፰—፲።

የተወደዳችሁ ወዳጆቼ፣ ስለ ክርስቶስ እውቀት ያሰብን እንደሆነ ገና የሚያዙ እንዴት ያሉ እጅግ በጣም ብዙ ግዛት ቀርቶአል። ለመሆኑ ይህን ያህል ስለ ምን ሞኞች ሆንን ? ከቅዱስ መጽሐፉ ጥቂት ብቻ ስለምናውቅ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስህ ስንት ገጾች ያልተያዙና ያልተገለጡ ግዛቶች ሆነው ይኖራሉ ? እግዚአብሔር የሚነ ግርህን የሚገልጽልህ ምልክት ያልተደረገባቸው ከግርጌአቸው ከቶ ያልተሰመሩብ ቸው ስንቶች ቁጥሮች አሉ ? ሁልጊዜ እየደጋገምን የምናውቀውን ወይም የሚገባ ንን ብቻ እናነባለን። ቀላሉን የእውነተኛውን ነገር ሀ ሁ እንወዳለን። ለምሳሌ ብዙ ምሥጢር የያዙና ግሩም ድንቅ የሆኑ እንደ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሦስትና ሌሎ ችም የመሳሰሉትን ምዕራፎችን በብዛት እናነባለን። ነገር ግን ለብሩህ አእምሮ የተገ ለጠ እግዚአብሔር ለሰው ደግነት ያደረገው ጠቅላላ ሥራ ሳይታወቀን ሳንመገበው

ሳንደሰትበትና ሳንወርሰው ቀርቶአል ። ጌታችን ኢየሱስን በቅዱስ ቃሉ ከላወቅኸው ከቶ ልታውቀው አትችልም ። ክርስቲያን ጓደኞቼ ሆይ ፣ በቃለ እግዚአብሔር መስክ ውስጥ ደህና አድርጋችሁ በርብሩና የሚያስከትለውን በረከት ግለጡ ።

በመንፈሳዊ አቋም በኑሮ ትምህርትና ልምምድ የተገኘ እውቀት ወይም ኤክስ ፒሪየንስ በኩልም ገና የሚያዙ ብዙ ግዛቶች ቀርተዋል ። በከነዓን እንደ ነበሩ ሁሉ ፣ ዛሬም በሕይወታችንም ውስጥ ብዙ ነገሥታት ፣ ጠላቶች ፣ ጽኑ አምባዎችና መጥፎ ጠባይም ክፉ ዐመልም ሥር ሰድደው ተንጀርግገው ይገኛሉ ። መጋደላችን ፣ ጸሎታ ችን ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ፣ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ፊት የምናቀርበው ልመናችን ሁሉ ምንም ቢበዛና በጽኑ ቢመሠረትም እነዚህ በሕይወታችን የተተከሉ ነገሮች በጽኑ ቀጥሮች የታጠሩ የጸኑና የማይሸነፉ ይመስላሉ ። በተፈጥሮ ባሕርያች ንና ጠባያችን ውስጥ እያደበ በሚኖረው በዚያ ክፉ ሰው ኩርኩም ሰላማችን ዘወትር ይደፈርሳል ። ያለ ማስጠንቀቂያ ያጠቃናል ፤ ከመቅጽበት እንበሳጫለን ፣ እንናደዳለን ፣ እንቆጣለን ፣ እንሳደባለን ፣ እንወቅሳለን ፣ እናማለን ፣ እንነቀፋለን ፣ እንተቻለንም ፣ በክርስቲያን ኑሮ ውስጥ ብዙ ከኑሮ የተገኘ ልምምድና እውቀት ቢኖረንም በስብከት ሀገራችንም (ሚሲዮን ጣቢያ) በመኖርም ፣ በክርስቲያን ሥራና ድርጅት መሪነትም ፣ ብዙዎችንም በማስተማር የረጅም ዘመናት ልምድና እውቀት ቢኖረንም እንኳ እነዚህ በውስጣችን የሚያደቡ ጠላቶች በየጊዜው አሸንፈውናል ። ጠላት በየጊዜው ማርኮ ናል ፣ አምባዎቹን ለማፍረስ የምናደርገውን ሁሉ ይቃወማሉ ።

ይህ ነገር ስለ አንተም እውነት አይደለም ወይ ? አሁን የምናጠናው መጽሐፈ ኢያሱ ቢጠቅምህ ለእኔም በየቀኑ በይበልጥ ይጠቅመኛል ። ይኸውም የልቡናዬንና የሕይወቴን ሁኔታ እንደ መስታወት አይበታለሁ ። አንድ ሰው ፣ «ይህ የክርስቲያንነት ኑሮ ራሱ ትግልና ውጊያ ነው» ቢለኝ ፣ ልቤ ከእርሱ ጋር ነው ። ምክንያቱም ፣ የክ ርስቲያን ኑሮ ትግልና ውጊያ መሆኑን እኔ ራሴ ተረድቼዋለሁ ። ዳሩ ግን እግዚአብ ሔር ይመስገን ፤ መቀበል እስክናውቅ ድረስ ነው እንጂ ፣ ድሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አለ ። እነዚህ የኃጢአት ግዛቶች ምንኛ ተቃውመውናል ! ጠላቶቻችን ምንኛ አሸን ፈውናል ! እኛም እንደ እስራኤል እግዚአብሔር የሰጠንን ግዛት በሙሉ መውረስ ያቅተናል ።

የዚህ ሁሉ ምክንያት በአንዳንዶች ዘንድ በክርስቲያን ራሱንና የሕይወቱን ተግ ባር ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ ስላላስረከበ ነው ። ከጌታችን ሥልጣንና ግዛት ውጪ አድ ርጎ እንዲህ ይላል ፣ «የምኖረው ለራሴ ነው ። መጨረሻዬም የግል ጉዳዬ ነው ። ንብረቴን አደራጅቼ ቤተ ሰቤንና ሥራዬን አካሄዳለሁ ። ይህ ሃይማኖቴን አይነካም» በአንዳንዶች ዘንድ ያለው ችግር ደግሞ ፣ በዚህ ዓለም በሚደረጉ ተግባሮችና ዓለማ ውያን ወዳጆች ላይ ጌታ ኢየሱስ ያለውን የጌትነት ሥልጣኑን ማመን ያመነታሉ ።

የተወደድክ ወዳጄ ሆይ ፣ በቃሉ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ዓይነተኛ ዓላማ አስብ «እስከ ክርስቶስ አካል እስከ ፍጻሜውም ልክ ድረስ» እስቲ አንድ

አፍቃ የክርስቶስን ኃይል ፣ ርኅራኄውን ቅድስውን ፣ ኃጢአት መጥላቱን ፣ ለአንተና ለእኔ ያለውን ፍቅሩን ፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የተቀደሰና የተለየ መሆኑን ፣ የራሱ ንም ሕይወት መሥዋዕትነት አስብ ። ዓይነተኛውና ታላቁ የእግዚአብሔር ስጦታ ይህ ነው ። ነፍሳችንም መውረስ የሚገባት ታላቁ ርስት እርሱን ነው ። የክቡር ጌታችን ሕይወትና ባሕርይ በየቀኑ በውስጣችን ካልተራባ ክርስቲያንነታችን በቂ አይደለም ፤ ፍሬም አያፈራም ፣ ፈጣንና ብርቱ ለዋጭ አይሆንም ። የማመናችንና የመማራችን ዋና ዓላማ ወደ እግዚአብሔር ልጅ ሙሉ ምሳሌና አካል ፣ ወደ ፍጹምም ሰውነት እንድንደርስ ነው ።

ገና የሚወረስ ብዙ ግዛት ቀርቶአል ። ይህም እውነት መሆኑን እናውቃለን ። ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ርስታችንን እንደምን ልንወርሰው እንችላለን ? በእውነቱ የምናገኝበት ዘዴ መኖር አለበት ። ደግሞም አለ ፦ እስቲ ላሳይህና በጥን ቃቄና በጸሎት እንድታስብበት ልጠይቅህ ።

አስተውል ፣ ክርስቶስን ራሱን በሙሉ መውረስ ማለት ምን እንደሆነ ከመረዳ ታችን በፊት ፣ በመጀመሪያ እኛ ራሳችን በጌታችን መያዝ ፣ መማረክና መወረስ አለ ብን ። «እኔም አሁን ይህን የወሰድሁ አይደለሁም» አለ ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ፣ እኔም በጳውሎስ ታማኝነት ፣ ግልጽነትና እውነተኛነት ደስ ይለኛል ። አንድ ሰው የጳውሎስን መልእክቶች እያነበበ ፣ ኃጢአት የሌለበት ፍጹምነት ሊገኝ ይቻላል ብሎ ሊያምን እንዴት ቻለ ? «የተፈጸምሁም አይደለሁም ፣ ነገር ግን እርጣለሁ አገኘው እንደሆነ ፣ እኔ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተገኝቻለሁና» ፊልጵ. ፫ ፣ ፲፪ ። አዎን ፣ እርሱን ለመቀበል መጀመሪያ ልባችንን እንክፈት በኋላም በሕያው እምነት ለግል እንረከበ ዋለን ።

በክርስቲያን የኑሮ ልምምድ ያሉትን ሦስት ታላላቅ ቃላት በየተራቸው ሳቀርብ ልሀ ተመልከት «ማስረከብ» «ቅድስና» «መቀበል» በቅድምያ ፍጹምና ቅሬታ የሌለ በት ራስን ለጌታ ማስረከብ ወይም መስጠት መኖር አለበት ። ደግሜም ልናገር ፣ ፈቃድና ራስን ለክርስቶስ ያለማመንታት በፍጹም ካላስረከቡ እውነተኛ ንስሐና መመለስም አይቻልም ። ሁለተኛ ፣ በሕይወታችን ያለን ሁሉ ፣ ችሎታም ሆነ ሕይወ ታችን ራሱ መቀደስ (መለየት) አለበት ። በመጨረሻም ፣ እግዚአብሔር በልጁና በቅዱስ መንፈስ አማካይነት የሚልከውን የልጁን ሕይወት ራሱን በሕያው እምነት ለግል መቀበል ይከተላል ። በእግዚአብሔር አሠራር ያለው የተቀደሰው አደራረግ ተራ ይህ ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስ በሙላት ለግሉ እስኪቀበለን ድረስ እኛ ክርስቶ ስን በሙላት ለግልነት ልንቀበለው አንችልም ። ክርስቶስ ፈቃዳችንንና ሁለመናች ንን በሙሉ አሸንፎና ማርኮ እኛም ካለን ሁሉ ጋር የእርሱ እስክንሆን ድረስ ክርስቶ ስን ለግላችን ልንረከበው አንችልም ።

ፍጹም በሆነ ራስን ማስረከብ ወደ ኢየሱስ ካልመጣን በሕይወታችን ውስጥ ድልን መፈለግና መጠባበቅ ዋጋ የለውም ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ባለ ስፍራ

እንዲያቆመን እንመኛለን ወይ ? ድልን እንዲሰጠን እንጠባበቃለን ወይ ? ርስታችንን እንድንረከብ እንፈልጋለን ወይ ? የእግዚአብሔር አብን የእግዚአብሔር ወልድንና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ሥልጣንና ጌትነት በልባችን ተቀብለን ራሳችንን ተግባራችንንና ያለንን ሁሉ ያለማስቀረት ለሥላሴዎች ስናስረክብ ብቻ ድልን ልንጠ ይቅና በክርስቶስም ርስታችንን ልንረከብ እንችላለን ።

ገና የሚያዙ ብዙ ግዛቶች እያሉ ለምን እንደ ኢያሱ እንሸመግላለን፣ በዕድ ሜም እናረጃለን ?

የደራሲው ሐሳብ እንደ ሰው ዕድሜ በርሮ ይሆናል እንጂ ኢያሱ ይህን ያህል የሸመገለ አይመስለኝም ። ነገር ግን እኔና አንተ በሰማይ በጌታችን ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ቆመን ያለፈውን ታሪካችንን ለየግላችን እየከለልን የምንመረምርበት ቀን እንደ ሥዕል ይታየኛል ። እርሱን ማየት ምንኛ ዕፁብ ድንቅ ነው ። ትግልና ውጊያ ሁሉ ያልቃሉ ። ወዳጄ ሆይ፣ ስማ፣ ዓለም ሳይፈጠር ለሕይወታችን ያዘጋጀውንና ልንኖ ርበት ይገባን የነበረውን በረከትንና አንዋኑዋር ምሳሌና ቅርጽ የሚያስረዳ ክርታ ያሳ የን ይሆን ወይ ? በክርታውም ላይ ከመንገዱ የወጣንበትን፣ የተሳሳትንበትንና የጠፋ ንበትን፣ እምነት ከማጣትና ካለመታዘዝ የተነሣ አንደኛውን ማዕረግ ትተን ሁለተኛ ውን ማዕረግ በረከት የመረጥንበትን ስፍራ ሁሉ ያሳየን ይሆን ወይ ? ወሰንና ተወዳ ዳሪ የሌለው ምሕረቱና ቸርነቱ የነበረበትን ስፍራ ያሳየን ይሆን ወይ ? በሕይወታችን ዘመን ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ አጥብቆ ሊይዘን ሲታገል ሳለ እኛ ከእጁ በሾለክንበት በዚያች ስፍራ ላይ ከጣቶቹ ሕይወታችን ተላክክ የቀረችውን የደሙን ምልክት ደህና አድርገን እናይ ይሆን ወይ ? ለሕይወታችን አዘጋጅቶ የነበረውን በዚያን ቀን ሲያሳ የን፣ በዚህ ዓለም የኖርነው በጸጋው ከቀደልን ዓላማው ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው እንድናይ እጸልያለሁ ።

ስለምን በመንፈሳዊ ድህነት እንኖራለን ? ስለምን እንደክማለን ? ደግሞስ እንወ ድቃለን ? ይህ ሕይወት አልቆ፣ ይህችም አጭር የኑሮ ስሜት ስታልፍ፣ እኛም አር ጅተን፣ ታሪኩም ተመዝግቦ ውጊያውም ሲያልቅ፣ በጌታችን ፊት ቆመን «አንተ ካሰብክልን ነገር ምንም አልተካፈልንም» የምንልበት ምክንያት ምንድር ነው ?

የዚህ ጥያቄ መልስ በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር ፩ እንደሚገኝ አምናለሁ ። የአገሬቱ አወራረስ በዕጣ ነበረ ። በመጽሐፈ ኢያሱ በሁለተኛው እኩሌታ ውስጥ «ዕጣ» የሚለውን ቃል ሃያ ሁለት ጊዜ ተመዝግቦ ታገኛለህ ። ርስቱን የሚካፈሉት በዕጣ ነበረ ። እግዚአብሔርም በታላቅ ጥበቡ ለየነገዱ የተሻለ ነው ያለውን አገር፣ አስቸ ጋሪ ተራራ፣ የልብ ሰቀቀን የሆነ የኑሮ ልምምድ፣ መሬር ፈተናም ሰጣቸው ።

ይህንን የምሥጢሩን እውነተኛነት ብንቀበል፣ ክርስቶስን ለግልነት የምንቀበ ለው በአዲስ መንገድ መሆኑን እንደምንረዳ አምናለሁ ። በናምነው የኑሮን ልምምድ ብንረግጥ ብንፈራገጥም፣ እግዚአብሔር የሰጠንንም ክፍል እምቢ ብንል፣ የእግዚአ ብሔር ዕጣ ለሕይወታችን ከልተሻለ አገሬቱን በፍጹም ከቶ አንካፈልም ። እግዚአብ

ሔር በሁሉ ነገር ምርጫውን እንዲያደርግለት አብርሃም አምኖአል ። ሎጥ የወንድሙ ልጅ ግን አላመነም ። አንዱ በሃይማኖት ተራመደ ። ሌላው በማየት ተራመደ ። አንዱ እግዚአብሔር እንዲመርጥለት ፈቀደ ፣ ሌላው የራሱን ምርጫ ራሱ መረጠ ። የእነዚህን ሁለት ሰዎች ፍጻሜ አስተውል ። እግዚአብሔር የኑሮውን ምርጫ እንዲያደርግለት በእምነት የፈቀደው ወደ ሙሉ በረከት ገባ ፣ ሁለተኛው ግን ከነታሪኩ ጠፋ ተረሳም ።

ክርስቲያን ጓደኞቼ ሆይ ፣ ርስታችሁን እግዚአብሔር እንዲመርጥላችሁ ታምኑትና ትፈቅዱለታላችሁ ወይ ? ወይስ ለሕይወታችሁ የራሳችሁን እቅድ ታዘጋጃላችሁ ? የራስህን መንገድ ትመርጣለህን ? ሥራህን ራስህ ትወጥናለህን ? በራስህ ብልህነትና ብልጠት ትተማመናለህን ? ወይስ እኔ በምወደው መዝሙር ያሉትን ቃላት ከቶውኑ አንብበህ ይሆን ወይ ?

ቢጨልምም እንኳ ያንተ መንገድ እንጂ የራሴ አይሁን
በገዛ እጅህ ምራኝ አንተም ምረጥልኝ የሕይወት መንገዴን
ቢለሰልስ ቢሻክርም ይሻለኛል እርሱን
ቢጠምም ቢቀናም መሪዬ ነውና ወደ ዕረፍት ብርሃን
ዕጣዬን ለመምረጥ ምንም አልደፍርም ቢቻለኝም እንኳን
አንተ ምረጥልኝ እንድራመድ በቅን
ጽዋዬንም ሙላው በደስታ ፣ ወይንም በኀዘን
ላንተ እንደመሰለህ ደጉንም ክፉዬን
ምረጥልኝ አንተ ፣ ዘመድ ሕማም እንዲሁም ጤናዬን
አንተ ምረጥልኝ ጭንቅን ፣ ማጣት ማግኘትን
በትልቅ በትንሽ ያንተ ምርጫ እንጂ የራሴ አይሁን ፣
ሁንልኝ መሪዬ ፣ ጉልበቴና ጥበብ ሁሉም በሁሉ ሁን ።

ወዳጄ ሆይ ፣ ርስትህን የምትወርሰው ከሆንክ መልሱ ይኸው ነው ።

የሚፈጸም አገልግሎታቸውን ሲያበቁ ሌዋውያን ወደ እነዚያ ከተሞች ሄደው እዚያ ይኖራሉ ። ከእግዚአብሔር ማደሪያ ታድሰው ፥ በአገልግሎቱ ደስታና በእርሱም በውስጣቸው ማደር ክብር ተሞልተው ደወየሄዱበት የእግዚአብሔርን በውስጣቸው ማደር ቅድስናና ስሜት ተሸክመው ይጓዛሉ ። በማደሪያው ሰውን ወደ እግዚአብሔር አመጡ ። በከተማዎቹ እግዚአብሔርን ወደ ሰዎች አመጡ ። ለሌዋውያን የተሰጠው ተወዳዳሪ የሌለው ክብር ይህ ነው ። የስግደት ሕይወት ፥ የአገልግሎት ሕይወት ፥ የምስክርነት ሕይወት ። «እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ርስታቸው ነው ።»

ጥቂቶቻችሁ የምትጠሩበት ሕይወት እንዲህ ያለ ነውን ? ከምድሪቱ ርስት አልሰጣችሁም ። ነገር ግን ሁሉን ነገር ሰጥቶአችኋል ። እርሱ ራሱ ርስታችሁ ነውና ምን ይቀርባችኋል ? ታዲያስ ፥ በዚህ ዓይነት መኖር ያደናግራልን ? ይህ በእግዚአብ ሔር ላይ ማጉረምረምንና ማማረርን አይበታትነውምን ? ወሰን የሌለው አዲስ አድ ማስ በፊትህ እንዳለ ፤ ድንበር የሌለው የተድላ ኑሮም እንዳለልህ ይህ ነገር መንገዱን አይከፍትልህምን ? ክርስቶስ የአንተ ፥ አንተም የእርሱ መሆናችሁን መረዳት ብቻ ገለልተኝነትና ብቸኝነትህን አያስወግደውምን ? የአለመፈለግንም ስሜት ወደ ታላቅ የልብ ተመስጦ አይለውጠውምን ? ለሕዝብ ወደ ማደሪያው (ቤተ ክርስቲያን) እንድ ትገባ ወደ እግዚአብሔር ከተማና መንደር እንድትወጣ በዓለም ካሉት አገልግሎቶች ሁሉ ለሚበልጥ አገልግሎት (ለአስታራቂነት) ለራሱ ይፈልግሃል ።

ሁለተኛም ፥ የሌዊን ነገድ ለዚህ ክብር ያዘጋጃቸው ታሪክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተለየ ፍቺ አለው ። በእግዚአብሔር አስተዳደር ውስጥ ይህን የላቀ ስፍራ ለመያዝ ያበቃቸው ምን እንደሆነ እንድታይ እፈልጋለሁ ። በኦሪት ዘፍጥረት ፴፬ ፥ ፳፫ — ፴፭ እንደምናነበው የአንድ አባትና እናት ልጆች የሆኑ ስምዖንና ሌዊ ነፍስ ስለገደሉ አባታቸው ያዕቆብ «በእናንተ ምክንያት በምድሪቱ ነዋሪዎች መካከል ስሜ ተዋረደ» ብሎ ዘለፋቸው ። ያዕቆብ በሚሞትበት ወቅት ስንኳ በአልጋው ላይ ሆኖ ጭካኔአቸ ውን ፥ ቁጣና በቀላቸውን ፥ አሳፋሪ ሥራቸውንም ከቶ አልረሳም ነበርና በአባትነት በረከት ፋንታ ረገማቸው «ሰይፎቻቸው የዓመፃ መሣሪያ ናቸው ። ቁጣቸው ርጉም ይሁን ፥ ጽኑ ነበርና ፤ ኩርፍታቸውም ፥ ብርቱ ነበርና ። በያዕቆብ እከፋፍላቸዋለሁ ፥ በእስራኤልም እበታትናቸዋለሁ» ዘፍጥ. ፵፱ ፥ ፭ ፥ ፯ ።

በስምዖንና በሌዊ የመጀመሪያ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ለወደፊቱ ምን ዓላማ እንደነበረላቸው የሚገልጽ አንዳች ነገር የለም ። የፊተኛው ኑሮአቸውና ሥራ ቸው አሳፋሪ ነበር ። በራሳቸው ፥ በነገዳቸውና በቤተ ሰቦቻቸው ላይ ውርደት አመጡ ። ወዳጆች ሆይ ፥ ደኅብያና ቅንቅን የበላቸውን ያለፉትን ዓመታት ግን እግዚ አብሔር እንደሚያሳድሳቸው እውነተኛ ነገር አይደለም ወይ ? የቆሸሹ ፥ ያደፉና የረ ከሱ የሰው ልቦችን ወስዶ ያነፃ የለምን ? በሸክላ ሠሪ እጅ የተበላሸውን ጭቃ ወስዶ ሌላ አዲስና የክብር ዕቃ አድርጎ ይሠራ የለምን ? አዎን ፥ በእውነት ይህን ሁሉ ያደ ርጋል ። ያለፈው ታሪካችን እንደምንም አስቀያሚ ፥ አሳፋሪ ፥ አዋራጅ ፥ ክርፋታምና ኃጢአተኛ ቢሆንም እግዚአብሔር በዚህ ዓለም አስተዳደሩና አገልግሎቱ ውስጥ

ከሁሉ የላቀውን ስፍራ እንዳይሰጠን አይከለክሉትም ፤ እርሱም እንዲከለክሉት አይፈ ቅድም ።

አዎን ፣ የመለወጫ ስፍራ አለ ። የሌዊ እርግማን ወደ በረከት የተለወጠበት ወቅት አንድ ቀን መጣ ። የስምዖን እርግማን ቀጠለና ነገዱም ፈጽሞ ተደመሰሰ ። ለሌዊ ግን እንዲህ አልነበረም ። እግዚአብሔር አምላክ ራሱ የሌዋውያን ርስት ሆነ ። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ? በኦሪት ዘጸአት ፴፪ ፣ ፳፮ መልሱን እናገኛለን ።

እንደምታስታውሰው ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕግ ከተቀበለበት ተራራ ሲወርድ ሕዝቡን ወደ ጣዖት አምልኮ አዘንብሎ አገኘው ። በሰፈሩም ደጅ ቆሞ ወደ ሠራዊቱ ሁሉ ጮኸ «የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ወደ እኔ ይምጣ» አለ ። ሌዋውያን እሺ አሉ ፣ ንስሐ ገቡና ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለበረከት ታተሙ ። እግዚአብሔርም ለክህነት አገልግሎት የመረጣቸውና ርስታቸውም ራሱ መሆኑን ያበሰራቸው ያን ጊዜ ነው ።

የሁለቱ ወንድማማች መጨረሻ እንዴት ተለያየ ? አንዱ ንስሐ መግባት አቃ ተው ፣ ሁለተኛው ግን ንስሐ ገባና የእግዚአብሔርም መንግሥት ሥራ በሕይወታ ቸው ሁሉ ቀጠለ ። ሌዋውያን እግዚአብሔርን ምርጫቸው ያደረጉት በበረከት ምድር ሳይሆን በበረሃ ሳሉ እንደሆነ አስተውል ። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ተስፋ ጨለማ መሰለ ። ዓላማውም ምን እንደሆነ በግልጽ አይታወቅም ነበር ። የወደፊቱ ጨለማ ነበረ ። ጉዞውም አድካሚ ፣ ኃጢአትና የጣዖትም አምልኮ በአካባቢአቸው በዝቶ ነበር ። ነገር ግን በዚያች ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ብሎ ፊቱንም ፈለጉ ። በሕይወታቸው ውስጥ አሳሳቢና አጠራጣሪ በነበረች በዚያች ወቅት እግዚአብሔርን መረጡ ።

እግዚአብሔር ከዚህ ታሪክ እንዴት ያለ ክቡር ቃላት ሊነግራችሁ ይፈልጋል ! በእውነትም ለሁላችን ነው ። እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠህ ። ገና ሳትወለድ ስለ አንተ ሁሉንም አውቆአል ። በሕፃንነትና በልጅነት ወራት ጠበ ቀህ ፣ በጎልማስነትና ሙሉ ሰው በሆንህበት ጊዜ ሁሉ ነበረ ። ከዓይኑና ከፊቱ ጥበቃ ውጪ የነበርክበት በሕይወትህ ዘመን ሁሉ አንዳች ደቂቃ አልነበረችም ። ከእርሱ ዘወር ባልክ ቁጥር እንኳን ዓይኖቹ ሁልጊዜ በአንተ ላይ ነበሩ ። ወዳጄ ሆይ ፣ ጉዞህ አድካሚ ፣ ብቸኝነት ፣ አስቸጋሪና ጨለማ ቢሆንም ፣ ባለፈው ጊዜ የደረሰብህ ሁሉ እንደምንም ቢሆን «አረማመዴንና መንገዴን እርሱ ያውቃል» የሚለውን አስተ ውል ።

በምድረ በዳው ፣ በኃጢአትና በጣዖት አምልኮ ተከበህ ሳለህ እጆችህን ለክርስ ቶስ ዘርግተህ ማናቸውም ጉዳይና ሰው ወደ ዓለም እንዳይጎትትህ እንቢ ያልክበት እግዚአብሔር በተለይ ያስታውስሃል ። በዚያን ቀን እግዚአብሔርን እንዴት ደስ ያለው ይመስልሃል ?

ከዚያ ወዲህ ያቀረበልህ ጥያቄ ይህ ነው «የራሴ በሆኑት ያፈቀድኩትን ልሠራ በቻው ሕጋዊ አይደለም ወይ ?» አዎን ፣ የእርሱ ለመሆንህ ማረጋገጫ እጅህን ያወጣ ህለት ቀን ራስህን ለክርስቶስ አስረከብክ ፣ ከዚያን ቀን ጀምሮ የእርሱ ነህ ።

ለጥቂቶች ፣ እግዚአብሔር ከምድሪቱ ርስት ፣ ቤት ፣ ምድራዊ መፈቀር አልሰ ጠም ። የሚታያቸው መከራና ከባድ ሸክም የሞላበት ጉዞ ነው ።

ምናልባትም የመከራና የጉስቁልና ጠባሳዎች በሕይወትህ ስለ አሉ ፣ እግዚአብ ሔር ስለ ስሕተትህ ሁሉ ሲቀጣህና ፣ ለአገልግሎቱም ለዘላለም የማትረባ ነህ እያለ ሲያስታውስህ እንደ ነበረ ታምናለህ ።

እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ ግን ነገሩ ሌላ ነው ። እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ርስትህ ነው ። ወደር የለሽ የሆነው ያንተ ዕጣ ፣ የምሕረተኛውን አምላክ ጸጋና ፍቅር ታላቅነት መሞከር ነው ። የማያጠራጥር ጌታህ መሆኑን በምድረ በዳህ መርጠኸው እንደሆነ ፣ የአንተ ፋንታና ርስት የስግደት ኑሮ ፣ የአገልግሎት ኑሮና የምስክርነት ኑሮ ነው ። ለምሳሌ ያህል ፣ በኋላ ጎጂነቱን በረጋገጠ ጋብቻ የተቆራኘ ፣ በሕይወቱ ሁሉ የትዝታውን ሸክም እንዳዘለ ይኖራል ። ይህም ሸክም ከእግዚአብ ሔር ቃል ውጪ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህም የክርስቶስ ጸጋ ብቻ ሸክሙን ሊያነ ሣው ይችላል ።

እግዚአብሔርን አመስግኑ ። አንድ ሰው ተሰብሮ ደቅቆ ተስፋ ሲቆርጥ ፣ ሊረ ዳና ሊጠገንም የማይቻል ሲመስለው ፤ በሕይወቱ ሁሉ ይወዳቸው የነበሩት ሁሉ ከዙሪያው ሲፈረካከሱና እንዳልነበሩም ሲሆኑ ፣ ቀድሞ ቤትና ትዳር በነበረበት ስፍራ አሁን ሌጣው በውድማ ሲቀር ፣ በዚያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ሊረዳው እጁን ይዘረጋለ ታል ። የተበላሸውን ጭቃ አንስቶ ክቡር ዕቃ በማድረግ ፣ ያደፈ የረከሰና የተሰበረ ሕይወትን ወስዶ ለጌታ አገልግሎት የሚረባ አዲስ ፣ የክብርና የቅድስና መሣሪያ አድርጎ የሚሠራው እግዚአብሔር ይመስገን ። እንዲህም ይላል «ከአሁን ጀምሮ እግዚአብሔር አምላክህ ርስትህ ፋንታህም ነው ።»

ለሌዊ ነገድ የተሰጠውን ክብርና ለክብሩም ያዘጋጃቸውን ታሪክ ነገርኩህ ። ያም ክብር በልባቸው ያሳደረውን ተስፋ ማስተዋል ይገባናል ። «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዳላቸው ርስታቸው እርሱ ነው ።»

በሌላ አነጋገርም ነገሩ እንደዚሁ እንዲሆን ከመጀመሪያ ጀምሮ ታቅዶአል ። የደረሰላቸው ነገር አጋጣሚ ሆኖ ወይም በስሕተት የተደረገ ወይንም ሁለተኛ ማዕረግ ምርጫ አልነበረም ። ነገር ግን መንገዱና አሠራሩ በማትመረመር ፣ ጥበቡም በማት ታወቀው በእግዚአብሔር ምክር ነበረ ።

የዚህ የነገሩ ክፍላችን ምሥጢር እንዲበራ የፈለግን እንደሆነ ፣ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የጻፈው መልእክት ለመጽሐፈ ኢያሱ ማብራሪያ መሆኑን ደግመን እናስታውስ ። በኤፌሶን ፩ ፣ ፲፩ ና ፲፬ ስለ ጌታ

ችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናነባለን ፤ «እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ ፥ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን ። ይኸውም ፥ በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው» ይህ አነጋገር ገብቶሃል ወይ ? «በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን» የተመረጠ ርስ ትና ዕጣ ፋንታ ፥ በእግዚአብሔር ምክር የተወሰነ ክፍል ፥ እንደ ፈቃዱ የተመረጠ ፥ እንደ አስተያየቱ የታቀደ ዓላማ ፥ እንደ ፈቃዱ የታለመ ርስት ነው ። ይህ ሁሉ ከማስተዋል በላይ የሆነ ነው ። ለምን ? ቢባል ፥ «በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው» ቀድሞ የነበረ ፥ አሁንም ያው ያቋማችን ሁኔታ ገጽና አምሳል ይህ ነው ። በኢየሱስ ክርስቶስ ርስትና ፋንታ አለን ፥ እግዚአብሔር አምላክ ራሱ ርስታችን ነው ።

ነገር ግን የአቋማችን ሁኔታ ከእግዚአብሔር አቋም ሁኔታ መግጠም አለበት ፤ ኅብረታችን ፍጹም መሆን ይገባዋል ። በኢየሱስ ያለን ርስት ፍጹም እንዲሆን ከተፈ ለገ ውጤት ሊኖረው ይገባል ። ውጤቱም በኤፌሶን ፩ ፥ ፲፰ ተገልጦአል ። በዚያም ክፍል ጳውሎስ ለሰሚዎቹ ይጸልያል ። «ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲ ሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው» በክርስቶስ ያለን ርስታችን ክርስቶስ በእኛ ካለው ርስቱ ይዋሃዳል ። እርሱን መቀበላችን ፥ እርሱ እኛን ከመቀበሉ ይዋሃዳል ።

በዚህ ምዕራፍ በተለይ ስለ እነርሱ ከተነጋገርኩበት ሰዎች መካከል የለህም ይሆናል ። በሰዎች ግምት ጥቂቶቻችን «የታደሉ» እንባላለን ። ምክንያቱም እግዚ አብሔር ባማረ ትዳርና የተባረኩ ልጆች ፥ ከድህነትም እንድንጠለል ከዓለማዊ ሀብ ትና ንብረት ሁሉን በማደል ባርከናል ። ለራሴ የምናገረውን እነግርሃለሁ ። እግዚአ ብሔር የሰጠንና ያለን ሁሉ ርስቱ የሆንነውን እኛን ከማግኘት አያግዱትም ፥ ጸጋው ንና ፍቅሩንም ለልባችን አስፈላጊዎች ከመሆን አያስቀሩም ። ለብቸኛ ልብ ፥ ለጨለ መበትና በምድራቱ ርስት ላልተሰጠው ሰው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል «እግዚአብ ሔር አምላክህ ርስትህ ነው» ይህ እግዚአብሔርም ፥ መልስ እንድትሰጠውና ልብህ በሙሉና አንተም ራስህ ያለ ጥያቄና ማመንታት የእርሱ መሆንህን እንድታስታውቅ ይጠብቅሃል ።

በታደለ ቤትና ትዳር እግዚአብሔር ከእኛ ለባረካቸው አሁንም ቢሆን እግዚአ ብሔር የእስራኤል አምላክ ርስታቸው ነው ። ሕዝቡን ሁሉ በሙሉ ፈጽሞ እስኪረ ከብ ይጠባበቃል ። እርሱ ራሱ ከሰጠን ምቾትና ተድላ የተነሣ ራሳችን ርስቱ መሆና ችንን ብዙዎቻችን ክደነዋል ። እግዚአብሔርም በብዙ ምድራዊ ነገሮች የተባረኩትን የብዙ ክርስቲያኖችን ልብ በጨለማና ፍርሃት እያኖረ ምድራዊና ሥጋዊ ነገሮች ሁሉ የሚገፉፉ ጥላዎች መሆናቸውን ሊያስረዳቸው የሚፈልገው ለዚሁ ይመስለኛል ። የገዛ ርስቱን ስለሚከዱት እንደዚህ ያሉትን ሰዎች እግዚአብሔር ሊያምናቸው አልቻ ለም ይሆናል ።

«እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ርስታችሁ ነው ።»

በዘላለም ፍቅር እጅግ ተወደድሁ
ያን ፍቅር ለማወቅ በጸጋው ተመራሁ ።
ሰማያዊው መንፈስ እየቀሰቀሰኝ
ይህ እርግጥ መሆኑን ደግሞ አስተማረኝ ።
ይህ የተሟላው ፍጹሙ ሰላም
ቅዱስ አመላላሽ ኦ አድራሽም
በዘላለም ፍቅር ዘወትር ሲወደኝ
እርሱ የእኔ ነው ፣ እኔ የእርሱ ነኝ ።
የእርሱ ፣ የእርሱ ብቻ ለዘላለም
ጌታዬና እኔን ማንም አይለይም ።
ኦ ብሩክ ዕረፍት በኢየሱስ ያለው
በወደደውም ልብ የሱስ የሚሞላው
ሰማይም ምድርም አርጅቶ ያልፋል
የንጋት ብርሃንም በምሽት ይዋጣል ።
እግዚአብሔር እስካለ እኔም እስካለሁኝ
እርሱ የእኔ ነው እኔም የእርሱ ነኝ ።

ምዕራፍ ፲፯።

# የደቀ መዝሙር ዋጋ ።

ኢያሱ ፲፬ ፣ ፲፭ ።

«የይሁዳም ልጆች በጌልገላ ወደ ኢያሱ ቀረቡ። ቄኔዛዊውም የዮፎኒ ልጅ ካሌብ አለው፦ ለአምላክ ሰው ለሙሴ ስለ እኔና ስለ አንተ እግዚአብሔር በቃዴስ በርኔ የተናገረውን ነገር ታውቃለህ። የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ምድርን እሰልል ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ እኔ የአርባ ዓመት ሰው ነበርኩ። እኔም በልቤ የነበረውን ቃል መለስሁለት። ከእኔ ጋር የወጡ ወንድሞቼ ግን የሕዝቡን ልብ አቀለጡ። እኔ ግን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽሜ ተከተልሁ። ሙሴም በዚያን ቀን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽመህ ተከትለሃልና እግርህ የረገጠው ምድር ለአንተና ለልጆችህ ለዘላለም በእርግጥ ርስት ይሆናል ብሎ ማለ። አሁንም፣ እነሆ፣ እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ቃል ከተናገረ በኋላ፣ እስራኤል በምድረ በዳ ሲዞሩ፣ እርሱ እንደ ተናገረኝ እግዚአብሔር እነዚህን አርባ አምስት ዓመት በሕይወት አኖረኝ። አሁንም፣ እነሆ፣ ለእኔ ዛሬ ሰማንያ አምስት ዓመት ሆነኝ። ሙሴም በላከኝ ጊዜ እንደነበርሁ፣ ዛሬ ጉልበታም ነኝ፣ ጉልበቴም በዚያን ጊዜ እንደነበረ፣ እንዲሁ ዛሬ ለመዋጋት ለመውጣትም ለመግባትም ጉልበቴ ያው ነው። አሁን እንግዲህ በዚያን ቀን እግዚአብሔር የተናገረውን ይህን ተራራማ አገር ስጠኝ። አንተ በዚያ ቀን ዔናቃውያን ታላላቆችና የተመሸጉ ከተሞችም በዚያ እንዳሉ ሰምተህ ነበር፤ ምናልባት እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ይሆናል፣ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረኝ አሳድዳቸዋለሁ።

ኢያሱም ባረከው። ለዮፎኒም ልጅ ለካሌብ ኬብሮንን ርስት አድርጎ ሰጠው። ስለዚህም የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ስለተከተለ ኬብሮን እስከ ዛሬ ለቄኔዛዊው ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ርስት ሆነች። የኬብሮንም ስም አስቀድሞ ቂርያት አርባቅ ትባል ነበር። ይህም አርባቅ በዔናቅ ሰዎች መካከል ከሁሉ ከፍ ያለ ነበረ። ምድሪቱም ከውጊያ ዐረፈች።» ኢያሱ ፲፬ ፣ ፮ — ፲፭ ።

መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አሥራ አራት አንድ ድንቅ የሆነ ታሪክ ይዟል፤ ታሪኩም፣ አንድ ሰውዬ በሰማንያ አምስት ዓመት ዕድሜው የምድሪቱን በሕዝብ መካከል ማከፋፈል አቋረጠና፣ እግዚአብሔር ከአርባ አምስት ዓመት በፊት ተስፋ የሰጠውን የራሱን ዕጣ ክፍል ለመቀበል ከሕዝቡ መሥመር ብቅ እንዳለ ይናገራል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ካሉት ታሪካዊና ታላላቅ ሰዎች ካሌብ አንዱ ነው። የታላቅነቱም ምሥጢር ምንኛ ጥልቅና ትሁት ነበረ! ታላላቅ ሰዎች ለመታወቅ የሚያዳግቱ ቀልፍልፎችና ተመሳጣሪዎች አይደሉም። ግን ግልጽና ትሁታን ናቸው። እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ሰው እንደ መጽሐፍ ልታነበው ትችላለህ። በእግዚአብሔር መንፈስ በተከፈቱ ዓይኖች እንደዚህ ያለውን ሰው ትልቅነት ልታይ ትችላለህ።

አምላካዊ አደራረግና የአንዋኑዋር ሥርዓቶች ዘላለማዊ የመንፈሳዊ በረከትም አቋሞቹ የማይለወጡ ናቸው። እግዚአብሔር አምላካችንን እንደ ካሌብ በፍጹም ልባችን መከተል ብንግርና ብናደርግ በኑሮህና በኑሮዬም የሚደርስልን ዋጋና ፍሬ የዚሁ ዓይነት እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። የካሌብ አምላክ፣ የእኛም አምላክ ነው።

የምንመኘው፣ የምንጓጓለትና የምንጠባበቀው ሁሉ፣ በጎልማስነት የነበረን እምነት በሽምግልና እንዳይለወጥ፣ ዕድሜ እየጨመርን በሄድን ቁጥር ጌታን ማየታችን እያደገ እንዲሄድ፣ የሕይወት ጉዞም ወደ ማለቅ ሲቃረብ፣ ያለፈውን አሰላስለን በቃኝ ሳንል፣ ከጠላት ጋር አዲስ ውጊያም ለመጋጠም ዝግጁዎች እንድንሆን ነው። የዚህ የብሉይ ኪዳኑ ሰውዬ «ታላቅ ልብ» ዓይነተኛ ምኞት ይህ ነበረ። እስቲ ተመልክተን እንረዳው እንደሆነ የትልቅነቱን ምሥጢር እንመርምር።

ይህ የእግዚአብሔር ሰው የማይናወጥ እምነት ነበረው። በኦሪት ዘኍልቊ ፲፫ እና ፲፬ እንደተጻፈው፣ ከአርባ አምስት ዓመት በፊት ወደነበረው አሳዛኝና አሳፋሪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ እንመለስ። ምድረ በዳውን በአጭር ጊዜ ውስጥ አቋርጠው ቃዴስ በርኔ ወደምትባል ስፍራ ደረሱ። ይህችም ምድር እግዚአብሔር ተስፋ ባስደረጋቸው ምድር ድምበር ላይ ነበረች። ነገር ግን በበረሃው ጉዞ ጊዜ ልባቸውን ያሸከረው ጥርጣሬ፣ ሰላዮችን ወደሚሄዱበት አገር እንዲልኩ አስገደዳቸው። እንደ ምታስታውሰው፣ ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው፣ በጠቅላላው አሥራ ሁለት ሰዎች አገሪቱን እንዲሰልሉ ተላኩ።

ስድስት ሳምንታት ሙሉ ዞረው ከሰለሉ በኋላ ሁለት ዓይነት መረጃ አቀረቡ። የብዙዎች ወገን መረጃና የአነስተኞች ወገን መረጃ ነበሩ። ብዙዎቹ መረጃ አቅራቢዎች አገሪቱ ወተትና ማር እንደምታፈስ አረጋገጡ። ሆኖም አስፈሪ የሆኑ ኃያላን ጀግኖች አሉበት አሉ። «ነገር ግን በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ኃያላን ናቸው፤ ከተሞቻቸውም የተመሸጉ እጅግ የጸኑ ናቸው፤ ደግሞም በዚያ የዔናቅን ልጆች አየን» ዘኍልቊ ፲፫፣ ፳፰። የዔናቅ ልጆች ረጃጅምና ጀግና ዘር ናቸው፤ ደግሞም እንዲህ አሉ «ወደእነዚያ ሕዝብ እንወጣ ዘንድ አንችልም» በካሌብና በኢያሱ የቀረበው የአነስተኞች ወገን መረጃ በዚያች ምድር ኃያላን መኖራቸውን አረጋገጠ። ነገር ግን በእግዚአብሔር አመኑ። «እግዚአብሔር ከወደደን ወተትና ማር ወደምታፈስሰው ወደዚች ምድር ያገባናል እርስዋንም ይሰጠናል» አሉ። ዘኍልቊ ፲፬፣ ፰። «ማሸነፍ እንችላለንና እንውጣ፣ እንውረሰው» አሉ። ዘኍልቊ ፲፫፣ ፴።

እነዚህ ሰዎች የብዙዎቹ ወገን ያዩትን ሁሉ አይተዋል። ነገር ግን ልዩነት ሆነ። የብዙዎቹ ወገን የኢያሱ ግን የኃያላኑን ጉልበት ከእግዚአብሔር አወዳደሩ። የብዙዎቹ ወገን ተንቀጠቀጡ። ሁለቱ ግን አሸነፉ። የብዙዎቹ ወገን ታላላቅ ኃያላንና ትንሽ አምላክ ነበሩአቸው። ካሌብ ታላቅ አምላክና ትንንሽ ኃያላን ነበሩት። በእምነቱ ውስጥ ማመንታት ነበረበት «እግዚአብሔር ከወደደን ...» አለ። ይህ ማመንታት ግን በእግዚአብሔር የመጠራጠር ነገር አልነበረም። ግን የመዋረድና የትህትና

ነበረ። እግዚአብሔር ከወደደን ፥ ሲል ወደኋላው ተመልሶ በበረሃው የተደረገውን የአንድ ዓመት ጉዞ ያስታውሳል። በበጉ ደም ከግብፅ የወጣበትን ቀን አስታወሰ። በቀን በደመና ዓምድ ፥ በሌሊት በእሳት ዓምድ የሚመራቸውን ታማኝነት አስታወሰ። እግዚአብሔርም ሕዝቡን እንደ ወደደ አወቀ። «ስለዚህ እናሸንፋለን።»

የሕዝቡም ጩኸት «ወደ ግብፅ እንመለስ» የሚል ነበረ። በግብፅ የነበሩበትን ገበርነትና ባርነት ረሱ። በቀረው ጉዞአቸው ያለውን መከራና አደጋ ለማስወገድ ብለው እግዚአብሔርን አቃለሉ። ስለዚህ በእምነትና በመታዘዝ የሚወረሰውን ምድረ በረከት ከካሌብና ከኢያሱ በቀር ከግብፅ ከወጡት ከነዚያ ትውልድ ማንም እንደማይገባበትና እንደማይወርሳት እግዚአብሔር በግልጥ ነገራቸው።

እግዚአብሔርም ስለ ካሌብ እንዲህ አለ «ባሪያዬ ካሌብ ግን ሌላ መንፈስ ከእ ርሱ ጋር ስለሆነ ፈጽሞም ስለ ተከተለኝ እርሱ ወደ ገባበት ምድር አገባዋለሁ። ዘሩም ይወርሳታል» ዘኍልቁ ፲፬ ፥ ፳፬። በአርባ አምስቱ አድካሚ የምድረ በዳ ጉዞ በማያቋርጥ ችግር ፥ የዘወትር ትግሎችና በልተፈጸሙ ተስፋዎች ዘመናት ሁሉ ካሌብ ይህን ተስፋ እንደ ክቡር ሀብት በልቡ ጠበቀ። በሕዝቡ ማጉረምረም መካከል ካሌብ በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን መከተል ዓላማው አደረገ። የሃይማኖት አባት እንደ ነበረው (እንደ አብርሃም) «ለእግዜአብሔርም ክብር እየሰጠ ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም» ሮሜ ፬ ፥ ፩ — ፳፩። ካሌብ በሙሴ እንዲያምፅ ማባበል ዋጋ የለውም። ከአጉረምራሚዎች ፥ ከተጠራጣሪዎችና ከማያምኑ መካከል ተገኝቶ አያውቅም። የግብፅ ነጭና ቀይ ሽንኩርት ከማራቸውም መካከል አልተገኘም። ለእግዚአብሔር ከልታዘዙትና ጣዖት ከመለኩት ውስጥ አል ተገኘም። የመታዘዝን ዋጋና ሽልማት አይቶአል። ይህም ለቀረው ሕይወቱ በእው ነት ሊጠብቀውና እግዚአብሔር ተስፋ ወደሰጠው አገር እስኪገባ ድረስ ይበቃዋል።

በእግዚአብሔር እውቀት የተሞላና በእርሱም በፍጹም ልቡ በአመነ ሰው መብ ትና ሥልጣን ይህ ሰው በሰማንያ አምስት ዓመት ዕድሜው ከመስመሩ ፊንጠር ብሎ ብቻውን ሲቆም የታየበት ያች ወቅት ምንኛ ግሩም ትሆን ይሆን ? ብዙ መከራዎች ደርሰውበታል ፥ በትግሉም ተስፋ ሊያስቆርጡት ያሰቡትን ሁሉ አሸነፈ። እርሱ ሲና ገር መስማት ምንኛ ያስደስታል ! አሁን ፥ ከአርባ አምስት ዓመት መጠባበቅ በኋላ ከብዙ የነፍስ ጭንቀት በኋላ ፥ እግዚአብሔር በዚያን ቀን እንደተናገረው ይህን ተራ ራማ ክፍለ ሀገር ስጠኝ አለ። ስንታችን ሰማንያ አምስት ዓመት እስኪሞላን እንደ ምንኖር አላውቅም። ነገር ግን ወደ ሕይወታችን መጨረሻ ስንደርስ የካሌብን እም ነት የመሰለ ፥ እግዚአብሔር እንደሚወደኝ በማወቅ በማይናወጥ ማረጋገጫ የተመሠ ረተ እምነት ይኖረኝ እንደሆነ ወይንም ስንት ዓመት እንደምኖር እግዚአብሔር ብቻ ያውቀዋል። አይወደንም ወይ ? በእኛስ ደስ አይለውም ወይ ? ወደ ቀራንዮ መስቀል ተመልከት። አይወደንም ወይ ? በእውነቱ ፥ እግዚአብሔር እኛን የወደደበትን ፍቅር

ከጥርጣሬ በላይ አድርጎ አሳይቶአል ። ይኸውም «ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ ።»

ኢየሱስን አየሁ ለአጭር ሰዓት
ከእርሱ በስተቀር ጠላሁኝ ተውኩኝ ።
በእርሱ ተያዘ የመንፈሴ እምነት
የተሰቀለውን ሰርክ በማየት ።

ስለዚህ ጉዳናው ቢጨልም ፣ ቢሻክር ፣ ብቸኞችም ብንሆን እግዚአብሔር ዘወትር እንደሚወደን እናውቃለን ። በጉዞው መጨረሻም ሽልማቱ እንደሚሆንልንና በእምነት በትዕግሥትም ተስፋውን እንደምንወርስ እናውቃለን ። ነገር ግን እምነታችን ያወላውላልና ወዮልን ። ከኑሮ ትግል የተነሣም እንጠወልጋለን ። ሁልጊዜ ጥንቁቆችና ዘወትርም ወደ ኢየሱስ የምናይ አይደለንም ። የግብፅ አምሮት እንደገና ተሰምቶናል ፤ አምላክ ይቅር ይበለንና በጎልማስነታችን ጊዜ የነበረው የተውነውም የኑሮ ፈንጠዚያ ሁሉ አሁንም ደጋግሞ ይታወሰናል ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመራመድ በምናደርገው ትግል ዘወትር ድፍረተ ቢሶች ሆነናል ። ብዙ ጊዜ አጉረምርመናል ። የክርስቲያን ኑሮ መከራና አስቸጋሪ ነው እያሉ ከሚያማርሩትና ከሚያጉረመርሙት ሠራዊት ጋር ተባብረናልና እግዚአብሔር ይማረን ። በአቋማችን ሁኔታ የእግዚአብሔር ልጆች ብንሆንም በተፈጥሮና በአንዋኑዋራችን በኩል በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ የዳኑ ኃጢአተኞች መሆናችንን ስንረዳ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ማዋረድ ይገባናል ።

የክርስቲያንነት ጓደኞቼ ሆይ ፣ ወደ ኢየሱስ እንደገና እስቲ ለአጭር ጊዜ ስንኳ ተመልከቱ ። ከምን አዘቅት እንዳወጣችሁና እንደአዳናችሁ አስታውሱ ። ወደ ልባችሁም የመጣውን ሰላም አስታውሱ ። እምነታችሁም የተገነባበት ጥልቅ መሠረት «እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» ዮሐ. ፫ ፣ ፲፮ የሚለው ክፍል ነው ።

የካሌብ ጉልበት እንዳልደከመ አስተውል ። ይህ አስገራሚ ምዕራፍ በቁጥር አሥራ አንድ ላይ ፣ ካሌብ በሰማንያ አምስት ዓመት ዕድሜው ልክ የአርባ ዓመት ዕድሜው እንደ ነበረ ሁሉ ጉልበታም መሆኑን ይነግረናል ። እንዲህ አለ «ሙሴም በላከኝ ጊዜ እንደ ነበርሁ ፣ ዛሬ ጉልበታም ነኝ ፤ ጉልበቴም በዚያን ጊዜ እንደነበረ ፣ እንዲሁ ዛሬ ለመዋጋት ፣ ለመውጣትም ለመግባትም ጉልበቴ ያው ነው» የማይናወጥ እምነቱ የማይደክም ጉልበት ሰጠው ። ይኸው የእግዚአብሔር የራሱ ኃይል ነው ። ለጉዞው መከራ ሁሉ የሥጋ ክንድና ጉልበት አይበቃም ። ቢሆንም ይህ ሰው ገና ሊታገል ፣ ሊዋጋና ሊሠራ ይችላል ። ይህም ሁሉ ሆኖ ገና በእግዚአብሔር ኃይል ተሞልቶአል ። አንድ ሰው ይህን ነገር ሊናገር ቢችል የሚለው እንዲህ ነው «የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል» ፪ኛ ቆሮ. ፬ ፣ ፲፮ ።

ሙሉ ሰው ሆኜ በዕድሜዬም እኩሌታ አባትና እናት ሊሆኑኝ ከሚችሉ ፣ በእር ጅናም ምክንያት ከቤት መውጣት ከተሳናቸው ፣ በሥጋቸውም ድኩማን ከሆኑ ፣ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ቤተ ክርስቲያንም መሄድ ካቃታቸው በአእምሮ ከዛሉ ፣ በእምነት ግን ብርቱዎችና ጎልማሶች ከሆኑ ሰዎች መገናኘት ለእኔ ምንኛ ክቡር ነገር ነው ። ምድራዊ ኑሮዬ በዚህ ዓይነት እንዲፈጸም እመኛለሁ ። አንተሳ ? ብርቱ ፣ ደፋር ፣ ታማኝና በእምነት ጸንቶ «መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ፣ ሩጫውን ጨር ሼለሁ ፣ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ» ማለት ድንቅ ነው ። ካሌብ በፍጹም የማያወላውል እምነት ስለነበረው የማይበገር ጉልበትና ኃይል አገኘ ።

የእርሱም ሽልማት የተሟላ ድል ነበረ ። በኢያሱ ፲፩ ፣ ፲፬ ምድሪቱን ከተካፈ ሉት ሁሉ ካሌብ ብቻ ጠላትን ፈጽሞ ለማባረር እንደቻለ እናገኛለን ። ሌሎቹ ያልተ ሳካ ሙከራ አደረጉ ። በመጽሐፈ ኢያሱ የመጨረሻ ክፍሎች እየተደጋገመ «ከምድ ሪቱም ጠላትን ፈጽሞ ሊያሳድዱአቸው አልቻሉም» የሚል ስለምናነብ አሳዛኝ ታሪክ ችን እናገኝበታለን ። የብረት ሰረገሎች አየሉባቸው ፣ ይህንንም ብዙ ጊዜ ተጽፎ እናገኛለን ። ካሌብ በወረሰው ዕጣ ውስጥ ግን ሦስት ኃያላን ሕዝቦች ቢኖሩም ድል አደረጋቸው ። እግዚአብሔርን ፈጽሞ የተከተለ ሰው ሁሉ ውጊያውን ሁሉ ፈጽሞ ድል ይነሣል ።

ጠላትን ማባረርና ማሳደድ ብዙዎቻችን ስላልቻልን ፣ ይህን ጉዳይ በእግዚአብ ሔር ፊት ሆነን እንመርምር ። በሰላምና በደስታ ሰዓታችን መራራ ኃፍረት የምናፍ ርበት ጠላት በውስጣችን እያደባ ይኖራል ። በጦር ልብሳችንና በሕይወታችን ያሉትን እንከፍና ደካማ በታዎችን ያውቃል ። ነገር ግን ጠላትን ከሕይወቴ ማስወገድ የማል ችልበት ምክንያት ፣ አብዛኛውን ጊዜ ጌታዬን በፍጹም ልቤ ያልተከተልኩት ስለሆነ መሆኑን እረዳለሁ ። መንፈሳዊ ጉልበትን የሚያንጠባጥብብን ቀዳዳ ባይኖረን ኖሮ ፣ የመንፈሳዊ አቋማችን ሥር ባይቆፈር ኖሮ ጠላቶች ሁሉ በጠፉ ነበር ። የተሟላ ድል የሚገኘው ፍጹም በሆነ ታዛዥነት ነው ። ጠላትን ለማባረርና ለማጥፋት እንዳንችል ያደረጉንን የቅድስና የታዛዥነት ማፍሰሻ ቀዳዳዎቻችንንና ስንጣቂዎቻችንን ፣ እንዲ ሁም እርሱን የመከተል መሰናክልና ስብራት ሁሉ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብ ሔር ብቻ ያውቃቸዋል ። ግን እግዚአብሔር ይቅር ይበለን ! መንፈስ ቅዱስም ልባ ችንን ያብራ ። ካሌብ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ተከተለና ጠላትን ፈጽሞ ደመሰሰ ።

ሌላ ነገር ደግሞ ስለ ካሌብ ተገንዘብ ። ከቶ የማያልቅ በረከት ተቀበሉ ። ለሴት ልጁና ለባልዋም የሚያከፍል ትርፍ ርስት እንደ ነበረው ከምዕራፍ አሥራ አምስት እናነባለን ። እግዚአብሔር ከሰጠው ርስት አዲሶቹ ጎጆ ወጪዎች የሚተዳደሩበትን ርስት ሰጣቸው ። የላይኞቹንና የታችኞቹን ምንጮች ሰጣቸው ። ካሌብ «መልካም መዓዛ ያለው ያትክልት ስፍራ ነበረ» ለማለት ይቻላል ። የልቡ አቋም ይህ ነበረ ። የኑሮው በረከት ለሌሎች ደረሰ ። ወደ ሌሎችም ጎረፈ ። ለሌሎችም የሚያከፍል የበረከት ምንጮች ነበሩት ።

ልብህ አይራብም ወይ ? እንዲህስ አይልምን ? «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ፥ እኔንም እንዲሁ አድርገኝ» የእኔ ልብ ይመኛል ። ከእግዚአብሔር ጸጋ ከተቀዳው ብሩህነትና መቻል የእርጅናን ዘመን ደረሰ ፥ እግዚአብሔር ከሰጠን ስጦታዎችም ትዳር ለሚይዙ ተተኪዎች ማካፈል ምንኛ ጸጋ ነው ። የጸጋን ፥ የበረከትንና የድልን መንገድ ለሌሎች ማስተማርን መቻል ፥ በእነዚህም ነገሮች ሳላፍር በከንፈሬ ብቻ ሳይሆን ከጣፋጭና ክርስቶስን ከሚመስል የአንዋኑዋር ልምምድ መናገርን መቻል ፥ አ ፥ ይህን የመሰለ የእርጅና ዘመን ።

የተወደዳችሁ ወዳጆቼ ፥ የዚህ ሁሉ ምሥጢር የሚከተለው ነው ። ከሌብ ከቶ ያልተቀነሰ ፍቅር ነበረው ። በአርባ ዓመት ዕድሜው ምድሪቱን በጎበኘበት ጊዜ አንዲት ስፍራ ልቡን ማረከችው ። የማረከችውም በፍሬዋ ፥ በወተትዋ ወይም በማርዋ አልነበረም ። ለዚህ ለታላቁ የሃይማኖት አርበኛ እነዚህ ሁሉ ውራጅና ሁለተኛ ማዕረግ ናቸው ። የስፍራዋም ስም ኬብሮን ነበረ ። በተላላጠና በተመላለጠ ተራራማና ዓለታማ ክፍለ ሀገር ናት ። በእርስዋም ጽኑ ምሽጎችና የኃያላን ኃያል ይገኙበት ነበር ። አብርሃም ድንኳኑን በዚያ ተክሎ ነበር ። እግዚአብሔር አብርሃምን እዚያ ፊት ለፊትና አፍ ለአፍ አነጋገረው ። በዚያም ፥ እግዚአብሔር የምድሪቱን መውረስ ተስፋ ለአብርሃም ሰጠ ። «ኬብሮን» ማለት ፥ አንድነት ፥ ፍቅርና ሕብረት ማለት ነው ። ከሌብ የወደዳት ስፍራ እርስዋ ነበረች ። ሁላችንም ፈልገን ማግኘት የምንመኝና የምትገባን ስፍራ ናት ።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠ ተራራማ የሆኑ ፥ በጽኑ ምሽግና በብርቱ ኃይል የሚጠበቁ ፥ ሰይጣን ግን በሚቻለው ሁሉ እንዳያገኙት የሚከላከላቸው ስፍራዎች አሉ ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሰጠው ርስት ፥ ሰይጣን በከፊል ሊያስቀርና በሚፈልጉት በማናቸውም ነገር ሊለውጥ ይታገላል ። ሜዳዎቹን ፥ ሸለቆዎቹን ፥ ማሩንና ወተቱን ይሰጣቸዋል ። ክርስቲያኖች ወደ ኬብሮን ተራራሲገፉ ሰይጣን ሲያይ ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሚገኘው አንድነት ፥ ፍቅርና ኅብረት የበለጠ ነገር አለመኖሩን ክርስቲያኖች ተረድተው ወደዚያ ሲያመሩ ዲያብሎስ ሲያይ የመጨረሻዋ ወታደርና ጥይት እስከትቀረው በሙሉ ኃይልና መሣሪያ ሊዋጋ ታጥቆ ይነሣል ።

የከሌብ ትዕግሥት ፥ እምነትና ፍጹም ማሸነፍ ምሥጢር ይህ ነው ። ከአርባ አምስት ዓመት በፊት በኬብሮን ያለውን የደቀ መዝሙር ዋጋ አየ ። እርሱም ከሁሉ የበለጠ ሽልማት ነው ። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ሰውን ፊት ለፊት ተገናኘ ፤ ከሌብ ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ አንድነት ፥ ፍቅር ፥ ኅብረትና ተወዳዳሪ የሌለው በረከት የሚገኝበትን ስፍራ አየ ። ስለዚህ ፥ መከራውና ጦርነቱ ከሁሉ የሚበልጥ ቢሆንም ፥ ኬብሮን የግሉ እስከትሆን ድረስ ገፋበት ።

«ስለዚህም የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ስለተከተለ ኬብሮን እስከ ዛሬ ለቄኔዛዊው ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ርስት ሆነች» ኢያሱ ፲፬ ፥ ፲፬ ።

## ምዕራፍ ፲፯ ።

# በሙላት መኖር ።

### ኢያሱ ፲፯ ፥ ፲፰ ።

«የዮሴፍ ልጆች ኢያሱን እኔ ብዙ ሕዝብ ስለሆንሁ እስከ አሁንም እግዚአብ ሔር ስለ ባረከኝ ለምን አንድ ክፍል አንድም ዕጣ ብቻ ርስት አድርገህ ሰጠኸኝ ? አሉት ። ኢያሱም ብዙ ሕዝብስ ከሆንህ ተራራማውም የኤፍሬም አገር ጠብቦህ እንደ ሆነ ወደ ዱር ወጥተህ በፌርዛውያንና በራፋይም ምድር ለአንተ ስፍራ መንጥር አላ ቸው ። የዮሴፍም ልጆች ተራራማው አገር አይበቃንም ። በሸለቆውም ውስጥ ለሚ ኖሩት ፥ በቤትሳንና በመንደሮችዋ በኢይዝራኤልም ሸለቆ ለሚኖሩት ከነዓናውያን የብረት ሰረገሎች አላቸው አሉት ። ኢያሱም የዮሴፍ ወገን ለሚሆኑ ለኤፍሬምና ለምናሴ አንተ ብዙ ሕዝብ ነህ ፤ ጽኑም ኃይል አለህ ። አንድ ዕጣ ብቻ አይሆንል ህም ። ነገር ግን ተራራማው አገር ለአንተ ይሆናል ፤ ዱር እንኳ ቢሆንም ትመነጥረ ዋለህ ፥ ለአንተም ይሆናል ። ለከነዓናውያንም የብረት ሰረገሎች ቢሆኑላቸው የበረ ቱም ቢሆኑ ታሳድዳቸዋለህ አላቸው ።» ኢያሱ ፲፯ ፥ ፲፬ — ፲፰ ።

እንደምታስታውሰው የመጽሐፈ ኢያሱ የመጨረሻ ክፍሎች የእስራኤል ልጆች ምድረ ከነዓንን የሚከፈሉበት የርስት አከፋፈልና አወራረስ ሥርዓት ይገልጻሉ ። የምድሪቱን ለየነገዱ ስለማከፋፈል ፥ የቃል ኪዳኑም ድንኳን በአገሪቱ አማካይ ስፍራ በሺሎ ስለመተከሉና የኃጢአት ፍርድ የወንጀለኛ መማጸኛ ከተሞች ስለመቋቋም ይናገራል ። ከምድሩ አከፋፈልና አወራረስ ብዙ የምንማራቸው ነገሮች አሉ ።

ማደሪያው በመሃል አገር ተተከለ ። እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ነበረ ፥ ሕዝቡም በስግደት በዙሪያው ይገኛሉ ። ይህ አደራረግ የክርስቲያኖች ስግደት ዓላማ መሠረት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ መሆኑን ያስታውሰናል ። የምንሰግደው ለእግዚአ ብሔር ነው እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለወግ አይደለም ። በየእሁዱ ጌታችን በአለበት እንሰበሰባለን ። እርሱ እንዲህ ብሎአልና «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በተሰበሰቡበት እዚያ በመካከላቸው እገኛለሁ ።» ማቴ. ፲፰ ፥ ፳ ።

የእስራኤል ልጆች ነገዶችም በማደሪያው ዙሪያ ተደረጉ ፤ ከምድሪቱም የተሰጣ ቸው የርስት አቀማመጥ በበረሃው ጉዞ ጊዜ በማደሪያው ዙሪያ እንደ ነበረው ዓይነት ነው ። ለእያንዳንዱም ነገድ ርስትና ክፍል እንደሚገባቸው ተሰጠ ። ለእኛም በክር ስቶስ የጸጋ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ ተሰጠን ። ጸጋ የሚሰጠው ሁልጊዜ እንደ ስጦታው መጠን እግዚአብሔር ለሰጠን ስጦታ የሚገባ ጸጋ እንጂ ለሰውዬው ተሰጥአና ችሎታ እንዲጠቅም ወይም ሰውዬው ለማድረግ የሚ ፈልገውን ነገር እንዲያስችለው አለመሆኑን እንረዳ ።

በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ ፲፯ እንደተጻፈው ስለ ዮሴፍ ልጆች አንዋኑዋርና የኑሮ ሁኔታ ስናጠና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ርስታችንን ለመውረስ እንድንከተለው የሚገባንን ሥርዓት ለማስተዋል እንድንችል ሐሳቤን ላጠቃልል ።

በመጀመሪያ ከሁሉ አስቀድመን ቅር የተሰኙበት ምክንያት እንመልከት ። ቁጥር ፲፬ እንዲህ ይላል «የዮሴፍ ልጆች ኢያሱን እኔ ብዙ ሕዝብ ስለሆንሁ እስከ አሁንም እግዚአብሔር ስለ ባረከኝ ለምን አንድ ክፍል አንድም ዕጣ ብቻ ርስት አድርገህ ሰጠኸኝ ? አሉት ።» ይህ ነገድ ለማማረር የተገደደበት ምክንያት ትልቅ ሕዝብ ስለ ነበረ ነው ። ስለዚህ የተሰጣቸው ክፍልና ዕጣ ለታላቅነታቸው ተገቢና ተስማሚ አልነበረም አሉ ። ያለፈው ዘመን በረከት የበለጠ ዋጋ ያስገኛል ብለው ተመኙ ። ለተሰጣቸው ቁራጭ ርስት የላቁና የበዙም እንደሆኑ አሰቡ ፣ ለማደግና ለመስፋፋት ለክርናቸውም ማስደገፊያ ተጨማሪ መሬት ፈለጉ ። በተጨማሪም ከቁጥር ፲፮ እንደ ምናነበው በተሰጠቻቸውም አነስተኛ ክፍለ ሀገር ከነዓናውያን ገና አሉ ። እነርሱም የብረት ሰረገሎች አሏቸውና የማይወገድ መሰናክል ነው አሉ ። ጠላት በአገሪቱ ይኖራል ።

እርግጥ ነው ፣ የዮሴፍ ልጆች ዮርዳኖስን ከተሻገሩት ሕዝብ ናቸው ። ምድረ ከነዓንን በመውጋትም ተካፍለዋል ። እንዲያውም የኢያሱ የራሱ ወገን ናቸው ። ኢያሱ የዮሴፍ ልጅ ከነበረው ከኤፍሬም ወገን ነው ። ስለዚህ የሚኩሩበት ምክን ያት ፣ መብትና ሥልጣንም አላቸው ። በዚህ ምክንያት ታላቅ ሕዝብ ነን ብለው አሰቡ ። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባውዛ አበራባቸው ። ከእግዚአብሔር ሠራዊት ውስጥ ለይቶ መቀበል የሚገባቸውን ትክክለኛ ዋጋ ይሰጣ ቸዋል ። «አይበቃንም» ብለው አጉረመረሙ ። የማጉረምረማቸውም ምክንያት መሠረቱ የከነዓናውያን በምድሪቱ ተንጀርግገው መኖር ነው ።

የአንድ ክርስቲያን ጠባይና ሁኔታ የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ወይም የክር ስቲያናዊ ማኅበር አባል በመሆኑ ሊፈረድና ሊረጋገጥ አይቻልም ። መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳችንን አጥብቆ ይመረምራል ፤ ልብና ኩላሊትንም ይበረብራል ። በመላው ዓለም እየዞርህ በብዙዎች የሚከበር ፣ የሚመሰገን ፣ የሚፈራና የታወቀ ቤተ ክርስቲ ያን ወይም ክርስቲያናዊ ድርጅት አባል መሆንህን ልታወራ ትችላለህ ። በእግዚአብ ሔር ፊት ግን እነዚህ ነገሮች የማይጠቅሙ ፈጽሞም ዋጋ የሌላቸው ሆነው ይታ ያሉ ። የእግዚአብሔር ብርሃን በነፍሳችን ላይ ሲያንፀባርቅ የነበረን የክብርና የዝና አክሊለ ብርሃን ከእኛ ይገፈፋል ። እግዚአብሔርም እያንዳንዳችንን ለየብቻ እንደሚ መረምረን እናገኛለን ። ታላቅነት ከቤተ ክርስቲያን አባልነት ወይም ኅብረት ክፍል የለውም ። ለእግዚአብሔር የሚያስደስት ታላቅነት ለቅድስና ኑሮ የሚደረግ የማያቋ ርጥ ትግል ነው ።

ይህ በዮሴፍ ልጆች የደረሰው ዛሬም በብዙዎች ሕይወት ውስጥ ተደጋግሞ ይደርሳል ። የዮሴፍ ልጆች በዕጣቸው አልተደሰቱም ። ለችሎታቸውና የተፈጥሮ ተሰጥኦዋቸው በቂና ተገቢ ዋጋ አላገኘም አሉ ። የሚያገለግሉበት ሰፊ የአገልግሎት

ስፍራና መብት ፈለጉ ። እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ ግን በተሰጣቸው ክፍል እንኳ ገና ጠላት ተንሰራፍቶ ይኖራል ።

የአንተም ቅርታ የዚሁ ዓይነት ሳይሆን አይቀርም ። ለችሎታህ ተገቢ ሥራ አላገኘህምን ? በተሰጠህ ፅጣ አልረካህምን ? ጌታን ለማገልገል የበለጠ ሰፊ ዕድል ለማግኘት ትወራጫለህን ? ልብህ በተለይ የወንጌል መልእክተኞችን ጣቢያ አተኩሮ ይመለከታልን ? የእግዚአብሔር ቃል ባውዛ በነፍስህ ውስጥ ጠላት ሥር ሰዶ ተንጀ ርግጎ እንዳለ ያሳይሃል ። እንዲያውም እግዚአብሔር የሰጠህን ርስት በሙሉ አልወ ረስክ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ይግለጥልሃ ።

«ከነዓናውያንም በምድሪቱ ይኑሩ» ጠላት በጣም በርትቶአል ። ዋናውም ቁም ነገር ልታስወጣቸው አልቻልክም ። ብዙ ጊዜ እንዲህ ትላለህ «ይህ ሁሉ ለእኔ ችሎታ አነስተኛ ስለሆነ ከቤቴ ራቅ ብዬ መሄድ ቢቻለኝ ፣ የጊዜውም ሁኔታ ትንሽ ልዩ ቢሆን ፣ ከዚህች አነስተኛ ሥራዬ ብላቀቅ ኖሮ ይሻለኝ ነበረ ። እግዚአብሔር የሰጠኝ ይህ ጠባብና አወናባጅ ዕድል ተስማሚዬ አይደለም ።»

ዛሬ እግዚአብሔር ሲናገርህ በሕይወትህ ያለው ችግር ለችሎታህ በቂ ወይም ተስማሚ ስፍራ ማጣትህ ሳይሆን ባለህበት ስፍራ በይበቃኛልነትና በሙላት አለመኖ ርህ መሆኑን አታይም ወይ ? ሰይጣን ምድሪቱን አብሮህ ይጋራል ። ስለ እርሱ ችላ ብለህ ለአንተ የእግዚአብሔር መንገድ ወይም ዓላማ ያልሆኑትን ትልልቅ ነገሮች ትፈልጋለህ ። የወደድከውን ያህል ወደ ልጓሙ ዛብ ልትንጠራራ ትችላለህ ፣ የእግዚ አብሔር መንፈስ ግን ያግድህና የቃሉን ባውዛ በሕይወትህ ያበራል ። ባለህበት ስፍራ በይበቃኛልነትና በሙላት እስክትኖር ድረስ ፣ በተሰጠህ የዕጣ ስፍራና አገልግ ሎት የተሟላህ እስክትሆን ፣ በክርስቶስም በልብህ እስክትፈጸም ፣ ጠላትም እስኪሸ ነፍ ድረስ በቆምህበት ቦታ እንድትቆይ ይይዝሃል ።

ይህን ሁሉ ችላ ብለህ የእግዚአብሔርንም ማገጃ ወርውረህ ልትጥል እንዱም ትችል የታወቀ ነው ፤ ጫፍዋን ብቻ በጥርስህ ይዘህ የእግዚአብሔርን የአመራር ሥር ዓት እምቢ ልትል ትችላለህ ፣ ወደ በለጠና የተሻለ ስፍራ ልትገባ ትችላለህ ፤ ለሚሲ ዮናዊ (የወንጌል መልእክተኛ) ማኅበር አመልክተህ ወደ ሌላ አገር ልትሄድ ትችላ ለህ ፣ ነገር ግን አሁን ባለህበት በመሟላት ባትኖር ፣ ወደ ተላክህበት አገር ስትደርስ በከባድ ኀዘን ጥላ ሥር ትሆናለህ ። መጨረሻውም ለአንተ ብቻ ሳይሆን ፣ ለሌሎችም አሳዛኝ ፍጻሜ ይሆናል ፣ ምክንያቱም ፣ ለላከህ ማኅበር ባይታወቅም ፣ ከአንተና ከእግ ዚአብሔር በቀር ማንም ባያውቅም ፣ በልብህና በአንዋኑዋርህ ያለው ጠላት ገና አል ተሸነፈም ፣ የድል ግርማም በሕይወትህ አልተገለጠም ፣ አልተውለበለበምም ።

በእግዚአብሔር ቃል ካላቸው ቅርታ የተነሣ እነዚህ ሰዎች የተሟላ አንዋኑዋር እንዲያገኙ እዚህ ላይ ታላቅ ጥሪ አለላቸው ።

አንድ ሰው «ይህን ተገንዝቤዋለሁ ፣ ደግሞ ይገባኛል ፤ ነገር ግን ይህ ሁሉ እን ደምን ይፈጸማል ?» ይለኝ ይሆናል ። እስቲ የግልን ኑሮ አሸንፎ ስለመኖር እንድት

ረዳ ላብራራልህ። ኢየሱ የቀረጼትን ቅርታ ምን እንደ አደረገ በቁጥር ፲፭ ላይ አስተውል «ብዙ ሕዝብስ ከሆንህ ወደ ዱር ውጣ፣ ለአንተም ስፍራ መንጥር» በዚህ አነጋገር ንቀት እንዳለበት እገምታለሁ። «ታላቅ ሕዝብ ነኝ ካልህ፣ ጽኑና ብርቱም ነኝ ብትል፣ በተሰጠህ ዕጣ ውስጥ ብዙ ያልተያዙ ስፍራዎች ሞልተዋል። ምንም ዱር ቢሆንም» አለ ኢያሱ «ዱሩን መንጥር፣ ዛፎቹንም ቁረጥ»

«እርሱስ ይሁን» አሉ፣ የዮሴፍ ልጆች «ይህ ሁሉ ደግ ነው፣ ነገር ግን ዱሩም ተመንጥሮ ስፍራው ገና አይበቃንም፣ ጠላትም በሸለቆዎቹ ተንሰራፍቶአል። ለእር ሱም የብረት ሰረገሎች አሉት»

«በጣም ጥሩ» አለ፣ ኢያሱ «እጅግ ታላቅ ሕዝብ ነህ አይደለምን? ይህን ያህል ታላቅ ኃይል ካለህ ተጠቀምበት። ተራራዎቹ የአንተ ናቸው። ዛፎቹን ቁረጡ! ሸለቆዎቹም ይሆኑልሃል» ይህ ሐሳብ በኢያሱ ፲፯፥፲፰ ይገኛል ለከነዓናውያንም የብረት ሰረገሎች ቢሆኑላቸው የበረቱም ቢሆኑ ታሰድዳቸዋለህ።»

ይህን ተስፋ አስቆራጭ መግለጫ አየህ ወይ? ከትልቅ ወገን ወይም ማኅበር ነን እንላለን፣ የእነዚህንም የክብር አክሊል ስላለን ታላቅ ሕዝብ ነን ልንል እንችላ ለን። «ደግ ነው» ይለናል ጌታችን «ትልቅ ነኝ ብለህ ታስባለህ፣ ጠላትን አስወጣ፣ በተሰጠህ ዕጣ ውስጥ ባለህበት ስፍራ ስለ ጠላትህ አሁን ምን በማድረግ ላይ ትገኛ ለህ?» የቃሉ ጥሪ ለውጊያና ለድል የማያቋርጥ፣ የማይራራ፣ የማያዳላና የማይታክት ነው። «ዛፎቹን ቁረጥ» ይላል። የእግዚአብሔር ቃል እምነት፣ የኃጢአትን ሥር መደብደብ አለበት። የደረቀው፣ የሞተውና የበሰበሰው እንጨት ተለቅሞ ወደ እሳት ይጣል። ያደረብን መንፈሱ አስፈላጊውን ኃይል ሁሉ ስለ አለው፣ አስቸጋሪ መስሎ የሚያፈጥብን ሁሉ ለእምነታችን ምላሽ እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደሚችል የሚያስረዱን ናቸው።

አዲስ ስፍራ፣ የተሻለ ዕድልና ለሥራው የተከፈተ ትልቅ በር ለምትፈልጉ ሁሉ ጌታ እንዲህ ይላችኋል። «እንዳታይ የሚጋርዱህ በሕይወትህ ያሉ ዛፎች ምን ይሆኑ? እድገትህን የሚያጨናግፉ ድልንም የሚነጥቁህ ዛፎች እንዴት ይደረጉ? ቁረጣቸው፣ መንጥራቸውም» የክርስቶስ መስቀል ወደ ኃጢአትና ርኵሰት ሁሉ ሥር ጠልቆ እንዲገባ ፈቅደህለታልን? በእንቅኑቀርህ ባሉ ዓመፃዎች ሁሉ ሥር ላይ ክርስ ቶስ ምሳሩን እንዲያሳርፍበት ጠይቀኸዋልን?

በረከታችንንና ድላችንን የሚሰርቁትን እነዚህን ነገሮች እያንዳንዳችን ለየግላችን እናውቃቸዋለን። ጌታ እንዲህ ይላል «ታላቅና ኃያል ሕዝብስ ከሆንህ በኃይልህ ተጠቀም፣ የቃሉንም ምሳር በሕይወትህ ባለው ኃጢአት ሥር አሳርፍበት» ይህን ትምህርት እስከንማር ድረስ ታማኞች የምንሆንበት ከዚህ የበለጠ የአገልግሎት ችሎታ የለም፣ ከዚህ የተሻለ ዕድልም የለም። እግዚአብሔር በኖረህና በሰጠህ ስፍራ የሚገባህን ከማድረግህ በፊት ለተሻለ ዕድል አታልቅስ። ክርስቲያን እንደመ ሆንህ ትዳርህ ጣፋጭ፣ ተወዳጅና ግልጽ ብሩህም ነውን? እንደዚህ ካልሆነ፣ እንዳይ

ሆን በሚከለክለው ሁሉ ሥር ላይ ምሳሩን አሳርፍበትና ቁረጠው። ጠላትን አስወጣ፣ አባርር። በተሰጠችን አነስተኛ ክፍል ማሸነፍ ከልቻልን እግዚአብሔር ለበለጠ ነገር ከቶ አያምነንም።

በመስቀሉ ምክንያትና ብርሃን ብናይ፣ ለመሆኑ ጠላት በምድሪቱ ሊኖር መብት አለው ወይ ? በነፍስህ ያለው መብቱ በቀራንዮ አልተወሰደበትምን ? በእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት ውስጥ ኃጢአት የእግሩ መረገጫ የምታህል ርስትና መብት የሌለው መሆኑ እውነተኛ ነገር አይደለምን ? ሁሉን ቻይ አምላክ በአለበት ሰይጣን አቅም የሌለው መሆኑ እውነተኛ ነገር አይደለምን ? በደሙ፣ በሞቱና በትንሣኤው ምክን ያት ጠላትን ፈጽሞ እንዲያጠፋ ለክርስቶስ መብትና ሥልጣን አልተሰጠውምን ? በሚያድርብን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እያንዳንዱን ፈተና ለማሸነፍ ጉልበት፣ ለእያን ዳንዱም ሥቃይ ጸጋ፣ መከራንም ሁሉ ለማሸነፍ ኃይል አልተሰጠንምን ?

እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር ይመስገን ታላቅ ሕዝብ ነን፣ ሆኖም የዮሴፍ ልጆች በሰቡት ዓይነት አይደለም። እነርሱ፣ ስለ ታላቅነታቸው፣ ዝናቸውና ወገና ቸው ታላቅነታቸውን ገመቱ። እኛ ግን በልባችንና በሕይወታችን የክቡር ጌታችን ኃይል፣ ሥልጣንና የበላይ ነኸነት አለ። አሁን የቆምክበትን በኃይሉ አሸንፈህ፣ ባለህበት ስፍራ ያለውንም ጠላት ስታሸንፍ፣ ዕድልህን ያስፋፋል። ከበለጠ የአገል ግሎት ዕድል ጋር የእግዚአብሔር ኃይል ምንጭ የበለጠውን ይጨመርበታል። እግዚአብሔር ዕድላችንን ቆጥቦ፣ ወስኖ የሰጠን፣ እኛ የተወሰነና የተቆጠበ ጸጋ ስለ ጠየቅነው ይመስለኛል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚደረገው ሥራ ሁሉ የሚስማማና የሚበቃ ጸጋ አለ።

ክርስቲያን፣ ለክርስቶስ ያለውን ችሎታውን እንዲያሟላለትና እንዲያስፋለት የልቡ ጸሎት «አምላኬ ሆይ፣ እንደ መድኃኒቴ አድርገኝ» የሚል እንዲሆን ይጸ ልይ። መንፈስ ቅዱስ ችሎታውን እንዲጨምርለት ክርስቲያን ይጸልይና የተጨመ ረለት ጸጋ የበለጠ ዕድል እንደሚሰጠው ይገነዘባል። ይህን አድራጎት አየህ ወይ ? ለሚያድርብህ ለክርስቶስ ችሎታህ የማይሰፋና የማይስፋፋ እንዳይመስልህ ላስታው ስህ። ክርስቶስ በእኛ የማደሩ ችሎታ እንደ ላስቲክ ይወጠራል ይሰፋልም። ዓመታ ቱም እየጨመሩ ሲሄዱ እርሱም ይጨምራል።

በቅርብ ጊዜ የሮቤርት ሙሬይ ማክ ቼይንን ማስታወሻዎች ሳነብ ነበርሁ። ይህ ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው በሰላሣ ዓመት ዕድሜው ሞቶ ወደ ክብር ስፍራ ከመሄዱ በፊት ስለ ሥራውና አገልግሎቱ የሚገልጽ እጅግ ብዙ መጻሕፍት ጽፎ ትቶልናል። ማክ ቼይን እንዲህ ሲል ጸለየ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ልቤና አእምሮዬ እንደ ወንድምና እህት እየተደጋገፉና እየተቃቀፉ አንድነት ይደጉ፣ በዘመ ኑም የልቤ ስፋት ችሎታና የአእምሮዬ ማስተዋል እየጨመሩ ይሂዱ» ይህ በእያንዳ ንዱ ክርስቲያን ሕይወት ሊደርስ የሚገባና ደግሞም የሚደርስበት የተባረከ እውነተኛ ነገር ነው። አንዳንዶች ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልተናል ይላሉ። ወዳ ጆቼ ሆይ፣ ይህ ብሩክ እውነተኛነት ነው። ሁላችንም ከልባችን እንዲሁ እንድንል

ባለው ኃጢአት ሥር ላይ ምሰር የማያኖርና ከጌታው በመተሳሰር በመንገዱ ሁሉ አብሮት መራመድን እምቢ የሚል ሰው በመንፈሳዊነቱ እያነሰ ይሄዳል። ለሕይወት ያለው ችሎታ እየሚሸሸ ይሄዳል፣ በእርሱም ያለው ጸጋ መገለጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰ ይሄዳል። እንዲህ ያለ ሰው ኢያደገና እየጨመረ የሚሄደው በራሱ ግምትና ታላቅነት ብቻ ነው።

የሚያድገውን ክርስቲያን እይ! ራስህ ስታድግ ተመልከት፤ የዚህን መልእክት ሥራና ሥልጣን በዚሁ ዘመናችንና በሕይወታችን ካላገኘን በመንፈሳዊነታችን እንጠወልጋለን። የክርስቲያን ዕድገት የሚገኘው በመንፈሳዊነት በመስፋፋት፣ የበለጠ ጸጋ በመቀበል፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስም ለበለጠ ሥራ ዕድልና ምስክርነት ስንታመን ነው።

## ምዕራፍ ፲፰።

# የምንጠነቀቃቸው አደጋዎች ።

### ኢያሱ ፲፰ ፣ ፫ ።

«የእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ በሴሎ ተሰበሰቡ፣ በዚያም የመገናኛውን ድንኳን ተከሉ። ምድሩም ጸጥ ብሎ ተገዛላቸው። ከእስራኤልም ልጆች ርስት ያልተከፈሉ ሰባት ነገድ ቀርተው ነበር። ኢያሱም የእስራኤልን ልጆች አላቸው ፡— የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር የሰጣችሁን ምድር ትወርሱ ዘንድ እስከ መቼ ለመግባት ቸል ትላላችሁ ?» ኢያሱ ፲፰ ፣ ፩ — ፫ ።

«እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ተናገራቸው ፡— ሳይወድድ ሳያውቅም ሰውን የገደለ ገዳይ እንዲሸሽባቸው በሙሴ እጅ የነገርኋችሁን መማፀኛ ከተሞችን ለዩ፣ ከደም ተበቃዩ መማጸኛ ይሆኑላችኋል። በከተማይቱም በር አደባባይ ቆሞ በከተማይቱ ሽማግሌዎች ጆሮ ነገሩን ይናገራል። እነርሱም ወደ ከተማይቱ ይቀበሉታል፣ የሚቀመጥበትም ስፍራ ይሰጡታል። ደም ተበቃዩ ቢያሳድደው፣ አስቀድሞ ሳይጠላው ባልንጀራውን በስሕተት ስለ ገደለው ነፍሰ ገዳዩን በእጁ አሳልፈው አይስጡት። በማኅበሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ፣ በዚያም ወራት ያለው ታላቁ ካህን እስኪሞት ድረስ በዚያች ከተማ ይቀመጥ፤ ከዚያም ወዲያ ነፍሰ ገዳዩ ይመለሳል፣ ወደ ከተማውም ወደ ቤቱም ሸሽቶ ወደ ወጣበትም ከተማ ይገባል» ኢያሱ ፳ ፣ ፩ — ፮ ።

«የሮቤልም ልጆች የጋድም ልጆች የምሴም ነገድ እኩሌታ ሄዱ። በሙሴም እጅ በተሰጠ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ተቀበሉአት ወደ ርስታቸው ወደ ገለዓድ ምድር ይገቡ ዘንድ በከነዓን ምድር ካለችው ከሴሎ ከእስራኤል ልጆች ዘንድ ተመለሱ። በከነዓን ምድር ወዳለው ወደ ዮርዳኖስ አቅራቢያም በመጡ ጊዜ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም ነገድ እኩሌታ በዚያ በዮርዳኖስ አጠገብ ታላቅ መሠዊያ ሠሩ። ...... በገለዓድም ምድር ወዳሉት ወደ ሮቤል ልጆችና ወደ ጋድ ልጆች ወደ ምናሴም ነገድ እኩሌታ መጡ፣ እንዲህም ብለው ተናገሩአቸው ፡— የእግዚአብሔር ማኅበር ሁሉ የሚለው ይህ ነው ፡— ይህ በእስራኤል አምላክ ላይ ያደረጋችሁት ኃጢአት ምንድር ነው ? ዛሬ እግዚአብሔርን ከመከተል ተመልሳችኋል። ዛሬም መሠዊያ በመሥራታችሁ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፃችኋል። .... የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም ነገድ እኩሌታ ለእስራኤል አእላፋት አለቆች እንዲህ ብለው መለሱላቸው ፡— የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር፣ የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር እርሱ አውቆታል፤ እስራኤልም ያውቀዋል። በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀንና ተላልፈን እንደሆነ ዛሬ አታድነን። እግዚአብሔርን ከመከተል እንድንመለስ፣ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህልን ቁርባን እንድናሳርግበት፣ የደኅንነትንም

መሥዋዕት እንድናቀርብበት ብለን መሠዊያ ሠርተን እንደሆነ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ይበቀለን። ይልቁንም ከልባችን ፍርሃት የተነሣ በሚመጣው ዘመን ልጆቻችሁ ልጆቻችንን ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር ምን አላችሁ ? እናንተ የሮቤልና የጋድ ልጆች እግዚአብሔር በእኛና በእናንተ መካከል ዮርዳኖስን ድንበር አድርጎአልና በእግዚአብሔር ዘንድ እድል ፈንታ የላችሁም ይሉአቸዋል ብለን ይህን አደረግን። በዚህም ልጆቻችሁ ልጆቻችንን እግዚአብሔርን ከመፍራት ያስተውአቸዋል። ስለዚህም መሠዊያ እንሥራ አልን፤ ነገር ግን ለሚቃጠል መሥዋዕት ወይም ለሌላ መሥዋዕት አይደለም። ነገር ግን በእኛና በእናንተ መካከል ከእኛም በኋላ በትውልዳችንና በትውልዳችሁ መካከል በሚቃጠል መሥዋዕትና በቁርባን በደኅንነትም መሥዋዕታችን እግዚአብሔርን እናመልክ ዘንድ በሚመጣውም ዘመን ልጆቻችሁ ልጆቻችንን በእግዚአብሔር ዘንድ ዕድል ፈንታ የላችሁም እንዳይሉ ምስክር ይሆናል። .... የካህኑም የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስና አለቆቹ ከሮቤል ልጆችና ከጋድ ልጆች ዘንድ ከገለዓድ አገር ወደ ከነዓን አገር ወደ እስራኤል ልጆች ተመለሱ፣ ወሬም አመጡላቸው። ነገሩም የእስራኤልን ልጆች ደስ አሰኘ። የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔርን አመሰገኑ፣ ከዚያም ወዲያ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የተቀመጡበትን ምድር ያጠፉ ዘንድ ወጥተው እንደወጉአቸው አልተናገሩም። የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆችም እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ይህ በመካከላችን ምስክር ነው ሲሉ መሠዊያውን ምስክር ብለው ጠሩት» ኢያሱ ፳፪፥፱፥፲፥፲፮፥፳፮—፳፯፥፴፪—፴፬።

ከመጽሐፈ ኢያሱ በዚህ ክፍል የከነዓንን ምድር ለመውረስ በእግዚአብሔር ሕዝብ የተደረገው የሰባት ዓመት ውጊያ አልቆአል። ዮርዳኖስን ተሻግረዋል፣ ኢያሪኮም ተሸንፋለች፣ ጠላትም ድል ሆኖ ምድሪቱም ለየነገዱ ተከፋፍላለች። አሁን ግን ከሁሉም ነገር የበለጠ ጉዳይ ገጠማቸው። በአገሪቱ እንደምን እንደሚኖሩ ከላወቁና ከልኖሩ በሕሩን መሻገር፣ ጠላትንም ማሸነፍ ሁሉ እንደ ጭንጋፍ ይቆጠራል።

ስለ እስራኤል ልጆች እውነት የነበረው ሁሉ ዛሬም ለክርስቲያኖች ሺህ ጊዜ እውነተኛና የሚደርስባቸው ነገር ነው። የክርስቲያን ሕይወት የተከታታይ ውድቀትና ስሜታዊ መነሣት መፈራረቂያ እንዲሆን አልታሰበም። እንደ እግዚአብሔር ዓላማ ከሆነስ የክርስቲያን ሕይወት ሳያቋርጥ በማሸነፍ ወደ ፊት ወደ ግቡ የሚገሠግሥ፣ እግዚአብሔር ራሱ የሚኖረው እንዲሆን ታስቦአል። እርግጥ ነው፣ ከመሠረቱ አንዳንድ ውድቀቶች አይጠፉም፣ ዮርዳኖስን መሻገር አለ፣ የመሸነፍ ምድረ በዳ ለድልና ለበረከት አገር ስፍራ መልቀቅ አለበት። ጠላት ድል መሆን አለበት፣ ክርስቲያን የነፍሱን ጠላት በየቀኑ እያሸነፈ መኖርን መማር ይገባዋል።

ከሁሉም የሚበልጠው ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ሙሉ በረከት ወዳለበት አገር ከገባ እዚያው እንዲኖር መማር ይገባዋል። እንደማምነው ሁሉ፣ ከመንፈስ ቅዱስ በእውነት አዲስ የተወለደና በክርስቶስ ደም የተዋጀ የእግዚአብሔር ሰው ለዘላለም የዳነ ቢሆንም ከከነዓን ወደ ምድረ በዳው ይመለስ ይሆናል። ለጥቂት ጊዜ በደህና ሮጦ ዮርዳኖስን ይሻገራል። ከክርስቶስ ጋር ሞቶ፣ ተቀብሮም እንደ ተነሣ

ያምናል። ነገር ግን የተረፈውን እንዋኑዋሩን በግብፅ ድንበር ላይ ይፈጽማል። ክርስቲያን በምድረ በረከት እንደምን ጸንቶ መኖር እንደሚገባው መማር በጣም አስፈላጊ ነው።

ባለፈው ምዕራፍ በሙላት ስለመኖር በተነጋገርን ጊዜ አንዱን ትምህርት እንዳ ገኘን አምናለሁ። አንዱን ቀን በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልተን በሚቀጥለው ደግሞ ከሙላቱ የበለጠ እንድንቀበል፤ ለክርስቶሳዊ ሕይወትም በውስጣችን ማደር ማዳበሪያ የሆኑትን በየቀኑ ለክርስቶስ መታዘዝና በእርሱም መታመን መሆናቸውን አየን።

የመጽሐፈ ኢያሱ ቀሪው ክፍል በምድረ በረከት እንደምን እንደሚኖሩ የሚገ ልጹ ሦስት ልዩ ምሥጢሮችን ይዘአል። ከምዕራፍ ፲፰ እስከ ፳፪ ስለምንጠነቀቃቸ ውና ስለምንከላከላቸው አደጋዎች ይነግረናል። ምዕራፍ ፳፫ የምንከተላቸውን ሥር ዓቶች ይነግረናል። የመጽሐፈ ኢያሱ የመደምደሚያው ክፍል፤ ምዕራፍ ፳፬ በዚ ያች አገር ወርሰን የምንደሰትባቸውን ጥቂቶቹን ታላላቅ መብቶችና ክብሮች ተድላዎ ችም ይገልጻል።

በእነዚህ ምዕራፎች ለክርስቲያን ኑሮ የሚሆኑ ታላላቅ ሥርዓቶችን እንደተማርን አምናለሁ። እነርሱም፤ የድልን መንገድና ሙሉ በረከት ወዳለበት ምድረ በረከት የሚመራውን መንገድ ነው። ክርስቲያን ባለፉት ክንውኖችና በአሁኑ የችሎታ ታላ ቅነት መታመን አይገባውም። እነዚህን ሁሉ በየቀኑ በሚደርስብን ደደብነት መለወጥ አለበት። ሚሲዮናዊ (የወንጌል ሠራተኛ) መማር ከሚገባው ታላላቅ ትምህርቶች ይህ አንዱ ነው። ልብን በሚመስጥ መሰነባበቻ የትውልድ አገራቸውን ለቅቀው የሚሄዱና ማድረግም የሚገባቸው ለክርስቶስ ታጥቀው ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ መም ራት ነው የሚሉት አብዛኛውን ጊዜ ወደ ተላኩበት ባዕድ አገር ሲደርሱ ልባቸውን በሚያነሳቁል የልቡና ጨለማ እንደሚነሰሙና እንደሚጠቁ የታወቀ ነው። አብዛ ኛው ጊዜአቸውም በየቀኑ የሚናገሩትን ማለት የሚሰብኩትን በማዘጋጀት እንደሚብ ክንና እርሱንም ካላዘጋጁ ትምህርታቸው ፍሬ ቢስ ሆኖ እነርሱም ከግባቸው ሳይደ ርሱ እንደሚቀሩ ያገኙታል።

እግዚአብሔር ከአገሪቱ ውስጥ የትም ስፍራ ቢያኖረን እንደምን በበረከት አገር መኖር እንደሚቻለን ማወቅ ተገቢ ዓላማችን ይሁን። እውነተኛውን የክርስቲያን ኑሮ የሚኖረውን ክርስቲያን መገናኘት የማይታሰብ የልብ ደስታን ይሰጣል። ልብን የሚመስጥ ደስታ የሆነበት ምክንያትም አልፎ አልፎ የሚታይ እንግዳ ነገር በመሆኑ ነው። በደኅንነቱ የሚደሰተውንና በተሟላ መንፈሳዊ ኃይል በእውነት የሚኖረውን ክርስቲያን መገናኘት ብቻ ራሱ ትልቅ በረከት ነው። በአገሪቱ እየኖርን በሙሉ እንድንደሰትበት ከሆነ፤ በክርስቲያንነት ኑሮም ክብርና ተድላ የሚቻሉ መሆናቸውን ከተረዳን ሁላችን ልንከላከላቸውና ልናስወግዳቸው የሚገባንን ሦስት አደጋዎች (መከራዎች) እነግራችኋለሁ።

በዚህ ዓለም የተከበረ ትዝታ የምትሰጠኝ አንዲት ትንሽ የመሬት ቁራጭ አለች። እርስዋም ሰማንያ ማይሎች የምትረዝም በእንግሊዝና በእስኮትላንድ ዳርቻ በስተደቡብ ትገኛለች። እዚያ በዱሮ ዘመን በእንግሊዝ አገር የሮሚ መንግሥት ወሰን በነበረችው በሃድሪን መንደር ቅጥሮች ፍርስራሽ ውስጥ ትራመዳለህ። የሮሚ ጦር ኃይል እዚያ በደረሰ ጊዜ በዚያን ዘመን የተደረጉትን ታላላቅ ድርጊቶች በአእምሮህ እንደ ሥዕል ልትሰበስብ ትችላለህ።

በዚያም ቀበሌ ትንሽ ተዘዋውረህ ብትጎበኝ ብዙ ያረጁና የወደቁ ግምቦች ታያለህ። ከእነርሱም አንዳንዶቹ ወድቀዋል፤ ጥቂቶች ግን በዚያን ዘመን እንደነበሩ ሆነው ተጠብቀው ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ሲፈርሱ ጥቂቶቹ ለምን ተጠብቀው አምረው ይገኛሉ ብለህ ብትጠይቅ የሚከተለውን መልስ ታገኛለህ። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት እንግሊዝና እስኮትላንድ መራራ ጥል ነበራቸው፤ በኖር ዘምበርላንድ የሚኖሩ እንግሊዛውያንም በስኮትላንድ ዜጎች ብዙ ጊዜ ተጠቁ። አጥቂዎቹም ከብቶቻቸውንና እህላቸውን ሁሉ ዘርፈውባቸው ወደ ግዛታቸው ይመለሱ ነበር። ስለዚህ ተጠቂዎቹ እንግሊዛውያን ሊከላከሉአቸው በግዛታቸው ድምበር ግምቦችና ምሽጎችን ሠሩ። ከእነዚህም ግምቦች አንዳንዶቹ የማያቋርጡ ምሥጢራዊ የውኃ ምንጮች ነበሩአቸው። ሌሎቹ ግምቦች ከብዙ ማይሎች ርቀት ውኃቸውን በቧንቧ ያገኙ ነበር። የእስኮትላንድ ወራሪዎች ግን የሚያደርጉትን የሚያውቁ ብልጦች ነበሩ። ቧንቧዎቹን ቆረጡና ከተማዋን ከብበው ነዋሪዎችዋን በረሃብና በውኃ ጥም እስኪያልቁ ጠበቁ። በግምቦቻቸው ምሥጢራዊ ምንጮች የነበሩአቸው ግን አልተደፈሩም። እነዚህም ግምቦች የአለመደፈራቸውን ማስታወሻ ይዘው እስከ ዛሬ ቆመዋል። ሌሎቹ ግምቦች ግን ፈርሰው ወደቁ ተደመሰሱ ጠፉም።

እያንዳንዳችን በውስጣችን የሕይወት ምንጭ አለን። ነገር ግን እነዚህ ምንጮች በውስጣቸው መኖራቸውን ያልገለጡ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ብዙዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚፈልጉትን ለማግኘት ከራሳቸውና ከቤታቸው ውጪ ይቅበዘበዛሉ። ለጨዋታ፥ ለመደሰት፥ ለሰላም፥ ለምቾት፥ ለተድላ፥ ለዘመኑ ብልጭልጭና መደሰቻ ሲሉ ከራሳቸውና ከቤታቸው ውጪ ይዞራሉ። ብዙም ሳይኖሩ የክርስቲያንነት ሕይወታቸውና አቋማቸው ይፈርሳል፤ ይወድማልም። አገሪቱ የምትወርስበትና እግዚአብሔርም በክርስቶስ የሰጣቸውን ጸጋ የሚያገኙበት መንገድ በሕይወታቸው ከለው ከማያቋርጥ የሕይወት ምንጭ ዘወትር መጠጣት መሆኑን የተረዱ የእግዚአብሔር ልጆች ግን አሉ። ኢየሱስ ብቻ ሊያረካና ሊያጠግብ እንደሚችል ከሙሉ ልባቸው ሊናገሩ ይችላሉ።

የነገሩ አስቸጋሪነት ግን ወደ አገሪቱ ገብቶ መውረስ ራስን መካድና የምናፈቅራትን አንዲት ጠባይ ወይም ዐመል መተው እንደሚጠይቅ ስለ ተረዳን ወደ ምድረ በረከት እንዳንገፋበት እንፈራለን። ወደ ኋላችንም እናፈገፍጋለን። የኑሮን ምቾት፥ ከዓለማውያን መቀራረባችንንና ሌሎቹ እንዴት ያሉ ከሰው የተለዩ ሰዎች ናቸው? እንዳይሉን የምንፈራውን ይሉኝታ ሁሉ ማስወገድ አለብን። እግዚአብሔር ያዘጋጀ

ልንን ለመውረስ እንዳንቀሳቀስ መንፈሳዊ ቸልተኞችና ሰነፎች የሚያደርጉን እነዚህ ነገሮች ናቸው ።

ባለፉት ክንውኖች የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት ቸል ብሎ ሊኖር ይደፍራል ? ይህን በማድረጉ የእግዚአብሔርን በረከት ከራሱ ከማራቁም በላይ ሌሎችን ሰዎች ይከለክላል ፣ ሰይጣንንም ያደፋፍራል ። ሊተነፍስ ከቆመ ማንም ክርስቲያን በሩጫው ሊያሸንፍ አይችልም ። በውጊያ ወቅት ዕረፍት የሚጠይቅ በጦርነቱ ድል ሊያደርግ አይችልም ። ከእግዚአብሔር ጋር ከመራመድ ለአንዲት ደቂቃ ነፃነት ወይም ስንብት ለመጠየቅ ማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ አይችልም ። ሽልማቱ በጭብጣችን ግቡም ልንደርስበት የሚቻል ሆኖ ሳለ ፣ ብዙዎቻችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለእኛ የሆነውን ድልና የተሰጠንን ሁሉ ከመቀበል የራቅን መሆናችንን መረዳት እን ዴት የሚያሳዝን ነው ። እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን ለመቀበል ስላልገፋንበት አጣ ነው ። በቸልተኝነትና በዝግተኝነት ተሸነፍን ።

ክርስቲያኖች ሆይ ፣ በየእሁዱ ጧት ጧት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሄዳችሁና እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ ከተማፀናችሁት ምን ያህል ጊዜ ሆኖአል ። አሁንም ትሄድ እንደሆነ የተሰጠህን ጉዳይ ለመፈጸም ብቻ ነው ። ለመዘመር ፣ የሰንበት ትም ህርትን ልትመራ ፣ ማስታወቂያዎችን ልትነግር ፣ ፈንታህን ለማድረግና ለመስበክም ይሆናል ። ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርክህ ። ነገር ግን በመንፈሳዊ ቸልተኝነትና ንዝላልነት እንዳትዋጥ ተጠንቀቅ ። ባለፉት ዘመናት ታላላቅ ነገሮችን የፈጸመ አም ላክ ዛሬም እንደሚፈጽም ከመጠባበቅ አታቋርጥ ። የሰዎችን ልብ ረሃብ ብንገልጥና እርሱ ወደ አዘጋጀልን ብንገፋ እርሱ ሁሉን ለማድረግ ይችላል ። አብዛኛውን ጊዜ ችግራችን ስንፍናና ታካችነት ቸልተኝነትም ነው ። «ምን ቸገረኝ ? ይህን ዓመታት እምብዛም አልጨነቅም» ወይም ደግሞ «ይህ ሁሉ ለሌሎች ሰዎች ፣ ለወጣቶችና ለልጆች ይጠቅማል ጥሩም ነው ግን ለእኔ አይደለም» እንላለን ። ክርስቲያን ወዳ ጆቼ ሆይ ፣ እስከ መቼ ድረስ ነው ? እግዚአብሔር በኢየሱስ የሰጣችሁን ሳትወርሱ እስከ መቼ ድረስ ቸል ትላላችሁ ? እንዴት ያለ መከላከል የሚገባን አደጋ ወይም ጉድለት ነው !

ሁለተኛው አደጋ ወይም ጉድለት በኢያሱ ምዕራፍ ፳፪ ተጽፎአል ። እርሱንም አለመግባባት ብዬ እሰይመዋለሁ ። ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ ታውቃለህን ? ከሌ ሎች ሰዎች ተስማምቶ ፣ ተግባብቶና ተባብሮ አለመኖር ማለት ነው ።

በአንድ ወይም በሁለት ዓረፍተ ነገሮች ታሪኩ እንዲህ ነው ። ሁለት ተኩል ነገዶች የሆኑ የሮቤል የጋድ ነገዶችና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ከሰባት ዓመታት በፊት ከወንዙ በሌላው ወገን ማለት ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ በምድረ በዳው ድምበር ለመኖር ወስነው ነበር ። ኢያሱም በአንድ ነገር ከተስማሙ እንደሚቻላቸው ነገራቸ ውና በሐሳባቸው ተስማማ ። ማድረግ የሚገባቸውም ይህ ነበር ። ከሌሎቹ ወንድሞ ቻቸው ጋር ወደ ከነዓን ይገባሉ ። ጠላትንም ለማሸነፍ ይረዳሉ ። ከዚያ በኋላ ወደ

መረጧት ግዛት ይመለሳሉ ። ኢያሱም ስለ ቸርነታቸው ፥ ደግነታቸውና ወንድሞቻ ቸውንም አገሪቱን ሲወጉ ለመርዳት በአንድ መንፈስ ስለ ተባበሩ አመሰገናቸውና በሚወርሱአት ግዛትም የእግዚአብሔር በረከትና ባለጠግነት እንዲከተላቸው መመኘ ቱን ገለጸላቸው ።

በምዕራፍ ፳፪ ቁጥር ፳፬ እንደተጻፈው ወደ ርስታቸው ለመሄድ የተለዩ ነገዶች ወደ ወንዙ ዳር በመጡ ጊዜ እንዲህ አሰቡ ። «እስቲ አሁን ተመልከቱ ፥ ይህን ዮርዳ ኖስን ተሻግረን ማዶ ስንደርስ ልጆቻችንና የኋለኛውም ትውልዶች እንዲህ ይላሉ ። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ ምን አላችሁ ? እነርሱ እዚያ ማዶ ናቸው ፥ እናንተም እዚህ ናችሁ ። ከእነርሱ ክፍል የላችሁም ፥ አልተዋጋችሁም ፥ ጠላትን ለማሸነፍም አልረዳችሁም ፥ ታዲያ ከእስራኤል ሕዝብ ምን አገናኛችሁ ?» ስለዚህም ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ በወንዝ ዳር መሠዊያ ተከሉ ። መሠዊያውም ለመሥዋዕት አልነበረም ። ነገር ግን ከዮርዳኖስ በሌላው ወገን ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋር አንድ ለመሆናቸው ምስ ክር እንዲሆን ነው ።

ሌሎቹም ነገዶች የሆነውን በሰሙ ጊዜ የተሳሳተ ትርጉም ሰጡት ። የተሠራው መሠዊያ ለስግደትና ለመሥዋዕት ነው ፤ በእግዚአብሔም ሕዝብ መካከል መለያየትን ያሳያል ፥ እነዚህም የተለዩት ሁለት ተኩል ነገዶች ከሃዲያን መሆናቸውን ያሳያል ። ከእንግዲህም በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀው ፥ ከሕጉም ተለዩ እንጂ እርሱን አያመል ኩም ብለው አሰቡ ። በእግዚአብሔርም ሕዝብ ልብ ክህደት ገባ አሉ ። ስለዚህ ከኢያሱ ጋር በከነዓን የቀሩት ነገዶች ከሃዲያን የመሰሉአቸውን ነገዶች ለመውጋት ተዘጋጁ ።

ነገር ግን ከመዋጋት በፊት ሮቤልናውያን ጋዳውያንና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ምን እንደሚያደርጉ ለማወቅና በግልፅ ሊገሥፁአቸው መልእክተኞችን ላኩባ ቸው ። መልእክተኞቹም ስለ ክህደታቸው ፥ አለመታመናቸውና በእግዚአብሔርም ስለ ማመፃቸው ከሰሱአቸው ። በዚህ አድራጎታቸውም ከቀጠሉ በእነርሱና በእስራ ኤልም ሁሉ መካከል የሚደርሰውን አደጋና ጉዳት ነገሩአቸው ። እነዚያም ሁለት ተኩል ነገዶች ሐሳባቸው ከንጹህ ሕሊና መሆኑን ፥ የሠሩትም መሠዊያ ለምስክርነት እንጂ ለስግደትና ለመሥዋዕት እንዳልነበረ ለመልእክተኞቹ ማስረዳትና ማሳመን አላስቸገራቸውም ። ለሌላ አምላክ ሊሠው አይደለም ። ነገር ግን ከሌሎቹ ወንድሞ ቻቸው ጋር ላላቸው ኅብረት ምስክር ማቆማቸው ነበረ ። ይህ ሐሳባቸውም ንጹህና ቅዱስ የፍቅርም እንደ ነበረና ሌሎቹም በሐሳባቸውና በፍርዳቸው ትክክለኞች እንዳ ልነበሩ ያስረዳል ። በሚያሳዝን ሁኔታ ሊፈጸም የነበረው በእውነቱ በበለጠ የወንድ ማማችነት ኅብረት ተፈጸመ ።

ከዚህ ላይ እንዴት ያለ ጠቃሚ ትምህርት እናገኛለን ? ክርስቲያን ከክርስቲያን ጋር በለመስማማት ፥ በለመተባበርና ባለመግባባት እንዴት ያለ አደጋና ጉድለት ያለ ይመስላችኋል ! እንዴትስ ያሉ ጎጂ ውጤት ያላቸው አለመግባባቶች አሉ ! በእነዚህ

በዚህ ምዕራፍ የመማፀኛ ከተሞችን መሠራት ታስታውሳለህ። እነርሱም ከወ ንዙ ወዲህ ሦስት፣ ከወንዙም ማዶ ሦስት፣ በጠቅላላው ስድስት ናቸው። በአገሪቱ (በከነዓን) የሚኖሩና ሁለት ተኩል ነገዶችም በቀላሉ ሊደርሱባቸው የሚቻሉ ከተ ሞች ነበሩ። ሳያውቅ ሳይወድም በንዝህላልነት ሰውን ለገደለ ሁሉ የመማፀኛ ስፍራ ዎች ነበሩ። ለዚህም የተሟላ ማብራሪያውን በአራት ዘዳግም ምዕራፍ ፲፱ ታገኛለህ። ለጊዜው ግን የንዝህላልነት ወይም ድንገተኛ ኃጢአት፣ ያልታሰበ መተላለፎች፣ በከፉ ምኞት ያልተፈጸሙ በደሎች ምሕረት እንደነበራቸው መናገሩ ብቻ ይበቃል። ይህን ዓይነት በደል የፈጸመ ሰው ሁሉ ከበቀል እንዲድን ወደ መማፀኛ ከተሞች ይሸሻል። እዚያም ሌዋውያን ይመረምሩታል። በሠራውም ወንጀል ከሐሳቡ የመ ነጨ ተንኮልና ቂም እንደ ሌለበት ቢረጋገጥ በዚያን ዘመን ያለው ሊቀካህናት እስኪ ሞት ድረስ በመማፀኛ ከተማ እንዲኖር ይፈቀድለታል። ከዚያ በኋላም ያለ ሥጋት ወደ አገሩ ለመመለስ ነፃ ይሆናል።

ከኃጢአቶቻችን አብዛኞቹ በንዝህላልነት እንደሚፈጸሙ ለማሰብ ትንሽ ጊዜ ረጋ ብለህ ታውቃለህን? ከፍጹሙ የእግዚአብሔር ቅድስና የማይገጥም ሁሉ ራሱ ኃጢአት መሆኑን አስተውለናልን? በለመጠንቀቃችን፣ በችኩልነታችንና ከሌሎች ክርስቲያን ወንድሞችም በለመግባባታችን ዘወትር እንደምናሳዝነው እናስተውላለን ወይ? አስበን ያደረግነው ላይሆን ይችላል፤ ሆኖም በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ኃጢ አት ነው። ስለ ይቅርታውና ስርየቱ እንዴት ማመስገን የሚገባን ይመስላችኋል!

ዛሬ ወደ ምንጩ ሄደን ከኃጢአታችን ታጥበን ልንነፃና፣ ሌሎችንም በንዝህላ ልነት ሳናውቅ ስለ ጎዳንና ስላቆሰልን ስላሳዘንንም ይቅርታ ልንቀበል እንችላለን። የመማፀኛ ከተማችን የተወጋው የኢየሱስ ጎን ነው። ሊቀ ካህናታችንም የሞተውና ከሙታንም የተነሣው ነው። ወደ መማፀኛ ከተማችን ሄደን መተላለፋችንን ተናዝ ዘን በደሙም መንፃት ፍጹም በሆነ እምነትና ነፃነት ወደ ፈለግንበት መሄድን ያስች ለናል። ሥራችን ዘወትር የማይጠቅም ስለሆነ፣ አሳሳች ከሆነና መልክም ከሚመስ ለን አገልግሎታችን ጋር ዛሬ ወደ እርሱ መሄድ በጣም እንመኛለን። ቃሉን፣ ፈቃ ዱንና ጸጋውን በግድ የለሽነት ከመመልከት እንዲያነፃን ወደ እርሱ መሄድ እንዴት አስቸኳያችን ነው! ሊቀ ካህናታችን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ በመማፀኛ ከተማችን ዘወትር ያለ ሥጋት እንኖራለን።

## ምዕራፍ ፲፱ ።

# የምንከተላቸው ሥርዓቶች ።

ኢያሱ ፳፫ ፡ ፲፮ ።

«እንዲህም ሆነ ፣ ብዙ ዘመን ከሆነ በኋላ ፣ እግዚአብሔርም እስራኤልን በዙሪያቸው ካሉት ጠላቶቻቸው ሁሉ ካሳረፈ በኋላ ፣ ኢያሱም በሸመገለ በዕድሜውም ባረጀ ጊዜ ፣ ኢያሱ እስራኤልን ሁሉ ሽማግሌዎቻቸውንም አለቆቻቸውንም ፈራጆቻቸውንም ሹማምንቶቻቸውንም ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፡— እኔ ሸምግያለሁ ፣ በዕድሜም አርጅቻለሁ ። እናንተም አምላካችሁ እግዚአብሔር በእነዚህ አሕዛብ ሁሉ ስለ እናንተ ያደረገውን ሁሉ አይታችኋል ። ስለ እናንተ የተዋጋ እርሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነው ። እነሆ ፣ እኔ ካጠፋሁአቸው አሕዛብ ሁሉ ጋር ከዮርዳኖስ ጀምሮ በፀሐይ መግቢያ እስካለው እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ለነገዶቻችሁ ርስት እንዲሆኑ የቀሩትን እነዚህን አሕዛብ በዕጣ ከፈልሁላችሁ ። አምላካችሁም እግዚአብሔር እርሱ ከፊታችሁ በብርቱ ይበትናቸዋል ፣ ከፊታችሁም ያሳድዳቸዋል ። አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ተናገራችሁም ምድራቸውን ትወርሳላችሁ ። ስለዚህም በሙሴ ሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ ለመጠበቅና ለማድረግ በጣም በርቱ ፣ ከእርሱም ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ አትበሉ ። በእናንተ መካከል ወደ ቀሩት ወደ እነዚህ አሕዛብ አትግቡ ። የአማልክቶቻቸውንም ስም አትጥሩ ፣ አትማሉባቸውም ፣ አታምልኩአቸውም ፣ አትስገዱላቸውም ። እስከ ዛሬ ድረስ እንዳደረጋችሁት ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ እንጂ ። እግዚአብሔር ታላላቆችንና ኃይለኞችን አሕዛብ ከፊታችሁ አስወጥቶአል ። እስከ ዛሬም ድረስ ማንም ሊቋቋማችሁ አልቻለም ። አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ተናገራችሁ ስለ እናንተ የሚዋጋ እርሱ ነውና ከእናንተ አንዱ ሰው ሺህ ሰውን ያሳድዳል ። አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትወድዱት ዘንድ ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ ። እናንተ ግን ተመልሳችሁ በመካከላችሁ ወደ ቀሩት ወደ እነዚህ አሕዛብ ብትጠጉ ፣ ከእነርሱ ጋር ብትጋቡ ፣ እናንተም ወደ እነርሱ እነርሱም ወደ እናንተ ብትደራረሱ ፣ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እስክትጠፉ ድረስ መውደቅያና ወጥመድ ፣ በጎናችሁም መግረፊያ ፣ በዓይናችሁም እሾህ ይሆኑባችኋል እንጂ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲያ እነዚህን አሕዛብ ከፊታችሁ እንዳያሳድዳቸው ፈጽማችሁ እወቁ ።

እነሆም ፣ ዛሬ የምድርን ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ ፣ እናንተም እግዚአብሔር ስለ እናንተ ከተናገረው ከመልካም ነገር ሁሉ አንድ ነገር እንዳልቀረ በልባችሁ ሁሉ በነፍሳችሁም ሁሉ እወቁ ፤ ሁሉ ደርሶላችኋል ። ከእርሱም አንድ ነገር አልቀረም ። አምላካችሁ እግዚአብሔር የተናገረው መልካም ነገር ሁሉ እንደ ደረሰላችሁ ፣ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እናንተን እስኪያጠፋ

ችሁ ድረስ እግዚአብሔር እንዲሁ ክፉት ነገር ሁሉ ያመጣባችኋል። አምላካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ቃል ከዳን ስታፈርሱ፣ ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት ስታመልኩ፣ ስትሰግዱላቸውም፣ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድድባችኋል፣ ከሰጣችሁም ከመልካሚቱ ምድር ፈጥናችሁ ትጠፋላችሁ» ኢያሱ ፳፫፣ ፩ — ፲፮።

መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ ፳፫ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ከገቡ ሃያ ዓመት ወደ ሞላቸው ጊዜ ያመጣናል። የዘመቻው ኃይለኛነት፣ የመሪነት ኃላፊነትና የአለፉት ዓመታት ሁሉ፣ የታላቁንና የጀግናውን መሪአቸውን ጉልበት ኀስመዋል፣ ምልክታቸውንም በእርሱ ላይ ትተዋል። አሁን እርሱ ራሱ እንደ ሽመገለና በዕድሜም እንደ አረጀ ሲናገር እናገኘዋለን። እርሱም ወደ ምድሪቱ ያገባቸው ሰዎች ሁሉ በተሰጣቸው ርስት ዱሮ ከነበሩባትና እግዚአብሔር ፈጽመው እንዲያስወጡአቸው ከዘዛቸው ጋር ተደባልቀውና ተስማምተው ይኖራሉ።

የምድራዊ ኑሮውም ወደ ማለቁ ሲቃረብ፣ ሕዝቡ ከአሕዛብ ጋር የሚያደርገው መግባባት የሚያስከትለው አደጋ ስለ ተሰማው፣ ኢያሱ ሕዝቡን ተገናኘና አነጋገራቸው። በመጀመሪያ መሪዎቻቸውን፣ ከዚያም በኋላ ሹማምንቶቻቸውንና ተራዎቹን ሰዎች ጠርቶ የመሰናበቻ መልእክት ሰጣቸው። ይህ ሽማግሌው ታላቅ አርበኛና የሕዝቡ መሪ፣ ሕዝቡን ሲያነጋግር ትዕይንቱን እንደ ሥዕል ልትመለከት ትችላለህ። ካሌብ ከእነርሱ መካከል ነው። ፊንሐስ ሊቀ ካህኑ እዚያ ነው። የርዳኖስን ተሻግረው በብዙ ውጊያዎችም ተካፋይ የነበሩ፣ በብርቱዎቹና በቀላሎቹም ጦርነቶች ከመሪአቸው ጎን የነበሩ በዚያ ተገኝተዋል። ሌሎችም አሉ። ለመሪነት የሚታጩ ወጣቱ ትውልድ፣ በአንዋኑዋርና በድል መንጣትም ወደ ፊት የሚገፉ በዚያ ናቸው።

ኢያሱ ለመሪዎች ባደረገው ንግግር፣ በምድረ በረከት ጸንተው እንዲኖሩ ከተፈለገ መከተል የሚገባቸውን ሥርዓቶች አስታወቃቸው። ከዚያ በኋላም ተስፋቸው እውነተኛ ፍጻሜ እንዲያገኝ ከተፈለገ ማድረግ የሚገባቸውን ለሽማግሌዎቻቸው፣ ለአለቆቻቸው፣ ለሹማምንቶቻቸውና ለሕዝቡም ሁሉ ነገረ፣ በልፉት ዓመታት በተደረገላቸው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን ታማኝነት እያረጋገጠ ሲናገር ልቤን ደስ ይለዋል። እንዲህ ይላል «እናንተም እግዚአብሔር ስለ እናንተ ከተናገረው ከመልካም ነገር ሁሉ አንድ ነገር እንዳልቀረ በልባችሁ ሁሉ በነፍሳችሁም ሁሉ እወቁ። ሁሉ ደርሶላችኋል። ከእርሱም አንድ ነገር አልቀረም» ኢያሱ ፳፫፣ ፲፬።

እንደ ኢያሱ ከበሰለና ከተሟላ የኑሮ ልምምድ እንድነግራችሁ ብችል ደስ ይለኝ ነበረ። ከዘላለማዊ ስፍራ አንድ መጥቶ ስለ እግዚአብሔር ለጥቂት ደቂቃዎች ቢነግራችሁ ምንኛ እመኛለሁ። በውጊያና በዘመኑ ጦርነቶች መካከል በዕድሜው ያጋመሰ ሰው ሊነግራችሁ የሚችል ብርታትና መንፈሳዊ መግለጫ ሊሰጡ የሚችሉ ቁም ነገሮች አሉ። ነገር ግን ከሁሉም ይልቅ የሚጠቅመው፣ በዘወትር ውጊያና ትግል ተካፋይ ሆኖ ከበሰለ እውቀት የሚናገረውንና ከትዕይንቱ ሊሰናበት የቀረበውን ሰው መስማት ነው። እንደዚህ ባለ ሰው እግር ሥር ተቀምጬ ከእርሱ ለመስማት ያለኝን ሁሉ በሰጠሁ።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ምኞት ብቻ ስለሆነ በፍጹም የማይቻል ነው። እግዚአብሔር በሰጠህ ምድረ ደኅንነት እንድትኖር ከፈለግህ፥ ልትከተላቸው የሚገባህን ሥርዓቶች ሳቀርብልህ በትዕግሥት እንድትሰማኝ እጠይቅሃለሁ። በመጀመሪያ፥ በክርስቲያን መሪነት ላይ ላላችሁ፥ ለዚህም በመዘጋጀትና በመሰልጠን ላይ ለምትገኙ አገልጋዮች፥ ለወንጌል መልእክተኞች (ሚሲዮናውያን) ለቤተ ክርስቲያን ሹማምንትና መሪዎች እናገራለሁ። መንፈስ ቅዱስ በምድረ በረከት የመኖርን ሥርዓት ሲያስተምረን፥ ከዚህ ከታላቁ አርበኛና መሪ ከኢያሱ አብረን እንማር።

ከሁሉ አስቀድሞ ኢያሱ ሕዝቡን ስለ ክሕደት አደጋ አስጠነቀቀ። ያስቸገረውዋናው ነገር፥ የሰባት መንግሥታት አሕዛብ አሁንም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ተደባልቀው ይኖራሉ። እነዚህ አሕዛብ በዚህ ምዕራፍ ሰባት ጊዜ ተወስተዋል። ይኸውም ከአሁን ቀደም እግዚአብሔር ምን እንዳደረገባቸው፥ አሁንም ሊያስወጣቸው ዝግጁ መሆኑንና ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እንዲኖሩ ከተደረገ ግን ታላቅ ፈተና እንደሚሆኑባቸው ነው። ምክንያቱም አብረው ከኖሩ በጋብቻ መቀላቀልና የጣዖት አምልኮም እንደማይቀር ነው።

መጽሐፈ ኢያሱ በአዲስ ኪዳን ያለው የኤፌሶን መልእክት ተመሳሳይ ነው ብለናል። ታላቁ ሐዋርያ፥ ጳውሎስ በኤፌሶን ወደብ ቆሞ የኤፌሶንን ሰዎች ሲሰናበታቸው የተናገረውን አስታውሳለሁ «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ። ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠፅ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ» የሐዋርያት ሥራ ፳፥ ፳፰ — ፴፩።

ከእርሱ ወደ ኋላ ፈጽመን መመለስና ጨርሶ መውደቅ የማይቻለን የክርስቲያንነት ኑሮ አቋም ወይም ደረጃ የለም። በዘመናችን ሁሉ በተቀበልነው የወንጌል ብርሃን ላይ በእርጅናችን ስንኳ ጀርባችንን ልናዞርበት እንችላለን። ብዙ ክርስቲያኖች ከከፍተኛና ከክብር ስፍራ ወድቀዋል። አወይ! የወደቁበትም አዘቅት ጥልቀት ይህ ነው አይባልም። በዚህ ምድራዊ ጉዞ በማናቸውም ደረጃ ላይ ብንሆን የጸደቅንበትን የቃል ኪዳኑን ደም ልናረክሰው፥ የጸጋንም መንፈስ ልንንቅ እንችላለን። በሽምግልናና በእርጅና ዘመናችን እንኳ ቢሆን በዘመኑ ሁሉ የቀሰምነውን መንፈሳዊ ባለጠግነት ሁሉ ልንወረውር እንችላለን።

ወዳጆቼ ሆይ፥ አሁን በእግዚአብሔር ፊት ሳለን የጥንቱ ትዝታ አያጫውተንምን? የፊተኞቹንም ጊዜያት ተስፋዎች አያስታውሰንምን? የዚያን የጥቢ ዘመናት የተብራሩ የወደፊት ተስፋዎች ማስታወስ እንደ ብርሃን ጭላንጭል አያሳየንምን? የዱሮውን የሕይወት አዝመራና የመከሩን ፍሬ ስናመዛዝን አንዳንድ ጊዜ አያሳዝነንምን? ወደ ወጣትነትህ ወይም ከረዳነትሽ ዘመን፥ ሙሉ ሰውም ወደ ነበርክበት ዘመን

ነው ። ቤተ ክርስቲያን ወደ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ ሊያነሣት የሚችለው ይህንን ጴንጤቆስጣዊ ኃይል ለሚታዘዙት ለጥቂቶች ሰዎች ብቻ ከልሆነ ከብዙዎቹ ተወስዶብቸዋል ። ክህደት ፈጣን መሸነፍን ያስከትላል ። በዚሁም ምክንያት የክርስ ቶስን ስም ያስነቀፉል «እግዚአብሔርም ከእንግዲህ ወዲያ ጠላትን አያሳድድም ።»

ሁለተኛው የክህደት ዋጋ በዚሁ ቁጥር የሚገኝ «ምቾት ማጣት» ነው ። «መውደቂያና ወጥመድ ፣ በጎናችሁም መግረፊያ ፣ በዓይናችሁም እሾህ ይሆኑብች ኋል» የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም አለመታገል ፣ ከጠላት መቻቻልና ምድሪቱ ንም እንዲጋራ መፍቀድ አሰቃቂ የሆነ ምቾት ማጣትን ያስከትላል ። በክርስቲያን ኑሮ ውስጥ ስንት የታሰቡ ነገሮች ሳይፈጸሙ ቀርተዋል ። ኃጢአትስ ፈጽሞ ሳይጠፋ ስንት ጊዜ አብሮ ተቀምጦአል ። የወደድነውና የተከበከብነው ፈተና ሁሉ ስንት ጊዜ በጎናችን መግረፊያ ፣ በዓይናችንም እሾህ ሆኖብናል ? እንደ ጊዜው ሁኔታና እንደ ዘመኑ መንፈስ የሚኖር ክርስቲያን አብዛኛውን ጊዜ ደስተኛ አይደለም ። በክርስቲያን ሕይወት ጠላት ቢቀመጥ ፣ የእግሩም መረገጫ ቢያገኝ ከመቅጽበት መግረፊያ ይሆን በታል ።

ሦስተኛው የክህደት ዋጋ ውርደት ነው ። «በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድባችኋል ፣ ከሰጣችሁም ከመልካሚቱ ምድር ፈጥናችሁ ትጠፋላችሁ» ኢያሱ ፳፫ ፣ ፲፮ ።

ታዲያ ለዚህ ሁሉ መከላከያ የለምን ? ትላለህ ። በእውነቱ ሞልቶአል ። ኢያ ሱም የክህደትን ውጤቶችና ዋጋዎች ሲነግራቸው መከላከያዎቻቸውንም በጥንቃቄ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ዘርዝሮአል ። ክህደትን ለመከላከል በዚህ ምዕራፍ ሦስት አስፈላጊ ነገሮችን አቅርቦአል ።

ከሁሉም የሚቀድመው መታዘዝ ነው ። «ስለዚህ በሙሴ ሕግ መጽሐፍ የተጻ ፈውን ሁሉ ለመጠበቅና ለማድረግ በጣም በርቱ ፣ ከእርሱም ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ አትበሉ» ኢያሱ ፳፫ ፣ ፮ ።

በመጀመሪያም ኢያሱ መሪነትን ከሙሴ በተረከበ ጊዜ የዚሁ ዓይነት ትእዛዝ እንደተቀበለ አስታውስ ። የሃይማኖታችን እውነተኛ ሥርዓቶችም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ እንደሚኖሩ የተረጋገጠ ነገር ነው ። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመንና ትውልድ ታላቁን የክርስቲያን አንዋኑዋር ሥርዓቶች እንዲያስተውል ፣ እንዲ ማርና እንዲያኙከውም ተጠርቶአል ። ከእነዚህም ሥርአቶች የመጀመሪያው መታ ዘዝ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱሳችንን እናምናለን እንላለን ፣ ለዚሁም እግዚአብሔር ይመስገን ። ነገር ግን መጽሐፍ ለሚለው እንታዘዛለን ወይ ? ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራእይ ዮሐ ንስ ድረስ እናምንዋለን ። ነገር ግን ሃያ አራቱን ሰዓት በትምህርቱ ብርሃን እንኖራለን ወይ ? በጸጥታህ ሰዓት ወደ መጽሐፍ ቅዱስህ ሄደህ እግዚአብሔር ሲናገርህ ሰምተህ ታውቃለህ ወይ ? ነገር ግን የማትፈልገውን ነገር መንፈስ በልብህ ላይ ስለጣለ

እርሱን ትተህ ደብዳቤ ለመጻፍ ጥሪ ለመመለስ ፣ ከባለቤትህ ልትነጋገር በችኩላ ትተህ ሄደህ ታውቃለህ ወይ ?

ሰዎች ስለምን ጸሎትን አያዘወትሩም ? መጽሐፍ ቅዱስን ለምን በብዛት አያነቡም ? ዛሬ ክርስቲያኖች አብዛኛውን ጊዜያቸውን መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብና በመጸለይ ለምን ከእግዚአብሔር ጋር አያሳልፉም ? ለዚህ ሁሉ የሚሆን አንድ ጥሩ ምክንያት ልነግርህ እችላለሁ ። ብዙውን ጊዜ አይመቻቸውም ። ወዳጆቼ ሆይ ፣ የዚህ ሁሉ ምክንያት የሚከተለው ነው ። ወደ ቅዱሱ መጽሐፉችሁ ስትመለሱ ፣ መንፈሱ አሁንም አሁንም እየደጋገመ ስለ አንዲት ኃጢአት ፣ ስለ አንድ ጠባይና ፀመል ፣ አለመጸለይህና ፍቅር በልብህ ስለ አለመኖሩ ይነግርሃል ። ለጌታህና ለመድኃኒትህ ደቅቀህ ፣ ተዋርደህ እስክትገዛ ድረስ ኃጢአትህን ሊያሳስብህና ንስሐ እንድትገባ ሊያደርግህ ይፈልጋል ። ስለዚህ አለመታዘዝህ ለጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ከሰጠኸው የጸጥታ ሰዓት ጨርሰህ እንድትለይ አደረገህ ።

ሁለተኛው ታላቁ የክህደት መከላከያ መነጠል ነው ። ተጠንቀቁ «በእናንተ መካከል ወደ ቀሩት ወደ እነዚህ አሕዛብ አትግቡ የአማልክቶቻቸውንም ስም አትጥሩ ፣ አትማሉባቸውም ፣ አታምልኩቸውም ፣ አትስገዱላቸውም ። .... ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ እንጂ» ኢያሱ ፳፫ ፣ ፯ ና ፰ ። ይህም ከከነዓናውያንና ከርኩሰቶቻችውም ጋር በምንም ዓይነት እንዳይገናኙ ነው ።

ዛሬም ለክርስቲያን የሚገባ ይኸው ነው ። ከዓለማዊነት በገሃድ መከላከል ማለት ነው ። ሰዎች በክርስቲያንነት ማፌዝን ትተው ኃጢአትንና ሰይጣንን መዋጋት አለባቸው ። አንድ ዓለማዊና ሥጋዊ በደል ሠርተን በኋላ ግን ትንሽ መንፈሳዊ ንግግር ብንሰማ ስለ ሠራነው በደል ራሳችንን እንወቅሳለን ፣ አምላክ ይማረን ። እንዴት ያለ ሚዳዊ ግብዝነት ነው ። መለየት ወይም መነጠል የክህደት መከላከያ ነው ። ይህም ማለት ከሥጋዊና ዓለማዊ ነገር በማናቸውም ዓይነትና ጊዜ በፍጹም አለመተባበር ነው ። ይህ የነገሩ የአሉታ ገጽ ነው ። ግን የአወንታ ገጽ ደግሞ አለው ። «ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ ፤ ተከተሉት» የተለየ ወይም ገለልተኛ ክርስቲያን የማያስፈልጉትን ነገሮች እያመነታ የሚተው ሰው አይደለም ። የተለየ ወይም የተነጠለ ክርስቲያን በሙሉ ልቡ ጌታውን የሚወድና ሌላ ተጨማሪ ነገር የማይፈልግ ነው ።

በዘመናቱ ሁሉ አንተን በይጎዳም አርአያህን ለመከተል የሚጠባበቅ ሌላውን በጣም የሚጎዳ ታክችነት በቀላሉ እንደምትሠራ እርግጥ ነው ። ጋዜጣን በማንበብ ፣ ራዲዮ በመስማትና ቴሌቪዥን በመጠበቅ ብዙ ጊዜ ማሳለፍህን «ይህ አይጎዳም» በማለት ራስህን ታጽናናለህ ። ነገር ግን ለተቀደሰ አንዋኑዋር እንደ ምሳሌ ሊወስዱህና ለመሪነት ለሚጠባበቁህ ያደረስክባቸውን ጉዳት ልታስቀር አትችልም ። እንዲህም ትል ይሆናል «ወደ ጸሎት ስብሰባ አለመሄድ ብዙም አይጎዳም በልሄድ የሚጎዳ ሰው የለም» ብዙ ወጣቶችም እንዲህ ይላሉ «ባልጸልይ ግድ የለም ፣ እርሱ መሪው ራሱ አይሄድም ፤ እኔም እንደ መሪዬ የምከተለው እርሱ ነው»

ሦስተኛው ታላቁ የክህደት መከላከያ ከሁሉም የበለጠ ነው። እንዲህ ነው «እግዚአብሔርን አምላካችሁን ትወድዱት ዘንድ ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ» ኢያሱ ፳፫ ፣ ፲፩። አ ወዳጆቼ ሆይ ፣ የአለመታዘዝና የአለመነጠል ፣ የአለመለየትም መሠረታቸው አለማፍቀር ነው። ጌታ ኢየሱስ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» አለ። አዎን ፣ ከዓለማውያን አለመነጠል ፣ በአረማመዳችን አለመጠንቀቅ ፣ በአንዋኑዋሬችንም አለመጸለይ መኖሩ ፣ መድኃኒታችንን በፍጹም ልብ ከማይወድ ልቡና ይመነጫል።

እነዚህ በኢያሱ ዕድሜ መጨረሻ ላይ የመጡ ቃላት በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ያለፉት ዘመናት የውጊያና የደም ማፍሰሻ ነበሩ። አሁን ጀግናው ተዋጊ የሰላም ሰው ሆነ። ያለፉት ዓመታት ማዕበል በጀምበርዋ መጥለቅ ጸጥ አለ። ሁልጊዜም ሲዋጋ የነበረው ሰውዬ አሁን «ተጠንቀቁ እንድትወድዱት» ይላል።

አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዖን ጴጥሮስን ጠልቆ ፣ መርምሮ ፣ አይቶና አውቆትም የተናገረው ነገር ትዝ ይለኛል። «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ፣ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን ?» ሁሉም ነገር በዚህ ቃል ተጠቃልሎአል። ክርስቶስን ውደድ ፣ እርሱንም በሙሉ ብትወርሰው ብቻ ልትረካ ትችላለህ። እርሱን ውደድና ለምስክሩ ትደፍራለህ። እርሱን ውደድና መጽሐፉንም ሕጉንም ትወዳለህ። እርሱን ብትወድ ከእግዚአብሔር ፍቅር በምንም ዓይነት የማይወዳደረውን የሰዎችን ፍቅር አያስኝህም። እርሱን ውደድና ትወርሰዋለህ ፣ አንተ የእርሱ ትሆናለህ። በጎነህ መግረፊያ ፣ በዓይንህም እሾህ የሆኑትም ነገሮች ወደ ጸጋውና ኃይሉ ሙላት ጠልቀህ የምትራመድባቸው ደረጃዎች ይሆኑልሃል። እርሱን ብትወድድ የሚወድዱትን ሌሎችን ልትወድድ ይቻልሃል «ተጠንቀቁ እንድትወድዱት»

ባለፈው ጊዜ ለሰበክሁት ስብከት አርእስት ብመርጥ ኖሮ ይህ ክፍል መሆን ነበረበት። ያለፉት ትውልዶች የእግዚአብሔር ቅዱሳን ፣ በዘላለማዊ ስፍራ ስለአዩት ስለ ሰማይና ገሃነም ፣ ስለ ተመለከቱት ነገር ሁሉ ሊነግሩን ቢችሉ ኖሮ የሚናገሩት ያለ መጨመር እነዚህን ቃላት ብቻ ነው። «ተጠንቀቁ እንድትወድዱ» የአለመጠንቀቅ አረማመድ ፣ የጸሎተ ቢስ መንፈስና የልብ ቅዝቃዜ ዋናው መከላከያ ፍቅር ነው። ዛሬ የክርስቲያኖንና የቤተ ክርስቲያንን ሕይወትና አቋም ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማውጣት የሚችል ፣ ለቤተ ክርስቲያን መታደስም ዓይነተኛ መሣሪያ የሚሆነው ነገር ለእውነት ጠበቆች ሆነን መቆም አይደለም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ የልባችን ፍቅር ነው።

ፍቅር ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም ራሱ ፍቅር ነው። ፍቅር ብቻ ጥልን ሊያሸንፍ ይችላል። የተዋጁትን ቤተ ሰብ ፣ ፍቅር ብቻ በአንድነት ሊያሥር ይችላል። በንጽሕና ፣ ያለ ንፍገት በብርቱ ብትወድ ወይም ብታፈቅር መድኃኒትህን ማፍቀር ማለት ምን እንደሆነ ትረዳለህ። ለማፍቀር አስቀድሞ መፈቀር አለብን። ለማስተላለፍ አስቀድሞ መቀበል አለብን። የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመናኘት መጀመሪያ በልባችን እንዲኖረን ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔርን ፍቅር በልባችን ባፈሰሰው በመንፈስ ቅዱስ ይህን በልባችንና በነፍሳችን ያለውን ፍቅሩን ልናስተውል እንችላለን ። በዚህ ዓይነት ፍቅርን የሚያውቅ ሰው አሁኑኑ በሰማይ ጓዳ ይገኛል ። ከእንግዲህ ወዲህ አይራብም አይጠማም ፤ ምክንያቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በሕይወቱ መፈጸሙን ተረድቶአል ። «እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም ፤ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል» ዮሐንስ ፬ ፥ ፲፬ ።

ለእግዚአብሔር መንፈስ ራስህን ስጥ ። የጴንጠቆስጤ ድርሻህን እስክትቀበል ድረስ ቸል አትበል ። የፍቅር መፈተኛው ፥ ስሜት ፥ የልብ ተመስጦና መናገር አይምሰልህ ። ዳሩ ግን መታዘዝ ነው ። ምክንያቱም ይህ ነው «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው» ዮሐንስ ፲፬ ፥ ፳፩ ።

በመጀመሪያይቱ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መልእክት ምዕራፍ ፲፫ ላይ ቻርልስ ወርድስወርዝ ያዜመው መዝሙር መልእክቱን ወደ ልባችን ያመጣል ።

አ መንፈስ ቅዱስ የመጣህ ለፍቅር
እንመኛለን ከአንተ ለመማር
ከጴንጠቆስጤ ስጦታህ ጭምር
ቅዱስ ሰማያዊ ፍቅር ።
ተራሮችን የሚነቅል እምነት
የምድርና የሰማይ ልሳናት
ሁሉም ባዶ ነው ደግሞም እውቀት
ሰማያዊ ፍቅር ከሌለበት ።
ፍቅር ታጋሽ በጎም ናት
ፍቅር አትጎዳም ርኅሩኅ ናት
ፍቅር ታይላለች ከሞት
ስለዚህም ስጠን የፍቅር እሳት ።
ትንቢት ማለፍዋ ፍጹም አይቀር
እየቀላለጠች በቀኑ ሐሩር
ከኛ ትኖራለች መልካሟ ፍቅር
ስለዚህም ስጠን አቤቱ ፍቅር ።
ሃይማኖት ተስፋን ፍቅር አየን
ሲኖሩ ተያይዘው እጅ እጃቸውን
ከእነዚህ ከሦስቱ የምትበልጥ ግን
ፍቅር ነች ይላሉ ዋናዋ መድኅን
ከሚጋርዱን ብርቶቹ ክንዶችህ
ወርቃማና ክቡር ከሆኑ ክንፎችህ
አቤቱ ስጠን ለምንጠጋህ
ሰማያዊ ፍቅርን ከቅድስናህ ።

አምን ፡ ምሥጢሩ ይህ ነው ፡ የክህደት ታላቁ መከላከያ በመንፈስ ቅዱስ በልባችን የሚፈስስ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው ። «በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም ።» ሮሜ ፭ ፡ ፭ ።

ምዕራፍ ፳ ።

# የምናገለግልበት ኃይል ።

ኢያሱ ፳፬ ፥ ፲፭ ።

«ኢያሱም የእስራኤልን ነገድ ሁሉ ወደ ሴኬም ሰበሰበ ፥ የእስራኤልንም
ሽማግሌዎች አለቆቻቸውንም ፈራጆቻቸውንም ሹማምንቶቻቸውንም ጠራ ። እነር
ሱም በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ ። ኢያሱም ለሕዝቡ ሁሉ እንዲህ አለ ። የእስራኤል
አምላክ እንዲህ ይላል ፥— አባቶቻችሁ ፥ የአብርሃምና የናኮር አባት ታራ ፥ አስቀድ
መው በወንዝ ማዶ ተቀመጡ ። ሌሎችንም አማልክት አመለኩ ። አባታችሁንም
አብርሃምን ከወንዝ ማዶ ወስጄ በከነዓን ምድር ሁሉ መራሁት ። ዘሩንም አበዛሁ ፥
ይስሐቅንም ሰጠሁት ። ለይስሐቅም ያዕቆብንና ዔሳውን ሰጠሁት ። ለዔሳውም የሴ
ይርን ተራራ ርስት አድርጌ ሰጠሁት ። ያዕቆብም ልጆቹም ወደ ግብፅ ወረዱ ።
ሙሴንና አሮንንም ላክሁ ፥ በመካከላቸውም እንዳደረግሁ ግብፅን ቀሠፍሁ ። ከዚያም
በኋላ አወጣሁአቸው ። አባቶቻችሁንም ከግብፅ አወጣኋቸው ፥ ወደ ባሕሩም ደረሳ
ችሁ ። ግብፃውያንም አባቶቻችሁን በሰረገሎችና በፈረሰኞች እስከ ኤርትራ ባሕር
ድረስ አባረሩአቸው ። ወደ እግዚአብሔርም በጮኹ ጊዜ በእናንተና በግብፃውያን
መካከል ጨለማ አደረገ ፤ ባሕሩንም መለሰባቸው ፥ አሰጠማቸውም ። ዓይኖቻችሁም
በግብፅ ያደረግሁትን አዩ ፤ በምድረ በዳም ብዙ ጊዜ ተቀመጣችሁ ። እኔም በዮርዳ
ኖስ ማዶ ወደ ተቀመጡበት ወደ አሞራውያን ምድር አመጣሁአችሁ ። ከእናንተም
ጋር ተዋጉ ፥ አሳልፌም በእጃችሁ ሰጠኋችሁ ፥ ምድራቸውንም ወረሳችሁ ። ከፊታ
ችሁም አጠፋኋቸው ። የሞዓብም ንጉሥ የሴፎር ልጅ ባላቅ ተነሥቶ ከእስራኤል
ጋር ተዋጋ ፥ እንዲረግማችሁም የቢዖርን ልጅ በለዓምን ልከ አስጠራው ። እኔ ግን
በለዓምን መስማት አልወደድሁም ። እርሱም ፈጽሞ ባረካችሁ ፥ እኔም ከእጁ አዳን
ሁአችሁ ። ዮርዳኖስንም ተሻገራችሁ ፥ ወደ ኢያሪኮም መጣችሁ ። የኢያሪኮም
ሰዎች ፥ አሞራዊው ፥ ፌርዛዊው ፥ ከነዓናዊው ፥ ኬጢያዊው ፥ ጌርጌሳዊው ፥ ኤዊያ
ዊው ፥ ኢያቡሳዊው ተዋጉአችሁ ፤ አሳልፌም በእጃችሁ ሰጠሁአቸው ። በፊታችሁም
ተርብ ሰደድሁ ፥ በሰይፍህም በቀስትህም ሳይሆን ሁለቱን የአሞራውያንን ነገሥታት
ከፊታችሁ አሳደዳቸው ። ያልደከማችሁበትንም ፥ ያልሠራችኋቸውንም ከተሞች ሰጠ
ሁአችሁ ፥ ተቀመጣችሁባቸውም ፥ ካልተከላችኋቸውም ከወይንና ከወይራ በላችሁ ።

አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ ፥ በፍጹምም በእውነተኛም ብል አምልኩት ።
አባቶቻችሁም በወንዝ ማዶ በግብፅም ውስጥ ያመለኩአቸውን አማልክት ከእናንተ
አርቁ ፥ እግዚአብሔርንም አምልኩ ። እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታ
ያችሁ ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራ
ቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደሆነ ፥ የምታመልኩ
ትን ዛሬ ምረጡ ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን ።

ሕዝቡም መልሰው እንዲህ አሉ ፦ እግዚአብሔርን ትተን ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከእኛ ይራቅ ። እኛንና አባቶቻችንን ከባርነት ቤት ከግብፅ ምድር ያወጣን ፥ በዓይናችንም ፊት እነዚያን ታላላቅ ተአምራት ያደረገ ፥ በሄድንበትም መንገድ ሁሉ ፥ ባለፍንባቸውም አሕዛብ ሁሉ መካከል የጠበቀን ፥ እርሱ አምላካችን እግዚአብሔር ነውና ። እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ ፥ በምድሪቱም የተቀመጡትን አሞራውያን ከፊታችን አሳደደ ፤ ስለዚህ እርሱ አምላካችን ነውና እግዚአብሔርን እናመልካለን ።

ኢያሱም ሕዝቡን እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና ፥ እርሱም ቀናተኛ አምላክ ነውና እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም ። መተላለፋችሁንና ኃጢአታችሁን ይቅር አይልም ። እግዚአብሔርን ትታችሁ እንግዶችን አማልክት ብታመልኩ ፥ መልካም ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ ክፉ ነገር ያደርግባችኋል ፤ ያጠፋችሁማል አላቸው ። ሕዝቡም ኢያሱን ፦ እንዲህ አይሁን ፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን አሉት ። ኢያሱም ሕዝቡን ፦ እንድታመልኩት እናንተ እግዚአብሔርን እንደ መረጣችሁ በራሳችሁ ላይ ምስክሮች ናችሁ አላቸው ። እነርሱም ፦ ምስክሮች ነን አሉ ። እርሱም አሁን እንግዲህ በመካከላችሁ ያሉትን እንግዶች አማልክት አርቁ ፤ ልባችሁንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር አዘንብሉ አላቸው ። ሕዝቡም ኢያሱን ፦ አምላካችንን እግዚአብሔርን እናመልካለን ፥ ድምፁንም እንሰማለን አሉት ።

በዚያም ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ ፤ በሴኬምም ሥርዓትና ፍርድ አደረገላቸው» ኢያሱ ፳፬ ፥ ፲፮ — ፳፭ ።

አሁን ወደ መጽሐፈ ኢያሱ የመጨረሻ ጥናት መጣን ። የመጽሐፈ ኢያሱን ትምህርት ጠቃሚነት በመግለጽ አገልግሎቴን በአሜሪካ አገር ጀመርሁ ። ይህ መጽሐፍ ለአዲስ የእውነት መግለጫ ፥ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጥልቅ ምሥጢርና ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለሚያስፈልገው መቀበት ሁሉ መክፈቻ ነው ። ይህ ሁሉ አስፈላጊ መሆኑን በራሴ ደርሶብኝ ተረድቻለሁ ። በመጽሐፈ ኢያሱ ተስሎ እንደምናገኘው ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሣኤው አንድ በመሆናችን ስለ አገኘነው ሙሉ ደኅንነት ያለውን መልእክት ከቀድሞው ይልቅ አሁን እርግጠኛ ነኝ ። ይህም ለዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ታላቁ ፍላጎትዋ ነው ።

በመጽሐፉ የመጨረሻ ምዕራፍ ኢያሱ ለሕዝቡ ወደ አደረገው የመሰነባበቻ መልእክት ስንመጣ ፥ የመልእክቱ ዓላማና እርእስት አገልግሎት በመሆኑ እናደንቅም ። ወደ ጥልቅ የሕይወት አቋም የሚመራ እያንዳንዱ አዲስ የእውነት መግለጫ ሁሉ ለአገልግሎት አዲስ ወደ መቀበት መምራት አለበት ። በእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል መግለጫ ላይ ስለ አልተመሠረተና አምላካዊ ኃይል ስለሌለበት ለእግዚአብሔር የምናደርገው አብዛኛው አገልግሎታችን ቶሉ ሸክም ይሆናል በሥራውም አለመደሰትን ያስከትላል ። እንደምታስታውሰው ፥ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ሲጽፍና የራሱን ሐዋርያነት ሲመሰክር ሳለ ፥ እግዚአብሔር ልጁን በእርሱ ሊገልጥ እንደፈቀደ

ይናገራል። ወዳጆቼ ሆይ፣ በመስቀሉ የማዳኑን ሥራ ያደረገው ጌታ ኢየሱስ ክርስ ቶስ፣ በመንፈሱ ደግሞ በእኛ የማጽደቁን ሥራ ማድረግ አለበት። እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ለክርስቲያን አቋምና የአንዋኑዋር ልምምድ ዕኩል አስፈላጊዎች ናቸው። እውነት ልባችንን ጨብጦ ከኑሮአችን ልምምድ አንድ አካል ሲሆን፣ ስለደረሱብንና ስለ አየናቸው፣ ስለምናውቃቸውም ነገሮች መናገር ስንችል ያን ጊዜ የክርስቲያን አገልግሎት ከጉልበታችን በላይ የሆነ የማንችለውም መሆኑ ቀርቶ አልፎ ተርፎ ወደ ውጪ ይጎርፋል።

መጽሐፈ ኢያሱን ደህና ሰንብት ስንለው የመጽሐፉን መልእክት በጠቅላላው እንድንረዳ እርምጃችንን እስቲ ወደ ኋላ እንመልስ። የዚህ መጽሐፍ መግለጫ ምን ድር ነው? የሚሰጠው የኑሮ ልምምድስ ምንድር ነው? የሚጠበበቀውስ የአገልግ ሎት ዓይነት እንዴት ያለ ነው? እነዚህን ሦስት ጥያቄዎች አሁኑኑ መመለስ እንሞ ክር፤ መልሶቹም በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል በአጭሩ ተጽፈዋል።

እንግዲህ፣ በመጀመሪያ፣ በመጽሐፈ ኢያሱ የሚገለጸው መግለጫ ምንድር ነው? ምዕራፍ ፳፬ን ብትበረብር መልሱን ከቁጥር ፪ እና ፲፫ መካከል ታገኛለህ። ቅዱሱና አምላካዊው ምድብ ተውላጠ ስም «እኔ» ከአሥራ ሰባት ጊዜ የበለጠ ይገ ኛል። (በአማርኛችን «እኔ» የሚለው ምድብ ተውላጠ ስም ሦስት ጊዜ ብቻ ተጽፎ ቢገኝም፣ ከእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል ብንተረጉም እንደሚከተለው ተጽፎ እናገኛለን፤ «እኔ ወሰድሁ ... እኔ ሰጠሁት ... እኔ መራሁት ... እኔ ላክሁ ... እኔ አወጣሁአቸው ... እኔ አስገባሁአችሁ ... እኔ ከጠላቶቻችሁ እጅ አዳንሁ አችሁ ... ጠላቶቻችሁን እኔ አጠፋሁ፣ ...) በአማርኛ ግን «እኔ አስወጣሁአችሁ» በማለት ፈንታ «አስወጣኋችሁ» ማለት በቂ ነው። ለወደፊቱ ማበረታቻ እንዲሆና ቸው ኢያሱ ያለፈውን ታሪካቸውን ያስታውሳቸዋል። ሕዝብ ሆነው ከተቋጠሩበት ከመጀመሪያ ታሪካቸው ጀምሮ ሁሉን ነገር ያገኙት በእግዚአብሔር ረዳትነትና በኃያል አምላክ ጉልበት ነው።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለአለን ደኅንነታችን ሁሉ ይህ በሞላው አዲስ ኪዳን የሚገኘው የሐዲስ ኪዳን ትምህርት ጭላንጭል ነው። ደጋግሜ ልናገርና፣ በአዲስ ኪዳን ያለው የኤፌሶን ሰዎች መልእክት የመጽሐፈ ኢያሱ ማብራሪያ ነው በማለት እንርጋና እስቲ የኤፌሶን መልእክት ምዕራፍ ሁለትን ተመልከት። በመጀ መሪያ «መግለጫ» አለን። «ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፣ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፣ በጸጋ ድናችኋልና፣ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ፣ ከእ ርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን» ኤፌሶን ፪፣ ፬—፯። ከዚህም በኋላ «አቋም» ወይም «የኑሮ ልምምድ» አለን። «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእና ንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» ኤፌሶን ፪፣ ፰፣ ፱። ቀጥሎም

«አገልግሎት» ነው ። «እኛ ፍጥረቱ ነንና ፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» ኤፌሶን ፪ ፣ ፲ ።

ስለ ሕይወታችንና ደኅንነታችን መግለጫው ምንድር ነው ? ደኅንነታችን የኃያል እግዚአብሔር አብ ፣ እግዚአብሔር ወልድና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሕብረት ሥራ የፈጸመው ከእኛ ምንም የማይጨመርበት የሥላሴዎች የግል አድራጎት ነው ። እግዚአብሔር ወሰነ ፣ እርሱ ላከ ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንም ሰጠ ። ወደ ምድረ በረከት ሊያስገባን ከግዞት አስወጣን ፣ ጠላቶቻችንን አጥፍቶ ከእጃቸው አዳነን ። እያንዳንዱ የክርስቲያን እንዋኑዋር የኑሮ ልምምድ እርምጃ የመንፈስ ቅዱስ አድራጎት ነው ። ለሕይወትህና ለሕይወቴ የዚያ አድራጎት ከሁሉ በላጭና የተሟላ እቅድ የሚከተለው ነው ። ከባርነት አስወጥቶ ፣ ከምድረ በዳው መርቶ ፣ ከኃጢአት ሊያድነን ፣ በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔርን መንፈስ አድራጎት ኃይልና ልምምድ ወደምንረዳበት ወደ ተሟላው ምድረ በረከት ሊወስደን ነው ። የእቅዱም አንጋሽነት ዓላማ አንድ ቀን በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት ፍጹማን አድርጎ ሊያቀርበን ነው ። ይኸውም በአቋም ፍጹማን ፣ ክርስቶስን ደስ የምናሰኝ ፣ በልምምድም ፍጹማንና ሙሉ ሰዎች ሊያደርገን ።

የመጽሐፉ ጠቅላላ መግለጫ ይህ ነው ። በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን እኛ የሆንነውና ያለን ሁሉ በሙሉ የእርሱ አድራጎት ነው ። ብትሻሻል ፣ ብታድግ ፣ በክርስቲያንነት ኑሮህም ወደ ፊት እየጨመርህ መሄድ ቢታይብህ ፣ ይህ ሁሉ በውስጥህ በመኖሩ ብቻ ነው ። ከእግዚአብሔር ያለን ሁሉ በልጁ በኩል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የመጣልን ነው ። ይህ ሁሉ ጠቅላላው የእግዚአብሔር መግለጫ ነው ። አሁን አንተ ድነሃል ፣ ሆኖም በአንተ ሥራ አይደለም ፤ ከማናቸውም ዓይነት ምግባርህ አይደለም ። እንድትድን ስላደረግኸውም ስለማገኘቸውም ውሳኔህ አይደለም ። ነገር ግን ዓለም ሳይመሠረት በክርስቶስ ስለተመረጥህ ድነሃል ። አንድ ቀን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአት ዘለፈህ ፤ ወደ ቀራንዮም አመለከተህ ፣ ልብህም ለጌታ ኢየሱስ ተከፈተ ፣ አንተም እንደገና አዲስ ተወለድህ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እያንዳንዳቸውን የዕድገትና የበረከት ደቂቃዎች ልትገነዘብ ትችላለህ ። ምክንያቱም ፣ መልካሙን ሥራ በአንተ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ ይቀጥላል ። ደኅንነት ይህ ነው ። በዳንክም ጊዜ እውነተኛውን ነገር ወደምትረዳበት ጉዞ ጀመርህ ፣ ይኸውም በእያንዳንዱ ኀዘንና መከፋት ፣ በእያንዳንዱ ደስታ በረከት ፣ በእያንዳንዱም ፈተናና መከራ ለክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ ሰው እንድትደረግ ነው ።

የመጽሐፈ ኢያሱ መግለጫ እርሱ ነው ፤ የጠቅላላው ቃለ እግዚአብሔር መግለጫ ነው ።

ነገር ግን ከዚህ የበለጠ ሌላ የኑሮ አቋምና ልምምድ እንድትመለከት ልጠይ ቅሀ ። አሁን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ሁሉ በአዩበት ብርሃን ፣ የሚገባቸውን ምርጫ እንዲያደርጉ ኢያሱ ምርጫዎቹን በፊታቸው እንደ አቀረበ ከቁጥር ፲፭ እናነ በለን ። «የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ» አላቸው ። ሕዝቡም በአንድ ሐሳብና በአ ንድ ቃል እግዚአብሔርን ለማምለክ መዘጋጀታቸውን ገለጹ ። ስለዚህም ኢያሱ የል ቡን አስተያየት ይገልጽላቸዋል «እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም» አላቸው ።

ለጥቂት ጊዜ ደህና አድርገህ ብትመረምር በዚህ ስፍራ እንግዳ የሆነ አለመግ ባት አለ ። በአንድ በኩል እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ሁሉን ነገር አድርጎላቸ ዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱ ለእግዚአብሔር አንዳች ነገር ሊያደርጉለትና ሊመለሱለት አልቻሉም ። አንተም እንዲሁ አይደለህም ወይ ? አዎን ፣ አንተም እን ዲሁ ነህ ብዬ አስባለሁ ። የኢየሱስ ክርስቶስን ጥሪ በፍጥነት ተቀብለናል ፤ ነገር ግን የገባነውን ቃልና የሰጠነውን ተስፋ ለመፈጸም ደካሞች ነን ። ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን ፤ ከእግዚአብሔርም ጋር እንራመዳለን ብለን ተስለናል ። ይህንንም ቁርጥ ሐሳብ (ምናልባት ስብከት ስንሰማ ያደረግነው ይሆናል) በየዕለቱ አንዋኑዋራችን ውስጥ በሥራ ላይ ለማዋል ስንፈልግ ሳለን ደካሞች ሆነን እንገኛለን ።

በአዲስ ኪዳንም ጌታችን ለሕዝቡ የተናገረው ቃል ፣ እኛ እርሱን ለማስደሰት ከራሳችን እንደማንችል የሚያስረዳ መግለጫ ነው ። ሐዋርያ ጳውሎስ ለገላትያ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ እንዲህ ይላል «እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ ? በመንፈስ ጀምራ ችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን ?» ውድቀታችን ብዙ ፣ ክንውናችን ግን በጣም ጥቂት ነው ። ልባችን በጣም ቀዝቃዛ ፣ ስሜታችንም ተለዋዋጭ ነው ። በክርስቲያን ኑሮ ዘመናችን ሁሉ እውነተኛ ቁራጥነትና መንፈስ ጠንካራነት ጎድሎናል ። ስለዚ ህም ወደዚህ መግለጫ እንመጣለን ። ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ ዓይነት ወደ መሆን ሊመጣ አይችልም ። ነገር ግን ለግንኙነቱ ሁሉ እንግዳ ነው ። ሕይወት ሊኖረን ይችላል ። ዳሩ ግን ስለ ትርፍ ሕይወት ምንም አናውቅም ። የበደሉንን ይቅር ልንላ ቸው እንችላለን ፤ ግን በኃጢአት ላይ የማያቋርጥ ኃይል የለንም ። ልንድን እንችላ ለን ልንጸድቅና ልንቀደስ ግን አቅቶናል ።

ዛሬ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ታላቁ ነገር ፣ በምናምነውና በአንዋኑዋራችን መከከል ያለውን አሳዛኝ ልዩነት ማስወገድ ነው ። ዛሬ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ በቀራንዮ በአደረገልን አቋማችንና በመንፈስ ቅዱስም በው ስጣችን ሊያደርገው ሲችል ሳለ ባላደረገው ነገር መከከል የሚያሳዝን ልዩነት እንዳ አለ አውቃለሁ ።

ለእያንዳንዳችን የሚያስፈልገው የመጀመሪያው ነገር በደኅንነታችንና በጽድቃ ችን በቅድስናችንም መከከል ፣ በክርስቶስ ደም በመቤዣችንና በመንፈሱም በመቀደ ሳችን መከከል የቀረውን ልዩነት ማስወገድ እንደሆነ አሳስባችኋለሁ ። አንድ ጠቃሚ ሥራ ሊሠራልን በመስቀል የሞተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ ዛሬም በመንፈሱ በው ስጣችን ሊሠራ በልባችን በር ቆሞአል ። የቤተ ክርስቲያንም ውስጣዊ መታደስም

በውስጣችን ያለው ፃ ሕይወት እየገነፈለ ለበረከት ወደ ሌሎች በመሠራጨቱ ብቻ ሊታወቅ ይችላል ። የክርስቲያን እምነት በእግዚአብሔር ቃል መግለጫ ብቻ ካላረፈ ሐሰተኛ ነው ። መግለጫውም ወደ መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ አንዋኑዋር ልምምድ ካልመራ ቀዝቃዛ ነው ። ደግሞም ስለሚጠፋብን ቶሎ እናጣዋለን ።

አንድ ጊዜ ዶክተር ግርሃም ስክሮጂ ሲናገር የሰማሁትን አስታውሳለሁ ። «ክርስቲያኖች ሁሉ የዘላለም ሕይወት አላቸው ። ግን ሁሉም ክርስቲያኖች የተትረፈረፈ ሕይወት የላቸውም ። ጤና ቢስ ሕይወት ሊኖር ይችላል ፤ እርምጃ የማያደርግ እንቅስቃሴ ሊኖር ይችላል ። ውጊያ ሊኖር ይችላል ግን ድል ይሆናሉ ። ልናገለግል እንችላለን ግን አይከናወንልንም ፤ እንሞክራለን ግን አናሸንፍም ። ልዩነቱ ሕይወት ሲኖረን የተትረፈረፈ ሕይወት የኑሮ ልምምድ የለንም ። ይህን ትርፍ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው እንድናገኝ አድርጎልን በመንፈሱም በውስጣችን እንደሚፈጸም እውነተኛ በማድረጉ ነው ። ትርፍ ሕይወት እርሱ ነው ። ችግራችን ግን እንደሚከተለው ነው ። በፋሲካ ቆመናል ፤ ግን ከጴንጠቆስጤ በስሕተት ወገን ነን ። በስርየት በኩል በደህና ወገን ነን ። ግን በኃይል በኩል በስሕተት ወገን ነን» ድነናል ግን አልጸደቅንም ። ይቅር ተብለናል ማለት ብቻ በቂ አይደለም ። መጽሐፉ ለቅድስና ተጠርተናል ይላል ።

ብዙዎቹ ማህበሮች ዛሬ እንዲህ ይላሉ ። ያስቸገረን ነገር የትምህርት መለያየት ነው ። የወንጌላውያንም ፤ የትምህርቱም መለያየት ወደ መደናገር መራን ። እኔ ግን ይህን አላምንም ። እኔ የማምነው ፤ ዛሬ ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ችግር ግማሽ በግማሽ የሆነ ደኅንነት ነው ። በዚህ ዓይነት ደኅንነትም ብዙ ሰዎች በቃን ብለው ይኖራሉ ።

ይህ እስራኤላውያን በምድረ በዳው ፤ በምስርና በከነዓን መካከል በነበሩበት ሁኔታ ፤ ደግሞም በመሸነፋቸውና በገርነታቸውም ይመሰላል በጳውሎስም አነጋገር ወደ ሮሜ ሰዎች በምዕራፍ ፯ በጻፈው ውስጥ ተገልጦአል ። ከኃጢአት ፍርድ ነፃ በመሆንና ከኃጢአት ኃይል ከመላቀቅ መካከል ያለው ልዩነት እርሱ ነው ። እንደ ገናም በመጀመሪያይቱ የቆሮንቶስ ሰዎች መልእክት ምዕራፍ ሦስት ተገልጾአል ። በዚህም ጳውሎስ ስለ ፍጥረታዊ ወይም ሥጋዊ ክርስቲያን ይናገራል ። እንዲህ ያለ ክርስቲያን ይጋደላል በሕሊናውም ውስጥ የፍርድ መከፋፈል አለ ። ነገር ግን ሕፃን ሆኖ ይኖራል እንጂ አያድግም ፤ የዚህን አንዋኑዋር ዓይነት ምሳሌ በፋሲካና በጴንጠቆስጤ መካከል ደቀ መዛሙርት በፍርሃት ተጨብጠው ፤ በአነጋገርም ሥራ ፈቶች ሆነው በነበሩት ሁኔታ እናገኛለን ። ጴጥሮስም በአንድነት ጠርቶአቸው እያመነታ ፤ ተስፋ በመቁረጥና በጥርጣሬ «ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ» ያለውን ታስታውሳለህ ። ከመሠረቱ ሥራ አልነበረውም ፤ ጥሪ አልነበረውም ፤ ሁሉም የሚደርስባቸውን እጅግ ይፈሩ ነበር ። በልቡ የሚፈራ ለእግዚአብሔርም ሥራ ያልተጠራና የታወቀ ሥራ የሌለው ሰው ትርፍ ሕይወት ሊኖረው አይችልም ። በትንሽም ሆነ በተፋፋመ ውጊያ መካከል ሁልጊዜ በክርስቶስ ሥራ ሰውን ሊያበረታ የሚችለው ጽኑ መሠረት ያለው

ጥሪ ሥራና ሥነ ሥርዓት ነው። ዛሬም ከቤተ ክርስቲያናችን የሚጎድለው ትልቁ ቁም ነገር እርሱ ነው። ይህም ሁሉ ኢያሱ ለእስራኤል ሰዎች ወደ ነገራቸው ትልቁ መልእክት ይመራናል። «እምላካችሁ እግዚአብሔርን ልታመልኩ አትችሉም።»

ይህ የክርስቲያን ሕይወት ታላቁ እንግዳ ነገር ነው። እግዚአብሔር በቀራንዮ መስቀል ሁሉን ነገር ሠርቶልን አሁንም በመንፈሱ በውስጣችን ሊሠራ የሚጠብቀን ቢሆንም «እግዚአብሔር አምላካችንን ልናገለግል አንችልም» ብለን መመለስ እጅግ እንፈራለን።

ነገር ግን ልጠይቃችሁ፤ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው አገልግሎት ምን ድር ነው? የኑሮንም ልምምድ የምንረዳበት ኃይል የት ይገኛል? እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሥራ ለመሥራት የማንችል መሆናችን ብዙ ጊዜ እንደተገለጠልን አም ናለሁ። ምኞታችን፤ ፍላጎታችንና ለሥራም ያለን አምሮታችን ቢበዛም እንኳ አንድ ነገር በየቀኑ አካሄዳችንና ኑሮአችን ተጽፎበታል፤ ይኸውም እግዚአብሔርን የሚያስ ደስት ነገር ለመሥራት ሥጋ ፍጹም ደካማ መሆኑ ነው። በሌላ በኩል ግን የተትረ ፈረፈ፤ የጸደቀ፤ የተቀደሰና አሸናፊ ሕይወት አለን።

ድካሜ ከእግዚአብሔር ኃይል እንዴት አድርጎ ይገጥማል? ይህን ትምህርታች ንን ለመፈጸም በምንቃረብበት በአሁኑ ጊዜ ይህን ጥያቄ መመለስ አለብን። ብዙ ሰዎች በአንድ የተለየ መለኮታዊ አድራጎት ወደዚህ ጥልቅ ሕይወት ገብተው ስለ አቋሙና ሁኔታው እውነተኛነት መጠየቅ ይጀምራሉ። ብዙ ሰዎች ይህን ሕይወት አላቸው፤ ብዙዎችም ያውቁታል፤ ብዙ ሰዎች እንደ ተጠመቁበትና አዲስ እንደ ተወለዱበት ቀን እውነተኛ በሆነ አድራጎት ወደ ተትረፈረፈው ሕይወት ገቡ፤ በም ድረ በዳውም አድርገው ወደ ምድሪቱ ገብተዋል። አሁንም ስለ እውነቱ ያወራሉ።

ዳዊት ኤል ሙዲ አንድ ጊዜ በግላስጎው የተናገረውን ልጥቀስ «አንድ ቀን በኒው ዮርክ ከተማ፤ ያውም እንዴት ያለ ቀን መሰላችሁ? ልገልጸው አልችልም። ስለ እርሱም ብዙ ጊዜ አልነጋገርበትም። ስም የማላገኝለት መለኮታዊ ነገር ነበረ። እግዚአብሔር ራሱን ገለጠልኝ ለማለት እችላለሁ። እኔም ስለ ፍቅሩ የማልረሳው ስሜት ወረረኝ፤ ስዚለህም እጁን በላዬ እንዲያቆይ መለመን ግድ ሆነብኝ። እንደ ገና ልሰብክ ሄድሁ። ስብከቶቼ ከዱሮው አልተለዩም። አዲስ እውነትና ትምህርት ላወራ ወይም ልገልጽ አልቻልሁም፤ ነገር ግን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ንስሐ ገቡና ተመለሱ። መላዋን ግላስጎው ብትሰጡኝ ከዚያች ቀን በፊት ወደ ነበርሁበት የእንዋኑዋር አቋምና ልምምድ መመለስ አልፈቅድም» ሙዲ ልዩ በሆነ በእግዚአብ ሔር አድራጎት ፈጽሞ ልዩ ወደሆነ የእንዋኑዋር ደረጃና የተትረፈረፈ ጥልቅ ሕይ ወት ገባ።

በሕይወቱ የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ እንደሚገኘው፤ ዳዊት ብሬይነርድ በፊቱ ስለ ቆሙት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በላብ ረጥቦና ደክሞም ነበረ።

ነገር ግን እርሱ ሲሰብክ ፥ ቁጡዎችና ጨካኞቹ ሕንዳውያን ሣር ከማጭድ ፊት እንደ ሚደፋ አንነበሱ ።

ብዙ ዘመን በወንጌል መልእክተኛነት በውጭ አገር ሲያገለግል ከቆየ በኋላ ለእ ረፍት ወደ አገሩ ወደ እንግሊዝ ተመልሶ ሳለ ሀድሰን ቴይለር አንድ ቀን በሐሳቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ለእግዚአብሔር ሥራ ያለው ድካሙ ፥ ጉድለቱና አለመጥቀሙ ከዱሮ ይልቅ አብልጦ ተገለጠለት ። ከዚያ በኋላም እንዲህ አለ ። «እግዚአብሔር በሀድሰን ቴይለር በኩል የሚያደርገው እንጂ ፥ ሀድሰን ቴይለር ለእግዚአብሔር የሚ ያደርገው አይጠቅምም» ከዚያን ቀን ጀምሮ «የተለወጠ» ወይም «የተቀየረ ሕይ ወት» ብሎ ራሱ ስም ያወጣለትን ሕይወት መኖር ጀመረ ። በዚህም ሕይወት «ከእን ግዲህ ወዲህ እኔ አይደለም ክርስቶስ እንጂ»

አንተም እንዲህ ትለኝ ይሆናል «እነዚህ ሰዎች የሃይማኖት አርበኞች ናቸው ፥ እነርሱ የተለዩ ናቸው ። እንዲህ ያለው ለእኔ አይደለም» የእነርሱ አርበኝነት ለእግዚ አብሔር ስለታዘዙ ብቻ ነው ። ሰይጣን ዛሬ ይህንን እውነተኛውን ነገር እንዳያምኑ የክርስቲያኖችን አእምሮ አሳወረና ግማሽ በግማሽ በሆነ ደኅንነት በቃን ብለው እንዲ ኖሩ አደረጋቸው ። እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር ስለታዘዙ ፥ ስለተጠባበቁት ፥ በመ ጽሐፉም ተስፋ የሰጠውን ስለ ተቀበሉ የሃይማኖት አርበኞች ሆኑ ። እነርሱ ልዩ ሰዎች መሆናቸውና የእኛ አለመሆን አሳዛኝ ማብራሪያ ነው ። እግዚአብሔር በተለይ የሚወደውና የሚጠላው የለውም ። ነገር ግን ከመጠነኛው የክርስቲያን ኑሮ የበለጠ በጣም ከፍ ያለና ከመዳንህ በፊት ከነበርክበት አንዋኑዋር ፥ ንስሐ ከገባህ ወዲህ ያለ ህበት እንደሚሻል ፥ ከበረሃም ኑሮ የበለጠ የክርስቲያን የኑሮ ደረጃን ለእያንዳንዳችን አለው ። እግዚአብሔር ይህን ሁሉ እንዲሰጠን የምንጠብቀው እኛ አይደለንም ። ዳሩ ግን ሊሰጠን እርሱ ራሱ ቆሞ ይጠብቀናል ። ኢያሱ ለሕዝቡ እንዲህ አለ «አሁን እንግዲህ በመካከላችሁ ያሉትን እንግዶች አማልክት አርቁ፤ ልባችሁንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር አዘንብሉ» ኢያሱ ፳፬ ፥ ፳፫ ።

የግል ምስክርነቴን እዚህ ላይ ስሰጣችሁ መንፈሳዊ ትምክህት ይመስለኛልና እየፈራሁ ነው ። ነገር ግን እግዚአብሔር ልቤን ያውቃል ። እግዚአብሔር ይህንን እውነት የገለጸልኝን ቀን አስታውሳለሁ ። ሰባኪ ሆኜ ልሄድ በተዘጋጀሁና በተነሣሁ ጊዜ በልቤ አማልክት እንዳሉ ተረዳሁ ። አንዱም ጣዖቴ የትምባሆ በርሳ ነበር ። ሌሎቹ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ የሆኑ የስሜቶችና የፍቅር ጣዖቶች ነበሩ ። በአንዱ የገንዘብ መውደድና ለእግዚአብሔር ቤት ተገቢውን የአለመስጠት ጣዖት ነበረ ። አንዱ ጣዖቴ እኔ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የማምነውን የማያምኑትን የምተችበት አንደበትና ለጉዋደኝነት የማልቀበልባቸው አስተያየቴ ነው ። የልብ ቅዝቃዜ ጣዖ ትም ነበረኝ ፥ ይህም ጸሎተ ቢስ አንዋኑዋር ነው፤ እግዚአብሔር ስለ እነዚህ አማል ክቴ ሰብሮ ያደቀቀኝን ቀን አልረሳውም ።

ፍጹም የሆነ ሰው ነኝ አላልኩም ። በእውነቱ ከዚያን ቀን ወዲህ የደረሱብኝን ውድቀቶችና የተሳሳትኩአቸውንም ስሕተቶች ሳስታውስ አፍራለሁ ። ነገር ግን ይህ

የተሰጠኝ ትርፍ ሕይወት የመጨረሻው ደረጃ ሳይሆን ወደ ከፍተኛ ደረጃና እንዋኑ ዋር ለመድረስ የመጀመሪያ እርምጃ መሆኑ በየቀኑ ይሰማኛል። ለልቤም ጥልቀት ይታወቀኛል። ኑሮዬን ከእግዚአብሔር ጋር ባደርግና እግዚአብሔርም በክርስቶስ የሰጠኝን ለመቀበል ዘወትር ብገፋበት በየቀኑ ስለ ኢየሱስ የበለጠና እየጨመረ የሚ ሄድ ነገር ይገለጥልኛል። በሃይማኖት አንድ ጊዜ ብቻ ለመጨረሻው እንቀበላለን የሚባል የክርስቲያንነት ኑሮ አቋምና የኑሮ ልምምድ የለም። ነገር ግን ከእግዚአብ ሔር ጋር ስትራመድ በዕድሜህ ሁሉ ልምምድህ ይጨምራል፤ እንደ ችሎታህ ስፋት መጠን ሕይወትህ እያደገ ይሄዳል። ሥጋዊነትህና ዓለማዊነትህም እየመነመነ ይሄ ዳል። ኢየሱስ ብቻውን የተወደደ ይሆንልሃል።

ስለዚህ ማገልገል ከፈለግን አስቀድመን ራሳችንንና ያለንን ሁሉ ለእርሱ እናስረ ክብ። ለማሸነፍ አስቀድመን እንታዘዝ። ማገልገል ከስግደትና ከማምለክ የበለጠ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ግርማና ሥልጣን መንበርከካችንን ይጠይቃል። ባሕርይአችን ወደ ቅድስናው ባሕርይ መለወጥ፥ የኃጢአተኛና የርኩስ ሰው በቀራ ንዮ እንጨት ላይ ስለተደረገው መሥዋዕት ወደ ቅዱሱ እግዚአብሔር መቅረብ መቻል ማለት ነው። ጽድቅና ቅድስና የሚገኘው ልክ በዳንኩበት መንገድ ብቻ መሆኑን ማወቅ ነው። ሁሉም በሃይማኖት ይገኛል። ለማግኘት ስለ ታገልኩ አይደ ለም፤ ለንጽሕናና ለአምልኮት ስለ ተፍጨረጨርኩ አይደለም። ነገር ግን ክርስቶስ የሆነልኝንና ያደረገልኝን የሚያደርግልኝንም ሁሉ በሃይማኖት ብቻ ልቀበለው እችላ ለሁ።

ድካማችንን በደንብ የምንረዳበትና እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ሊያደርገንና ሊያደርግልን የወደደውን ሁሉ በሃይማኖት ብቻ እንደምንቀበል የምንረዳበት ቀን እንዴት የተባረከ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን የጉልበትና የኃይል ሁሉ ምንጭ አድርጎ ያቀርብልሃል። ሞክረሃል፥ ግን አቃተህ። እንግዲህ አሁን ማመን አትጀም ርም? በገዛ ጉልበትህና ሥራህ ሞክረህ ሁሉም የድካም ድካም ብቻ ሆኖአል። አሁን የእርሱን ኃይል ለምን አትሞክርም? ደግሞም አትጨብጥም? ይህንን የምታ ደርግ ከሆንክ ራስህንና የራስህን ሁሉ መተው መክድም ዝግጁ መሆን አለብህ። በሥጋዊ ነገሮች ተጣብቀን ዓለማውያን ሰዎች ክርስቲያንነት ምንም ያይደለ ነገር ነው እንዲሉ እናደርጋለን ወይ? ወዳጆቼ ሆይ፥ ይህ አይገባም። ወደ ትርፍ ሕይወት ልትገባ ከፈለግህ የምታደርገውን ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ካለህ ፍቅር አንፃጽ ርና መርምር። ቀራንዮን በግልጽ እንዳታይ ማናቸውም ነገር አይጋርድህ።

ስለ ሕይወቱ ሥርዓት አውጉስቲን አንድ ጊዜ እንዲህ አለ «ለራሴ የብረት ልብ አሳያለሁ። ለሰው ግን የፍቅር ልብ፥ ለአምላኬም የነበልባል ልብ አሳያለሁ» እግዚ አብሔር ከልጆቹ ውስጥ እያንዳንዳችን የሚጠራን እንዲህ ላለ አገልግሎትና ሕይወት ነው። በመጽሐፉም የቀረበልህና እንድትቀበለው የሚፈለግብህ አቋም እርሱ ነው።

«የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» ኢያሱ ፳፬ ፣ ፲፭ ።

እንጣሥቶ ላስጀመረኝ ፣ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው ፤ ለዘለዓለም ፣ አሜን ።